





የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች
ቅፅ 5

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

## ቅፅ 5

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ሚያዝያ 2001 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
# ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

## ቅፅ 5

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>



## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት

ከዚህ ዕትም በፊት በነበሩ ቅፆች በርካታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ታትመው በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ ፍርድ ቤቶችና ለሌሎችም የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሠራጩ ተደርጓል:: ይህም በዋናነት፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል ተብሎ በመደንገጉ ፍርድ ቤቶች የሰበር ችሎቱ የሰጠውን የሕግ ትርጉም ተከትለው እንዲሠሩ ለማስቻል ነው:: በየፍርድ ቤቶች ለተመሣሣይ ጉዳዮች ይሰጥ የነበረውን የተለያዩ ወሳኔዎች በማስቀረት የፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች ወጥነት እንዲኖራቸውን ተገማችም እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑም ነው::

በሌላ በኩል ውሣኔዎቹ በጥራዝ መልክ መዘጋጀታቸው ጥናትና ምርምር ለሚያካሂዱ የሕግ ተማሪዎችና ምሁራን፣ ለጠበቆችና ለህብረተሰቡ በአጠቃላይ ውሳኔዎቹን በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል የሚል እምነት አለን::

**ተገኔ ጌታነህ**

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት**

ማውጫ ገጽ


ውሎች - ውክልና ........................................ 1

የሰ/መ/ቁ 17320 ........................................ 2
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ ሸዋርካብ ተሾመ
የሰ/መ/ቁ 20890 ........................................ 12
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ ዓለምነሽ ኃይሌ
የሰ/መ/ቁ 23861 ........................................ 17
ሊቀስዩማን አሰፋ በሻውረድና የሣህሊተ ምህረትና
ክርስቶስ ሣምራ ደብር አስተዳደር
የሰ/መ/ቁ 26399 ........................................ 20
አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና እነ አቶ ሳሙኤል ጎሳዬ
የሰ/መ/ቁ 32241 ........................................ 29
ወ/ሮ ካሰች ተካልኝ እና እነ አቶ ኃ/ማርያም አበበ

ውሎች - ዋስትና ........................................ 34

የሰ/መ/ቁ 21355 ........................................ 35
አንበሳ የተከማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እና አንበሳ
ኢንሹራንስ ኩባንያ
የሰ/መ/ቁ 25115 ........................................ 39
አቶ ማሞ ጎበና እና አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም
የሰ/መ/ቁ 26565 ........................................ 42
ግሎባል ኢንሹራንስ ኢ.ማ እና ንብ ትራንስፖርት ኢ.ማ

ውሎች - ስጦታ ........................................ 48

የሰ/መ/ቁ 17742 ........................................ 49
እነ ወ/ሮ አበበች ታደሰ እና እነ አስር አለቃ ሲሣይ ካብትህይመር
የሰ/መ/ቁ 23921 ........................................ 55
ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግሥቱ እና 10 አለቃ ታደሰ ወርቁ
የሰ/መ/ቁ 32337 ........................................ 57
ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይሕደጎ እና እነ ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ

ውሎች - ብድር ........................................ 64

የሰ/መ/ቁ 22891 ........................................ 65
ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ገ/ማርያም ከበደው
የሰ/መ/ቁ 31737 ........................................ 69
አቶ ገብሩ ገ/መስቀል እና ቄስ ገ/መድኅን ረዳ

ውሎች - ልዩ ልዩ ........................................ 75

የሰ/መ/ቁ 24173 ........................................ 76
የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ወ/ሮ አይዳ ሐሰን
የሰ/መ/ቁ 24574 ........................................ 79
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፓ/ጠ/ቤ/ጽ/ቤት እና አቶ
ይትባረክ ሣህሉ
የሰ/መ/ቁ 25434 ........................................ 83
የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን እና ፍሬተርስ
ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግ ማኅበር
የሰ/መ/ቁ 26565 ........................................ 88
ግሎባል ኢንሹራንስ ኢ.ማ እና ንብ ትራንስፖርት ኢ.ማ
የሰ/መ/ቁ 29369 ........................................ 94
በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዮት የሆለታ ግብርና ምርምር
ማዕከል እና አቶ ተመስገን አድነው
የሰ/መ/ቁ 39947 ........................................ 98
የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ሲሳይ ጥላሁን
የሰ/መ/ቁ 31480 ባህመድ........................................ 102
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና እና አቶ መሐመድ

ከውል ውጪ ........................................105

የሰ/መ/ቁ 19388 ........................................106
ዘይነባ ሐሰን እና ፍሬው ተካልኝ
የሰ/መ/ቁ 21296 ........................................113
የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት እና ውበት አድባሩ
የሰ/መ/ቁ 22509 ........................................118
አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ እና ዳርጌ ሰምሮ

የሰ/መ/ቁ 23924 ....................................................121
አቢሲንያ ባንክ እና አቶ አበበ ከበደ
የሰ/መ/ቁ 24818 ....................................................125
ይልቃል በእውቀቱ እና ስዩም አባዲ
የሰ/መ/ቁ 27565 ....................................................128
የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ደምሴ ወርቅነህ
የሰ/መ/ቁ 27623 ....................................................131
ማኀበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ውባየሁ አበበ
የሰ/መ/ቁ 28612 ....................................................133
የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን እና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን
የሰ/መ/ቁ 28750 ....................................................136
የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 28865 ....................................................141
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ካሣ ግዛው
የሰ/መ/ቁ 30032 ....................................................145
የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ እና ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ
የሰ/መ/ቁ 30442 ....................................................149
የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን እና ወ/ሮ ድንቋ አመኔ
የሰ/መ/ቁ 31099 ....................................................153
የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ እና ወ/ሮ ኒሻን አለማየሁ
የሰ/መ/ቁ 32144 ....................................................156
ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር እና ወ/ሮ አልሻ ሲራጅ
የሰ/መ/ቁ 32250 ....................................................159
ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም እና እነ አቶ ከተማ ተሠማ
የሰ/መ/ቁ 33975 ....................................................162
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ አበበች ስዩም
የሰ/መ/ቁ 34138 ....................................................166
እነ ሲስተር ገነት ጌታቸው እና ወንድወሰን ኃይሉ ወልደማርያም
የሰ/መ/ቁ 34906 ....................................................171
የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት እና ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቂ

**የቤተሰብ ህግ** ....................................................174

የሰ/መ/ቁ 21740....................................................175
ወ/ሮ አስረስ መስፍን እና ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ
የሰ/መ/ቁ 23021....................................................180
ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህ እና ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ
የሰ/መ/ቁ 23493....................................................185
ወ/ሮ አንማው ዘገየ እና ወ/ሮ ወርቂ መኮንን
የሰ/መ/ቁ 23632....................................................188
ወ/ት ፀዳለ ደምሴ እና አቶ ክፍሌ ደምሴ
የሰ/መ/ቁ 24295....................................................192
ወ/ሮ ጽጌ ድረሴ እና ወ/ሮ መሰለች ረዳ
የሰ/መ/ቁ 24625....................................................195
ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ እና ወ/ሮ ራሕማ ዓሊ
የሰ/መ/ቁ 25005....................................................198
መኮንን በላቸው እና ወ/ሮ አለሚቱ አደም
የሰ/መ/ቁ 25281....................................................201
ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ እና አቶ ቀልቤሣ አበው
የሰ/መ/ቁ 25588....................................................204
መርዳን ሃሰን ዑመር እና መውሊድ ተኸል
የሰ/መ/ቁ 26839....................................................208
ወ/ሮ አስካለ ለማ እና ሣህለ ሚካኤል በዛብህ
የሰ/መ/ቁ 26953....................................................211
አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ እና ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ
የሰ/መ/ቁ 27697....................................................215
አቶ ርዕሶም ገ/መድኅን እና ወ/ሮ አልማዝ ጊላሚካኤል
የሰ/መ/ቁ 27869....................................................220
ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ እና ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ አቶ ትሁት ማሞ
የሰ/መ/ቁ 29343....................................................224
1. ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ
2. ወ/ት ሌንሳ ኢላላ እና ወ/ት አበባ አድማሱ
የሰ/መ/ቁ 29402....................................................231
ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ እና የ፺አለቃ አስመላሽ ኃይለስላሴ

የሰ/መ/ቁ 30959 ........ 234
1. ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ሥላሴ/
2. ወ/ሮሙሉ ገ/ሥላሴ እና
1. አቶ ዘለቀ ዘውዴ
2. አቶ አንዳላር ዘውዴ
የሰ/መ/ቁ 31430 ........ 237
ወ/ሮ አዲስ አለም እና የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ
የሰ/መ/ቁ 31891 ........ 240
እነ አቶ አንለይ እንየው እና ወ/ሮ መሬም ጡሃ
የሰ/መ/ቁ 31946 ........ 244
ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው እና ተመስገን ደሣለኝ
የሰ/መ/ቁ 32130 ........ 247
እነ እማዋይሽ ከሣ እና ወ/ሮ አስቴር አህመድ
የሰ/መ/ቁ 33126 ........ 251
ወ/ሮ የዝና ተስፋሁን እና መምህር ጥሩአየሁ እውነቱ
የሰ/መ/ቁ 33411 ........ 255
ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ እና አለቃ ኪሮስ ገብሩ
የሰ/መ/ቁ 33440 ........ 259
ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ግርማ ገ/ሥላሴ
የሰ/መ/ቁ 33875 ........ 262
ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን እና ወ/ሮ መሠረት አድማሱ
የሰ/መ/ቁ 34149 ........ 268
እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ እና አቶ አለሙ በቀለ
የሰ/መ/ቁ 34387 ........ 271
አቶ ከበደ ሙሔ እና ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ
የሰ/መ/ቁ 35376 ........ 275
አቶ ዳንኤል አሰፋ እና ወ/ሪት ሔለን ውበቱ

## የንግድ ህግ

የሰ/መ/ቁ 23389 ........ 281
የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አክ/ማኅበር እና
እነ ባህሩ አብርሃም
የሰ/መ/ቁ 25306 ........ 284
አቶ ተስፋዬ ገለቴ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
የሰ/መ/ቁ 27161 ........ 288
አቶ ኤልያስ ከፊለ እና እነ አቶ ከድር አህመድ
የሰ/መ/ቁ 28923 ........ 291
የባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ አክስዮን ማሕበር እና
1. የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነገረፈጅ
አቶ አዳነ መጋቡ

## በአዋጅ የተወረሱ ቤቶች ........ 296

የሰ/መ/ቁ 22297 ........ 297
የጅማ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት ተወካይ
ቲጃኔ አባቡልጉ እና አቶ ሸዋረገድ አባድር
የሰ/መ/ቁ 23608 ........ 300
የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች
እና የአቶ ኑር በዛ ተረጋ ወራሾች
የሰ/መ/ቁ 27548 ........ 306
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና
1. ወሮ ቆጽለ መርሻ 2. ወ/ሮ ፀምረ መርሻ
የሰ/መ/ቁ 29822 ........ 310
የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት እና እነ
ወ/ሮ በቀለች አማረብህ
የሰ/መ/ቁ 29860 ........ 318
ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው እና እነ ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ
የሰ/መ/ቁ 31490 ........ 322
የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ሴራኮ እስራኤላዊያን
የሰ/መ/ቁ 31682 ........ 326
አዲስ ከተማ ክ/ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ እና
1. ዘላለም ይልማ ባልቻ
2. መሠረት ይልማ ባልቻ
3. አዳሙ ይልማ ባልቻ
የሰ/መ/ቁ 32376 ........ 330
አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ
ሽዋንግዛው
የሰ/መ/ቁ 34249 ........ 335
እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ እና እነ አቶ አለሙ ወንድሙ

እርቅ ግልግል ........................................................................ 338

የሰ/መ/ቁ 22857 ........................................................................ 339
እነ አቶ ተክሌ ደግፌ እና እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ
የሰ/መ/ቁ 25912 ........................................................................ 343
የአቶ ብር ቆርቾ ወራሽ ብርቅነሽ ብሩ እና አቶ ክፍሌ ሐብደታ
የሰ/መ/ቁ 29386 ........................................................................ 346
ወ/ሮ ወለላ ተሰማ እና እማሆይ በላይነሽ መለሠ
የሰ/መ/ቁ 30536 ........................................................................ 353
ወ/ት ዓለምነሽ ዋቅቶላ እና
1. አቶ ይልቃል ጌጤ 2. ካጀ ኢ/ል ኃ/የተ/የግ/ኩባንያ
የሰ/መ/ቁ 30727 ........................................................................ 356
የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ/ማህበር እና ጄቲቲ ትሬዲንግ ሥራ አስኪያጅ

ልዩ ልዩ ........................................................................ 361

የሰ/መ/ቁ 20036 ........................................................................ 362
ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ
የሰ/መ/ቁ 23334 ........................................................................ 366
የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ እና
1. አቶ ደበሣ ገለታ 2. አቶ ኤባ ደመራ
የሰ/መ/ቁ 25899 ........................................................................ 369
የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ስዩም ካሣ
የሰ/መ/ቁ 26480 ........................................................................ 372
የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ እና አቶ ቢንያም ዓለማየሁ
የሰ/መ/ቁ 28883 ........................................................................ 375
ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ሚስተር ኒኮላ አስ ፓፓቻት ዚስ
የሰ/መ/ቁ 29005 ........................................................................ 378
አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት እና
1. ግርማቸው ይላላ
2. አዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን
የሰ/መ/ቁ 30298 ........................................................................ 381
አቶ የሺወንድም አቡሐይ እና አቶ አየነው ማለደ


# ውሎች
# ውክልና

የሰ/መ/ቁ. 17320

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁዮናስ

ሒሩት መለሠ

መድኀን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነገረ ፈጅ ደረጀ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1ኛ/ ዶ/ር ሻውል ገብሬ - ጠበቃ ወንድሜነህ ዳኜ

2ኛ/ ወ/ሮ ሽዋርካብ ተሾመ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 03926 ሰኔ 30 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 23780 መስከረም 26 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ጥቅምት 8 ቀን 1997 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪዎች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ በሕጋዊ ጋብቻ ተሣሥረው የሚኖሩ ባልና ሚስት መሆናቸውን ገልፀው በጋብቻ እያሉ በወቅቱ በነበረው አስተዳደራዊ ስያሜ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 10 ቀበሌ 22 ቁጥሩ 715/2 የሆነ ቤት በጋራ ሠርተን እኛ በቡልጋሪያ አገር በነበርንበት ጊዜ አቶ ገዛኸኝ በልሁ ይህንን ቤታችንን እንዲያስተዳድርልን እንዲሸጥልን ወክለነው ነበር፡፡ አቶ ገዛኸኝ በልሁ እኛ በሰጠነው የውክልና ማስረጃ ሌላ የውክልና ማስረጃ በማዘጋጀት ከሰጠነው የውክልና ስልጣን ውጭ ቤታችንን መያዣ በማድረግ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ/ ተበድሯል፡፡ ስለዚህ አንደኛ ተከሣሽ የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁለተኛ ተከሣሽ ለሆነው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ብድር የሰጠውና የእኛን ቤት በመያዣነት የያዘው ተበዳሪው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤቱን በመያዣነት አስይዞ ለመበደር የሚያስችለው የውክልና ሥልጣን ያለው መሆኑን ሣያረጋግጥ ነው፡፡ ሁለተኛው ተከሣሽ አቶ ገዛኸኝ በልሁ ከአንደኛው ተከሳሽ የእኛን ቤት በማስያዝ ብድር የተበደሩት የተጭበረበረ የውክልና ሰነድ አቅርበው ነው፡፡ ስለዚህ በማናውቀውና ፈቃዳችንን ያልሰጠንበትን የተጭበረበረ የውክልና ሰነድ በመቀበል አንደኛ ተከሣሽ ቤታችንን በመያዣነት መያዙ ሕጋዊ ባለመሆኑ የመያዣ ውሉ ፈርሶ በባንኩ የተያዙት የባለቤትነት ሰነዶች ተመላሽ እንዲሆኑ ውሣኔ ይስጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሣሽ የሆነው አመልካች ነገረ ፈጅ ለተጠሪዎች ወኪል ለሆነው ለአቶ ገዛኸኝ በልሁ የከሳሾችን ቤት በመያዣነት በመያዝ ብር 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ያበደርነው ከሣሾች ወኪላቸው ቤቱን አስይዞ ብድር ለመበደር የሚያስችለው የውክልና ስልጣን የሰጡት መሆኑን በወኪላቸው በኩል ከቀረቡት ማስረጃዎች አረጋግጠን ነው፡፡ ስለዚህ ከሳሾች ፈቃዳችንን ሳንሰጥ አላግባብ ቤታችን በመያዣነት ተይዟል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ እንደዚሁም ተጠሪዎች ለማስረጃነት ይጠቅመናል ያሉትን የፖሊስ የምርመራ መዝገብና የተጭበረበረ የውክልና ሰነድ በመጠቀም በወንጀል ጉዳይ ተጠርጣሪ የሆነውን የተጠሪዎቹን ወኪል የአቶ ገዛኸኝ በልሁን የምስክርነት ቃል ከሰማ በኋላ ተከሳሹ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የከሳሾችን ቤት ለማስያዝ ህጋዊ የውክልና ስልጣን ስለሌለው ለአቶ ገዛኸኝ በልሁ የከሳሾችን ቤት በመያዣነት በመያዝ ብድር የሰጠው በአግባቡ አይደለም ስለዚህ የመያዣ ውሉ ፈራሽ ነው የባለቤትነት ሰነዱን ይመልስ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንን ውሣኔ ለማስቀየር ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ለዚህ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከአዲስ አበባ አስተዳደር የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በኩል በቁጥር 10760/484 የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም የተመዘገበው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ያቀረቡት የውክልና ሰነድ ትክክለኛ የውክልና ሰነድ ስለመሆኑ የአዲስ አበባ የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት መጠየቅና ማረጋገጥ ነበረበት፡፡ ሰነዱን አረጋጋጦ የመዘገበው የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ሣይጠይቅ የፖሊስን የምርመራ መዝገብ የተጠሪዎችን ፓስፖርትና የተጠሪዎች ወኪል የሆኑትን የአቶ ገዛኸኝ በልሁን ምስክርነት በመቀበል ሕጋዊ ስልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ የተሰጠውን የውክልና ሰነድ በተጭበረበረ ተግባር የተገኘ ሀሰተኛ ሰነድ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተጠሪዎች በቡልጋሪያ በሚገኘው የኢተዮጵያ ኤምባሲ በኩል ለወኪላቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ የሰጡት የውክልና ስልጣን ቤቱን እንደወካዮቹ ሆኖ ለማከራየት ለመሸጥ ለመለወጥና በስሙ ለማዞር የሚያስችለው የውክልና ስልጣን ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ የውክልና ማስረጃ መሠረት የተጠሪዎች ወኪል ቤቱን በመያዣነት አስይዞ ብድር ለመውሰድ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ይህንን ግልጽ የሕግ ድንጋጌ ሣያገናዝቡ ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የውክልና ስልጣን ከሌለው ሰው ጋር ነው ውል የተዋዋላችሁት በማለት የመያዣ ውሉ እንዲሰረዝ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ለተወካያችን አቶ ገዛኸኝ በልሁ የሰጠነው ውክልና ቤቱን በመያዣያነት ለማስያዝና ከባንክ ብድር ለመውሰድ የሚያስችለው የውክልና ስልጣን አይደለም፡፡ ተወካያችን ለአመልካች ቤታችንን በመያዣነት ያስያዘው እኛ አገር ውስጥ በሌለንበት ፈቃዳችንን ባልሰጠንበት ሁኔታ የሐሰት መታወቂያ በማዘጋጀት ሌላ ሰው በአንደኛው ተጠሪ ስም አቅርቦ በቁጥር 10760/484 የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም የአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ የሰጠው እኛ



የማናውቀውን እና ያልፈረምንበትን በማጭበርበር ወንጀል የተገኘ ሰነድ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ሀሰተኛ የውክልና ሰነድ መሠረት ቤታችን በመያዣነት መያዙ ሕጋዊ ስላልሆነ፣ የመያዣ ውሉ ፈርሶ የቤቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጡት ሰነዶች እንዲመለሱልን የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በአቶ ገዛኸኝ በልሁ እና በተጠሪዎቹ መካከል የተወካይና የወካይ ግንኙነት እንዳለ ተረድተናል፡፡ ተጠሪዎች ቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ተወካያቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፊት በነበረው ስያሜ ወረዳ 10 ቀበሌ 22 ቁጥሩ 715/2 የሆነውን ቤታቸውን እንዲያስተዳድርላቸው እንዲሸጥላቸው የወከሉት መሆኑን ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስና ማስረጃ ያሣያል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ተወካያቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤታቸውን እንዲያስተዳድሩ እንዲሸጡ እንዲለውጡና ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ እንዲችሉ ቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል የውክልና ስልጣን የሰጡ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ይህም የውክልና ማስረጃ በመጀመሪያ ተጠሪዎች ለተወካያቸው የሰጡት የውክልና ማስረጃ ለመሆኑ ክርክር አልተነሣም፡፡

ተጠሪዎች አናውቀውም ብለው የሚከራከሩት የተጠሪዎች ተወካይ የሆነው አቶ ገዛኸኝ በልሁ የወካዮችን ቤት በመያዣነት በማስያዝ ገንዘብ ለመበደር እንደሚችል የሚዘረዝረው በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በኩል ተመዝግቦ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም. አንደኛው ተጠሪ ለተወካይ አቶ ገዛኸኝ በልሁ ሰጥተውታል የተባለው የውክልና ማስረጃ ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህ ሰነድ የተጭበረበረ ሰነድ በመሆኑ፣ ይህንን መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቤታችንን በመያዣነት መያዙ ሕጋዊ ውጤት ሊሰጠው አይገባም በማለት የሚከራከሩ ሲሆን፣ አመልካች በበኩሉ ይህ የውክልና ሰነድ የተጭበረበረ

ለመሆኑ ሰነዱን አረጋግጦ የሰጠው የመንግሥት አካል ያላረጋገጠውና በቂ ማስረጃ ያልቀረበበት ነው በማለት ይከራከራል፡፡ ስለዚህ ተከራካሪዎቹ የሀሣብ ልዩነት ያላቸው በዚህ በሁለተኛው የውክልና ሰነድ ትክክለኛነትና ሕጋዊነት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም የተጠሪዎቹ ወኪል የሆነው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ሁለት የውክልና ማስረጃ እንዳለውና ማስረጃዎቹንም የውክልና ስልጣኑን ለማስረዳት የተጠቀመባቸው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪዎቹ ተወካይ አቶ ገዛኸኝ በልሁ የወካዮቹን ቤት በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ ላይ አተኩሮ የሁለቱን የውክልና ማስረጃዎች ይዘትና ሕጋዊ ውጤት አልመረመረም፡፡ በአንፃሩ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ አድርጎ የያዘው በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በኩል የተሰጠው ሁለተኛ የውክልና ማስረጃ ትክክለኛ ማስረጃ ነው ወይስ በማጭበርበር ተግባር የተገኘ የሀሰት የውክልና ማስረጃ የሚለውን ነጥብ ነው፡፡

አቶ ገዛኸኝ በልሁ የተጠሪዎች ወኪል መሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱበትና የታመነ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪው ነጥብ የተወካይ የውክልና ስልጣን እስከ ምን ድረስ ነው የሚለው ሲሆን የጉዳዩም ዋና ጭብጥ ወካይ የሆኑት ተጠሪዎች ተወካይ ለሆነው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤታቸውን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው የውክልና ስልጣን ሰጥተውታል ወይስ አልሰጡትም የሚለው ነው፡፡

ይህንን ጭብጥ ለመወሰን በተጠሪዎቹ እና በአቶ ገዛኸኝ በልሁ መካከል የወካይና የተወካይ ግንኙነት ያለ መሆኑንና ወካዮች ለተወካዩ የሰጡትን የውክልና ስልጣን ይዘትና ወሰን ያሣያሉ ተብለው የቀረቡ የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ተዓማኒነትና ክብደት በዝርዝር መመርመርና መመዘን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ተጠሪዎች ቡልጋሪያ በሚገኘው በኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል ለተወካዩ የተሰጡት የውክልና ማስረጃ በሁለቱም ማለትም በአመልካችም ሆነ በተጠሪዎች በኩል ክርክር ያልተነሣበት ተዓማኒነት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ማስረጃ በይዘቱ የተጠሪዎች ተወካይ የሆነው አቶ



ገዛኸኝ በልሁ የወካዮቹን ቤት እንዲያስተዳድር፣ እንዲሸጥ እንዲለውጥና ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ የሚችል መሆኑን በግልጽ የያዘ መሆኑን አመልካችና ተጠሪዎቹ ተማምነዋል፡፡ ተዓማኒነቱም ሆነ ይዘቱ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የተስማሙበት ተጠሪዎች ቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል አረጋግጠው ለተወካያቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ የሰጡት የውክልና ማስረጃ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ስንመረምረው ሁለት መሠረታዊ ባሕሪያትና ውጤት ያለው ነው፡፡ የመጀመሪያው ተጠሪዎቹ ተወካዩ ቤታቸውን እንዲያስተዳድር ጠቅላላ የውክልና ስልጣን የሰጡት መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን የውክልና ማስረጃው የተወካይ አቶ ገዛኸኝ በልሁ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2204 ድንጋጌዎች የአስተዳደር ሥራ ተብለው የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲያከናውን ስልጣን የሚሰጥ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በውክልና ማስረጃው ውስጥ በዝርዝር ባይገለጹም “ቤታችንን እንዲያስተዳድር” የሚለው ቃል፣ ተወካይ የወካዮቹን ቤት የመጠበቅ የማከራየት የቤት ኪራይ የመቀበል ደረሰኝ የመስጠትና ሌሎች አስተዳደራዊ ተግባራትን እንዲያከናውን የውክልና ስልጣን የሰጡት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ይኸው የውክልና ማስረጃ የተጠሪዎች ተወካይ ቤቱን ለመሸጥ የመለወጥና ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ ልዩ የውክልና ስልጣን ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ የውክልና ማስረጃው ለተወካዩ ልዩ የውክልና ስልጣን የሚሰጥ ከሆነ ሕጋዊ ውጤቱ በውክልና ማስረጃው ላይ ከተፃፉት ተግባራት በተጨማሪ፣ በውክልና ማስረጃው የተገለፁትን ጉዳዮችና እንደ ጉዳዩ ክብደትና እንደ ልምድ አሰራር በውክልና ማስረጃው የተገለጹትን ጉዳዮች ተከታታይና ተመሣሣይ የሆኑ አስፈላጊ ተግባራትን የመፈፀም ስልጣንን የሚያካትት መሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንኡስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ስለዚህ የተጠሪዎች ተወካይ ቤቱን አስመልክቶ የተሰጠው ልዩ የውክልና ስልጣን፣ በውክልና ማስረጃው በግልጽ የተመለከቱትን ጉዳዮችና በውክልና ማስረጃው ባይገልፁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ

አንቀጽ 1 የሚሸፈኑ ጉዳዮችን የመፈፀም ችሎታ እንደሚጨምር ለመረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም የተጠሪዎቹን ቤት የመሸጥ የመለወጥና ለሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ ስልጣን በውክልና ማስረጃው ያለው የተጠሪዎች ተወካይ የተጠሪዎቹን ቤት በመያዣነት የማስያዝ ስልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለው ጥያቄ ከላይ ከተጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አንፃር መመዘን ያለበት ሲሆን የንብረቱን ባለቤትነት ለሦስተኛ ወገን የማስተላለፍ ስልጣን ያለው ሰው ከዚህ መለስ የሆኑ ተግባራትን የመፈፀም ችሎታ እንዳለውና በተለይም ንብረቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል ስልጣን እና ችሎታ እንዳለው “ለራሱ ዕዳ ዋስትና እንዲሆን አንዱን የማይንቀሣቀሥ ንብረትን በዕዳ መያዣነት አድርጎ ለመስጠት የሚችለው የማይንቀሣቀሰውን ንብረት ለመሸጥ ችሎታ ያለው ሰው ነው” ከሚለው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም ተጠሪዎች ለወኪላቸው አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤቱን እንዲሸጥ እንዲለወጥና ለሶስተኛ ወገን እንዲያስተላልፍ በቡልጋሪያ የኢትዮጵያ አምባሲ በኩል የሰጡት የውክልና ስልጣን ተወካያቸው ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው ስልጣንና ችሎታ የሚያጎናጽፈው መሆኑንን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ አንቀጽ 1 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋሉ፡፡ በመሆኑም ለአቶ ገዛኸኝ በልሁ ተጠሪዎች በመጀመሪያ የሰጡት የውክልና ስልጣን ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል የውክልና ስልጣን ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ተወካያችን አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤታችን እንዲሸጥ እንዲለወጥ እንጂ በመያዣነት እንዲያስይዝ የውክልና ስልጣን አልሰጠነውም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የሕግ መሠረት እና ድጋፍ የለውም፡፡

ተጠሪዎች ለተወካያቸው የሰጡት የመጀመሪያው የውክልና ማስረጃ የተጠሪዎች ተወካይ ቤቱን በመያዣነት የማስያዝ ስልጣንና ችሎታ ያለው



መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህም የተጠሪዎች ተወካይ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሠረት ቤቱን በመያዣያነት ያስያዘና ከአመልካች ገንዘብ የተበደረ ለመሆኑ ብቃት ያለው ማስረጃ ነው፡፡ ይህ ከሆነ የተጠሪዎች ተወካይ ቤቱን በመያዣነት የማስያዝና የመበደር ስልጣን ያለው መሆኑን ለማስረዳት ታስቦ ያቀረበው ሁለተኛው የውክልና ማስረጃ ተዓማኒነት የሌለውና በሀሰት የተዘጋጀ ሰነድ ሆኖ ቢገኝ እንኳን በክርክሩ ውጤት ላይ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ ምክንያቱም የተጠሪዎች ተወካይ ሁለተኛው ሰነድ በአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በኩል ተረጋጋጦ ሣይሰጠው በፊት ተጠሪዎች በቡልጋሪያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል፣ ለተወካያቸው የውክልና ስልጣን ከሰጡበት ቀን ጀምሮ የተጠሪዎቹ ተወካይ አቶ ገዛኸኝ በልሁ ቤቱን በመያዣነት የማስያዝ ስልጣንና የሕግ ችሎታ ያለው በመሆኑ ነው፡፡ አመልካች ከተጠሪዎቹ ተወካይ ጋር የመያዣ ውል የተዋዋለው ተጠሪዎቹ የተወካያቸውን ልዩ ውክልና ከመሻራቸው በፊት በመሆኑ በአመልካቾችና በተጠሪዎቹ ተወካይ መካከል የተፈፀመው የመያዣ ውል ሕጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡

ተጠሪዎች አመልካች ከተወካያቸው ጋር የመያዣ ውል የተዋዋለው የአዲስ አበባ ውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በቁጥር 10760/484 የመዘገበውን ሀሰተኛ ማስረጃ እና የውክልና ሰነድ መሠረት በማድረግ በመሆኑ የመያዣ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን የተከራከሩ ቢሆንም፣ ተጠሪዎች ከዚህ የውክልና ማስረጃ በፊት ለተወካያቸው በሰጡት የውክልና ማስረጃ መሠረት ተወካይ ቤቱን በመያዣነት የማስያዝ ስልጣን አለው፡፡ ስለሆነም የተጠሪዎቹ ተወካይ ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው የውክልና ስልጣን እና ችሎታ ባለው ጊዜ ከአመልካች ጋር የመያዣ ውሉን የተዋዋለ መሆኑ ከተረጋገጠ አመልካቹ ውሉን ሲፈጽም አንደኛውን ወይም ሁለተኛውን ሰነድ አይቶ ከተጠሪዎች ወኪል ጋር ውል የተወዋለ መሆን አለመሆኑ መሠረታዊ ጉዳይ አይደለም፡፡ መሠረታዊው ነጥብ የተጠሪዎች ተወካይ ከአመልካች ጋር ውል ሲዋዋል ቤቱን የመሸጥ የመለወጥ ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ቤቱን

በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው ስልጣንና ችሎታ ባለው ጊዜ ውስጥ ውሉን የተዋዋሉ መሆኑ ወይም አለመሆኑ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር በአመልካችና በተጠሪዎቹ ተወካይ መካከል የተደረገው የመያዣ ውል ተጠሪዎች በቡልጋሪያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል አረጋግጠው በላኩለት የውክልና ማስረጃ መሠረት የተጠሪዎች ተወካይ የወካዮቹን ቤት ለመሸጥ፣ ለመለወጥ ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2206 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3049 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ቤቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችለው ስልጣንና ችሎታ በነበረው ጊዜ ሆኖ እያለ ይህንን መሠረታዊ ነጥብ ሣይመረምር እና ሣይመዝን ሁለተኛ የውክልና ማስረጃ ተዓማኒነት ያለው ማስረጃ ነው ወይስ በሀሰትና በማጭበርበር የተገኘ የሚለውን ነጥብ ብቻ ነጥሎ በማየት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪዎች ተወካይ መካከል የተደረገው የመያዣ ውል ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንደዚሁም የይግባኝ ክርክሩን በመስማት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ያፀናው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያበለት ውሣኔ ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 03926 ሰኔ 30 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፣ ይፃፍ፡፡
2. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 23780 መስከረም 26 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል ይፃፍ፡፡
3. አመልካች ከተጠሪዎች ወኪል ከአቶ ገዛኸኝ በልሁ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በፊት በነበረው ስያሜ በወረዳ 19 ቀበሌ 22 የሚገኘው ቁጥሩ 715/2 የሆነውን ቤት በመያዣነት በመያዝ ብር 200,000



/ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ያበደረው ብድር በሕግ ፊት አስገዳጅነት ያለው ውል ነው ብለናል፡፡ አመልካቹ ይህንኑ አውቆ በአዋጅ ቁጥር 90/1997 በተሰጠው ስልጣንና ሀላፊነት መሠረት ተገቢውን ይፈጽም ዘንድ የፍርድ ግልባጭ ከመሸኛ ጋር ይሰጠው፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በአዳሪ ተሰርቶ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ.ቁ. 20890

ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ

አክሊሉ ተስፋዬ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዓለምነሽ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ከሥር 2ኛ ተከሣሽ ጋር ያደረገው የብድር ውል የተጭበረበረ የውክልና ሰነድን መሠረት በማድረግ ስለሆነ አመልካች የተጠሪን ቤት መያዣ በማድረግ የሰጠው ብድር ፈራሽ ነው በማለት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ የአሁን ተጠሪ የሆኑት በአሁን አመልካችና በሥር 1ኛ እና 2ኛ ተከሣሾች በሆኑት ላይ በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተከሣሽ የቡሌ ሆራ ወረዳ ፍትሕ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ ሆኖ ሲሠራ ለ2ኛ ተከሣሽ የግል ቤቴን ለባንክ መያዣ ሰጥቶ ገንዘብ እንዲበደር የሚል ውክልና እኔ ሳላውቀው በተጭበረበረ ሁኔታ በመስጠት እንዲሁም 2ኛ ተከሣሽም ይህንኑ እኔ ያልሰጠሁትን ውክልና ለ3ኛ ተከሣሽ ለአሁን አመልካች በማቅረብ ገንዘብ የተበደረ ስለሆነ የብድርና የመያዣ ውሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙ አከራክሮና የውክልና ሰነዱ ላይ ያረፈው ፊርማ የተጠሪ ስለመሆኑ በፌዴራል ፖሊስ የፎረንሲክ ምርመራ መምሪያ በኩል ተመርምሮ ውጤቱ እንዲገለጽለት ትእዛዝ ሰጥቶ መምሪያው በትእዛዙ መሠረት ሰነዱን መርምሮ ፊርማው የተጠሪ አለመሆኑን በመግለጽ ለፍ/ቤቱ ሙያዊ አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ 1ኛ ተከሣሽ የሐሰት ማስረጃ በመስጠት 2ኛ ተከሣሽ ደግሞ የሐሰት ማመልከቻ በማቅረብ የከሣሽን (ተጠሪ) ቤት ለ3ኛ ተከሣሽ (ለአመልካች) በማስያዝ ገንዘብ መበደሩ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ተሰጥቷል በተባለው ውክልና ላይ ያረፈው ፊርማ የከሣሽ አለመሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ጥቅምት 16 ቀን 1998 ዓ.ም በካርታ ቁጥር 36/81 በተመዘገበው በ210 ካ/ሜትር ቦታ ላይ በተገነባው የከሣሽ ቤት የተደረገው የመያዣና የብድር ውል ፈራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪን አከራክሮ በአመልካችና በሥር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገውን ውል ለማፍረስ የሚችል በቂና ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይ? የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ መዝገቡን በመመርመር አመልካች ከሥር 2ኛ ተከሣሽ ጋር ውሉን የተዋዋለው ተጠሪ ለሥር 2ኛ ተከሣሽ የሰጡትን ልዩ ውክልና መሠረት በማድረግ ነው፣ የውክልና ሥልጣኑ የተፈረመው ውል ለመዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት ስለሆነና ይህ ሰነድ የጽ/ቤቱ ማህተምና የባለሥልጣን ፊርማ ያለው መሆኑን ብቻ አመልካች ማረጋገጥ ከሚጠበቅበት በስተቀር ማስረጃውን ለመጠራጠርም ሆነ ስለማስረጃው ተጨማሪ ማጣራት ለማድረግ ግዴታ የሌለበት በመሆኑ በከፍተኛው ፍ/ቤት የብድሩ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተቀባይነት የለውም በማለት ሽሯል፡፡

ተጠሪም በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ የካቲት 10 ቀን 1990 ዓ.ም ተሰጠ የተባለው የውክልና ማስረጃ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክፍል ተመርምሮ በውክልና ሰነዱ ላይ የይግባኝ ባይ ፊርማ ነው ተብሎ የሠፈረው የይግባኝ ባይ (የአሁን ተጠሪ) አለመሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ የውክልና ማስረጃው ይዘትም ሲታይ ስርዝ ድልዝ ያለበትና በግልጽ

ለመጠራጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎች የሚስተወሉበት ሆኖ እያለ አመልካች ቤቱን በመያዣ በማድረግ ብድር ከመሰጠቱ በፊት ተገቢውን ማጣራት ሲገባው አጠራጣሪ ሆኖ የሚታየውን የውክልና ማስረጃ በመቀበል የብድር ውል ወደ መፈረም የገባው ያለአግባብ ነው በማለት በሰፊው ተችቶ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር በአመልካችና በሥር 2ኛ ተከሣሽ መካከል የተደረገው የመያዣና የብድር ውል በሕግ አግባብነት ስላልተቋቋመ ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል።

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የውክልና ውሉ ፊርማው የተጭበረበረ መሆኑ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ በመረጋገጡና ውል አዋዋይም ተጠሪ እኔ ፊት ቀርቦ አልፈረመችም በማለቱ የመያዣና የብድር ውሉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲፈርስ መወሰኑ ለሰበር ችሎት ቀርቦ መጣራት የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል።

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ከአመልካች ጋር የተደረገው የብድርና የመያዣ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ከሕጉ አኳያ አግባብነቱ እንደሚከተለው ተመርምሯል።

አመልካች ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት መያዣ በማድረግ የብድር ውል የተዋዋለው ተጠሪ ለሥር 2ኛ ተከሣሽ የሰጡትን ልዩ የውክልና ሥልጣን መሠረት በማድረግ ነው።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህ የውክልና ሥልጣን በአግባቡ የተሰጠ አይደለም ወደሚል ድምዳሜ መድረስ የቻለው በአንድ በኩል የውክልና ሰነዱ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ተመርምሮ በሰነዱ ላይ ያረፈው ፊርማ የተጠሪ አይደለም ተብሎ ስለተረጋገጠና በሌላም በኩል ተጠሪ ወረዳው ፍትሕ ጉዳይ ጽ/ቤት ቀርቦ በውክልናው ሰነድ ላይ እንዳልፈረመች ውክልናውን አስፈርሟል በተባለው ሠራተኛም ጭምር የተረጋገጠ በመሆኑና የውክልና ሰነዱም ሲታይ ስርዝ ድልዝ ያለበትና በግልጽ ለመጠራጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎች



የሚስተውሉበት ስለሆነ ቤቱን መያዣ በማድረግ ብድር ከመሰጠቱ በፊት ተገቢውን ማጣራት ማድረግ ይጠበቅበት ነበር የሚል ትችት በማስፈር ነው።

በመሠረቱ በባለሥልጣን ፊት የተደረጉ ጽሁፎች በግልጽ ከሚደረጉ ጽሁፎች የሚለዩ ሲሆን በግል የሚደረጉ ጽሁፎች (non-authentic deeds) ተዋዋዮች በግል ችሎታቸው የሚያዘጋጇቸው ውልን የሚመለከቱ ሰነዶች ናቸው። በባለሥልጣን ፊት የሚደረጉት ደግሞ ለዚሁ ሥራ ተብሎ የተሰየመ ባለሥልጣን ሰነዱን የተመለከታቸውና ምስክርነቱንም የሰጠባቸው ናቸው።

ሰነዱ በባለሥልጣን ተረጋግጦ እስከቀረበ ድረስ በሰነዱ መሠረት ግዴታ የሚገባው ወገን ማረጋገጥ ያለበት ፊርማውንና ማኀተሙን በመመልከት ሰነዱ በባለሥልጣን ፊት መረጋገጡን ብቻ እንጂ ከዚህ አልፎ የሰነዱን ትክክለኛነት ሊሆን አይችልም።

እዚህ ላይ ተጠሪ በሰነዱ ላይ ያረፈው ፊርማ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ተመርምሮ የተጠሪ ፊርማ እንዳልሆነ ቢረጋገጥም ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ማጣራት የሚጠበቅበት ውሉ በባለሥልጣን ፊት መደረጉንና ባለሥልጣን ምስክርነቱን የሰጠበት ስለመሆኑ እንጂ የፊርማውን ትክክለኛነት ማጣራት የሚጠበቅበት አይሆንም። ይልቁንም በመርህ ደረጃ በባለሥልጣን ፊት በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉትን ፊርማዎችና የሰነዶቹን ይዘት ማስተባበል እንደማይችል ይሄውም ውሉን የሚያዋውሉት ሰዎች የሕዝብ አደራ የተቀበሉና አደራውን ወደ ጎን በማድረግ ሐሰተኛ ሰነድ ያዘጋጃሉ ተብሎ ስለማይገመት ነው።

ስለሆነም ሰነዱ ተመርምሮ ፊርማው የተጠሪ አለመሆኑ ቢረጋገጥም ይህ ሁኔታ ሰነዱን ባፈራረመው ባለሥልጣንና ከዚሁ ባለሥልጣን ጋር ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ፈጽሟል በሚባለው ግለሰብ ላይ የክስ ምክንያት ከሚሆን በስተቀር በባለሥልጣን የተረጋገጠውን የውክልና ሰነድ አመልካች ከቶውንም ሊጠራጠር ስለማይችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በመሻር የመያዣና የብድር ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም።

## ው ሣ ኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በአመልካችና በሥር 2ኛው ተከሣሽ መካከል የተደረገው የብድርና የመያዣ ውል በተጭበረበረ ሰነድ ላይ ተመሥርቶ የተደረገ ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ይህንኑ ውሣኔ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 23861

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ሊቀስዩማን አስፋ በሻህውረድ ወኪል ጀነነው አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሣህሊተ ምህረትና ክርስቶስ ሳምራ ደብር አስተዳደር አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል

## ፍ ር ድ

ለዚህ አቤቱታ መንስኤ የሆነው የአመልካች ወኪል ጀነነው አሰፋ የተባለው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክስ መስርቶ ክሱ በመታየት ላይ እያለ ፍ/ቤቱ አቶ ጀነነው አሰፋ ክሱን የመሠረተው "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ" ብሎ ፅፉል፣እሱ ወኪል እንጂ ከሳሽ ሊሆን አይችልም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረጉና በከፍተኛው ፍ/ቤትም አያስቀርብም በመባሉ ነው፡፡

ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው አቤቱታ መሠረተ ሃሳብም አቶ ጀነነው አሰፋ የአመልካች ወኪል በመሆኑ ክሱን የመሠረተውም አመልካችን ወክሎ እንጂ በራሱ ስላልሆነ ክሱ ውድቅ የተደረገው በማይገባ ነው በማለት ነው፡፡

አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ለተጠሪ መጥሪያ ተልኮለት ባለመቅረቡ ክርክሩ በሌለበት ታይቷል፡፡

የሥር ፍ/ቤት የአመልካቹ ወኪል "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ" በማለቱ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.33 መሠረት ክስ ማቅረብ አይቻልም ብሏል፡፡ ፍ/ቤቱ ውሣኔ በሠጠበት በግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም በውሣኔው ላይ የመዘገበው "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ" ብሎ ነው፡፡ በነሐሴ 2 ቀን 1995 ዓ.ም በቀረበው የክስ ማመልከቻ ላይ ግን "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ ሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ወኪል" ተብሎ ተፅፏል፡፡

የውክልና ሥልጣን ያለው ሰው በዋናው ባለመብት ስም የክስ ወይም የአቤቱታ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 58 ይደነግጋል፡፡ አቶ ጀነነው አሰፋ የሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ወኪል መሆኑ በፍ/ቤቱም የተገለፀ በመሆኑ አመልካቹን ወክሎ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ ክስ የመሠረተውም በውክልናው መሠረት ለመሆኑ ለየካ ምድብ ፍትሃብሄር ችሎት የፃፈው የክስ ማመልከቻ ያረጋግጣል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ በመጥቀስ በጉዳዩ ላይ መብት ስለሌለው ሊከስ አይችልም ማለቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም ክስ የመሠረተው በውክልናው እንጅ ባለመብት ነኝ በማለት ስላልሆነ ነው፡፡

ፍ/ቤቱ ውሣኔ በሰጠበት ዕለት "ከሳሽ ጀነነው አሰፋ" ብሎ ይመዝገብ እንጂ የክስ ማመልከቻው ከሳሹ (ወኪሉ) የሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ወኪል መሆኑን ያሣያል፡፡ ወኪሉ ወኪል መሆኑን እስካሣየና እስከገለፀ ድረስ በማመልከቻው ላይ የራሱን ወይም የወካዩን ስም አስቀድሞ መፃፉም ቢሆን ወኪልነቱን ለውጦ ባለመብት የሚያደርገው አይሆንም፡፡ በክስ ማመልከቻው ላይ ባለመብት ናቸው ተብለው ዋነኛ የጉዳዩ ባለቤት ተደርገው በዝርዝሩ የተጠቀሱት የአሁን አመልካች ሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ናቸው፡፡ ይህ እየታወቀ ወኪሉ በከሳሽነት ዘንግ ሆኖ ክስ መስርቷል በሚል ክሱ ውድቅ መደረጉ ስህተት ነው፡፡

ወኪሉ በክስ ማመልከቻው ላይ የራሱን ስም ከወካዩ አስቀድሞ መፃፉን ፍ/ቤቱ ግልፅነት ይጎለዋል እንኳን ብሎ ቢገነዘብ ይህንኑ አስተካክሎ እንዲያቀርብ ማድረግ ሲችል ክሱን ያለመቀበሉ ተገቢ ባልሆነ አሠራር ሙግት እንዲራዘምና ባለጉዳይ እንዲጉላላ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ተወስኗል፡፡



**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33 በመጥቀስ መዝጋቱም ሆነ ከፍተኛው ፍ/ቤትም ይግባኙን መሠረዙ ተገቢ ስላልሆነ ውሣኔዎቹን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348/1/ መሠረት ሽረናል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቶ ጀነነው አሰፋ የሊቀስዩማን አሰፋ በሻህውረድ ወኪል በመሆን የመሠረተውን ክስ ተቀብሎ ግራ ቀኙን በማከራከር ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥ ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 26399

ኅዳር 05 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ኃ/ማርያም ባዩ - ጠበቃ አቶ ማርቆስ ወ/ሰንበት ቀረበ።

**ተጠሪ፡-** 1ኛ/ አቶ ሳሙኤል ጎሳዬ

2ኛ/ ወ/ሪት ፀሐይ ጎሳዬ

3ኛ/ ወ/ት መንበረ ጎሳዬ

4ኛ/ ወ/ት ወይንሸት ጎሳዬ

5ኛ/ መቅደስ ጎሳዬ

ከ2ኛ እስከ 5ኛ ያሉት ጠበቃ አቶ ኃይሉ አግዘው አልቀረቡም።

1ኛው ተጠሪ በዚህ የሰበር ክርክር እንዲቀርብ በምትክ መጥሪያ ጥሪ ተደርጎለት በጥሪው መሠረት አልቀረበም። በሌላ ወገን አመልካችነት በተመሣሣይ ጥሪው ተደርጎ አለመቅረቡን በማረጋገጥ ጉዳዩ ይኸው ተጠሪ በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ በሰበር መ/ቁ. 22556 ትዕዛዝ የተሰጠበት ስለሆነ ይህም ጉዳይ እርሱ በሌለበት እንዲሰማ ተደርጓል።

እኛም ጉዳዩን ተመልክተን ፍርድ ሰጥተናል።

<u>ፍ ር ድ</u>

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በመ/ቁ 23363 ሐምሌ 03 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልበትን ነጥብ በመደርደር አመልካች ይኸው ውሣኔ እንዲሻር በመጠየቁ ነው።

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው።



ከተራ ቁጥር 2 እስከ 5 ድረስ የተዘረዘሩት ተጠሪዎች በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ ሆነው በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርበዋል። የክሱም ፍሬ ቃል ከሟች አባታችን ከአቶ ጎሳዬ ሩጋቶ በወረዳ 05 ቀበሌ 06 የቤት ቁጥር 586 የተመዘገበውንና በውርስ የተላለፈልንን የጋራ ሀብታችንን እንዲያስተዳድርልን እና እንዲሸጥ ውክልና ሰጥተነው የነበረ ቢሆንም ውክልናው ከተሻረ በኂላ መሻሩን እያወቀ ስለሸጠው የተደረገው የሽያጭ ውል ይፍረስልን የሚል ነው።

ክስ የቀረበለት ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ ጥር 03 ቀን 1994 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሽያጭ ውል እንዲፈርስ አድርጎ ተዋዋዮቹ ወገኖች ሻጭና ገዢ ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ወስኗል።

የአሁን አመልካችም ይህ ውሣኔ በተሰጠበት ጉዳይ የክርክር ተካፋይ መሆን ይችል የነበረ መሆኑን በማሳየት ውሣኔው ተነስቶና የእርሱ ክርክር ተሰምቶ እንደገና ዳኝነት ይሰጥበት ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሠረት አቤቱታ አቅርቧል። በዚህም አቤቱታ ላይ፡-

- ከሣሾች ካቀረቡት ክስ እና ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሣኔ መረዳት እንደሚቻለው ውሉ ተሰርዞ ይረከቡት የተባለው የንግድ ድርጅት እና የንግድ ሥራው የሚከናወንበት ቤት የባለሃብትነትና የይዞታ ባለመብት በመሆን ይዘው የሚጠቀሙበት አቤቱታ አቅራቢ ወይም ተቃዋሚ በመሆናቸው የተሰጠው ውሣኔ መብቴን ይነካል።
- እንዲሁም ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ 3ኛ ወገኖች ከተዋዋይ ወገኖች መካከል አንዱን ብቻ በመክሰስ ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉትን ውል ለማሰረዝ የሚያስችል የሕግ መሠረት የላቸውም።
- የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ ለማስደገፍ የጠቀሳቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2190/2/ እና 2193/1/ ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች አይደለም።
- በቁጥር 2190/1/ እና /2/ የተደነገገው በመሠረቱ በቁጥር 2191 እና በቁጥር 2193/1/ ከተደነገጉት ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ከ3ኛ ወገን ጋር

የተደረገውን ውል ማፍረሱን ወካይ በግልጽ ወይም በዝምታ ለ3ኛ ወገን ባስታወቀው ጊዜ ውሉ እንዲፈርስ እንደሚቆጠር የውሉ መፍረስም ስለሚያስከትለው ውጤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1808-1818 የተደነገገው ተፈፃሚ እንደሚሆን በቁጥር 2193/1/ ሥር የተመለከተው ከሚገልጽ በስተቀር ውሉ እንዲፈርስ ወካዩ በፍ/ቤት ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ተዋዋዮችን የክስ ተከፋይ ሲያደርግ ወይም ከተዋዋዮቹ መካከል ተወካዩን ብቻ የክሱ ተከፋይ በማድረግ ከ3ኛ ወገን ጋር የተደረገውን ውል በማፍረስና በ3ኛ ወገን እጅ የሚገኘውን ንብረት ለማስለቀቅ እንደሚያስችል የሚደነግግ አይደለም፡፡

- ተወካይ የተባለው ተከሣሹ እና ተቃዋሚው የተዋዋሉበት ንብረት ከመጋቢት 09 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ ተመዝግቦ የሚገኘው በዚሁ በሻጩ ስም በመሆኑ፣
- የውክልና ሰነዱም ከአባታቸው የውርስ ሀብት ውስጥ የሚደርሳቸውን ድርሻ እንዲያስተዳድርላቸው፣ እንዲሸጥና እንዲለውጥላቸው የሚያሳይ እንጂ ክርክር ያስነሳውን ንብረት በተለይ የሚጠቀስ ባለመሆኑ፣
- ተቃዋሚው በተከሣሹ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ድርጅት ገዝተውና የንግድ ሥራው የሚከናወንበትን ቤት በስማቸው በማስመዝገብ ድርጅቱን ለሌላ ለ3ኛ ወገን በሽያጭ አስተላልፈውት የሚገኝ በመሆኑ፣
- ከሳሾች የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ ስለመሆኑ አግባብ ባለው ማስረጃ ያላረጋገጡ በመሆኑ የሚሉትን በመጥቀስ እንደዚሁም የሕግና የፍሬ ነገር ክርክሮች ታይተው እንደገና ሊወሰንልን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተከሳሽም የተቃዋሚውን የመከራከሪያ ነጥብ እንደሚቀበሉት ገልፀው የተሰጠው ውሣኔ እንዲሻር ጠይቀዋል፡፡

በከሣሾች በኩል የቀረበው ክርክር ደግሞ ሲታይ፡-



- ምንም እንኳ ከሳሾች በተቃዋሚውና በተከሳሹ መካከል የተደረገው ውል እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2190/2/ በተደነገገው መሠረት ውሉን የማፍረስ መብታቸው በሕግ የተሰጠ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ፍሬ ነገር ከሕጉ ጋር በማገናዘብና በመተርጎም ውሣኔ የመስጠት ሥልጣኑን ተጠቅሞ ይህን ሕግ የተመለከተውን ጉዳይ ተቀብሎ ወስነ እንጂ ክርክሩ የውል ይፍረስ አይፍረስ ጉዳይ አይደለም፡፡

ስለሆነም ከሳሾች ውሉን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2190/2/ መሠረት በማፍረሳቸው ተቃዋሚው የሚኖረው መብት ውሉ እንዳይፈርስ ወይም እንዳይፀና በማለት መከራከር ሳይሆን በውሉ መፍረስ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ካለ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2193፣ 2194 እና 2195 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ በመክፈል በተለየ ክስ ዳኝነት መጠየቅ ነው፡፡

የንግድ ሥራው የሚንቀሳቀስበትን ቤት በስማቸው ማስመዝገባቸውን መነሻ በማድረግ የተከራከሩ ቢሆንም የንግድ ሥራ የሚንቀሳቀስበት ቤት የንግድ ድርጅቱ አካል መሆኑ በንግድ ሕጉ የተደነገገ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

የሽያጭ ውል የተደረገበት የንግድ ድርጅት በተከሳሽ ማለትም በተወካዩ ስም የተመዘገበ ነው የተባለውን አስመልክቶ ለማስረዳት ያቀረቡት ማስረጃ በቤት ቁጥር 586/ሀ/ የተጠቀሰ መሆኑን የሚያስረዳ እንጂ የአባታችን ንብረት የሆነውን ቁጥር 586 የሚጠቅስ አይደለም፡፡ ይህም ንብረት በቁጥር 586/ሀ/ እና/ለ/ ተብሎ ተከፍሎ አይታወቅም፡፡

ሿሚው ለእንደራሴው የሰጠውን ሥልጣን የሚሽርበት ሁኔታ የተለየ ሥርዓት እንደሚከተል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2183 የተመለከተ በመሆኑ የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ ስለመሆኑ በተገቢው ማስረጃ አልተረጋገጠም የሚለው መከራከሪያ ሕጋዊ መሠረት የለውም የሚል ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 360/2/ መሠረት ጉዳዩን የመረመረው ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 01927 ሰኔ 12 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተቃዋሚው ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የንግድ መደብሩን አስመልክቶ የተደረገ ውልን ለማሰረዝ ብቻ ሳይሆን የማይንቀሳቀስ ንብረት የሆነውን ቤት ጭምር ለማስለቀቅ ነው በማለት ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አስቀድሞ ውሣኔ የሰጠበት ጉዳይ የንግድ ድርጅትን የሚመለከት ነው። የንግድ ድርጅት ሲባል ደግሞ ድርጅቱ የሚገኝበትን ቤት የመከራየት መብትንም የሚያካትት በመሆኑ ክርክር በቤቱም ላይ ተደርጓል፤ ውሳኔም በቤቱ ላይ ተሰጥቷል ለማለት አያስችልም።

በሌላ በኩል ተዋዋይ ወገን ያልሆኑ ሦስተኛ ወገኖች ተዋዋይ ወገኖች ያደረጉትን ውል ለማሰረዝ ከተዋዋይ ወገኖች አንዱን ብቻ ነጥለው ለመክሰስ የሚያስችላቸው የሕግ መሠረት የላቸውም በሚል የቀረበውን ጉዳይ በሚመለከት ወካዮች ከሳሾች እንደራሴው ቀሪ በሆነው ሥልጣኑ የሠራውን ሥራ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090/2/ መሠረት በተሰጣቸው መብት መሠረት መሻራቸውን ፍ/ቤቱ ከማረጋገጥ አልፎ ውል እንዲፈርስ ወይም እንዲሰረዝ የሰጠው ውሣኔ የሌለ መሆኑን ካለማገናዘብ የቀረበ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም በሌላ አገላለጽ የድርጅቱ ሽያጭ ውል የፈረሰው በፍ/ቤቱ በተሰጠው ውሣኔ ሳይሆን ከሳሾች በሕግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ነው።

እንደራሴው ቀሪ በሆነው ሥልጣኑ የሠራውን ሥራ ወካዩ የመሻር ሥልጣን ያለው ለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2190/2/ የተደነገገ በመሆኑ ይህንን በማድረግ በቁጥር 2191 እንደተደነገገው የ3ኛ ወገን ጥያቄ የማቅረቡ ጉዳይ እንደቅድመ ሁኔታ የሚታይ አይደለም። የ3ኛ ወገኑም ግዴታ አይደለም ስለሆነም በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክርም ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

እንደዚሁም የሽያጭ ውሉ ከመፈፀሙ በፊት የወክልና ሥልጣኑ የተሻረ መሆኑን የመስቀለኛ ጥያቄ በተቃዋሚዎች አማካኝነት በቀረበላቸው ምስክሮች በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑና ይህንንም ጉዳይ በምስክር ለማስረዳት የሚከለክል ሕግ ባለመኖሩ ማስረጃው ተቀባይነት የለውም በሚል ያቀረቡት ክርክር ዋጋ ያለው አይደለም፤ የሚሉትን ምክያቶች በመንተራስ ተቃዋሚው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2195 መሠረት ኪሣራ ከሚጠይቁ በቀር በዚህ መዝገብ የተሰጠውን ውሣኔ ለማሻር የሚያበቃ ምክንያት አልተገኘም በማለት ከዚህ በፊት የሰጡትን ውሣኔ አጽድቋል።



ይግባኙን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ውሣኔውን አጽንቷል።

የሰበር አቤቱታው ፍሬ ቃል በሥር ፍ/ቤት በተሰጠው ውሣኔ ላይ ተፈጽሟል የተባለውን የሕግ ስህተት በዝርዝር የሚገልጽ ከመሆኑ በቀር በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት ከተነሣው ክርክር የተለየ ባለመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም። እንዲሁም ለሰበር አቤቱታው በተጠሪ በኩል የተሰጠው መልስ ከዚህ በፊት ከተደረገው ክርክርም የተለየ አይደለም።

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል።

በአንድ ውል ተዋዋይ ያልሆኑት ሦስተኛ ወገኖች አንዱን ተዋዋይ ለብቻ ለይተው ለመክሰስ የሚያስችላቸው የሕግ መሠረት ሳይኖር በዚህ አኳኋን የቀረበው ክስ ሥነ-ሥርዓታዊ አልነበረም፣ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚለውን ነጥብ እንደ አንድ የሰበር ቅሬታ አድርገው አመልካች ማቅረባቸውን ተገንዝበናል። ይሁን እንጂ እንደተባለው የአሁን አመልካች በዚህ በተነሣው ክርክር የሙግት ተካፋይ መሆን እየተገባው ተከፋይ ሳይሆን ጉዳዩ እንዲታይ መደረጉ በአንድ ሙግት የክርክር ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች እነማን ናቸው? የሚለውን አስመልክቶ ከሚደነግገው የሕግ ክፍል አንፃር ሲታይ የክሱ አቀራረብ የሕግ ግድፈት የተፈፀመበት መሆኑን ያሳያል። ይሁን እንጂ ይህ መሆኑ እንደታወቀ በክርክር አመራር ረገድ የተፈፀመን ጉድለት ፍርድ ከተሰጠም በኋላ ቢሆን ፍርዱን በሰጠው ፍ/ቤት እንደገና ከሚታይላቸው ሥርዓቶች ይህ አንዱ መሆኑ ተረጋግጦ አመልካች የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነበት ጉዳይ የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካ መሆኑን መነሻ በማድረግ ውሣኔው እንዳልተሰጠ ተቆጥሮ አመልካች ባለበት ክርክሩ

እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ ከመሰማት መብትም ሆነ ከሚዛናዊ የዳኝነት አካሄድ አንፃር በአመልካች ላይ የተጓደለበት ሥርዓት ከላይ በተገለፀው ሁኔታ ተስተካክሎ አመልካች አለኝ የሚለውን የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ክርክር የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የቀረበው የሰበር ቅሬታ ነጥብ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካቾችን የመከራከር መብት ከጠበቀ በኋላ ከዚህ በፊት ሰጥቶት የነበረውን ውሣኔ ለማጽናት በዋነኛነት መሠረት አድርጎ የያዘው ነጥብ ለተወካይ የተሰጠው የውክልና ሥልጣን ቀሪ ከሆነ በኋላ በወካዩ ስም ሕጋዊ ተግባር ፈጽሞ ከተገኘ እና ወካዩም ይህንኑ ተግባር ካላፀደቀው ወይም ካልተቀበለው ተወካዩ የፈፀመው ውል ፈራሽ መሆኑን ሕጉ ይደነግጋል፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ ውልን የማፍረስ መብት ለወካዩ በሕግ የተሰጠው ሥልጣን በመሆኑ በዚህ አኳኋን የተፈፀመው ውል ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን አስመልክቶ ፍ/ቤቶች ዳኝነት የመስጠት መብት የላቸውም የሚለውን ነው፡፡

ይሁን እንጂ ስለዚሁ ጉዳይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች እርስ በርሳቸው አስተሳስረን ከተመለከትናቸው ከዚህ መሰል ትርጉም የሚያደርሱ ሆነው አይታዩም፡፡

ይኸውም እንደራሴው ቀሪ በሆነው ሥልጣን መሠረት በሌላ ሰው ስም ወይም ወካይ በነበረው ሰው ስም በሠራ ጊዜ በስሙ የተሠራበት ሰዉ እንደፈቃድ በስሙ የተሠራውን ሥራ ለማጽደቅ፣ ለመቀበል ወይም ለመሻር መብት አለው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2191/2/ ከተደነገገ በኋላ በዚሁ በተሰጠው መብት ተጠቅሞ አንዱን መንገድ እንዲከተል ወይም እንዲመርጥ ከእንደራሴው ጋር የተዋዋሉት ሦስተኛ ወገኖች ለማስገደድ እንደሚችሉ እና aሚው ከሦስተኛ ወገኖች በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ወዲያውኑ ካላስታወቃቸው እንደራሴው የሠራውን ሥራ እንዳልተቀበለው ሕጉ ግምት የወሰደ ለመሆኑ ተከታይ በሆነው ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡



እንግዲህ aሚው በግልጽም ይሁን በዝምታ እንደራሴው ሥልጣኑ ቀሪ ከሆነ በኋላ የሠራውን ሥራ ያልተቀበለው መሆኑ ከተረጋገጠ የዚሁ ያለመቀበል ውጤት በቁጥር 2193 ተደንግጓል፡፡ የዚህን ድንጋጌ ይዘት ስንመለከት aሚው ይህንኑ የእንደራሴውን ሥራ ካልተቀበለው ምን ጊዜም ይኸው ውል ፈራሽ ነው የሚል አይደለም፡፡ ይልቁንም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808 እስከ 1818 ድረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተከትሎ የውሉ መፍረስ ወይም መሰረዝ ሊወሰን የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም እነዚህኑ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመከተል ውሉ ሊፈርስ የማይችልበት አጋጣሚ ያለ መሆኑን የሚያሳይና ነገር ግን ውሉ የሚፈርስ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ውሉ በመፍረሱ ምክንያት በቅን ልቦና ከእንደራሴው ጋር በተዋዋሉት 3ኛ ወገኖች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ካሣ የሚጠየቅበት መንገድ የሚያመቻች ድንጋጌ ነው፡፡

ይህ ሆኖ እያለ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የaሚው ፈቃድ ያልተሰጠበት መሆኑ በተረጋገጠ ጊዜ ሕጉ በእራሱ ውሉን ፈራሽ ያደርገዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ይህንኑ በሕግ የተሰጠውን ሥልጣን ከማወቅ አልፎ ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ነጥብ ላይ ዳኝነት የመስጠት ሥልጣን የለውም በሚል የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች የንግድ ድርጅቱን ከ1ኛ ተጠሪ ከገዛ በኋላ መልሶ ለሌላ ሦስተኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፈውና በእጁ የማይገኝ የመሆኑ ጉዳይ በተጠሪዎችም የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ እንደራሴው የውክልና ሥልጣኑ ቀሪ ከሆነ በኋላ የፈፀመው ተግባር ነው ከተባለና ይህንኑ ተግባር aሚው አልተቀበለውም ከተባለ የዚሁ የአለመቀበል ውጤት ከላይ እንደተመለከተው ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808-1818 የተመለከቱትን ድንጌዎች ተከትሎ የሚወሰን ይሆናል፡፡

ከላይ ከተረጋገጠው ፍሬ ቃል አንፃር አግባብነት ያለው ድንጋጌ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1816 ነው፡፡ ይኸውም ግራ ቀኙ በጉዳዩ ላይ በተከራከሩበት ጊዜ

አከራካሪውን ንብረት ሌላ ሦስተኛ ወገን ከአመልካች ገዝቶ በእጅ አድርጎት ይገኛል፡፡ በዚህም ድንጋጌ መሠረት በቅን ልቦና ለሆነ ሦስተኛ ወገን የተሠራው ሥራ ውጤት ጠቃሚ ከሆነ ይህ ይፍርስ አይፈርስ የሚለው ውል እንደረጋ እንዲቀር ያደረጋል የሚል በመሆኑ የዚህ ክርክር አድማስ በአመልካችና በተጠሪዎች ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን የሦስተኛ ወገኖችንም ጥቅም የሚጠብቅ ነው፡፡ ስለሆነም የዚህን 3ኛ ወገን መብት ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑት የቀና ልቦና እና የተሠራው ሥራ ውጤት ጠቃሚነት መስፈርቶች የተሟሉ ሆነው እስከተገኙ ድረስ የ3ኛውን ወገን መብት ከመጠበቅ አንፃር ይህ አከራካሪ የሆነው ውል የሚፈርስ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በመሆኑም የተሸጠው ንብረት በሻጩ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ነው? ወይስ አይደለም? ሻጩ በእራሱ አቋም የሠራው ሥራ ነው? ወይስ ቀሪ በሆነው በእንደራሴነቱ ሥልጣን? ወደሚሉት አከራካሪ ነጥቦች ዘልቆ መመርመር ሳያስፈልግ ከላይ በተገለፀው የሕግ ትርጓሜ አመልካች እና 1ኛ ያደጉት ውል ሊፈርስ የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01927 ሰኔ 12 ቀን 1995 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23363 ሐምሌ 03 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና 1ኛ ተጠሪ ሳሙኤል ጎሳዬ ጥር 24 ቀን 1993 ዓ.ም. በወረዳ 05 ቀበሌ 06 በቤት ቁጥር 586/ሀ/ በተመዘገበው ቤት ላይ ያደረጉት ውል ሊፈርስ አይገባም፤ የረጋ ነው ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 32241

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ካሣች ተካልኝ - ጠበቃ ጌታቸው ሞላ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ኃ/ማርያም አበበ - ቀረቡ፡፡
2. ወ/ሮ ትዕግሥት ዱሬሣ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን ንብረት እንዲያስተዳድር በአመልካች አማካኝነት ጥቅምት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. የውክልና ስልጣን ተሰጥቶት የነበረ ሲሆን ከዚያ በኋላም 1ኛ ተጠሪ አመልካችን አግባብቶ ቃለመሐላ ትፈጽሚያለሽ በማለት ወደ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመውሰድ አመልካች አንብቤ ምንነቱን ያልተረዳሁትን ሰነድ ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. እንድፈርም አድርጎኛል፡፡ ከዚያም አመልካች ያለአግባብ ለ1ኛ ተጠሪ ውክልና መስጠቴን ስገነዘብ በማግስቱ ሚያዝያ 20 ቀን 1998 ዓ.ም. ውክልናውን ሽሬያለሁ፡፡ ሆኖም ሰነዶቹ 1ኛ ተጠሪ እጅ ስለነበሩ በአራዳ ክ/ከተማ የሚገኘውን የአመልካችን ጅምር ቤትና ኒሳን የቤት መኪና ለባለቤቱ ለ2ኛ ተጠሪ እጅግ አነስተኛ በሆነ ዋጋ ሸጧል፡፡

ስለሆነም 1ኛ ተጠሪ ከትሮ አጋሩ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው የቤትና የመኪና ሽያጭ ውል ከእራሱ ጋር እንደተደረገ ስለሚቆጠር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188

መሠረት ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ በሁለቱ ተጠሪዎች መካከል ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. የተደረገው የቤትና የመኪና ሽያጭ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃም ለተጠሪዎች ደርሶ የየበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

በዚህም መሠረት 1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን ንብረቶች ለ2ኛ ተጠሪ ያስተላለፉት ከአመልካች በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣና መሠረትና ከሥልጣናቸውም ወሰን ሳያልፉ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2189/1/ መሠረት ከሣሽ እራሳቸው እንዳደረጉት ስለሚቆጠር በዚህ ክስ ውስጥ 1ኛ ተጠሪ የተካተትኩት ያለአግባብ ስለሆነ ከክሱ ልሰናበት ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህንኑ መቃወሚያ መርምሮ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ውል ይፍረስልኝ የሚል ሲሆን እንዲፈርስ በተጠየቀው ውል ተዋዋይ ወገኖች ደግሞ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ስለሆኑ 1ኛ ተጠሪ አመልካችን በመወከል ውሉን ያደረጉ በመሆኑ ውሉ በማናቸውም ምክንያት የሚፈርስም ሆነ የሚቀጥል ቢሆን ውጤት የሚኖረው በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ በክሱ ውስጥ የተካተቱት ያለ አግባብ ነው በማለት ከክሱ አስወጥቷል፡፡

2ኛ ተጠሪም በበኩላቸው ባቀረቡት ክርክር አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ የሚያስችል ውክልና መስጠታቸውን በማረጋገጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤትና መኪና ከ1ኛ ተጠሪ መግዛታቸውን ውሉ በተደረገበት ሚያዝያ 19 ቀን 1998 በ1ኛ እና በ2ኛ ተጠሪ መካከል የጋብቻ ግንኙነት እንዳልነበረና ጋብቻው የተፈጸመው ከዚያ በኋላ መሆኑን ገልጸው የሽያጩ ውል ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188 ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ 1ኛ ተጠሪ ከባለቤቱ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው ውል ከእራሱ ጋር እንዳደረገው ይቆጠራል በማለት ያነሱትን ክርክር በተመለከተ በሕጉ ላይ የተደነገገው ተወካዩ



ከእራሱ ጋር ውሉን በሚያደርግ ጊዜ ሲሆን አመልካች ይፍረስልኝ በማለት የሚጠይቁት ውል ግን 1ኛ ተጠሪ አመልካችን ሻጭ እራሱን ገዢ በማድረግ ሳይሆን 2ኛ ተጠሪን ገዢ በማድረግ ስለሆነ ከእራስ ጋር የተደረገ ውል የሚያስብል ሁኔታ የለም ካለ በኋላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ጋብቻ የፈጸሙት ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ስለመሆኑ የክብር መዝገብ ኮፒ በማስረጃነት የቀረበ በመሆኑ ውሉ በተደረገበት በሚያዚያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. ሁለቱ ሰዎች ባልና ሚስት አልነበሩም፡፡ ባልና ሚስት ነበሩ ቢባል እንኳ የየራሳቸው ሰውነት /Personality/ በጋብቻው ምክንያት እንደሚጠፋና እንደ አንድ ሰው እንደሚቆጠሩ በሕግ ያልተመለከተ በመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት ውል ከገዛ እራሳቸው ጋር እንደተደረገ አይቆጠርም በማለት በውሣኔው ላይ አስፍሮ በመጨረሻም አመልካች በወኪላቸው አማካይነተ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጓቸው የቤትና የመኪና ሽያጭ ውሎች በአግባቡ በተሰጠ ሥልጣን የተደረጉ በመሆኑ ውሉ የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የቤትና የመኪና ሽያጭ ውሉ አይፈርስም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ በዚሁ መሠረት ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የጉዳዩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ የዚህን ሰበር ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ 1ኛ ተጠሪ አመልካችን በመወከል ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የቤትና የመኪና ሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባልን? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. በተሰጠ የውክልና ሥልጣን በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥንም ጨምሮ ለ1ኛ ተጠሪ የውክልና ስልጣን የሰጡ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

አወዛጋቢው ነጥብ ይህ የውክልና ስልጣን ከተሰጠ በኋላ 1ኛው ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤቶችና መኪና በሽያጭ ለ2ኛ ተጠሪ ማስተላለፋቸው ከውክልና ሕግ አኳያ አግባብነቱን በተመለከተ ነው፡፡ ይህንንም የክርክር ነጥብ የግራ ቀኙ ግንኙነት በተለይ ከሚገዛው የውክልና ሕግ ጋር በማገናዘብ ተመልክተናል፡፡

1ኛ ተጠሪ ከላይ በተመለከተው ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. የውክልና ሥልጣኑን ከአመልካች ከተቀበሉ በኋላ የዚያኑ ዕለት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ቤትና መኪና በወካዩ በአመልካች ስም ለ2ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፉ ሲሆን አመልካች ይህንን ሽያጭ የሚቃወሙት በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ መካከል የባልና ሚስት ግንኙነት ስላለ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188/1/ አኳያ ከራስ ጋር እንደተደረገ ስለሚቆጠር ፈራሽ ነው በማለት ነው፡፡

የተጠቀሰውም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188/1/ ድንጋጌ እንደራሴው ከእራሱ ጋር ውሉን ተዋውሎ በተገኘ ጊዜ ሿሚው ይሄው ውል እንዲፈርስ መጠየቅ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ነገር ግን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንደጠቀሰው የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ ጋብቻቸውን የፈጸሙት ሽያጩ ከተደረገ በኋላ ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. በመሆኑ በሕግ ዓይን የሽያጭ ውል በተደረገ ጊዜ በሁለቱ መካከል ጋብቻ አለ ለማለት ስለማይቻል አመልካች የጠቀሱት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2188/1/ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም እንደራሴው የውክልና ሥልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታ እንዳለበት /Duty to avoid conflict of interest/ ከእንደራሴውም ጋር ውሉን የፈጸመው 3ኛ ወገን የሚያውቅ



ወይንም ማወቅ የሚገባው ሆኖ በተገኘ ጊዜ በሿሚው ጥያቄ መሠረት ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ብ/ቁ. 2187/1/ ላይ ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ክርክሩም ከዚሁ ድንጋጌ አኳያ ሲታይ የሽያጭ ውሉ በተደረገ ጊዜ ተጠሪዎች ባልና ሚስት እንዳልነበሩ የተረጋገጠ ቢሆንም ሚያዝያ 19 ቀን 1998 ዓ.ም. ሽያጩ ተደርጎ ሚያዝያ 30 ቀን 1998 ዓ.ም. ከ10 ቀን በኋላ ጋብቻቸውን መፈጸማቸው ሲታይ ሽያጩ በተደረገ ጊዜ በሽያጭ የሚተላለፈው ንብረት በቅርብ እርቀት የእራስ ንብረት ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ውሉ የተደረገ መሆኑን አጉልቶ የሚያሳይ ነው፡፡ እንደራሴ ደግሞ ምንጊዜም ቢሆን የሿሚውን ፍላጎትና ጥቅም ብቻ መሠረት አድርጎ ግዴታውን ሳይወጣ ከቀረና የእራሱን ፍላጎትና ጥቅም መሠረት ካደረገ የጥቅም ግጭት መኖሩ የማይቀር ይሆናል፡፡ 2ኛ ተጠሪም እንደራሴው 1ኛ ተጠሪ በሚያደረገው የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት መኖሩን እየተገነዘቡ ውሉን ማድረጋቸው የተረጋገጠ በመሆኑ በዚሁ ሁኔታ የተፈጸመው ውል ፈራሽ ነው እንዲባል አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ከተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2187/1/ አኳያ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሉ ሊፈርስ አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69247 በሐምሌ 9 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57884 በሐምሌ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. 1ኛ ተጠሪ አመልካችን በመወከል በአራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/08 በካርታ ቁጥር 26651 ተመዝግቦ የሚገኘውን ጅምር ቤትና የሰ/ቁ. 2-52117 ኒሳን የቤት መኪና ላይ ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል የጥቅም ግጭት /Conflict of interest/ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ ስለሆነ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# ውሎች
# ዋስትና



የሰ/መ/ቁጥር 21355

ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት ነገረፈጅ አቶ ፈቃደ ጉደታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ ጉዳዩ በይግባኝ ተጠሪን የሚያስቀርብ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን መሠረዙ ለጉዳዩ መነሻ የሆነውን ውል ህጋዊነት በተሳሳተ መንገድ በመተርጐሙ የተነሳ በመሆኑ የተፈፀመው መሠረታዊ የህግ ስህተት ይታረምልን በሚል ነው፡፡

የነገሩም መነሻ የአሁኑ አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ ሲሆን ተጠሪ ተከሣሽ ነበር፡፡ አመልካች ያቀረበውን ክስ ተጠሪ ለመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ ገብቷል፡፡ ከአመልካች ጋር ውል ያደረገው በሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበረው በገባው ግዴታ መሠረት ውሉን ሳይፈጽም ያቋረጠ በመሆኑ ተጠሪ በመልካም ሥራ አፈፃም ረገድ የገባውን ግዴታ ሊፈጽም ይገባል የሚል ነው፡፡

ተጠሪም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ክርክር ከአመልካች ጋር ውል ያደረገው ድርጅት ውል ለማድረግ የሚያስችለው ህጋዊ ሰውነት የሌለው በመሆኑ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1678 መሠረት ፈራሽ ነው፡፡ ውሉ ፈራሽ ከሆነም

ይህንኑ ውል መሠረት በማድረግ የተገባው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ስምምነትም ሊፈርስ ይገባል ስለሆነም ክስ የቀረበበትን ገንዘብ እንድከፍል አልገደድም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተ በኋላ ተጠሪ ኢንሹራንስ ኩባንያው ከአመልካች ጋር ውል ያደረገው 1ኛ ተከሣሽ ባት ማስታወቂያ አገልግሎት ችሎታ የሌለው መሆኑን እያወቀ ዋስትና የሰጠ መሆኑን እንዲያስረዳ ታዞ ይህንን አልፈፀመም፤ ይህም 1ኛው ተከሣሽ ባት ማስታወቂያ አገልግሎት ህጋዊ ሰውነት ያልነበረው መሆኑን ያመለክታል፡፡ ውል ለመዋዋል ችሎታ የሌለው ሰው የፈፀመው ውልም ፈራሽ ነው፡፡ ሥራ አፈፃፀም ዋስትናው ምክንያት የሆነው ውል ፈራሽ ከሆነም፤ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1923/1/ መሠረት ዋስትናውም ቀሪ ነው፣ ወይም ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን የይግባኝ መዝገብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 337 መሠረት ዘግቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም

- የቀረበው ጉዳይ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1923/2/ አንፃር መታየት ሲገባው የሥር ፍ/ቤት በወሰነው በንዑስ ቁጥር 1 የተመለከተውን መሠረት ማድረጉ፣
- ተጠሪ ከ1ኛው ተከሣሽ ከባት የማስታወቂያ አገልግሎት ጋር የመልካም ሥራ አፈፃፀም ውል ሲያደርግ ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን ማረጋገጡን እያመለከተ ይህ ግንዛቤ ውስጥ አለመግባቱ፣
- ውል ከተደረገ በኋላ ህጋዊ ሰውነቱን አጥቶ ከሆነ መቼ እንዳጣ ወይም ምዝገባው መቼ እንደተሰረዘ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የዋስትና ግዴታው ፈራሽ ነው በሚል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት እንዲታረም የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህም የሰበር አቤቱታ መነሻ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸውን አሰምተዋል፡፡ በይዘቱም በሥር ፍ/ቤት ያደረጉትን ክርክር የሚያጠናክር ነው፡፡ እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡



እንደተመለከትነውም ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ ከነበረው ከባት ማስታወቂያ ድርጅት ጋር የመልካም ሥር አፈፃፀም ዋስትና ውል ያደረገ መሆኑን ክዶ አልተከራከረም፡፡ ህጋዊ ሰውነት ከሌለው ወገን ጋር የመልካም ሥር አፈፃፀም ዋስትና ውል ማድረጉን መነሻ በማድረግም ውሉ ህጋዊ ውጤት እንደይኖረውም ስለማድረጉም አልተገለፀም እንዲሁም ፍሬ ነገሮች የሚያመለክቱት ተጠሪ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ውል ከባት የማስታወቂያ አገልግሎት ጋር ባደረገበት ጊዜ ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን ያውቅ የነበረ መሆኑን ነው፤ እራሱ ላደረገው ውል ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን ተቀብሎ በመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትናው ውል ምክንያት ያለበትን ግዴታ እንዲፈጽም በተጠየቀ ጊዜ ተዋዋዩ ህጋዊ ሰውነት የሌለው ወገን ነው የሚለው ክርክር ወጥነት የሌለው እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፡፡

ምናልባትም ከአመልካች ጋር ውል የፈፀመው ባት የማስተወቂያ አገልግሎት ችሎታ የለውም፡፡ ችሎታ ከሌለው ሰው ጋር ውል አድርጌያለሁ፡፡ ውል ላደርግ የቻልኩትም ውሉ በተደረገበት ጊዜ ችሎታ /ህጋዊ ሰውነት/ የሌለው መሆኑን አላውቅም ነበረ በማለት ከተከራከረ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/258/1/ መሠረት ይህንኑ የማስረዳት ግዴታው በእራሱ በተጠሪ ላይ ሊሆን ይገባል፡፡

የሥር ፍ/ቤት በዚህ መሠረት ክርክሩን መምራት ሲገባው ባት የማስታወቂያ አገልግሎት ህጋዊ ሰውነት ያለው መሆኑን አመልካች ያስረዳ፤ እንዲሁም መልስ ሰጭ ከባት ማስታወቂያ አገልግሎት ጋር ውል ባደረገበት ጊዜ የማስታወቂያ አገልግሎት ድርጅቱ ህጋዊ ሰውነት የሌለው መሆኑን እያወቀ ነው ያደረገው የሚለውን አመልካች ያስረዳ በማለት የማስረዳት ሸክሙን ወደ አመልካች ማዞሩ ሥነ-ሥርዓታዊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በክርክሩም ሂደት ተጠሪ ከላይ የተመለከተውን ሁኔታ አላስረዳም፡፡

ስለሆነም ባት የማስታወቂያ አገልግሎት ከአመልካች ጋር ያደረገው ውል በህግ ፊት ሊፀና የማይችል ስለመሆኑ አልተረጋገጠም እንጂ ግዴታው

የማይፀና ነው እንኳ ቢባል ዋሱ አመልካች አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ በውል አለመጽናት ምክንያት የሆነው ጉድለት ሳያውቀው ያደረገው የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና ግዴታ መሆኑን ያላስረዳ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1923/2/ መሠረት የገባው ዋስትና የፀና ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የሥር ፍ/ቤቶች በሥር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሣሽ የነበረው ባት ማስታወቂያ አገልግሎት ድርጅት ለመክሰስ የሚያስችለው ህጋዊ ሰውነት የለውም በሚል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ የሰጡት ዳኝነት የተሻረ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ አንቀሳቅሶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍ/በ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343 መሠረት መልሰናል፡፡
2. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/ቁ. 10894 ሚያዚያ 22 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. ፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 32599 ሰኔ 06 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር ፋይል ቁጥር 25115

ጥቅምት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
አብዱራሂም አህመድ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** አቶ ማሞ ጉበና አልቀረቡም ከተባለ በኋላ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ ለሰበር ሊቀርብ የቻለው የሰበር አመልካች (የሥር ከሣሽ) ግንቦት 28 ቀን 1998 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የሥር አመጣጥ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአሁኑ የሰበር ተጠሪና (የሥር 2ኛ ተከሣሽ) በሥር 1ኛ ተከሣሽ (ጉዳያቸው በሌሉበት የታየው) ላይ ያቀረቡት ክስ ከሥር 1ኛ ተከሣሽ ለነበሩት በጥቅምት 14 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ላንድሮቨር መኪና በብር 14,000 (አሥራ አራት ሺ.ህ) ሸጠው ከዚህ ውስጥ ብር 10,000 (አስር ሺ.ህ) ተቀብለው ቀሪውን ብር 4,000 (አራት ሺ.ህ) በጊዜ ባለመክፈላቸው ብር 5000 (አምስት ሺ.ህ) አድርገው ለመክፈል ተጨማሪ ውል ማድረጋቸውንና ያሁኑ ተጠሪም ባልተነጣጠለ ሃላፊነት ዋስ በመሆናቸው ዋናውን ገንዘብ ከነወለዱ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን ፍርድ ቤቱም ክስና ክርክሩን ከመረመረ በኋላ የሥር 1ኛ ተከሣሽ በቀረበው ክስ መሠረት እንዲከፍሉ፣ያሁኑ ተጠሪ ግን ተራ ዋስ በመሆናቸው በርሣቸው ላይ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 መሠረት ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፣ ውሳኔው በፌ/ከ/ፍ/ቤትም በይግባኝ ፀንቷል፡፡

የሰበር ማመልከቻው የቀረበው የተጠሪን ዋስትና አስመልክቶ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ማመልከቻውን ከመረመረ በኋላ በተጠሪ ላይ ያልተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል ተጠሪን አስቀርቦ ለማከራከር ያዘዘ ቢሆንም ተጠሪ ለመቅረብ ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ጉዳዩን በሌሉበት እንዲታይ አዟል፡፡

በዚህም መሠረት ፍርድ ቤቱ የሰበር ማመልከቻውን ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርም[ል፡፡

ከፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ለመረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ተራ ዋስ መሆናቸውንና በውሉም ስምምነት ላይ የሥር 1ኛ ተከሣሽ ገንዘቡን ሳይከፍሉ ቢቀሩ ተጠሪ ሃላፊ ሆነው ገንዘቡን እንደሚከፍሉ መገለፁን አስፍሮ በተጠሪ ላይ የቀረበውን ክስ ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 መሠረት ውድቅ በማድረግ ተጠሪን በነፃ አሰናብቷል፡፡ ይህ ፍርድ ቤት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 እንደተመለከተው የድንጋጌው ንኡስ ቁጥር /1/ ተራ ዋስ በገባው ዋስትና መሠረት ለመክፈል የሚገደደው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ እንደሆነ ለመረዳት ችሏል፡፡ በሌላም አነጋገር ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት በቂ አቅም (ችሎታ) ያለው እስከሆነ ድረስ ገንዘብ ጠያቂው ዋናውን ባለዕዳ ትቶ ዋሱ ገንዘቡን አንዲከፍለው ለመጠየቅ አይችልም፡፡ ምክንያቱም የተራ ዋስትና ዋናው መሠረት በቅድሚያ ዋናው ባለዕዳ ከገባው ውል አኳያ ግዴታውን እንዲወጣ በመቀጠልም ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለመወጣት ካልቻለ (አቅም ከሌለው) ተራው ዋስ ገንዘቡን እንዲከፍል ለመስቻል ታስቦ በሕጉ እንዲካተት የተደረገ በመሆኑ ነው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ አመልካች ከሥር ጀምሮ ያቀረበው ክስ መስተናገድ የነበረበት ከዚህ ድንጋጌ መንፈስ አኳያ በዚህ ቅደም ተከተል መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ለእዳው አከፋፈል ዋናው ባለዕዳ ላይ ሃላፊነትን በማስቀመጥና ዋናው ባለዕዳ ለመክፈል አቅም የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ተራው ዋስ (ተጠሪ) እዳውን እንዲሸከም በሚያስችል መልኩ መወሰን ሲኖርበት ተጠሪ እስከናካቴው ክሱ ካስከተለው ኪሣራና ወጪ ጋር በነፃ እንዲሰናበት መደረጉ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡



አንዲያውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1931 ላይ እንደተመለከተው ዋስ የሆነ ሰው በዋናው ባለዕዳ ላይ ክስ ለማቅረብ ገንዘብ ጠያቂው ለመወሰኑ ማስጠንቀቂያ ሲደርሰው ክሱ ለሚያስከትላቸው ወጪዎችም ጭምር ሃላፊ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በፍ/ብሕ/ቁ.1939 እዳው መከፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ ዋሱ ገንዘብ ለባለዕዳው መክፈል እንደሚችል ተገልፆአል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት ድንጋጌዎች ዋሱ ባንድ በኩል እዳውን በመክፈል ራሱን ነፃ እንዲያደርግና በሌላም በኩል ገንዘብ ጠያቂው ክስ መሥርቶ ከዋናው ገንዘብ በላይ ክሱ ለሚያስከትላቸው ወጪዎች እንዳይዳረግ ከወዲሁ የጥንቃቄ እርምጃዎችን እንዲወሰድ ለማድረግ እንዲያስችሉት መደንገጋቸው ሲታይ ተጠሪ ተራ ዋስ በመሆኑ ብቻ ስለእዳው አከፍፈል ከላይ እንደተመለከተው የቅደም ተከተል ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከሃላፊነት ነፃ የሚሆንበት አንዳችም የሕግ መሠረት እንደሌለ ፍርድ ቤቱ ተገንዝቧል፡፡

በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1939 ተራ ዋስን (ተጠሪን) ሃላፊ አያደርግም በማለት ድንጋጌውን በተሳሳተ አኳኋን በመተርጐም የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.43622 ግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም ፣እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት 41054 መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም ተጠሪን በተመለከተ የሰጡት ውሣኔ ተሽ[ል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ ኪሣራና ወጪ ጋር የሥር 1ኛ ተከሣሽ ለመክፈል ካልቻሉ ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፣መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ.ቁ. 26565

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ካሣዬ ተ/አረጋይና ተፈራ ደምሴ ጠበቆች

ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በመድን ውል መሠረት ለደንበኛው የከፈለው ካሣ እንዲተካለት በፌ/ከ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ክስ መስርቶ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለሆነ ተጠሪ ካሣ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይሄው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ተጠሪ ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ደንበኛ የሆነው ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር በጅቡቲ በኩል ከውጭ ወደ አዲስ አበባ ለሚያስመጣው 9,600 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ በጉዞ ላይ ለሚደርስበት ማንኛውም አደጋ ከሣሽ የመድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን የመድን ሽፋን ከተሰጠው 9,600 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ ውስጥ 3,200 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ) ካርቶን የአንገፑ የተከሣሽ በሆነ የጭነት መኪና ተጭኖ ከጅቡቲ ወደ አ/አበባ በመንዝ ላይ እንዳለ ከመኪናው በተነሣ እሣት ጭነቱ በሙሉ ወድሟል በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ 9,600 (ዘጠን ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ የመድን ዋስትና የተገባው ለብር 2,066,045.66 (ሁለት ሚሊየን ስልሳ ስድስት ሺህ አርባ አምስት ከስልሳ ስድስት) ሲሆን ለወደመው 3,200 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ) ካርቶን እርሾ ብር 688,681.87 (ስድስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሰማኒያ አንድ ከሰማኒያ ሰባት) ስለሚሆን በዚሁ መሠረት ከሣሽ በመድን ሰጭነቱ ይህንኑ ብር 688,681.87 ለደንበኛው ለፔትራም ኃ/የተ/የ/ማኀበር የከፈለ ሲሆን ተከሣሽ ይህንን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃ ለተጠሪ ደርሶ በሰጠው መልስ ጉዳቱ መድረሱን ሣይክድ የተከሣሽ ንብረት የሆነው ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ በጥቅምት 6 ቀን 1996 ዓ.ም የደረሰበት የእሣት ቃጠሎ አደጋ ድንገተኛ ደራሽና ያልታሰበ የመኪናው ሾፌር ቃጠሎውን ለመከላከል ባደረገው ሙከራ ሰውነቱ እንደተቃጠለና የተሽከርካሪውም ሞተር አዲስ መሆኑን ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት አደጋ እንዳላጋጠመው አደጋው ፍፁም ሊመልሱት የማይቻል በሹፌሩም ሆነ በአካባቢው ከነበሩ ሰዎች አቅም በላይ የሆነ ከፍተኛ ኃይል /force majeaure/ ስለሆነ ከንግድ ሕግ ቁጥር 591 አኳያ ተከሣሽ ኃላፊነት ስለማይኖርበት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲያንጉዘው በነበረ እቃ ላይ ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው ወይንስ አይደለም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ አይደለም የሚባል ከሆነ ተከሣሽ በከሣሽ የተጠየቀውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይ? የሚሉትን ጭብጦች መሰርቶ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በጅቡቲ የሚገኘው ኤክስፐርት በአደጋው ቦታ በመሄድ ስለአደጋው አደራረስ ባቀረበው ሪፖርት መኪናው ከነጭነቱ ሙሉ በሙሉ በእሣት መቃጠሉን እሣቱ ሊነሣ የቻለው የኤክትሪክና የመካኒክ ሲስተሙ ድክመት ስለገጠመው በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው ኬብል ሥራውን ስላቋረጠና ከብረት ጋር

ስለተፋጨ የኤሌክትሪክ ጭረት ተነስቶ ኃይለኛ ንፋስ በመኖሩ ተቀጣጣይ የሆኑት አካሎች በእሣት ተያይዘው እሣቱም ተስፋፍቶ ወደ ተሣቢው ስለደረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ሌላው በማስረጃነት የቀረበውና አሽከርካሪው ለፖሊስ በሰጠው ቃል መኪናውን ከጅቡቲ ወደ አ/አበባ እያሽከረከረ ሲጓዝ በመኪናው ጋቢና የእሣት ሽታ እንደሸተተውና የተሣቢውን ጭነት ሲመለከት እንደተቃጠለና በወቅቱም ኃይለኛ ንፋስ ስለነበር መኪናውን አቁሞ ወርዶ እሣቱን ለማጥፋት እንደሞከረ በዚህ ጥረቱም እጁን እንደተቃጠለ የእሣቱን መንስኤ በተመለከተ በመኪናው ውስጥ የኮንታክት ችግር ያስነሣ እንደሚመስለው ነገር ግን ሞተሩ አዲስ መሆኑንና ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት አደጋ እንዳላጋጠመው በመግለጽ ቃሉን እንደሰጠ ያስገነዝባል፡፡

የእቃ አጓዡ በሚያጓጉዘው ዕቃ ላይ ለሚደርስ ጥፋት ኃላፊ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 590 ላይ የተደነገገ ቢሆንም በዚሁ ሕግ ቁጥር 591 ላይ ደግሞ በእቃው ላይ ጥፋት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑን አጓዡ ካስረዳ በኃላፊነት ተጠያቂ እንደማይሆን ተመልክቷል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተከሣሽ ባቀረበው ማስረጃ ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት አጓዡ ሊገምተውና ሊያስቀረው በማይችል አደጋ ምክንያት መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ስለሆነ ተከሣሽ ለተከሰሰበት የንብረት ጉዳት ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሣሽም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

ከዚህ በኋላም ከሣሽ (የአሁን አመልካች) የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት አቅረቦ ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በእርሾው ላይ የደረሰው ቃጠሎ ከአቅም በላይ ምክንያት ስለመሆኑ ከሕጉ አኳያ ተመርምሮ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡



በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተመለከተውም አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሣያገኝ የቀረው ቃጠሎው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ በመሆኑም አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተመርምሮ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነው፡፡

አንድ አጓዥ በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ጓዞች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው ወይም የማስረከቢያው ጊዜ ቢዘገይ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የንግድ ሕግ ቁጥር 590 የሚያመለክት ሲሆን አጓዡ ከዚህ ኃላፊነት የሚድነው ደግሞ ንብረቱ ሊጠፋ፣ ጉዳት ሊደርስበት ወይም ሊዘገይ የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በዕቃው ውስጣዊ ጉድለት ምክንያት ወይም በላኪና በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት ሲሆን እንደሆነ በዚሁ የንግድ ሕግ በቁጥር 591 ላይ ተመልክቷል፡፡

የግራ ቀኙ ግንኙነትን የሚገዛው ይሄው የንግድ ሕጉ ስለሆነ ክርክሩ መታየትም ያለበት ከዚሁ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ነው፡፡ ይሁንና በንግድ ሕጉ ውስጥ "ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ከልዩ ሕጉ ወደ ጠቅላላ ሕጉ ማለትም ወደ ፍ/ብ/ሕጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላው ስለሚመለከቱ ድንጋጌዎች ማምራት የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረትም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻለው መቼ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1792 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ድንጋጌ ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው ባለዕዳው ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍፁም መሰናክል በሆነ አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመ ጊዜ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለዕዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈፃፀም ከባድ የሆነ ወጭ

በባለዕዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለዕዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለዕዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገምት ወይም ሊያስብና ጥንቃቄ ሊያደረግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪውን ከኃላፊነት ነፃ ያደረጉት የክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት በቃጠሎ ሊወድም የቻለው ተሽከርካሪው የኤሌክትሪክና የመካኒክ ሲስተሙ ድክመት ስለገጠመው በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው ኬብል ስራውን ስላቋረጠ ከብረት ጋር በመፋጨቱ ምክንያት በተነሣው እሣት ስለሆነና ይህም አንገዡ ሊገምተውና ሊያስቀረው የማይችል በመሆኑ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈጠረ ነው በማለት ነው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ያሉት ከተሽከርካሪው የቴክኒክ ችግር ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ይሁንና የተሽከርካሪው ባለቤትና አንጓዥ የሆነው ተጠሪ ተሽከርካሪውን በሚገዛበት ጊዜ የቴክኒክ ደኅንነቱ አስተማማኝ መሆኑን ለሥራ ከሚሰማራበት አገርም ሆነ አካባቢ የአየር ንብረት ጋር ተስማሚ መሆኑን አጣርቶ ተሽከርካሪውን መግዛት እንዳለበት የሚታመን ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጎ ግዢውን ከፈፀመ በኋላም ቢሆን ለሥራ በተሰማራበት አካባቢ ምንም ዓይነት የቴክኒክ ችግር እንዳያጋጥመው ለጉዞ ከመሰማራቱ በፊትና በጉዞ በየጊዜው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ሣያደርግ ቀርቶ ጉዳት ቢደርስ እንደሕጉ አገላለጽ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከላይ



እንደተመለከተው በተሽከርካሪው ግዢ ወቅትም ሆነ ከግዢ በኋላ ተሽከርካሪው የቴክኒክ ችግር እንዳይደርስበት አስቀድሞ ሊገምተውና ሊከላከለው ሲገባ ይህንን የመከላከልና የጥንቃቄ ዕርምጃ አስቀድሞ ሣይወስድ በመቅረቱ በጉዞ ላይ ተሽከርካሪው በደረሰበት የቴክኒክ ብልሽት ምክንያት በተነሣው ቃጠሎ የመድን ሽፋን የተገባለት ንብረት መውደሙ የተረጋገጠ ስለሆነ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ሊባል ስለማይችል የሥር ፍ/ቤቶች ለንብረቱ መቃጠል ምክንያት የሆነው አደጋው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ትርጉም የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 41594 በታህሳስ 26 ቀን 1998 ዓ.ም እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23649 በግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በተጠሪ መኪና ተጭኖ ሲጓጓዝ የነበረውና አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው እርሾ በቃጠሎ ጉዳት ሊደርስበት የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ቃጠሎው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የካሣ ክፍያ ጥያቄውን አስመልክቶ የያዘውን ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አኳያ መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

# ውሎች
# ስጦታ



የሰ/መ/ቁ. 17742

መጋቢት 02 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ አበበች ታደሰ - ከጠበቃ ኪሮስ ገብሩ ጋር ቀረቡ፡፡

2. ህፃን እርአዮ ኪሮስ

3. ህፃን ወጊሐለይ ኪሮስ

4. ህፃን ይካአሉ ኪሮስ

ተጠሪ፡- 1. አስር አለቃ ሲሣይ ካብትህይመር

2. ወ/ሮ ይመኙሻል ፈቃዱ

3. ወ/ሮ አባይነሽ ደምሴ

} ጠበቃ ዮሴፍ እሸቴ ቀረቡ፡፡

4. የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ /ተተኪ መሬት አስተዳደር ባለሥልጣን/ - አልቀረበም፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካቾች በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የአሁኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘውን ስፋቱ 440 ካ.ሜ. ከሆነ የቦታ ይዞታ ላይ 220 ካ.ሜ. ቀንሰው በላዩ ላይ ካለው ቁጥር 272 ቤት ጋር በስጦታ ለ1ኛ አመልካች ባለቤትና ለቀሪዎቹ አመልካቾች አባት ለአቶ ኪሮስ አለማየሁ በስጦታ ከሰጡ በኂላ ይህንኑ ቤት ከራሣቸው ቤት ጋር ቀላቅለው ለ3ኛ ተጠሪ የሸጡ በመሆኑና 4ኛ ተጠሪም ይህንኑ የሽያጭ ውል የመዘገበው ስለሆነ የሽያጩ ውል እንዲፈርስ ቤቱን የሚመለከቱ አስረጂ ሰነዶችን

ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ 4ኛ ተጠሪም የቤቱን የባለቤትነት ስም በአመልካቾች ስም እንዲያዛውር ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍ/ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታ በግልጽ ኑዛዜ መልክ መደረግ ሲገባው ክርክር የተነሣበት የስጦታ ውል ግን የግልጽ ኑዛዜ ፎርምን አያሟላም የቀበሌው ፍ/ሸንጎ የስጦታ ውሉን መዝግቧል የተባለ ቢሆንም የፍ/ሸንጎ ውልን ለመመዝገብ የስልጣን ስለሌለው የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የአመልካቾችን ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ሲሆን የፌ/ከ/ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ ላይ የቀረበለትን ይግባኝ ባለመቀበል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በአጭሩ የስጦታ ውሉ በፍ/ሸንጎ ቀርቦ ተረጋግጧል ከዚህ በኂላም ውሉ ለሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ተልኮ ከቤቱ ማህደር ጋር ተያይዟል ውሉ በቀበሌ ፍ/ሸንጎ የተረጋገጠ በመሆኑ 2 ምስክሮች በቂ ናቸው፡፡ የስጦታ ውሉ ከተደረገ ከ10 ዓመት በኂላ እንዲፈርስ ሊጠየቅ አይችልም፤ የሚል ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የስጦታ ውሉ ውድቅ የተደረገበትን የሕግ አግባብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር አድርጓል፡፡ ተጠሪዎችም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት በዚህ ጉዳይ ሊታዩ የሚገባቸው ጭብጦች፤ 1/ ሕጋዊ ውጤት ያለው የስጦታ ውል አለ? የለም? 2/ አለ ከተባለ በስጦታ በተሰጠው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ሕጋዊ ውጤት አለው? የለውም? 3/ ሕጋዊ ውጤት የለውም የሚባል ቢሆን 4ኛ ተጠሪ የቤቱን የባለቤትነት ስም በአመልካቾች ስም እንዲያዛውር ሊገደድ ይችላል? አይችልም የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በክርክራቸው የሰጦታ ውል እንዳላደረጉ እና ተደርጓል ቢባል እንኳን ውሉ ሕጋዊ ፎርማሊቲን ያላሟላ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡



እኛም መዝገቡን እንደመረመርነው 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ሰኔ 16 ቀን 1984 የተፃፈ የስጦታ ውል አድርገው ይኸው የስጦታ ውል ለፍ/ሸንጎ ቀርቦ ከተረጋገጠ በኂላ ለስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ተልኮ ከቤቱ ማኀደር ጋር መያያዙን ተረድተናል፡፡ በተለይ 4ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስ በፍ/ሸንጎ የተረጋገጠ የስጦታ ውል ቀርቦለት ከቤቱ ማኀደር ጋር ማያያዙን መግለፁ ተጠሪዎቹ የስጦታ ውሉን ማድረጋቸውን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍ/ቤትም ተጠሪዎች የስጦታ ውሉን ማድረጋቸውን አረጋግጦ ነገር ግን በሟች አርቲስት ኪሮስ አለማየሁና በተጠሪዎቹ መሃከል የተደረገው የስጦታ ውል ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት አያሟላም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎቹ የስጦታ ውሉን አላደረግንም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ከዚህ በመቀጠል ሊታይ የሚገባው ነጥብ ደግሞ ይህ የስጦታ ውል ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልቷል? አላሟላም? የሚለው ነው፡፡ አመልካቾች በስጦታ ተሰጥቶናል የሚሉት የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታ መደረግ ያለበት ደግሞ ግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት አይነት መሆኑን በፍ/ሕ/ቁጥር 2443 ሥር ተመልክቷል፡፡ ግልጽ ኑዛዜም መደረግ ያለበት በ4 ምስክሮች ፊት እንደሆነና ኑዛዜውም በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ ኑዛዜው ማመልከት እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁ. 881/2/ ሥር ተቀምጧል፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው በዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው ሰው ፊት የተደረገ ከሆነ 2 ምስክር በቂ እንደሚሆን በፍ/ሕ/ቁ. 882 ሥር ተመልክቷል፡፡

ከዚህ ተነስተን ወደተያዘው ጉዳይ ስናመራ የስጦታ ውሉ በ3 ምስክሮች ፊት የተደረገ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የአመልካቾች ክርክር ስጦታው በፍ/ሸንጎ የተረጋገጠ በመሆኑ 3 ምስክሮች በቂ ናቸው የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ የፍ/ሸንጎ ውል ለማዋዋል ስልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ፍ/ሸንጎ ውል ለማዋዋል ስልጣን አለው? የለውም የሚለው መልስ ማግኘት የሚገባው ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የስጦታ ውሉ የተደረገው ሰኔ 16 ቀን 1984 ዓ.ም. ነው፡፡ የስጦታ ውሉም ለፍ/ሽንን ቀርቦ ፀድቋል የተባለው ስጦታ የተደረገላቸው አርቲስት ኪሮስ አለማየሁ ከሞቱበት ከጥቅምት 3 ቀን 1986 ዓ.ም. በፊት በየካቲት 15 ቀን 1985 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ ወቅት ስራ ላይ የነበረው ማኅበራዊ ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 37/1982 ሲሆን ይህ አዋጅ በእያንዳንዱ ቀበሌ የማኅበራዊ ፍ/ቤቶች አቋቁሟል፡፡ እነዚህ ፍ/ቤቶችም በመደበኛ ፍ/ቤቶች መልክ የተደራጁ ሆነው በተሠጣቸው የሥልጣን ወሠን ውስጥ የዳኝነት ሥራ የሚያከናውኑ በሕግ የተቋቋሙ ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ በዳኛ ፊት ወይም በውል አዋዋይ ፊት መደረግ ስላለባቸው ውሎች የሚደነግጉት የፍ/ሕጉ ድንጋጌዎች ውሉ በዳኛ ፊት መደረግ እንዳለበት ከሚገልፁ በቀር በየትኛው ፍ/ቤት በሚገኝ ዳኛ ፊት መደረግ እንዳለበት የሚያስቀምጡት የተለየ መስፈርት የለም፡፡ ወይም በሌላ ሕግ ውል ለማዋዋል ስልጣን ስላለው ዳኛ ተለይቶ የተቀመጠ ድንጋጌ የለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት የሚያስችል ማንኛውም ዳኛ ውል ለማዋዋል ስልጣን አለው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በማኅበራዊ ፍ/ቤት የሚያስችሉ ዳኞች ውል ለማዋዋል የሚከለክላቸው ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የስጦታ ውልም በማኅበራዊ ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት 2 ምስክሮች ብቻ መኖራቸው በቂ ስለሚሆን ስጦታ ውሉ ሕጋዊ ውጤት ያለው መሆኑን ተረድተናል፡፡

ከዚህም በላይ ምንም እንኳን የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ የስጦታ ውል የግልጽ ኑዛዜ ፎርምን ከመከተሉ በተጨማሪ በፍ/ሕ/ቁ 1723 መሠረት ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ወይም በዳኛ ፊት ሊደረግ ይገባል አይገባም የሚለው ነጥብ አከራካሪነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በተያዘው ጉዳይ ግን ውሉ በግልጽ ኑዛዜ ፎርም መሠረት ከመደረጉ በተጨማሪ በዳኛ ፊትም ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የስጦታ ውሉ ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፤ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ክርክር ያስነሣው ቤት ለአርቲስት ኪሮስ አለማየሁ ሰኔ 16 ቀን 1984 ዓ.ም. በስጦታ



የሰጡ መሆኑ ከፍ ሲል ተረጋግጧል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነት በሕግ ወይም በውል ሊተላለፍ እንደሚችል በፍ/ሕ/ቁ. 1184 የተመለከተ ሲሆን ንብረቱ በውል የተላለፈ ከሆነ ይኸው ውል በማይንቀሣቀስ ንብረት መዝገብ መመዝገብ እንደሚገባው የፍ/ሕ/ቁ 1185 ተጨማሪ መስፈርት ያስቀምጣል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ቤቱ በስጦታ ውል ለስራና ከተማ ልማት ሚ/ር ቀርቦ በቤቱ ማኅደር ውስጥ ተያይዞ መቀመጡ በፍ/ሕ/ቁ 1185 የተመለከተው መስፈርት መሟላቱን ያመለክታል:: ይህም በመሆኑ ክርክር የተነሣበትና በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘው ቁጥር 272 የሆነው ቤት ሀብትነት ለሟች ኪሮስ አለማየሁ ተላልፏል ማለት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው ግን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለ3ኛ ተጠሪ የሸጡት በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 367 የሆነውን የራሣቸውን ቤትና በስጦታ የሰጡትን ቁጥር 272 ጭምር ነው:: ቁጥር 272 የሆነው ቤት ሀብትነት ደግሞ ለሌላ ሰው ያስተላለፉ በመሆኑ ይህንኑ ቤት ለሌላ ሰው በሽያጭ ሊያስተላልፉ የሚችሉበት ሕጋዊ መብት አይኖራቸውም፡፡ አንድ ውል በሕግ ፊት የሚፀናው ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ ውሉ በሚቻል ነገር ላይ የተደረገና ሊፈፀም የሚችል ሲሆን ነው /የፍ/ሕ/ቁ. 1678/ለ/ እና 1715 ይመለከቷል/:: በሌላ ሰው ንብረት ላይ የተደረገ የሽያጭ ውል ቤቱን ለገዢው ማስረከብ የማይቻል በመሆኑ ውሉ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቁጥር 272 የሆነውን ቤት ሀብትነት ለአመልካቾች ካስተላለፉ በኂላ ይህንኑ ቤት በተመለከተ ከ3ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡

የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካቾች ሀብትነቱ የተላለፈላቸውን ቤት ስመ ንብረት 4ኛ ተጠሪ በስማቸው እንዲያዛውርላቸው ጠይቀዋል፡፡ ነገር ግን የማይንቀሰቀስ ንብረት ባለቤትነት ወደ ሌላ ማዛውር በአስተዳደር መ/ቤት የሚከናወን የአስተዳዳሪው ተግባር እንጂ በፍ/ቤት ውሣኔ የሚሰጥበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካቾች አስፈላጊውን ሰነዶች ሁሉ አቅርበው 4ኛ ተጠሪ ስም እንዲያዛውር ጠይቀው የከለከላቸው ለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በሆኑም አመልካቹ ስም ለማዛወር የሚያስችሉትን አስፈላጊ ማስረጃና

ሰነዶች በማቅረብ ስም እንዲያዛውርላቸው የሚመለከተውን የአስተዳደር መ/ቤት ከሚጠይቁ በቀር ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም። በመሆኑም 4ኛ ተጠሪን በተመለከተ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አላገኘውም።

**ው ሣ ኔ**

1/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 11201 ጥቅምት 9 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24848 ጥቅምት 26 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል።

2/ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ሰኔ 16ቀን 1984 ዓ.ም. ያደረጉት ስጦታ ውል ፈራሽ ሊሆን አይገባም።

3/ በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችና በ3ኛ ተጠሪ መሀከል በወረዳ 17 ቀበሌ 17 ክልል በሚገኘው በ220 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ ያረፈው ቁጥር 272 በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ፈራሽ ነው።

4/ 4ኛ ተጠሪ በተራ ቁ. 3 ላይ የተገለፀውን ቤት ስመ ንብረት እንዲያዛውር የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት ስለሌለው ተቀባይነት የለውም።

5/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ 23921

ጥቅምት 12 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ተገኔ ጌታነህ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
መስፍን እቁበዮናስ
ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግሥቱ ቀረቡ።

ተጠሪ፡- 10 አለቃ ታደሰ ወርቁ ቀረበ።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፈርደናል።

**ፍ ር ድ**

ለዚህ ፍርድ ቤት ለቀረበው አቤቱታ መነሻ የሆነው አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ለተጠሪው በጥር 1989 ዓ.ም. ያደረግሁት የስጦታ ውል በማታለል የተደረገና ተጠሪውም ሊጦረኝ ሲገባ ስለማይጦረኝ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ተቀባይነት በማጣቱና ይግባኝ አቅርባም ይግባኙ በመሠረዙ ነው።

የሥር ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ያደረገው በጉድለት ምክንያት ውል እንዲሠረዝ የሚቀርብ ጥያቄ በሁለት ዓመት ይርጋ ቀሪ ይሆናል፤ በማለትና ተጠሪ አመልካችን የመጦር ግዴታ በውሉ አልተሰጠውም በማለት ነው።

እኛም የስጦታ ውሉ ሊፈርስ የሚገባው መሆን ያለመሆኑን አይፈርስም ከተባለስ ተጠሪው ስጦታ ሰጪዋን አመልካችን ሊጦር ይገባል ወይንስ አይገባም የሚሉትን ነጥቦች መርምረናል።

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለተ አመልካች ለተጠሪው የስጦታ ውል ያደረገችው ጥር 27 ቀን 1989 ዓ.ም ሲሆን ይህ የስጦታ ውል እንዲፈርስ ክስ የመሠረተችው ደግሞ በግንቦት 24 ቀን 1996 ዓ.ም ነው። የፍ/ሕ/ቁ 2441/1/ ሥጦታ እንዲቀነስ ወይም እንዲሻር የሚቀርብ ጥያቄ ሥጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ እስከ ሁለት ዓመት ካልቀረበ በቀር ዋጋ የሌለው እንደሆነ

ደንግጓል። አመልካች የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ ክስ የመሠረተችው የስጦታ ውሉ ከተደረገ ከ7 ዓመታት በኂላ ነው።

በመሆኑም የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ የቀረበውን ክስ የሥር ፍ/ቤቶች ያለመቀበላቸው የሚነቀፍ አይደለም።

በሌላ በኩል ግን ስጦታ ተቀባይ በስጦታ ውሉ ላይ በግልጽ ያልተመለከተ እንኳን ቢሆን ሰጪው በድኅነት ላይ ከወደቀ ቀለብ የመስጠት ግዴታ እንዳለበት በፍ/ሕ/ቁጥር 2458/1/ ላይ ተደንግጓል። የሥር ፍ/ቤት ጥያቄውን ከዚህ ሕግ አኳያ መመርመር ሲገባው ተጠሪው አመልካችን ለመጦር የውል ግዴታ የላቸውም ማለቱ ከሕጉ የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል።

**ው ሣ ኔ**

1. የስጦታ ውሉ አይፈርስም በማለት በሥር ፍ/ቤት የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል።
2. ተጠሪ ለአመልካች ቀለብ የመስጠት የውል ግዴታ የለበትም በሚል የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ግን ተሽሯል። አመልካች በድኅነት ላይ ወድቃ የምትገኝ ከሆነ ተጠሪ ቀለብ የመክፈል ግዴታ በሕጉ የተጣለበት በመሆኑ ይህንኑ በማስረጃ አጣርቶ ተገቢውን እንዲወስን የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ታዟል። ይፃፍ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 32337

ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

አሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይሕደጎ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ

2. አቶ ደሣለኝ በርሔ

3. ወ/ሮ ኤልሣ በርሔ

4. ወ/ሪት ይርጋዓለም በርሔ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል፤ ማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 05409 ሚያዚያ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመዝገብ ቁጥር 19936 ግንቦት 7 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20118 ሐምሌ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይሻርልን በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው። ፍሬ ጉዳዩም ተጠሪዎች በከፍተኛው ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው ተከሣሽዋ የአሁን አመልካች የአባታችን የአስር አለቃ በርሄ ምሩፅ የጋራ ንብረት የሆነ ቤት የያዙች ስለሆነና እኛ ደግሞ የአባታችን ወራሽ ስለሆን እንድታካፍለን ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል። አመልካች በበኩሏ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም ሟች ቤቱን ለእኔና ለሁለት ልጆቼ

የካቲት 5 ቀን 1989 በውልና ማስረጃ በተመዘገበ የቁም ኑዛዜ ሰጥቶናል የሚልና ሌላውን ቤት በተመለከተ እኔ ነኝ የሰራሁት የሚል መከራከሪያ አቅርባለች። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃና ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ በውልና ማስረጃ የፀደቀው የቁም ኑዛዜ ስጦታ ሰነድ በዳኛ ፊት ወይም በአዋዋይ አካል የተደረገ አይደለም፣ ስጦታው በግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት ፎርም መፈፀም ያለበት በመሆኑና በሰነዱ ላይ የፈረሙት ሶስት ምስክሮች ስለሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን አያሟላም። ስለዚህ ሕጋዊ ውጤት ስለሌለው ተከሣሽ የተከሣሾችን የውርስ ድርሻ ያካፍሉ በማለት ወስኗል።

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው፤ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት ስለሌለ ይግባኙ ፍሬ የለውም በማለት ሠርዞታል። አመልካች ይኸ ትእዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ጉዳዩን ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርባ ሰበር ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን የሕግ ክርክር ከሰማ በኋላ ሟች ያደረገው ሰነድ የቁም ኑዛዜ ስጦታ የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን ድርሻዩን ለሁለቱ ልጆች ሰጥቻለው ካለ በኋላ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 937 መሠረት ስጦታው እንዲፀድቅላቸው የሚል በመሆኑ ሰነዱ ኑዛዜ ነው። ሆኖም ኑዛዜው ሌሎቹን ልጆች ከውርስ የሚነቅል በመሆኑና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 937 መሠረት ሟችን በዚህ አይነት መንገድ ተወላጆቹን ከውርስ መንቀል ስለማይችል፣ የሟችን ድርሻ ሌሎች ልጆችም እኩል የመካፈል መብት አላቸው በማለት በልዩነት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስኗል። ከተሰየሙት አምስት ዳኞች ወስጥ ሁለቱ ስጦታ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 ግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት አሠራር መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ክርክር የተነሣበት ሰነድ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 882 መሠረት የተፈፀመ በመሆኑ ሕጋዊ የስጦታ ሰነድ ስለሆነ ስጦታ ከተደረገላቸው ልጆች ውጭ ያሉት የሟች ልጆች ለመጠየቅ አይችሉም በማለት በልዩነት ሀሣባቸውን አስቀምጠዋል።

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባቀረባቸው የሰበር አቤቱታ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የተለያዩ መሠረታዊ የሕግ ስህተቶችን ሰርተዋል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውልና ማስረጃ የተረጋገጠውንና ሶስት ምስክሮች የፈረሙበትን ሰነድ ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ያልተፈረመ ስለሆነ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሲሆን፤ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ኑዛዜው፣ ሌሎቹ ልጆችን ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የለውም የሚል ውሣኔ ሰጥቷል። ስጦታ ሰጭው ገና በቁም ሣሉ ያደረጉት የቁም ስጦታ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤት ኑዛዜ ነው ማለታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክተዋል። ተጠሪዎች በበኩላቸው ሰነዱ "የኑዛዜ የቁም ስጦታ" የሚል በመሆኑ ሟች ያደረገው ኑዛዜ እንጅ የቁም ስጦታ ውል አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ ኑዛዜው በሕግ የተቀመጡ ፎርማሊቲዎችን ስለማያሟላ ውጤት የለውም መባሉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል። አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር አመልካችና ተጠሪዎች ያቀረቡት የሕግ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ እኛም የግራ ቀኙን የመከራከሪያ ነጥቦችና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ መርመረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነውም

1. ሟች ያደረጉት " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች "ስለ ስጦታ ውል" የተደነገጉት ናቸው ወይስ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት ናቸው? የሚለው ነጥብ
2. ሟች ያደረጉት " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" በሕግ የተደነገገውን ሥርዓትና ፎርም ያሟላ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብና
3. ሟች ያደረጉት የቁም ኑዛዜ ስጦታ ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው?

የሚለው ነጥብ በዝርዝር ማየትና መወሰን አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ፣ ሟች በሕይወት እያሉ ከሚመለከተው የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት በመቅረብ " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" የሚል ሰነድ የካቲት 6 ቀን 1989 ዓ.ም አድርገዋል፡፡ ይኸ ሟች የተውት ሰነድ መሠረታዊ ባህሪ፣ አመልካችና ተጠሪ ለሚያደርጉት ክርክር መነሻ ነው፡፡ ስለሆነም ሟች ባደረጉት "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ላይ ተፈፃሚነት ያለው የሕግ ክፍል መለየት፤ የመጀመሪያውና ቀዳሚው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስለ ስጦታ ውል በፍትታብሔር ሕግ ውስጥ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ስንመለከት የኢትዮጵያ ሕግ "የስጦታ ውል" ወይም "ስጦታ" በማለት እውቅና የሚሰጠው፣ ስጦታ ሰጭው ከመሞቱ በፊት የሕግ ውጤት እንዲኖራቸው አስቦ የሰጣቸው ስጦታዎችን ነው፡፡ የብዙ አገሮች ሕግጋት ለሁለት ዓይነት ስጦታዎች ዕውቅና እና ውጤት ይሰጣሉ፡፡ እነርሱም ማለት ሟች በሕይወት እያለ ተፈፃሚ ለሚሆን ስጦታ /Donation enter vivos/ እና ሟች ከሞተ በኂላ ተፈፃሚ የሚሆን ስጦታ" Donation Martis causa በማለት ይሰይሟቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ ሕግ ስጦታ ነው በማለት እውቅና እና ጥበቃ ለሚሰጠው ለመጀመሪያው አይነት ስጦታ ማለትም ሟች ከመሞቱ በፊት ተፈፃሚ እንዲሆን እና ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው አስቦ ለሚሰጠው ስጦታ ነው፡፡ ሟች ከሞተ በኂላ ተፈፃሚ እንዲሆን አስቦ የሚያደርገው ስጦታ፣ የኢትዮጵያ ሕግ ስጦታ ነው ብሎ እውቅና እና ጥበቃ እንደማይሰጠውና እንደዚህ አይነት ስጦታ የውርስ ሕግ የኑዛዜ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው "ሰጭው ሲሞት ይፈፀማሉ ተብለው በተወሰኑት ስጦታዎች ላይ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚዎች ይሆናሉ" በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2428 በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የሟች " የቁም



ኑዛዜ ስጦታ" ያደረጉት ስጦታው በሕይወት እያሉ ተፈፃሚ እንደሆን አስበው ነው ወይስ ከሞቱ በኂላ ተፈፃሚነት እንዲኖረው የሚለውን ነጥብ ስንመለከት በመጀመሪያ ሟች በግልጽ "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" የሚል ርዕስ የተጠቀሙ መሆኑና "ኑዛዜ" የሚለው ቃል ስጦታው ሟች ከሞተ በኂላ ተፈፃሚ የሚሆን እንደሆነ ስለሚያመለክት፤ በሁለተኛ ደረጃ ሟች በቁም ኑዛዜ ስጦታ ያደረጉበት ቤት የባልና የሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑና ጋብቻው በፍች ወይም በሞት ምክንያት ካልተቋረጠ በስተቀር ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ባል ወይም ሚስት ከጋራ ንብረቷ አንዱን ክፍል ለይቶ መስጠት ስለማይችልና በሶስተኛ ደረጃ ሟች ባደረጉት የቁም ኑዛዜ ስጦታ ጽሑፍና የጠቀሱት የሕግ ድንጋጌ፣ ማለትም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 967 ሟች ከሞተ በኂላ ኑዛዜው ስለሚከፈትበት ቦታ የሚደነግግ በመሆኑ ሟች ያደረገው " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ሟች ከሞተ በኂላ፤ ተፈፃሚ እንዲሆን አስቦ ያደረገው በመሆኑ፤ በጉዳዩ ተጠቃሽ የሚሆኑትና ተፈፃሚነት ያላቸው ስለኑዛዜ የተደነገጉት ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ በማይንቀሣቀስ ንብረት ለመስጠት የሚደረግ የስጦታ ውል በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ አስራር አይነት ካልተደረገ ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 ይደነግጋል፡፡ ሟች ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው የውልና ማስረጃ ክፍል ሶስት፤ ምስክሮች ባሉበት "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" አድርጓል፡፡ ይኸም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገገውን ፎርም የሚያሟላ በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሰነዱ የሕጉን ፎርም አያሟላም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ስለሆነም ሟች ያደረጉት "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 882 የተደነገጉትን የሕግ ፎርማሊቲዎች የሚያሟላ ነው፡፡

ሶስተኛውን ነጥብ በተመለከተ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሟች ያደረገው የቁም ኑዛዜ ስጦታ የሌሎችን ወራሾች ከውርስ መንቀል ውጤት እንዳለው በመግለጽ ውድቅ አድርጎታል፡፡ ሟች ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆች ወይም ሌሎች ወራሾች ቢኖሩትና ከነዚያ መካከል ለአንደኛው የኑዛዜ ስጦታ ቢያደርግ፣ የሌሎቹን ወራሾች ከሟች ውርስ መነቀል አያስከትልም፡፡ ይህንንም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 913 የኑዛዜው ቃል የተናዛዡን ተቃራኒ ሀሣብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር ከውርስ ሀብት አንድ ድርሻ ወይም አንድ ንብረትን ሟቹ ለወራሾቹ መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ ደንብ እንጅ እንደ ኑዛዜ ስጦታ ነው ተብሎ አይቆጠርም በማለት ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይም የሟችን ልዩ ሀሣብ የቀረበው ሰነድ የማያሣይ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ሟች የውርስ ንብረት ሲደለደል ቤቱ "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ላደረጉላቸው ልጆች እንዲደርሣቸው ያላቸውን ፍላጎት ከሚገልጽ በስተቀር ከሁለቱ ልጆች የተለየ የኑዛዜ ስጦታ መስጠቱን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ስለሆነም ቤቱን ሙሉ በሙሉ "የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ላደረጉላቸው ልጆች ለማስተላለፍ የሚችል ሰነድ አይደለም፡፡

ከዚሁ ጋር መታየት ያለበት፤ ሟች ያደረጉት የቁም ስጦታ አይደለም እንጅ ቢሆንም እንኳን ተጠሪዎች የውርሱን ንብረት የመካፈል መብታቸው እንደማይገደብ ስለ ውርስ ንብረት ክፍያ በተለይም የጋራ ወራሾች ስለሚመልሷቸው ንብረቶች የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በውጤት ደረጃ አመልካች የሟች ድርሻ ለተጠሪዎችና ለሌሎች ወራሶቹ የማካፈል ግዴታ አለበት በማለት የትግራይ ክልል በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሚቀየር አይደለም፡፡ ነገር ግን በሕግ አተረጓጎም ወቅት የተለያዩ ስህተቶችን የፈፀሙ ሆነው አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም በውሣኔው ተጠቃሽ ያደረጓቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ከላይ በተገለፀው መንገድ በማስተካከል በውጤት ደረጃ ግን የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ አጽንተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. ሟች ያደረጉት " የቁም ኑዛዜ ስጦታ" ተራ የክፍያ ደንብ እንጅ የተጠሪዎች የውርሱን ንብረት የመካፈል መብት የማይገድብ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪዎች የውርሱን ንብረት የማካፈል ግዴታ አለበት ብለናል፡፡
2. ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጓቸው የሕግ ድንጋጌዎች ትርጉምና ተፈፃሚነት ተሻሽሎ ውሣኔያቸው በውጤት ደረጃ የፀና መሆኑን እንዲያውቁት ይፃፍ፡፡

ይህ ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

# ውሎች

# ብድር



የሰ/መ/ቁ. 22891

ኅዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ገ/ማርያም ከበደው - አቶ ኃይም ወ/ጊዮርጊስ

2. አቶ ገ/የሱስ ገ/ፃድቃን - ጠበቃ ኃይሉ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው 1ኛ ተጠሪ በትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባልና ሚስት የሆኑት 2ኛ ተጠሪና አመልካች ብር 53,398 (ሃምሳ ሦስት ሺህ ሦስት መቶ ዘጠና ስምንት) ተበድረውኝ ለብድሩ አከፋፈል ቼክ የሰጡኝ ቢሆንም ገንዘቡ ያልተከፈለኝ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ገንዘብ በብድር ከከሳሽ የወሰዱት 2ኛ ተጠሪ አቶ ገ/ኢየሱስ ገ/ፃዲቅ ብቻ ከመሆናቸውም በላይ ብድሩም ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ ያልተረጋገጠ ስለሆነ 2ኛ ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለከሳሽ እንዲከፍሉ 1ኛ ተጠሪን በተመለከተ ገንዘቡን ሊከፍሉ አይገባም በማለት ውሣኔ ሰጥቶ ከሳሽ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ተከሳሾች ባልና ሚስት በመሆን ሕይወታቸውን በንግድ ሥራ የሚመሩ እንደመሆኑ መጠን በንግድ ሕ/ቁ. 19 መሠረት አንደኛው ተጋቢ የሚገባው ዕዳ ሌላውንም ተጋቢ የሚያስገድድ በመሆኑ የከፍተኛው ፍ/ቤት በዚሁ መሠረት ሚስትንም የዕዳው ተጠያቂ ማድረግ ሲገባው ተጠያቂነት

የለባትም በማለት ውሣኔ መስጠቱ ከሕጉ ጋር ያልተገናዘበ ነው በማለት ይህንኑ ውሣኔ ሽሮ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ሁለቱም ተከሳሾች እንዲከፍሉ በማለት የበኩሉን ውሣኔ ሠጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘትም የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ክሱ በቼክ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ሰበር ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ለመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት ትዕዛዝ በመስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም በአመልካች በኩል የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች፣ ቼክ ሳትሰጥ በቼክ ተከሳ በቼኩ ላይ የተመለከተውን ዕዳ በንግድ ሕግ ቁጥር 19 መሠረት የንግድ ዕዳ ወይም አግባብ ባለው የቤተሰብ ሕግ አመልካችን የሚመለከት ዕዳ መሆኑ በማስረጃ ሳይጣራ በአመልካች ላይ መፈረዱ ለሰበር ቀርቦ መጣራት እንዳለበት በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የክርክሩ ጭብጥ 1ኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡበትን ገንዘብ አመልካች ለመክፈል ይገደዳሉ የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ የሰበር አቤቱታው ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

በቅድሚያም 1ኛ ተጠሪ በትግራይ ክልል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን ያቀረቡት በቼክ ላይ ተመስርተው ወይንስ በብድር የሚለውን ነጥብ ማየት ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ በመሆኑ ይህንኑ ተመልክተናል፡፡

1ኛ ተጠሪ በክስ ማመልከቻቸው ላይ ገንዘቡ በምን ምክንያት ለከሳሾች እንደተሰጠ ዘርዝረው ያቀረቡ እንደመሆናቸው መጠን ክሱ በቼክ ላይ ተመስርቶ እንዳልቀረበና ቼኩን እንደተራ ማስረጃ በመቁጠር ክሱን እንደመሠረቱ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተከሳሾች በኩል የሥር 2ኛ ተከሳሽ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ገንዘቡን ከከሳሽ በብድር መውሰዳቸውን ያመኑ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ግን ብድሩን ክደዋል፡፡

የብድሩ ዕዳ በሥር 1ኛ ተከሣሽ በአሁኑ አመልካች ከተካደ ደግሞ የብድሩን መኖር በተመለከተ አግባብነት ያለውን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት



ሸክሙ የሚወድቀው በከሳሽ ላይ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ረገድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2472 ላይ እንደተለከተው የሥር ከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ አግባብነት ያለውን ማስረጃ አቅርበው ብድሩን በካዱት አመልካች ላይ የብድሩን መኖር አላስረዱም፡፡ ይህንንም መሠረት አድርጎ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለመክፈል አይገደዱም በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ዕዳው ይመለከታቸዋል በማለት ውሣኔ የሰጠው ከላይ እንደተመለከተው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ነጋዴዎች ስለሆኑ ከ1ኛው ተጋቢ የሚጠየቅ የንግድ እዳ በን/ሕ/ቁ.19 መሠረት ሌላውንም ተጋቢ ስለሚመለከተው ኃላፊ ናቸው በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ክሱ የቀረበው ከላይ እንደተመለከተው በቼክ ላይ ተመስርቶ ሳይሆን በብድር ላይ ተመስርቶ ከመሆኑም በላይ ብድር መኖሩም በማስረጃ የተረጋገጠው በ1ኛው ተጋቢ ላይ ብቻ ነው፡፡ በአንድኛው ተጋቢ ብቻ በብድር መወሰዱ የተረጋገጠው ገንዘብ ከንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ የተወሰደ ብድር ነው ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ ብድሩ ለጋራ ጥቅም መዋሉ ቢረጋገጥ እንኳን የዕዳው አከፋፈል ወደ ጋራ ንብረት ወይንም ወደ ሌላው ተጋቢ የግል ንብረት የሚሄደው በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ እንጂ የብድር ውል ባልተዋዋለው ወገን ላይ ክስ ሊመሰረትም ሆነ ፍርድ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከንግድ ሕጉ ጋር የተጣጣመ ባለመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች በዚሁ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ሲያቀርቡ ክሱ የቀረበው ከላይ እንደተመለከተው በቼክ ላይ ተመስርቶ ሳይሆን በብድር ላይ ተመስርቶ ቼኩ በተራ ማስረጃነት የቀረበ በመሆኑ ጉዳዩን በሰበር ለማየት የሚችል ሆኖ ሳለ በቼክ ላይ ተመስርቶ የቀረበ ክስ በመሆኑ በሰበር ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበል መቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይሁንና

የክልሉም ሆነ የፌዴራሉ ሰበር ችሎት የተቋቋሙበት ዓላማ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን ማረም በመሆኑ ጉዳዩን ወደ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መመለስ ሳያስፈልግ ቀጥሎ የተመለከተው ተወስኗል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19141 በሐምሌ 21 ቀን 1997 ዓ.ም. እንደዚሁም የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 11571 በ ጥቅምት 30 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረተዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ክልል ምዕራባዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በግንቦት 23 ቀን 1997 ዓ.ም. ይህን ጉዳይ አስመልክቶ አመልካች ክስ በቀረበበት ጉዳይ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም በማለት የሰጠው ውሣኔ ከሕጉ ጋር የተገናዘበ ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31737

የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ገብሩ ገ/መስቀል - ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ፡-** ቄስ ገ/መድኅን ረዳ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የብድር ውልን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ከአሁን ተጠሪ ጋራ በነበረን የንግድ ግንኙነት ተጠሪ ብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ/ እንዳበድራቸው በስልክ ሲጠይቁኝ ፈቃደኛ በመሆን ገንዘቡን ልኬላቸው መቀሌ ከሚገኘው ወጋገን ባንክ ፈርመው ተቀብለዋል፣ በኋላ ተጠሪ ገንዘቡን እንዲመልሱልኝ በተደጋጋሚ ብጠይቃቸውም ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆኑም፣ ስለዚህ ገንዘቡን ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲሁም የጠበቃ አበል ከነወጪና ኪሣራው ይክፈሉኝ በማለት ተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ የተባለውን ገንዘብ መቀበሌን አልክድም፣ ነገር ግን ገንዘቡን ከአመልካች ላይ የወሰድኩት ብድር ጠይቄ ሳይሆን አመልካች ከአሁን በፊት ከእኔ በብድር የወሰዱትን ገንዘብ ለመመለስ ልከውልኝ ነው፣ የገንዘብ መላኪያ ወረቀቱም በምንም አይነት የብድር ማስረጃ ሊሆን አይችልም፣ ከብር 500 /አምስት መቶ/ በላይ በሆነ ገንዘብ የተደረገ የብድር ውል በጽሁፍ ካልተደገፈ ዋጋ አይኖረውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ በመጀመሪያ የማስረዳት ሸክሙ የሚወድቀው በማን ላይ ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ግራ ቀኙ ግንኙነታቸው በንግድ ላይ የተመሠረተ መሆኑን አልተካካዱም፣

የአሁን ተጠሪ ገንዘቡን መቀበላቸውን አልካዱም፣ አመልካች ተጠሪ ገንዘቡን የላኩት ቀደም ሲል ለነበረባቸው ዕዳ መክፈያ መሆኑን የማስረዳት የመጀመሪያ ግዴታ የሚወድቀው ተጠሪ ላይ ነው፣ ይሁን እንጂ ተጠሪ ይህንኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የማስረጃ ዝርዝር ከመልሳቸው ጋር አላቀረቡም፣ በማስረጃ ያልተደገፈ የፍሬ ነገር ክርክር ደግሞ ዋጋ የሚሰጠው አይሆንም ካለ በኋላ ተጠሪ ገንዘቡን ከአመልካች መቀበላቸውን አምነው አመልካች ገንዘቡን የሰጧቸው በፊት ለነበረ ዕዳ መክፈያ መሆኑን እስካላረጋገጡ ድረስ ባለዕዳ ናቸው፣ በመሆኑም ተጠሪ ክሱ የቀረበበትን ብር 50,000 /ሃምሳ ሺህ/ ክሱ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ የባንክ ወለድ ጋር ለከሣሽ ይክፈሉ በማለት ወሰነ፡፡

ተጠሪ ይህንን ውሣኔ በመቃወም ለትግራይ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ያቀረቡት ይግባኝ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ ሰበር ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር አዳምጦ በማስረጃነት የቀረበው የሐዋላ ወረቀት /ደረሰኝ/ በግራ ቀኙ መካከል የብድር ውል መኖሩን የሚያረጋጋጥ ማስረጃ አይደለም የሐዋላ ወረቀት ገንዘብ ከአንድ ባንክ ወደ ሌላው የተላከ መሆኑን ከማረጋገጥ ውጪ በሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ካልተደገፈ በቀር ገንዘቡ የተላከው በብድር መሆኑን አያስረዳም፣ ተጠሪ ገንዘቡ የተላከልኝ አመልካች ለነበረባቸው ዕዳ መክፈያ እንዲሆን ነው በማለት መመለሳቸውም ቢሆን ብድሩን አምነዋል የሚያስብላቸው አይደለም፣ በመሆኑም አመልካች ገንዘቡን የላኩት በብድር መሆኑን ተጠሪ አላመኑም ክህደት ካለ ደግሞ ብድሩ መኖሩን የማረጋገጥ /የማስረዳት/ ኃላፊነቱ የአሁን አመልካች ነው፣ ስለዚህ የብድር ውል መኖሩ በመልካች ሳይረጋገጥ ወይም በተጠሪ ሳይታመን የቀድሞው ብድር መኖሩን ተጠሪ የማስረዳት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ ተጠሪ በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ አመልካች ለተጠሪ ልኬላቸው የነበረውን ገንዘብ



መቀበላቸውን ተጠሪ ራሳቸው አምነውና በማስረጃም ተረጋግጦ ገንዘቡን የተቀበልኩት ለዕዳ መክፈያ ሆኖ ነው የሚል መልስ በተጠሪ  ስለተገለፀ ብቻ ቀድሞውኑ አመልካች የተጠሪ ተበዳሪ መሆኔን የማስረዳት ሸክም እያለባቸው የማስረዳት ሸክሙ የአመልካች ነው አመልካች ገንዘቡን በብድር መላካቸውን አላስረዱም ተብሎ በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ችሎቱም የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎችና የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር አመልካች ለተጠሪ ገንዘብ ልከውላቸዋል እየተባለ በበታች ፍ/ቤት አመልካች ይህንን ገንዘብ በብድር መልክ ስለመስጠታቸው የብድር ውል አቅርበው አላስረዱም በሚል ተጠሪ የተከሰሱበትን ገንዘብ አይከፍሉም ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆኑና አለመሆኑ ሊጣራ የሚገባ ነጥብ ሆኖ ስላገኘነው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ከስር ጀምረው የሚከራከሩት ገንዘቡን ለተጠሪ የላኩት ተጠሪ እንዳበድራቸው በስልክ ባቀረቡልኝ ጥያቄ መሠረት ስለሆነ ገንዘቡን ይመልሱልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ በበኩላቸው አመልካች ገንዘቡን ሲልኩልኝ የቻሉት ቀደም ሲል ያበደርኳቸውን ገንዘብ ለመመለስ እንጂ እንዲያበድሩኝ ጠይቄ አይደለም በማለት መከራከራቸውን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

ተጠሪ በአመልካች የተላከላቸውን ገንዘብ መቀበላቸውን አልካዱም፣ ገንዘቡን መቀበላቸው በማስረጃም ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን ገንዘቡን የተቀበልኩት አመልካች ቀደም ሲል የነበረባቸውን ዕዳ ለመክፈል ልከውልኝ ነው የሚል ክርክር ተጠሪ ከጅምሩ ጀምሮ ማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡ በመሠረቱ ተከራካሪ ወገኖች በመከራከሪያነት የሚያቀርቧቸውን ፍሬ ነገሮች ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም በአዎንታዊ መልኩ የተከራከረ ወገን የክርክሩን ፍሬ ነገር የማስረዳት ሸክም ይወድቅበታል፡፡ የአሁን ተጠሪ የክርክሩ መነሻ የሆነውን ገንዘብ ከመቀበሌ በፊት ለአመልካች ገንዘብ አበድሬያለሁ ቢሉም ገንዘቡ ከብር 500 (አምስት መቶ) የሚበልጥ እንደመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472/1/ ላይ

ከተደነገጉትና የብድርን መኖር ማስረዳት ከሚቻልባቸው ሶስት መንገዶች በአንዱም ቢሆን የአመልካች አበዳሪ መሆናቸውን አላስረዱም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለመከራከሪያ ያቀረቡትን ይህንን ፍሬ ነገር የማስረዳት ኃላፊነታቸውን አልተወጡም፡፡ በአንፃሩ ግን አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ በብድር መስጠታቸውን ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ የብድር ውልን በጽሁፍ ማስረዳት እንደሚቻል በተደነገገው መሠረት ገንዘቡን የላኩበትን የሐዋላ ወረቀት በማቅረብ አረጋግጠው ያስረዱ ስለሆነ በክሳቸው ላይ ያቀረቡትን ፍሬ ነገር የማስረዳት ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፡፡ ስለዚህ አመልካች ገንዘቡን ለተጠሪ ማበደራቸውን ባስረዱበትና ተጠሪ ደግሞ እንደአባባላቸው ገንዘቡ የተላከላቸው አስቀድሞ ለነበረ ዕዳ መክፈያ መሆኑን ባላረጋገጡበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ገንዘቡን ለአመልካች ለመመለስ አይገደዱም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. ክርክር የተካሄደበትን ብር 50,000 /ሃምሳ ሺ.ህ/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ በድምጽ ብልጫ ተወስኗል፡፡
2. የትግራይ ብ/ክ/መ/ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 18404 በሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. የክልሉ የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03390 በ5/4/99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18102 በ12/4/99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
4. የዞኑ ከፍ/ፍ/ቤት በውሣኔው መሠረት ያስፈጽም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡



## የልዩነት ሃሣብ

ጉዳዩ ሲጀመር አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት በብድር የወሰደውን ብር 50 ሺ.ህ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472/1/ መሠረት በብድር ተሰጥቷል የሚባለው ገንዘብ ከብር 500 /አምስት መቶ/ በላይ ከሆነ ይህንኑ ማስረዳት የሚቻለው በጽሁፍ በፍ/ቤት በተደረገ የዕምነት ቃል ወይንም በመሐላ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡

ከሳሽ በአስረጂነት ያቀረቡት ሰነድ በባንክ አማካይነት በሐዋላ ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ ለተከሳሽ ብር 50 ሺ.ህ መላካቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው፡፡ የሐዋላ ሰነዱ በመካከላቸው የብድር ግንኙነት መኖሩን የማያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ ተከሣሽም በባንክ በኩል የተላከውን ገንዘብ መቀበላቸውን ቢያምኑም ነገር ግን ገንዘቡን ከተከሳሽ የተቀባበሉት ከሳሽ እንደሚሉት ከእራሳቸው በመበደራቸው ምክንያት ሳይሆን ቀደም ሲል ለከሳሽ አበድረውት ለነበረ ገንዘብ በመክፈያነት እንደተቀበሉ ገልጸው ብድሩን ክደው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የብድር ውል አለ በማለት ክስ ያቀረቡት ከሣሽ ሕጉ እንደሚጠይቀው የብድር ውል ስለመኖሩ አለማስረዳታቸውን ነው፡፡

በሌላ በኩልም በአብላጫው ድምጽ ውሣኔ ላይ ተከሣሽ ገንዘቡን መቀበላቸውን እስካመኑ ድረስ በሌላ ግንኙነት የተቀበሉት ገንዘብ ስለመሆኑ ከመከራከር በስተቀር ይህንኑ ግንኙነት በማስረጃ ያላረጋገጡ ስለሆነ ክሱ የቀረበበትን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል የተባለውን በተመለከተ የብድር ውል አለ በማለት ከሳሽ ክስ እስካቀረቡ ድረስ የብድር ውል አለ የለም የሚለው በጭብጥ ተይዞ የሚፈታ ፍሬ ነገር እስከሆነ ድረስ ከማስረጃ አቀራረብ አኳያ ይህንኑ በጭብጥ ተይዞ የሚፈታውን ፍሬ ነገር ማስረዳት የሚጠበቅበት ከሣሽ መሆን እንደሚገባው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ውልን አስመልክቶ ሰለ ማስረጃ አቀራረብና አቀባበል በሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕጉ ክፍል ሥር አንድ ግዴታ እንዲፈጸምለት የሚጠይቅ ወገን ግዴታው ሰለመኖሩ ማስረዳት ይጠበቅበታል ተብሎ በቁጥር 2000/1/ ላይ የተደነገገውም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡

ስለሆነም በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት በአብላጫ ድምጽ የተሰጠው ውሣኔ ከማስረጃ አቀራረብ መርህ አኳያ ተገቢነት ያለው ባለመሆኑ የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ሊጸና ይገባል በማለት ስሜ በተራ ቁጥር 3 ላይ የተጠቀሰው ዳኛ ከሥራ ባልደረቦቼ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



# ውሎች

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 24173

ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት - ነገረ ፈጅ አቶ ማስረሻ በለጠ ቀረበ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይዳ ሐሰን - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአመልካቹ አማካይነት ወደውጪ ሃገር የተላከን ጫት ዋጋ ይከፈል ዘንድ የቀረበውን ክስ መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው አመልካች አሜሪካን አገር እንዲያደርስላት በውል ያስረከበችውን ጫት በውሉ መሠረት አለማድረሱን በመግለጽ የጫቱን ዋጋ ከነመላኪያው በጠቅላላው ብር 18,000 እንዲከፍላት እንዲወስንላት ጠይቃለች፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ነገር ነጥቦችን በማንሳት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን ክርክሩን አልተቀበለም፡፡ በመጨረሻም የጫቱን ዋጋ ከነመላኪያው እንዲከፍል ወስኖበታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 3 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተወሰነው አመልካች ገንዘቡን



እንዲከፍል የተወሰነበት በሕጉ አግባብ ነው ወይ? የሚለው ነጥብ መጣራት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እንደተገነዘብነው አመልካች ለክሱ መነሻ የሆነውን ጫት ከተጠሪ መረከቡንና በዓለም አቀፍ የፖስታ ሕብረት ስምምነት መሠረት ጥቅሉን ወደሚመለከተው /ወደተላከበት/ አገር መላኩን ገልጾአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ግዴታውን በአግባቡ መወጣቱን በመግለጽ ከኃላፊነት ነፃ እንዲሆን፤ ኃላፊ ነህ የሚባል ከሆነም መጠየቅ ያለበት በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት /እንደ ክሱ አቀራረብ/ ሳይሆን፣ በተቋቋመበት አዋጅ ቁ. 240/58 መሠረት እንደሆነ በማስመልከት ተከራክሮአል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ግን አመልካች ጫቱን ለተላከለት ሰው ስለማድረሱ አላስረዳም በማለት በፍሬ ነገር ረገድ ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርገውታል፡፡ የካሣውን አወሳሰን በተመለከተ የቀረበውን ክርክርም በአዋጅ ቁ. 240/58 የተገለጸ ነገር የለም የሚል ምክንያት በመስጠት አልተቀበሉትም፡፡ አመልካች አቤቱታ ያቀረበው በፍሬ ነገር ረገድ የተሰጠውን ምክንያት ጭምር በመቃወም ሲሆን፣ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት የቻለበት ዋናው ምክንያትም ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት የሌለው የፍትሐብሔር ሕጉን መሠረት አድርጎ የተወሰነ ነው የሚል እንደሆነ ከክርክሩ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች ጫቱን በአግባቡ ወደተላከው ቦታ አድርሻለሁ በማለት ያቀረበው የፍሬ ነገር ክርክር ከማስረጃ አንፃር ተመዝኖ ውድቅ ሆኖአል፡፡ በዚህ ረገድ ያለው ክርክር የማስረጃ አመዛዘንን የሚመለከት በመሆኑ በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም፡፡ አመልካች ጫቱን ለተላከለት ሰው አለማድረሱን ከተረጋገጠም ቀጥሎ መታየት ያለበት የሕጉ ክርክር ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሥራ ላይ የፖስታ አገልግሎትን ሕግ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ. 240/58 በአመልካቹ አማካይነት የተላከን ዕቃ ወይም ፖስታ ጠፍቶአል፣ ተበላሽቶአል፣ ተሰርቋል፣ ወዘተ በሚል ጥያቄ ሲቀርብ ካሣ የሚከፈልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ደንግጎአል፡፡

የአወሳሰኑ ሁኔታም በዝርዝር አስቀምጦአል፡፡ በዚህ ረገድ የአዋጁ አንቀጽ 50፣ 51 እና 53 እንደዚሁም 54ን በተለይ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ የሚከፈል ካሣ ካለ መጠኑ የሚወሰነው በዓለም የፖስታ ሕብረት ስምምነት /ኮንቬንሽን/ በተወሰነው እና ከሌሎች አገሮች ጋር በሚደረጉ ልዩ ስምምነቶች መሠረት እንደሆነ በአንቀጽ 54 ተመልክቶአል፡፡ እንግዲህ ከአዋጁ አጠቃላይ መንፈስ፣ በተለይ ደግሞ ከተጠቀሱት አንቀጾች በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው ፖስታው /ዕቃው/ በመጥፋቱ፣ በመሰረቁ፣ በመበላሸቱ፣ ወዘተ ምክንያት አመልካች ካሣ እንዲከፍል የሚጠይቅ ቢሆን መጠየቅ ያለበት በአዋጁ መሠረት እንደሆነ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በዚህ ረገድ ካሣ የሚጠየቅበትንና መጠኑም የሚወሰንበት ራሱን የቻለ ልዩ ሕግ ተደንግጎአል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ሕግ በመተው ካሣው በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት እንዲከፈል መወሰን መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደፍ/ቤት በመ/ቁ. 06053 በነሐሴ 19 ቀን 1997 ዓ.ም. እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 01854 መጋቢት 19 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጡአቸው ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. ተጠሪ ያቀረበችው የካሣ ክፍያ ጥያቄ መታየት ያለበት በአዋጅ ቁ. 240/58 መሠረት በመሆኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ከዚህ አዋጅ አንፃር በመመርመር ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ ይስጥ ብለናል፡፡ ይፃፍለት፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 24574

ኅዳር 11 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፓ/ጠ/ቤ/ጽ/ቤት አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ይትባረክ ሣህሉ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በጅጅጋ ዞን ከፍ/ቤ/ት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በቀረበው ክስ ነሐሴ 3 ቀን 1994 ዓ.ም. በተደረገ ውል ከሣሽ ሁለት የጭነት መኪናዎችን ለ1 ዓመት እንድገለገልበት ከተከሳሽ ተከራይቼ መኪናዎቹ በሥራ ላይ እንዳሉ አንደኛው መኪና የመገልበጥ አደጋ ደርሶበት በውሉ መሠረት በዚህ መኪና መሥራት እንድችል ተከሣሽ መኪናውን አስጠግኖ ማስረከብ ሲገባው ይህንን ግዴታውን ባለፈፀሙ በጠቅላላው ብር 290,377.12 (ሁለት መቶ ዘጠና ሺ ሶስት መቶ ሰባ ሰባት ብር ካስራ ሁለት ሣንቲም) ጥቅም የተቋረጠብኝ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽም ቀርቦ በሰጠው መልስ የውሉን መኖር አምኖ ነገር ግን መኪናው ሊገለበጥ የቻለው ከሣሽ ከክብደት በላይ በመጫኑ ምክንያት ነው ብሎ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የተከራከረ ሲሆን ከዚህም ሌላ ከሳሽ በውሉ መሠረት አለመፈጸሙን ገልጾ የመኪና ኪራይ ገንዘብ፣ መኪናውን ለማስጠገን ወጭ ተደርጓል ያለውን ገንዘብና የገደብ መቀጫ ጨምሮ በድምሩ ብር 252,246 (ሁለት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺ ሁለት መቶ አርባ ስድስት) እንዲከፈለው በመጠየቅ የተከሳሽ ከሳስነት ክስ አቅርቧል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ

የቀረበለትም የዞን ከፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ ከሳሽ በክስ ከጠየቀው ገንዘብ ብር 65,254 (ስልሳ አምስት ሺ ሁለት መቶ ሀምሳ አራት) ውድቅ አድርጎ ቀሪው ብር 225,123.12 (ሁለት መቶ ሀያ አምስት ሺ አንድ መቶ ሀያ ስድስት ብር ከአስራ ሁለት ሣንቲም) ተከሣሽ ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት ሲወስን በተከሳሽ በኩል የቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በተመለከተ ፍ/ቤቱ በውሣኔው ምንም ሳይል አልፎታል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለሱማሌ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ የአመልካችን መኪና ተከራይቶ ሲሠራበት መኪናው ተገልብጦ ሥራ በማቆሙ ተጠሪ የቀረበትን ገቢ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑ እንዲሁም የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መታለፉ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም ይሄው ነጥብ በመሆኑ ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በውሉ ግዴታ ውስጥ ባለዕዳው የጉዳት ኪሣራ ከፋይ የሚሆነው ውሉን አሟልቶ ባለመፈጸሙ ወይንም ውሉን ከስምምነቱ ውጭ አዘግይቶ በመፈጸሙ የተነሳ በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ በገንዘብ ሊተመን የሚችል ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ሲታወቅ እንደሆነና የጉዳት ኪሣራ ክፍያ ጥያቄውም ውሉን አስገድዶ ከማስፈጸም /forced performance/ ወይንም ውሉ እንዲሰረዝ ከመጠየቅ ጋር ሊቀርብ እንደሚችል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1790 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክሱን ያቀረበው በኪራይ ከአመልካች የተረከበው መኪና በሥራ ላይ እንዳለ በመገልበጡ ምክንያት ሥራ በማቆሙ የቀረበትን ገቢ አመልካች እንዲከፍለው በመጠየቅ ነው፡፡ ግራ ቀኙ ባቋቋሙት ውል መሠረት አመልካች መኪናውን ለተጠሪ



አሳስረከበም ወይንም ያስረከበው አዘግይቶ ነው የሚል ክስ በተጠሪ በኩል ባለመቅረቡ አመልካች የውል ግዴታውን አልፈፀመም ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ የውሉም ይዘት ሲታይ ተጠሪ በኪራይ በተረከባቸው መኪናዎች ላይ በአደጋ ምክንያት ጉዳት ቢደርስ ለመድን ድርጅትና ለአመልካች በወቅቱ የማሳወቅ ኃላፊነት ተጠሪ እንዳለበትና አመልካችም በበኩሉ ለደረሰው ጉዳት ተገቢው ዕርምጃ እንዲወሰድ የሚያደርግ መሆኑ ከመመልከቱ በስተቀር ጉዳት የደረሰበትን መኪና በተገቢው ጊዜ እንዲጠገን ባለማድረጉ የጉዳት ኪሣራ በተጠሪ ላይ ከደረሰ አመልካች ካሣ የሚከፍል ስለመሆኑ አልተመለከተም፡፡

ስለሆነም የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ በሕጉ ላይ ስለ ጉዳት ኪሣራ አከፋፈል ከተቀመጠው ዓላማ ጋር የማይጣጣምና ውሉንም መሠረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች በበኩሉ በውሉ አፈጻጸም ረገድ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በመግለጽ ብር 252,246 /ሁለት መቶ ሃምሣ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አርባ ስድስት/ ኪሣራ እንዲከፈለው በጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የመሠረተ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ዳኝነት ሳይሰጥበት አልፎታል፡፡ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሳይሰጥበት የታለፈ ጉዳይ እንደተነፈገ የሚቆጠር መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ቁ. 5/3/ ላይ የተመለከተ ቢሆንም የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት ዳኝነት ከተጠየቀባቸው ነገሮች በተወሰኑት ላይ ውሣኔ ተሰጥቶ በተወሰኑ ላይ ደግሞ ውሣኔ ሳይሰጥ ቢቀር የታለፈው እንደተነፈገ እንደሚቆጠር ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ጨርሶ ያልታየ በመሆኑ እንደተነፈገ ይቆጠራል ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ሰበር ሰሚ ችሎት ቀጥሎ የተመለከተውን ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 83/96-380 በሰኔ 21 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የሱማሌ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28/98 በየካቲት 25 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች መኪና በተጠሪ እጅ እያለ በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ በተጠሪ ላይ በተቋረጠ ገቢ አመልካች የጉዳት ኪሣራ ለመክፈል የሕግም ይሁን የውል ግዴታ ስለሌለበት ሊከፈል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. በአመልካች በኩል የቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ ዳኝነት ሳይሰጥበት የታለፈ ስለሆነ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች በኩል የቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 25434

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን - ጥሩወረቅ ሀ/ማርያም - ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ፍሬተርስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማኅበር - ጠበቃ ፍቃዱ ያሚን- ቀረበ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 00241 ሰኔ 10 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 33291 መጋቢት 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ይታረምልኝ በማለት አመልካች ሰኔ 13 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ አመልካች 26 ኮንቴነሮችን በማስጫን ከተጠሪው ጋር ውል የነበረው መሆኑን ገልፆ፣ በመያዣነት ካስያዝኩት ገንዘብ ውስጥ ብር 104,190 /አንድ መቶ አራት ሺ አንድ መቶ ዘጠና/ አላግባብ ቀንሶ ስላስቀረና ከነሐሴ 3 ቀን 1990 ዓ.ም. ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፈል ይወሰንልኝ በማለት አመልካች ያቀረበው ክስ ሲሆን፣ ተጠሪም በበኩሉ ክስ የቀረበበት ገንዘብ ከሳሽ ኮንቴነሮቹን በወቅቱ ባለመመለሳቸው እና ከሰላሣ ቀን በላይ በማቆየቱ መክፈል ያለበት መቀጫ ስለሆነ ሊመለስለት አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የውሉ የቅጣት ድንጋጌ በክፍት ቢታለፍም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1791 ንዑስ

አንቀጽ 1 መሠረት ለደረሰው ኪሣራ ከሣሽ ካሣ መክፈል ስላለበት ቅጣቱም በቀን ብር 75 /ሰባ አምስት ብር/ መሆኑን ተከሣሹ ከሌሎች ደንበኞቹ ጋር ያደረገውን ውል በማስረጃነት ስላቀረበ ከሳሽ ቀሪ የማስያዣ ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት የቀረበውን ጥያቄ አልተቀበልነውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የፍሬ ጉዳይ እና የሕግ ምክንያት የለም በማለት ሠርዞታል፡፡ አመልካች በውል ሰነዱ መቀጫ ለመክፈል ያልተስማማንና የመቀጫ ድንጋጌው በክፍት /ዳሽ/ የታለፈ መሆኑ እየታወቀ ፍርድ ቤቱ ከሣሽ በክስ ማመልከቻው ያልጠየቀውን ኮንቴነሮቹ በወቅቱ ባለመመለሳቸው በተከሣሽ ላይ ካሣ የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት ጭብጡን በመቀየር የወሰነ ስለሆነ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪው በበኩሉ ውሉ የቅጣት ድንጋጌ ያለው መሆኑን ጠቅሶ የቅጣት መጠኑ ባለመገለፁ ብቻ አመልካች አልተስማማም ማለት ስለማይቻል ይኸም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1713 መሠረት ሊፈፀም ስለሚገባው የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ባቀረበው የመልስ መልስ በሰበር አቤቱታው ላይ ያቀረባቸውን ነጥቦች በማጠናከር ተከራክሯል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔና ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም ግራ ቀኙ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪው አመልካች የጠየቀውን ገንዘብ በመያዣነት ተሰጥቶት ከነበረው ገንዘብ ውስጥ በመቀነስ ያስቀረ መሆኑ አልተካደም፡፡ ተጠሪው የሚከራከረው የቀነሰኩት በውሉ መሠረት ከ30 ቀን በላይ ኮንቴነሮቹ ባለመመለሳቸው አመልካች መክፈል የሚገባውን የቅጣት ገንዘብ ነው በማለት ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል፣ ኮንቴነሮቹ በመዘግየታቸው አመልካች ቅጣት ለመክፈል የተስማሙበት መሆኑን ያረጋግጣል ወይስ አያረጋግጥም? የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1791 ንዑስ አንቀጸ 1 መሠረት



አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ሕጋዊ መሠረት አለው ወይስ የለውም የሚሉትን ነጥቦች ማየት አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ የውሉ አንቀጽ 4 ኮንቴነሩ ወደብ ከደረስ ከሰላሣ ቀን በኋላ፣ ኮንቴነሩ በቀን ብር ______ ለመክፈል አመልካች ግዴታ መግባቱን ያሣያል፡፡ እንግዲህ በቀን ብር ዳሽ የሚለው የውሉ አራተኛው አንቀጽ እንዴት ነው መተርጎም ያለበት የሚለው የመጀመሪያው ነጥብ ነው፡፡ ተጠሪው፣ ይህ በቀን የሚከፈለውን የብር መጠን የማይገልጽ የውሉ አንቀጽ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1713 መሞላት አለበት በማለት የሚከራከር ቢሆንም ይኼ ድንጋጌ የዚህ አይነት አከራካሪና አጠራጣሪ ጉዳይ ለመፍታት አያገለግልም፡፡ እንደዚህ አይነት አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም የውሉ ድንጋጌ መተርጎም ያለበት በውሉ አስገዳጅ የሆነውን ወገን በሚጠቀምበት ሁኔታ ሣይሆን ለውሉ ተገዳጅ የሆነውን ወገን ምቹ በሚሆንበት አኳኋን መሆን እንደሚገባው አንቀጽ 1738 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው አመልካች በየቀኑ የሚከፍለው የመቀጫ ገንዘብ መጠን የሚደነግገው የውሉ አንቀጽ አራት መተርጎም ያለበት ተጠሪውን በሚጠቅም መንገድ ሣይሆን በዚህ ድንጋጌ ተገዳጅ የሆነውን አመልካቹን በሚጠቅም መንገድ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር የውሉ አንቀጽ 4 ላይ የሚታየው ክፍተት አመልካች ለተጠሪው የቅጣት ገንዘብ ለመክፈል ያልተስማማ መሆኑን የሚያሣይ እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1738 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካችና በተጠሪው መካከል የቅጣት ክፍያን አስመልክቶ ውል አለ ወይስ የለም የሚለውን ጭብጥ ከውል ድንጋጌዎች አተረጓጎም አንፃር አይቶ ሣይወስን ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለተ፣ ተጠሪው ለቀረበበት ክስ፣ የተከራከረው፣ ቀንሼ ያስቀረሁት ገንዘብ አመልካች በውላችን መሠረት ኮንቴነሮቹ ከሰላሣ ቀን በላይ ለዘገየበት በቀን ብር 75 /ሰባ አምስት ብር/

ተሰልቶ መከፈል ያለበት የመቀጫ ገንዘብ ነው በማለት ነው፡፡ ተጠሪው የአመልካቹ ማለትም የሥር ከሣሽ ማመልከቻ ሲደርሰው በሥር ተከሣሽ የሆነው ተጠሪው አመልካች በሰላሣ ቀን ውስጥ ኮንቴነሮቹን ባለማንሣቱ ደረሰብኝ የሚለው ኪሣራ በዝርዝር በመግለጽ አመልካች የውል ግዴታውን ባለመፈፀሙ ለደረሰበት ኪሣራ ካሣ ሊክሰኝ ይገባል የሚል፣ በተከሳሽ ከሳሽነት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 ንዑስ አንቀጽ 1/ረ/ እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥግዓት ሕግ ቁጥር 234 መሠረት አልጠየቀም፡፡ ተጠሪው አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጎች መሠረት በማድረግና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 215 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አስፈላጊውን ዳኝነት ከፍሎ፣ ጥያቄውን ሣያቀርብ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ኮንቴነሮቹን በወቅቱ ባለማንሣቱ በተጠሪው /ተከሣሽ/ ላይ ላደረሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1791 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በራሱ አነሳሽነት የሰጠው ውሣኔ፣ ከላይ የተገለጹትን መሠረታዊ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች በግልጽ ባላቀረቡት እና በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት አይቻልም የሚለውን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረታዊ ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 00241 ሰኔ 10 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 33291 መጋቢት 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪው አመልካች ክስ የቀረበበትን ብር 104190/ አንድ መቶ አራት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና/ ከነሐሴ 3 ቀን 1990 ዓ.ም. ጀምሮ



ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፍል ወስነናል፡፡ በውሣኔው መሠረት አመልካች የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ ውሣኔውን ያስፈጽም ዘንድ ግልባጩ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ.ቁ. 26565

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ካሣዬ ተ/አረጋይና ተፈራ ደምሴ ጠበቆች

ቀረቡ

ተጠሪ፡- ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በመድን ውል መሠረት ለደንበኛው የከፈለው ካሣ እንዲተካለት በፌ/ከ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ክስ መስርቶ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለሆነ ተጠሪ ካሣ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም ይሄው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ተጠሪ ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አመልካች በተጠሪ ላይ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ደንበኛ የሆነው ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በጅቡቲ በኩል ከውጭ ወደ አዲስ አበባ ለሚያስመጣው 9,600 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ በጉዞ ላይ ለሚደርስበት ማንኛውም አደጋ ከሣሽ የመድን ሽፋን የሰጠ ሲሆን የመድን ሽፋኑ ከተሰጠው 9,600 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ ውስጥ 3,200 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ) ካርቶን የአንገፍ የተከሣሽ በሆነ የጭነት መኪና ተጭኖ ከጅቡቲ ወደ አ/አበባ በመጓዝ ላይ እንዳለ ከመኪናው በተነሣ እሣት ጭነቱ በሙሉ ወድሟል፡፡ በኢንሹራንስ ፖሊሲው ላይ 9,600 (ዘጠን ሺህ ስድስት መቶ) ካርቶን እርሾ የመድን ዋስትና የተገባው ለብር 2,066,045.66 (ሁለት ሚሊየን ስልሳ ስድስት ሺህ አርባ አምስት ከስልሳ ስድስት) ሲሆን ለወደመው 3,200 (ሦስት ሺህ ሁለት መቶ) ካርቶን እርሾ ብር 688,681.87 (ስድስት መቶ ሰማኒያ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ ሰማኒያ አንድ ከሰማኒያ ሰባት) ስለሚሆን በዚሁ መሠረት ከሣሽ በመድን ስጭነቱ ይህንኑ ብር 688,681.87 ለደንበኛው ለፔትራም ኃ/የተ/የ/ማኅበር የከፈለ ሲሆን ተከሣሽ ይህንን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ ስላልሆነ ገንዘቡን ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች ክስና ማስረጃ ለተጠሪ ደርሶ በሰጠው መልስ ጉዳቱ መድረሱን ሣይክድ የተከሣሽ ንብረት የሆነው ከባድ የጭነት ተሽከርካሪ በጥቅምት 6 ቀን 1996 ዓ.ም የደረሰበት የእሣት ቃጠሎ አደጋ ድንገተኛ ደራሽና ያልታሰበ የመኪናው ሾፌር ቃጠሎውን ለመከላከል ባደረገው ሙከራ ሰውነቱ እንደተቃጠለና የተሽከርካሪውም ሞተር አዲስ መሆኑን ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት አደጋ እንዳላጋጠመው አደጋው ፍፁም ሊመልሱት የማይቻል በሹፌሩም ሆነ በአካባቢው ከነበሩ ሰዎች አቅም በላይ የሆነ ከፍተኛ ኃይል /force majeure/ ስለሆነ ከንግድ ሕግ ቁጥር 591 አኳያ ተከሣሽ ኃላፊነት ስለማይኖርበት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ተከሣሽ ሲያጓጉዘው በነበረ እቃ ላይ ጉዳት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው ወይንስ አይደለም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ አይደለም የሚባል ከሆነ ተከሣሽ በከሣሽ የተጠየቀውን ገንዘብ የመክፈል ግዴታ አለበት ወይ? የሚሉትን ጭብጦች መሰርቶ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በጅቡቲ የሚገኘው ኤክስፐርት በአደጋው ቦታ በመሄድ ስለአደጋው አደራረስ ባቀረበው ሪፖርት መኪናው ከነጭነቱ ሙሉ በሙሉ በእሣት መቃጠሉንም፣ እሣቱ ሊነሣ የቻለው የኤክትሪክና የመካኒክ ሲስተሙ ድክመት ስለገጠመው በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው ኬብል ሥራውን ስላቋረጠና

ከብረት ጋር ስለተፋጨ የኤሌክትሪክ ጭረት ተነስቶ ኃይለኛ ንፋስ በመኖሩ ተቀጣጣይ የሆኑት አካሎች በእሣት ተያይዘው እሣቱም ተስፋፍቶ ወደ ተሣቢው ስለደረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሲሆን ሌላው በማስረጃነት የቀረበውና አሽከርካሪው ለፖሊስ በሰጠው ቃል መኪናውን ከጅቡቲ ወደ አ/አበባ እያሽከረከረ ሲጓዝ በመኪናው ጋቢና የእሣት ሽታ እንደሸተተውና የተሣቢውን ጭነት ሲመለከት እንደተቃጠለና በወቅቱም ኃይለኛ ንፋስ ስለነበር መኪናውን አቁሞ ወርዶ እሣቱን ለማጥፋት እንደሞከረ በዚህ ጥረቱም እጁን እንደተቃጠለ የእሣቱን መንስኤ በተመለከተ በመኪናው ውስጥ የኮንታክት ችግር ያስነሣ እንደሚመስለው ነገር ግን ሞተሩ አዲስ መሆኑንና ከዚህ በፊት ምንም ዓይነት አደጋ እንዳላጋጠመው በመግለጽ ቃሉን እንደሰጠ ያስገነዝባል፡፡

የእቃ አጓዥ በሚያጓጉዘው ዕቃ ላይ ለሚደርስ ጥፋት ኃላፊ እንደሆነ በንግድ ሕግ ቁጥር 590 ላይ የተደነገገ ቢሆንም በዚሁ ሕግ ቁጥር 591 ላይ ደግሞ በእቃው ላይ ጥፋት የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ መሆኑን አጓዡ ካስረዳ በኃላፊነት ተጠያቂ እንደማይሆን ተመልክቷል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተከሣሽ ባቀረበው ማስረጃ ለክሱ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት አጓዡ ሊገምተውና ሊያስቀረው በማይችል አደጋ ምክንያት መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ስለሆነ ተከሣሽ ለተከሰሰበት የንብረት ጉዳት ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሣሽም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

ከዚህ በኋላም ከሣሽ (የአሁን አመልካች) የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት አቅርቦ ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በእርሾው ላይ የደረሰው ቃጠሎ ከአቅም በላይ ምክንያት ስለመሆኑ ከሕጉ አኳያ ተመርምሮ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡



በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከላይ እንደተመለከተውም አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ሣያገኝ የቀረው ቃጠሎው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በሚል ነው፡፡ በመሆኑም አደጋው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ተመርምሮ ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነው፡፡

አንድ አጓዥ በከፊል ወይም በሙሉ እቃዎች ወይም የተመዘገቡ ጓዞች ሲጠፉ ወይም ጉዳት ሲያገኛቸው ወይም የማስረከቢያው ጊዜ ቢዘገይ በኃላፊነት እንደሚጠየቅ የንግድ ሕግ ቁጥር 590 የሚያመለክት ሲሆን አጓዡ ከዚህ ኃላፊነት የሚድነው ደግሞ ንብረቱ ሊጠፋ፣ ጉዳት ሊደርስበት ወይም ሊዘገይ የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በዕቃው ውስጣዊ ጉድለት ምክንያት ወይም በላኪና በተቀባዩ ጥፋት ምክንያት ሲሆን እንደሆነ በዚሁ የንግድ ሕግ በቁጥር 591 ላይ ተመልክቷል፡፡

የግራ ቀኙ ግንኙነትን የሚገዛው ይሄው የንግድ ሕጉ ስለሆነ ክርክሩ መታየትም ያለበት ከዚሁ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ ነው፡፡ ይሁንና በንግድ ሕጉ ውስጥ "ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ትርጉሙን ለማወቅ ከልዩ ሕጉ ወደ ጠቅላላ ሕጉ ማለትም ወደ ፍ/ብ/ሕጉ በተለይም ደግሞ ስለውሎች በጠቅላላው ስለሚመለከቱ ድንጋጌዎች ማምራት የግድ ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረትም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ አለ ለማለት የሚቻለው መቼ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1792 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህም ድንጋጌ ከአቅም በላይ የሆነ ሊመልሱት የማይቻል ኃይል ደርሷል የሚባለው ባለዕዳው ባላሰበው ነገር ድንገት ደራሽ ሆኖበት ግዴታውን እንዳይፈጽም ፍፁም መሰናክል በሆነ አይነት የሚያግደው ነገር ባጋጠመ ጊዜ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ ደግሞ በአእምሮ ግምት ባለዕዳው ቀደም ብሎ ሊያስብበት የሚችል መሆኑ የታወቀ አንድ ድንገተኛ ደራሽ ነገር ወይም ለውሉ አፈፃፀም ከባድ የሆነ ወጭ

በባለዕዳው የሚደርስበት ቢሆን ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል ነው ተብሎ እንደማይገመት ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በእነዚህ የሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ተከስቷል ሊባል የሚችለው ባለዕዳው በምንም መልኩ በቅድሚያ ሊያስበው ወይም ሊገምተው የማይችል ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡ ነገር ግን ባለዕዳው ሁኔታው ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊያስብና ጥንቃቄ ሊያደረግበት የሚችል ከሆነ ሁኔታው ድንገተኛ ደራሽ ነገር ቢሆን እንኳን ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ተብሎ እንደማይገመት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪውን ከኃላፊነት ነፃ ያደረጉት የክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት በቃጠሎ ሊወድም የቻለው ተሽከርካሪው የኤሌክትሪክና የመካኒክ ሲስተሙ ድክመት ስለገጠመው በኤሌክትሪክ መስመሩ ላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው ኬብል ስራውን ስላቋረጠ ከብረት ጋር በመፋጨቱ ምክንያት በተነሣው እሣት ስለሆነና ይህም አንገፑ ሊገምተውና ሊያስቀረው የማይችል በመሆኑ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የተፈጠረ ነው በማለት ነው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን አይችልም ያሉት ከተሽከርካሪው የቴክኒክ ችግር ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ይሁንና የተሽከርካሪው ባለቤትና አንቿ የሆነው ተጠሪ ተሽከርካሪውን በሚገዛበት ጊዜ የቴክኒክ ደኅንነቱ አስተማማኝ መሆኑን ለሥራ ከሚሰማራበት አገርም ሆነ አካባቢ የአየር ንብረት ጋር ተስማሚ መሆኑን አጣርቶ ተሽከርካሪውን መግዛት እንዳለበት የሚታመን ከመሆኑም በላይ በዚህ ረገድ አስፈላጊውን ጥንቃቄ አድርጎ ግዢውን ከፈፀመ በኋላም ቢሆን ለሥራ በተሰማራበት አካባቢ ምንም ዓይነት የቴክኒክ ችግር እንዳያጋጥመው ለጉዞ ከመሰማራቱ በፊትና በጉዞ በየጊዜው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ሣያደርግ ቀርቶ ጉዳት ቢደርስ እንደሕጉ አገላለጽ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከላይ



እንደተመለከተው በተሽከርካሪው ግዢ ወቅትም ሆነ ከግዢ በኋላ ተሽከርካሪው የቴክኒክ ችግር እንዳይደርስበት አስቀድሞ ሊገምተውና ሊከላከለው ሲገባ ይህንን የመከላከልና የጥንቃቄ ዕርምጃ አስቀድሞ ሣይወስድ በመቅረቱ በጉዞ ላይ ተሽከርካሪው በደረሰበት የቴክኒክ ብልሽት ምክንያት በተነሣው ቃጠሎ የመድን ሽፋን የተገባለት ንብረት መውደሙ የተረጋገጠ ስለሆነ ሁኔታው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው ሊባል ስለማይችል የሥር ፍ/ቤቶች ለንብረቱ መቃጠል ምክንያት የሆነው አደጋው ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ትርጉም የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

6. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 41594 በታህሳስ 26 ቀን 1998 ዓ.ም እንደዚሁም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23649 በግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም ጉዳቱ የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
7. በተጠሪ መኪና ተጭኖ ሲጓጓዝ የነበረውና አመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው እርሾ በቃጠሎ ጉዳት ሊደርስበት የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
8. ቃጠሎው የደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ተብሎ የተወሰነ ስለሆነ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የካሣ ክፍያ ጥያቄውን አስመልክቶ የያዘውን ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ አኳያ መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
9. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
10. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 29369

መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ ግብርና ምርምር ማዕከል ነ/ፈጅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ተመስገን አድነው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተከሳሽ በከሳሽ መ/ቤት ተቀጥረው ሲሠሩ ከሳሽ መ/ቤት የሚሠራውን የምርምር ሥራ በአዳዲስ ሳይንሳዊ ዕውቀት ለማሻሻል እንዲቻል ተከሳሽ በሀረማያ ዩኒቨርስቲ በኤም-ኤሲ-ሲ ደረጃ እንዲማሩ የተደረገ ሲሆን በትምህርት ላይ በነበሩበት ጊዜም የ24 ወር ደመወዝ ብር 23,520 (ሃያ ሦስት ሺ አምስት መቶ ሃያ ) ተከፍሏቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ተከሳሽ ባቀረቡት ፕሮፖዛል መሠረት ብር 54,409 (ሃምሳ አራት ሺህ አራት መቶ ዘጠኝ ብር ) ከሳሽ ለዩኒቨርስቲው ከፍሎላቸዋል፡፡

ተከሳሽ ወደ ትምህርት ከመሄዳቸው በፊት ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ወደ ከሳሽ መ/ቤት ተመልሰው በትምህርት ላይ ለቆዩባቸው ለእያንዳንዱ ወር የ3 ወራት የሥራ አገልግሎት ለመስጠት ጥቅምት 13 ቀን 1993 ዓ.ም የውል ግዴታ ገብተው የነበረ ሲሆን ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኃላ ግን የጀመሩትን የምርምር ሥራ ትተው ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለቀው የሄዱ ስለሆነ እንደውሉ ተገደው እንዲፈጽሙ ተከሳሽ በውሉ መሠረት ለመፈጸም ፈቃደኛ ካልሆኑ ከሳሽ መ/ቤት ለትምህርቱ የከፈለላቸውን በድምሩ



ብር 77,929.00 (ሰባ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር) እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጡት መልስ ከሳሽ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ የውልም ሆነ የሕግ ድጋፍ እንደሌለው በመዘርዘር ክሱ ከኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ከሳሽ ባቀረበው ክስ ተከሳሹ እንደ ውሉ ተገዶ ይፈጸምልኝ በማለት የጠየቀውን በተመለከተ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1776 (1) አኳያ ተቀባይነት የለውም ካለ በኂላ ከሳሽ በአማራጭ የጠየቀውና ለትምህርት ተብሎ የተከፈለው ውጭ ሊተካልኝ ይገባል የሚለውም የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771(2) ድንጋጌ መሠረት ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም ወይንም እንዲፈርስ ከመጠየቅ ጋር ተያይዞ መቅረብ የሚገባው ሲሆን ከሳሽ ግን ውሉ እንዲፈርስ ባልጠየቀበት ሁኔታ ኪሳራ ሊከፍለው ስለማይችል ክሱ በአግባቡ አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348(1) መሠረት አጽንቷል፡፡

ይህ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ አመልካች ለተጠሪ አወጣሁት የሚለው ወጭ እንዲተካለት ያቀረበው አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው ከላይ እንደተጠቀሰው ተጠሪ በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት በከሳሽ መ/ቤት እንዲያገለግል ይህ ተቀባይነት ካላገኘ የከሳሽን መ/ቤት ያገለግላል በሚል እምነት ለትምህርት የገንዘብ ወጭ የተደረገለት ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ሊተካልኝ ይገባል በማለት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1776 ላይ እንደተመለከተው የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈጻሚነት (Specific Performance) ጥያቄ ሊመጣ የሚችለው የውሉ አፈፃፀም ለባለገንዘቡ የተለየ ጥቅም የሚሰጠው ከሆነና የባለዕዳውንም የግል ነፃነት

የማይነካ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነና ዳኝነት የተጠየቀበትም ጉዳይ የባለዕዳውን /የተጠሪን/ የግል ነፃነት የሚነካ በመሆኑ ተጠሪ ውሉን ተገዶ እንዲፈጽም ይወሰንልን በማለት አመልካች ዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ የሚነቀፍ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩልም በአማራጭ የጠየቀው ዳኝነት ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት ማገልገል የለበትም ከተባለ ለትምህርት የወጣው ወጭ ሊተካልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ይህንን የዳኝነት ጥያቄ ሳይቀበለው የቀረው የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ የሚቀርበው ለብቻው ሣይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771 መሠረት አንድም ከውል ይፈጸምልኝ ጋር አሊያም ከውል ይፍረስልኝ ጋር እንጂ ብቻውን ስላልሆነ አመልካች ውሉ እንዲፈርስ ባልጠየቀበት ሁኔታ የኪሳራ ክፍያው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

በእርግጥ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1771 (1) እና (2) መሠረት የኪሳራ ክፍያ ጥያቄ ከውል ይፈጸምልኝ ወይንም ይሰረዝልኝ ጋር ተጣምሮ ሊቀርብ እንደሚችል መገንዘብ ቢቻልም በተያዘው ጉዳይ ከውሉ ባህሪይ አኳያ ተጠሪን አስገድዶ ማስፈጸም አይቻልም ከተባለ ውጤቱ የውሉን ቀሪ መሆን የሚያስከትል ስለሆነ አመልካች ደረሰብኝ የሚለው ኪሳራ ካለ ከመጠየቅ በስተቀር ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡

በዚሁ መሠረትም አመልካች ሊተካልኝ ይገባል የሚለው ኪሳራ በአንድ በኩል ተጠሪ በትምህርት ላይ እያለ የተከፈለውን ደመወዝና በሌላ በኩልም ለዩኒቨርስቲው ተከፍሏል ያለውን ገንዘብ ነው፡፡

ተጠሪም በሰጠው መልስ በትምህርት ላይ እያለ ደመወዝ እንደተከፈለውና ሲማርበትም ለነበረው ዩኒቨርስቲ የትምህርት ወጪ መክፈሉን ሳይክድ ገንዘቡን ለአመልካች ለመመለስ ግዴታ የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ሆኖም በግራ ቀኙ መካከል ጥቅምት 13 ቀን 1993 ዓ.ም የተፈረመውን ውል ይህ ችሎት አስቀርቦ እንደተመለከተው ተጠሪ በሥልጠና ለሚቆይበት የ24 ወራት ጊዜ አመልካች ደመወዝ እንደሚከፍለውና ለሥልጠና የሚያስፈልገውንም ወጭ አመልካች እንደሚሸፍን እንደዚሁም ከሥልጠናው በኋላ ለእያንዳንዱ ወር የሥልጠና ጊዜ ሶስት ወር ተጠሪ አመልካችን ማገልገል እንደሚጠበቅበት መስማማታቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡



በግራ ቀኙ በኩል የተደረገው ስምምነት ይህንን የሚመስል ከሆነ ተጠሪ ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ አመልካችን ለማገልገል ፈቃደኛ ካልሆነ ኪሳራ የመክፈል ኃላፊነት እንደሚኖርበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ነገር ግን የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ኪሳራ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ክሱን ሳይቀበሉ መቅረታቸው ከውሉና ከሕጉ ጋር ያልተገናዘበ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 06098 በጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ 34431 በታህሳስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች ኪሳራ የመክፈል የውልና የሕግ ኃላፊነት አለበት ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች መክፈል በሚገባው የካሣ መጠን ላይ ግን የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያልታየ ስለሆነ በዚሁ መሠረት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት መጠኑን በተመለከተ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃ አኳያ ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተገዝቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 30947

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽ ኮርፖሬሽን ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሲሳይ ጥላሁን ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

በጉዳዩ ላይ ክርክር የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም በአዘጋጀው የክስ ማመልከቻ ተጠሪው ከአመልካች ጋር መጋቢት 20 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረገው የቴሌፎን ደንበኝነት ውልና ተጨማሪ ሲ.ዲ.ኤ.ም.ኤ ደብልዩ.ኤል.ኤል ውል መሰረት እንዲጠቀምበት በተሰጠው ቁጥር 2512569 በሆነ ስልክ መስመር በግንቦት 1997 ዓ.ም ላገኘው አገልግሎት መክፈል የሚገባውን ብር 85,032 (ሰማንያ አምስት ሺ ሰላሳ ሁለት) የአገልግሎት ሒሳብ አለመክፈሉን በዚህ ምክንያትም ድርጅቱ አገልግሎቱን ማቋረጡን ገልጾ ተጠሪ ይህንን ሒሳብ እንዲከፍል እንዲወሰንበት ሲል ክስ አቅርቧል፡፡

ተጠሪውም ታህሳስ 3 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ በክሱ ቁጥሩ የተጠቀሰውን ስልክ በውል መረከቡን አምኖ በክሱ የተጠቀሰው ክፍያ እንዲከፍል ምንም አይነት ጥሪም ሆነ ማስታወቂያ እንዳልደረሰው ስልኩንም ከ18 ቀን ባልበለጠ ጊዜ እንደተጠቀመበትና ክፍያው የተጋነነ መሆኑን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከውላቸው ጋር በማገናዘብ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ከሳሽ ያቀረበው የውል ሰነድ አንቀጽ 11 የሚከፈለው ገንዘብና የሚከፈልበት ጊዜ ተጠቅሶ ለተከራዩ እንደሚቀርብ ስለሚደነግግ ከሣሽ ይህን ማስታወቂያ ወይም ጥሪ ሳያቀርብለት እንዲከፍለው ክስ ማቅረቡ ተቀባይነት የለውም፡፡ በውሉ በስልኩ የተገለገለው ደንበኛ ማስታወቂያው በጊዜው ሳይደርሰው ቢቀር ደግሞ በመጠየቅያው ላይ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እንዳይከፍል እንደሚያግደው ተብሎ የተደነገገውም ለተከሳሹ መብት የሚሰጥ እንጂ ተከሳሹ ማስታወቂያ ሳይደርሰው እንዲከፍል ግዴታ የሚጥልበት አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጐታል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/337 መሰረት በመሰረዝ መዝገቡን ዘግቶ መልሶታል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔና የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ቅሬታውም ተጠሪው ከተሰጠው በራሪ ወረቀትና በ1997 ዓ.ም ነፃ የመረጃ ማዕከል አማካኝነት የተጠቀመበትን የአልግሎት ሒሳብ ስለሚያውቅ እንደዚሁም የውሉ አንቀጽ 11 ማስታወቂያ በማይሰጣቸው ሁኔታዎች ደንበኞች መክፈል የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በግልጽ ባስቀመጡበት ሁኔታ ማስጠንቀቂያ የመስጠት አስፈላጊነት እንደዋና ምክንያት ሊቆጠር አይችልም፡፡ ተጠሪው አገልግሎት ማግኘቱን አምኗል፡፡ ክርክሩ የተጠየቀው ሒሳብ የተጋነነ ነው የሚል ነው፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሒሳቡ የተጋነነ መሆን ያለመሆኑን ተጣርቶ ክፍያው እንዲፈፀም መወሰን ሲገባው በውሉ አንቀጽ 11 ደንበኛው ማስታወቂያ ባይደርሰውም ክፍያውን ከመፈፀም አይድንም ተብሎ የተደነገገውን ያለአግባብ በመተርጐም ክሱን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያሳያል፡፡ ፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ መሰረዙ በአግባቡ አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ መጀመሪያ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት እንደገና አከራክሮ የቀረበውን ክስ ከማስረጃው ይዘትና ከሕግ አኳያ መርምሮ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ነው፡፡

አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪው ቀርበው መልስ ባለመስጠታቸው ክርክሩ በሌሉበት እንዲታይ ታዟል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪው

የስልክ ክፍያውን እንዲፈጽሙ ጥሪ ስላልተደረገላቸው ወይም ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጣቸው ክፍያውን ሊፈጽሙ አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪው ስልኩን ሲገለገሉበት ከአመልካች ጋር ውል መስርተው ማስገባታቸውንና በዚሁ ስልክ መጠቀም መጀመራቸውን አልካዱም፡፡ የስልክ አገልግሎት ክፍያ እንድከፍል ጥሪ አልተደረገልኝም ማስታወቂያም አልደረሰኝም ማለታቸው ደግሞ ሒሳቡ ተመርምሮ ክፍያው ሲታወቅ እከፍላለሁ የሚል ሐሳብ ያላቸው መሆኑን እንጂ ማስታወቂያ ስላልደረሰኝ ክፍያውን አልከፍልም፣ እንድከፍልም ሕጉ አያስገድደኝ ማለታቸው ያለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ የስልክ አገልግሎት ክፍያ በየወሩ የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን ተጠሪው ክፍያውን በወቅቱ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡ በውላቸው አንቀጽ 11 ስር የተደነገገውም ተጠሪው የክፍያ ማስታወቂያ ሣይደርሳቸውም የአገልግሎት ክፍያውን መክፈል እንደማይጠበቅባቸው የሚያሳይ እንጅ ተጠሪው ካልፈለጉ ላለመክፈል የሚችሉበት ምክንያት የሚሳጣቸው አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ግራ ቀኙን በክፍያ መጠኑ አከራክሮ ተገቢውን መወሰን ሲገባው ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ የአመልካች የስልክ አገልግሎት ክፍያን የመሰብሰብ መብት የሚከለክል በመሆኑ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከ/ፍ/ቤትም ይግባኙን መሰረዙ አግባብ አይደለም፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56323 የካቲት 16 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና ፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46451 የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡



2. ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና በአገልግሎት ክፍያ መጠኑ ላይ ያለው ክርክርም አጣርቶ ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341/1/ መሰረት ጉዳዩን መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ እንዲቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ. 31480

ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሠ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች ፡- የኢት/ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ወንድምአገኝ ቶሎሣ ቀረበ

ተጠሪ ፡- አቶ መሐመድ ባህሙድ - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የመዋዋል ችሎታን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ለአቅመ አዳም ላልደረሰው ልጄ ለወጣት አህመድ መሐመድ ሞግዚትና አሳዳሪ ሆኜ የተሾምኩ ሲሆን ንብረትነቱ የልጄ የሆነውንና ግምቱ ብር 20,000 /ሃያ ሺህ ብር/ የሆነውን ቤት እኔን ሞግዚቱን ሳያስፈቅዱ አመልካች ባንክና አቶ ሐሰን የተባሉት ግለሰብ ሳደረጉት የብድር ውል መያዣ እንዲሆን ልጁን የዋስትና ግዴታ አስገብተው ከማስፈረማቸውም በላይ በቤቱ ላይ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ወጥቶ ገዢ ስላልተገኘ ባንኩ ቤቱን ተረክቦ በወር ብር 500 /አምስት መቶ ብር/ እያከራየው ይገኛል፤ ስለዚህ ባንኩ ያለአግባብ የያዘውን ቤትና የኪራዩን ሂሳብ እንዲመልስ ይወሰንልኝ በማለት በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ የቤቱ ባለቤት የሆነው አህመድ መሐመድ ለአቅመ አዳም የደረሰ ነው፣ ለአካለመጠን አልደረሰም ቢባል እንኳን ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፣ አህመድ መሐመድ አሜሪካን አገር እየኖረ ባለበት ወቅት ተጠሪ የእሱ ሞግዚትና አሳዳሪ ነኝ በማለት ያለአግባብ ያገኙትን ማስረጃ



ተቃውመን ጉዳዩ በሂደት ላይ ይገኛል፣ ባንኩ ውሉን ያደረገው ችሎታ ካለው ሰው ጋር መሆኑ እንዲረጋገጥ ፍ/ቤቱ ግለሰቡን በአካል አስቀርቦ ይመልከትልን፣ ውሉ ቤቱ በሚገኝበት ዲክሲስ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የተመዘገበና የፀና ውል ነው፣ የቤቱ ግምት ብር 9,000 /ዘጠኝ ሺህ ብር/ ሲሆን በወር ከብር 15 /አስራ አምስት ብር/ በላይ የሚከራይ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ አህመድ መሐመድ በሞግዚት ስር የሚገኝ የ16 ዓመት ልጅ መሆኑ በፍ/ቤት ስለተረጋገጠ ልጁ የመዋዋል ችሎታ ሳይኖረው ከባንኩ ጋር የተረገው ውል በህግ ፊት ዋጋ የለውም፣ አመልካች የልጁ ዕድሜ 20 ዓመት ነው በአካልም ቀርቦ ይታይ ከማለት ውጪ ይህንን የሚደግፍ ማስረጃ አላቀረበም፣ ስለዚህ ውሉ ውድቅ ነው፣ አመልካች ለተጠሪ ቤቱን ይመልስ እንዲሁም ቤቱን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ መልሶ እስከሚያስረክብበት ጊዜ ያለውን የቤቱን ኪራይ በወር ብር 100 /አንድ መቶ ብር/ ሂሳብ ታስቦ ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ቅሬታውን ባለመቀበል ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ የመያዣ ውሉ የተፈረመው በ1988 ዓ.ም ስለሆነ ተጠሪ ያቀረቡት የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው፣ በስር ፍ/ቤት ግለሰቡ በአካል ቀርቦ ይታይልን ዕድሜውም ይመርመርልን በማለት ያቀረብነው መከራከሪያ የታለፈው ያለአግባብ ስለሆነ ይታረምልን የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ህግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የበታች ፍ/ቤት የመያዣ ውሉ ይፈርሳል ብሎ የወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የመያዣ /የዋስትና/ ውል በአመልካችና በአቶ አህመድ መሐመድ መካከል የተፈረመው ሚያዝያ 5 ቀን 1988 ዓ.ም መሆኑንና ተጠሪ ለ16 ዓመቱ ልጃቸው ለአህመድ መሐመድ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ሆነው የተሾሙት

በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 04027 ሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አቶ አህመድ መሐመድ በ1997 ዓ.ም 16 ዓመት ታዳጊ ከነበረ አከራካሪውን ውል ከአመልካች ጋር ባደረገበት ወቅት /በ1988 ዓ.ም/ የሰባት /7/ ዓመት ህፃን ነበረ ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ባንክ ከአንድ የሰባት /7/ ዓመት ልጅ ጋር የዋስትና /የመያዣ/ ውል አድርጓል ለማለት የማይቻል ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተገለፀው እውነታ ተገናዝቦ ሲታይ አቶ አህመድ መሐመድ ውሉን ከአመልካች ጋር ያደረገው ችሎታ ሳይኖረው ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ልጁ ችሎታ ሳይኖረው የፈረመው ውል ፈራሽ ይሁንልኝ በማለት ተጠሪ ያቀረቡትን ጥያቄ ተቀብሎ ውሉ ፈራሽ ነው፣ አመልካች ለተጠሪ ቤቱንና የኪራይ ገንዘቡን ይመልስ ሲል የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 07730 ግንቦት 18 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 42931 ግንቦት 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አቶ አህመድ መሐመድ ክርክር የተነሳበትን ውል ከአመልካች ጋር ያደረገው ችሎታ እያለው ስለሆነ ውሉ አይፈርስም፤ ቤቱንና የኪራይ ገንዘቡንም አመልካች ለተጠሪ እንዲመልስ አይገደድም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



# ከውል ውጪ

የሰበር መ/ቁ. 19338

መጋቢት 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ዘይነባ ሐሰን

ተጠሪ፡- ፍሬው ተካልኝ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁን አመልካች በምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ በመሆን በተጠሪ ላይ የሚከተለውን ክስ አቅርበዋል፡፡ ተከሣሽ ባደረሰብኝ ድብደባ ምክንያት ቀኝ ዓይኔ የጠፋ ሲሆን ተከሣሹም በወንጀል ተከሶ ተቀጥቷል፡፡ በአይኔ ላይ የደረሰውን ጉዳት በሕክምና ለመከታተል ከሚረዳኝ አንድ ሰው ጋር በመሆን ወደ አዲስ አበባ ለሕክምና ስንመላለስ ለትራንስፖርት ብር 2950.90 (ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ ሃምሣ ብር ከዘጠና ሣንቲም) ለሆስፒታልና ለመድኃኒት ክፍያ ብር 363.16 (ሶስት መቶ ስልሣ ሶስት ብር ከአሥራ ስድስት ሣንቲም)፣ ለሰው ሠራሽ ዓይን ማስተከያና ለመነጽር ብር 415.00 (አራት መቶ አሥራ አምስት)፣ አ.አበባ ከተማ ለቆየንበት መቶ ሠላሳ አምስት ቀናት ለምግብ፣ ለአልጋና ለታክሲ በቀን ብር ስልሳ ብር ሒሳብ በድምሩ ብር 8100 (ስምንት ሺ አንድ መቶ) እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 1000 ይከፈለኝ በማለት ጠይቃለች፡፡ በተጨማሪም ዓይኔ ሲጠፋ 10ኛ ክፍል የደረስኩና ዕድሜዬም 20 ዓመት የነበረ ሲሆን በጉዳቱ ምክንያት ትምህርቴን በማቋረጤ የመንግሥት ሠራተኛ የመሆን ፍላጐቴ እውን ሊሆን ባለመቻሉ ዓይኔ ባይታወር ኖሮ በትንሹ በወር ብር መቶ ሃያ መቀጠር እችል የነበረ ሲሆን በመንግሥት ሥራ ላይም እስከ 55 ዓመት እድሜ ብሠራ 35 ዓመት በሥራ ላይ እቆይ የነበረ በመሆኑ ይህም ሲሰላ 120x12x35= ብር 40,000.00 (አርባ ሺ.ህ) ይሆናል፡፡ ስለሆነም በአጠቃላይ ብር 52,830.56 (አምሳ ሁለት ሺ.ህ ስምንት መቶ ሰላሳ ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም) ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በካሳ መጠኑ ላይ ብቻ ክርክሩን መሠረት በማድረግ የካሳ ክፍያው ጥያቄ በጣም የተጋነነ ከመሆኑም በላይ የማስረጃም ድጋፍ የሌለው ስለሆነ በነጻ ልሰናበት ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የምእራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃ ጋር አገናዝቦ መርምሮ ከሳሽ በደረሰባት ድብደባ ምክንያት አንድ ዓይኗን ያጣች ስለሆነና አንድ ዓይን ያለው ሰው ሁለት ዓይን ካለው ሰው ጋር እኩል የመሥራት ችሎታ እንደማይኖረው ይታመናል ካለ በኋላ ጉዳቱ ሲደርስ ከሳሽ እድሜዋ 27 ዓመት የነበረ ሲሆን ጉዳቱ ባይደርስባት ኖሮ በቀን ብር 4 ሂሳብ በወር ብር 120 በዓመት ብር 1440.00 እንደምታገኝ መረዳት ይቻላል፡፡ ከሳሽ እስከ 50 ዓመት ድረስ ትኖራለች ተብሎ ስለሚገመት በአጠቃላይ ብር 41,760.00 ገቢ ታገኝ ነበር፡፡ ይሁንና በደረሰባት ጉዳት ምክንያት 40%(አርባ በመቶ) የመስራት አቅሟ የቀነሰ ስለሆነ ይህም ሲሰላ ብር 16,800.57(አስራ ስድስት ሺ.ህ ስምንት መቶ ብር ከሃምሳ ሰባት ሳንቲም) ስለሚሆን የሞራል ካሳ ብር 1000 (አንድ ሺ.ህ) ጨምሮ በድምሩ ብር 17,800.57 (አስራ ሰባት ሺ.ህ ስምንት መቶ ብር ከሃምሣ ሰባት ሣንቲም) ተከሳሽ ለከሳሽ እንዲከፍል እንደዚሁም ለመድኃኒት መግዣ ብር 363.05 ለመነጽር ብር 415.40 ለትራንስፖርት ብር 1060.30(አንድ ሺ. ስልሳ ከሠላሳ) በአዲስ አበባ ቆይታ የአልጋ የምግብና የታክሲ ከሳሽንና ረዳቷን ጨምሮ ብር 1740.00(አንድ ሺ. ሰባት መቶ አርባ) በአጠቃላይ ብር 21,378.92 (ሃያ አንድ ሺ.ህ ሶስት መቶ ሰባ ስምንት ብር ከዘጠና ሁለት ሳንቲም) ተከሳሽ ለከሳሽ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት

የይግባኝ ቅሬታውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/377 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበለትም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ የአሁን አመልካች በአንድ ዓይኗ መጥፋት ምክንያት ሠርታ ገቢ ለማግኘት የሚከለክላት ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የወደፊት ጉዳት ካሳ ሊከፈላት ይገባል በማለት የሰጡት ውሳኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2090(1) አኳያ ተገቢ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ የተወሰነውን የካሳ ክፍያ በመሻር ሕክምናውን ለመከታተል ተጠሪ ያወጣችው ወጭና የሞራል ካሳን በተመለከተ እንዲከፈላት የተወሰነውን አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ መርምሮ በአመልካች ላይ አንድ ዓይን የመጥፋት የአካል ጉዳት የደረሰባት መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሠርታ ለመኖር የሚከለክላት ነገር የለም በሚል የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበታች ፍ/ቤቶች ካሳ እንዲከፈላት የተሰጠውን ውሳኔ የመሻሩ አግባብነት ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ በፈጸመው ድብደባ ምክንያት የአመልካች የቀኝ ዓይን የጠፋ ስለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

በአመልካች ላይ የደረሰው ጉዳት የአካል ጉዳት እንደመሆኑ መጠን አመልካች ማስረዳት የሚጠበቅባት ጉዳት የደረሰባት መሆኑን ጉዳቱን ባደረሰው የተጠሪ ድርጊትና በተገኘው ውጤት መካከል ቅርብና ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት /cause and effect relationship/ መኖሩን ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2067 መሠረት ኃላፊነቱ በጥፋት ላይ ያልተመሠረተ ጥብቅ /Strict/ ስለሆነ የጉዳት አድራሹን የአእምሮ ሁኔታ /State of mind/ ማስረዳት አይጠበቅባትም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም በዚሁ ላይ



ተመሥርተው የኃላፊነት ውሳኔ የሰጡ ከመሆኑም በላይ ኃላፊነቱ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻው የጉዳዩ ጭብጥ ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊ ነው ከተባለ ካሳ ለመክፈል ይገደዳልን? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በቅድሚያም ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2090(1)፣ 2091 እና 2092 ድንጋጌዎችን መረዳት እንደሚያስፈልግ ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡

በዚህም መሰረት የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ቀጥሎ የተመለከተው ይዘት አላቸው፡፡

<u>2090 የኪሣራ አከፋፈል</u>

(1) በመደቡ በጉዳቱ ምክንያት ተበዳዩ የሚካሰው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ የሆነ ካሣ በመክፈል ነው፡፡

<u>2091 የኪሣራው ልክ</u>

ለደረሰው ጉዳት አላፊ መሆኑ በሕግ የታወቀው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ ኃላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት፡፡

<u>2092 ለወደፊት ሊደርስ ስለሚችል ጉዳት</u>

ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ ሲሆን አስኪፈፀም ሳይጠብቅ ካሳ ሊከፈለው ይገባል፡፡

የብዙ አገራት ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ሕጎች ሁለት ግቦችን ማለትም ጉዳቱን የመካስ /Insurace goal/ እና የጥፋት ባህሪን የመግራት /Deterrence goal/ ተብለው የሚታወቁትን መርሆች መሠረት በማድረግ የተቀረጹ ሲሆን የኢትዮጵያ ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ሕግም ይህንኑ ዓላማ አካቶ እንደተቀረጸ በሕጉ ላይ ማብራሪያ የጻፉት ፕሮፌሰር ጆርጅ ቺቺኖቪች /The Ethiopian law of compensation for damages/ በሚለው ማብራሪያቸው ላይ አንጸባርቀውታል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2091 እና 2092 መርሆች መሠረት ካሳና ጉዳት እኩል መሆን እንዳለበት ይህ ማለትም በመርህ ደረጃ ተጎጂው ከጉዳቱ አትራፊ መሆን እንደማይገባውና ከደረሰበትም ጉዳት በታች መካስ እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተግባርና በተጨባጭ ሲታይ የጉዳት መጠኑ በፍርድ ቤቱ የሚወሰን ቢሆንም ጉዳዩ የሕግ ጥያቄ ብቻ ባለመሆኑ ውስብስብነት ያለው ከመሆኑም ሌላ ሕጉ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትም የተረጋገጠ ሲሆን እንዲካስ ስለሚፈቅድ ወደፊት ስለሚሆን ነገር እርግጠኛ መሆን ስለማይቻል በካሳ አወሳሰን ረገድ ስሌትን የማዛነፍ ውጤት ያስከትላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተየያዘም በካሳ አወሳሰን ረገድ ከንብረት ጉዳት ይልቅ አተማመኑ የበለጠ ውስብስብ የሚሆነው የደረሰው ጉዳት የአካል ጉዳት በሚሆን ጊዜ ነው፡፡ በእርግጥ በጉዳቱ ምክንያት የተከፈለ ወጪ፣ ለመድኃኒት መግዣ እንደዚሁም ለሰው ሠራሽ የአካል ምትክና ተጎጂው ወደ ሆስፒታል የተመላለሰበት ወጪ የጉዳት ካሳው አካል ስለሆነና በቀላሉም በማስረጃ የሚረጋገጥ በመሆኑ በአወሳሰን ረገድ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ጉዳቱ የዘላቂነት ባህሪይ ሲኖረውና የተጎጂው የመሥራት አቅም በሙሉ ወይንም በከፊል ሲጓደል በጉዳት ካሳው አተማመን ረገድ አስቸጋሪ ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም፡፡

ስለሆነም ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት ሲባል መታየት የሚገባው በአጠቃላይ በተጎጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል ቅነሳ **/General utility/** አንጻር እንጂ ከጉዳቱ በፊት ሲሠራው የነበረውን ሥራ ላለመሥራት ጉዳቱ ያስከተለውን ልዩ ጫናና የቅነሳ መጠን /special utility/ ግምት ውስጥ በማስገባት አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በተጨባጩ ዓለም ሲታይ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ሥራ ለመሥራት ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ እንደ ሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ነው፡፡



በእጃችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ በአመልካች ላይ የደረሰው ጉዳት የአንድ ዓይን መጥፋት ሲሆን ይህም ጉዳት ዘላቂ ከፊል ስንኩልነት /Permanent partial disablement/ ተብሎ የሚመደብ ነው፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ለአመልካች የወደፊት ጉዳት ካሳ ሊከፈላት አይገባም ያለው አንድ ዓይኗን ያጣች ቢሆንም ወደፊት ሥራ ሠርታ ገቢ ከማግኘት ጉዳቱ አይከለክላትም በማለት ነው፡፡

ነገር ግን ጉዳት መድረሱ በተጨባጭ እስከተረጋገጠ ድረስ ለተጎጂው ካሳ አይከፈለውም ማለት ከላይ የተመለከተውንና ጉዳትን የመካስና የጥፋት ባህሪን የመግራት የሕጉን ዓላማንና ግብ የሚጻረር ነው፡፡ አመልካች በደረሰባት የአንድ ዓይን መጥፋት ምክንያት ሙሉ ለሙሉ የመሥራት ችሎታዋን አጥታለች ባይባልም ከላይ እንደተመለከተው ካሳ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን አለበት ሲባል ከአጠቃላይ የመሥራት ኃይል ቅነሳ ጋር ተገናዝቦ እንጂ ከልዩ የመሥራት ኃይል ቅነሳ ጋር ተገናዝቦ ባለመሆኑ አመልካች አንድ ዓይኗን ማጣቷ በወደፊት ሕይወቷ የገቢ መጠን መቀነስ ባያስከትልም እንኳን በአጠቃላይ እንደ ሰው ለመኖር በእያንዳንዱ የእለት ሕይወቷና እንቅስቃሴ ላይ ጉዳት /Punitive damage/ መድረሱ ምክንያታዊ እርግጠኛነት /Reasonable Certainty/ ያለው በመሆኑ ከአጠቀላይ የሕጉ ዓላማም ሆነ ከቁጥር 2091 እና 2092 ድንጋጌዎች አንጻር ካሳን መወሰን አግባብነት ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳት የደረሰበት ወገን የደረሰበትን ጉዳት ልክና ጉዳት አድራሹ ካሳ በመክፈል ረገድ ያለበትን ግዴታ ማስረዳት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2141 ላይ የተመለከተ ቢሆንም ተጎጂው ጉዳት የደረሰበት መሆኑን አረጋግጦ ነገር ግን የካሳውን መጠን ለመገመት አስቸጋሪ ሁኔታ በሚያጋጥም ጊዜ በቁጥር 2102 መሠረት ዳኞች የካሳውን መጠን በርትዕ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ ይህም ጉዳት የደረሰበት ሰው የካሳውን መጠን በማስረዳት ረገድ ያለበትን ሸክም በመጠኑም ቢሆን እንደሚያቀልለት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ጉዳት የደረሰባት ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ ጉዳቱም በወደፊት ሕይወቷ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ እንደማይቀር ምክንያታዊ እርግጠኛነት ያለው ስለመሆኑም የተረጋገጠ በመሆኑ ሊወሰን የሚገባውም የካሳ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2102 መሰረት በርትእ መወሰን የግድ የሚል በመሆኑ በዚሁ መሠረትም የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የካሳውን መጠን በርትእ መወሰኑ በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ ማጽናቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይህንኑ ውሳኔ በመሻር ለአመልካች የወደፊት ካሳ ሊከፈል አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል።

**ው ሳ ኔ**

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 04500 ጥር 9 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል።
2. የምዕራብ ወለጋ ዞን ከፍ/ቤት በመ.ቁ. 210/93 በሚያዝያ 16 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ.2444/95/1 በኅዳር 8 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ጸንቷል።
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ 21296

ታህሳስ 1 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍሰሐ ወርቅነህ
ሐጐስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ውበት አድባሩ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ክስ ባቀረበበት ጉዳይ አመልካች ኃላፊ ነው በማለት ካሣ እንዲከፍል ውሣኔ በመስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው።

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በሞግዚቱ አማካይነት በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካችና በሥር 1ኛ ተከሣሽ ላይ ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነውን መኪና 1ኛ ተከሣሽ ሲያሽከረክር ተሳፍሬ በመጓዝ ላይ ሳለሁ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሰብኝ ስለሆነ የሞራል ካሣን ጨምሮ ብር 31ሺህ ተከሣሾች እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል።

የሥር 2ኛ ተከሣሽ የአሁን አመልካችም በሰጠው መልስ በኃላፊነትና በካሣ መጠኑ ላይ ክርክር ያቀረበ ሲሆን በኃላፊነት ረገድ ባቀረበው ክርክር ከሣሽ በመኪናው ተሳፍሮ ሲጓዝ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት ጉዳቱ የደረሰ መሆኑን አምኖ ነገር ግን ከሣሽ የተሳፈረው ገንዘብ ከፍሎ ሳይሆን በነፃ ለምኖ ስለሆነ ኃላፊነት የለብኝም ብሏል።

1ኛ ተከሣሽም የመኪናው ባለንብረት 2ኛ ተከሣሽ ስለሆነ በኃላፊነት ተጠያቂ ልሆን አልችልም በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማስረጃ ከሰማ በኋላ 2ኛ ተከሣሽን በከሣሽ ላይ ጉዳቱ የደረሰው በነፃ ተሳፍሮ በመጓዝ ላይ እንዳለ ነው ቢልም ያቀረባቸው ምስክሮች ይህንን ካለማስረዳታቸውም በላይ አስረድተው የነበረ ቢሆን እንኳን 2ኛ ተከሣሽ በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን የማይችለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2081(2) ላይ እንደመለከተው መኪናው የተሰረቀበት መሆኑን ባስረዳ ጊዜ ብቻ ስለሆነ ሁለቱም ተከሣሾች ኃላፊ ናቸው በማለት በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከርክሮ ኃላፊነትን በተመለከተ ይግባኝ ባይ /የአሁን አመልካች/ መ/ስጭው በመኪናው ተሳፍሮ የተጓዘው ገንዘብ ሳይከፍል በነፃ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2089(1)መሠረት ኃላፊነት የለብኝም የሚል ክርክር ቢያቀርብም የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት መ/ሰጭም የይግባኝ ባይን መኪና እራሱ ይዞ በሚገለገልበት ጊዜ ጉዳት ደርሶ በሚገኝበት ጊዜ እንጂ መኪናዋ በይ/ባይ ቁጥጥር ሥር እያለች መ/ሰጪው ዋጋ ሳይከፍል ስለተጓዘ ብቻ ተፈፃሚነት አይኖረውም በማለት በዚህ ረገድ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ አድርጎ የካሣ መጠኑንም በተመለከተ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የደረሰውን ጉዳት መሠረት ያደረገ ስለሆነ ይግባኙ ተቀባይነት የለውም ብሎ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት በአመልካች መኪና በነፃ ሲጓዝ ከሆነ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው ተብሎ መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2089(1) አኳያ አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን ጠርቷል፡፡ ሆኖም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ተጠሪ ባለመቅረቡ የአመልካችን የቃል ክርክር ብቻ ችሎቱ አዳምጧል፡፡



ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ክስ በቀረበበት ጉዳይ አመልካች ኃላፊ ነው መባሉ በአግባቡ ነው አይደለም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ተጠሪ ተሳፍሮበታል የተባለው መኪና ባለንብረት እንደመሆኑ መጠን የሚኖርበት ኃላፊነት ጥብቅ /strict/ ስለሆነ ተጠሪ ማስረዳት የሚጠበቅበት አመልካች የዚሁ ተሽከርካሪ ባለቤት መሆኑንና በዚሁ ንብረትም ሲጓዝ ጉዳቱ የደረሰ መሆኑን ብቻ ሲሆን በዚሁ መሠረትም ተጠሪ በማስረጃ አረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩልም ጥፋት ሳይኖር ለሚደርስ ኃላፊነት ሕጉ ሦስት መከላከያዎችን ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህም የተጎጂው ጥፋት፣ የውል ግንኙነት መኖርና ጥቅም የሌለው ግንኙነት /disinterested parties/ መሆናቸውን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2069፣ 2071፣ 2086፣ 2088፣ እና 2089 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

በዚህ አንቀጽ በሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ባቀረበው ክርክር ተጠሪ በመኪናው ላይ የተሳፈረው ገንዘብ ከፍሎ ሳይሆን በነፃ መሆኑን ገልጾ ይህንን ፍሬ ነገር ያስረዱልኛል ያላቸውን ሁለት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ እነዚህ ሁለት ምስክሮች የሰጡት የተሟላ የምስክርነት ቃል ዋናው የፍ/ቤቱ መዝገብ ወይንም ምስክርነት ቃላቸው ተገልብጦ ባለመቅረቡ ምክንያት ዝርዝር ቃላቸውን መገንዘብ ባይቻልም ፍ/ቤቱ ከሰጠው ውሣኔ ላይ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ገንዘብ ከፍሎ በመጓዝ ላይ የነበረ አለመሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በይ/ባይ መኪና የተሳፈረው ጥቅም ሳይኖር መሆኑን ይህ ችሎት ለመገንዘብ ችሏል፡፡

ግንኙነቱ ጥቅም የሌለው በሆነ ጊዜ ደግሞ ጉዳት የደረሰበት ወገን ከውል ውጭ ኃላፊነት ድንጋጌዎችን ጠቅሶ ለመከርከርና ካሣ ለመጠየቅ እንደማይችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2089 (1) ላይ ተመልክቷል፡፡ ባለሀብቱም ሆነ የንብረቱ ጠባቂ ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉት ጥፋት ከፈፀሙ ብቻ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ ቁጥር (2) ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው

ተጎጂው ከውል ውጭ ኃላፊነትን ድንጋጌ ጠቅሶ ካሣ መጠየቅ የሚችለው አደጋው የደረሰው በባለቤቱ ወይም በጠባቂው ጥፋት መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ሲሆን የባለቤቱ ወይም የጠባቂው ኃላፊነት የሚመሰረተው በቁጥር 2084(1) ወይንም 2082(1) ድንጋጌ ሳይሆን በጥፋት ላይ የተመሠረተ ኃላፊነትን በሚመለከት በቁጥር 2028 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል ማለት ነው፡፡ ከዚህም አኳያ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ማስረጃ ሲታይ አመልካች የተሽከርካሪው ባለንብረት መሆኑን በዚህ ተሽከርካሪም ተሳፍሮ ሲጓዝ መንገድ ላይ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ነው፡፡ ይህ ማስረጃ በጥፋት ላይ ላልተመሰረተ ኃላፊነት በቂ ቢሆንም ጉዳቱ የደረሰው በንብረቱ ባለቤት ወይንም በጠባቂው ጥፋት መሆኑን ግን የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡

ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 2089(2) አኳያ ሳይመለከት አመልካች ኃላፊ ነው ማለቱ በአግባቡ ካለመሆኑም በላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ጉዳዩን ከዚህ ድንጋጌ ጋር አያይዞ መርምሮ በቁጥር 2089 (1) አነጋገር መሠረት ባለሀብቱ ወይም ጠባቂው አንድ ጥቅም ሳያገኝ በእንስሳው፣ በሕንፃው ወይም "በሌላ ነገር" ይገለገል የነበረው ተብሎ ከተዘረዘረው "በሌላ ነገር" የሚለው ቃል ተሽከርካሪን የሚያጠቃልል ስለመሆኑ አከራካሪ እንደሆነ በውሣኔው ላይ አስፍሮ፣ ያጠቃልላል ቢባል እንኳን ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት የአመልካች መኪናን እራሱ ይዞ በመገልገል ላይ ሳይሆን የመኪናዋ ሹፌር መኪናዋን ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ እያለ ስለሆነ ድንጋጌው ተፈፃሚነት የለውም በማለት ያስፈረው ውሣኔ አግባብነት የለውም፡፡ ይሁንና በቁጥር 2089 (1) ሥር ከተዘረዘረው ላይ "ሌላ ነገር" የሚለው ቃል ሌላ ሰው ሊገለገልበት የሚችል ተሽከርካሪን ጨምሮ ሌላ ማንኛውም ዓይነት ንብረት እንደሚያጠቃልል መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ በሕጉ ላይ መገልገል የሚለው ቃል ተጠሪ የአመልካችን መኪና እራሱ ይዞ እያሽከረከረ በሚገኝበት ጊዜ ነው የተባለውንም በተመለከተ ያለጥፋት ኃላፊነት /strict liability/ ከአንድ ንብረት ባለቤትነት ከሕንፃ፣ ከእንስሳ፣ ከተሽከርካሪና ከሌሎችም ዓይነት



ንብረቶች ሊመነጭ የሚችል እንደመሆኑ መጠን በእነዚህ ንብረቶች ላይ መገልገል እስከተቻለ ድረስ ከማንኛውም ሁኔታ ጥቅም ሳይኖር የተገለገለ ሰው ጉዳት ቢደርስበት ኃላፊነት እንደሚኖር መገንዘብ ከሚቻል በስተቀር ተጎጂው እራሱ ተሽከርካሪውን ማሽከርከር አለበት የሚለው አገላለጽ በጠባቡ የተተረጎመና በተለይም ከተሽከርካሪ ውጭ ባሉ የተለያዩ ንብረቶች ላይ ተፈፃሚነት ሊኖረው ስለማይችል ፍ/ቤቱ ለሕጉ የሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የሰሜን ወሎ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60/94 ግንቦት 21 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የአማራ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 222/95 በግንቦት 29 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ ጥፋት መፈፀሙ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ኃላፊ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደመዝገብ ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ.22509

ጥቅምት 7 ቀን 2000

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፣** አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ ቀረበ

**ተጠሪ፣** ዳርጌ ሰምሮ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

መዝገቡ የቀረበው የአሁኑ አመልካች ታህሳስ 24 ቀን 1999 ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አሻሽሎ ባቀረበው ክስ፣ንብረትነቱ የአሁኑ አመልካች በሆነ የሰሌዳ ቁጥር 01-13261 ኢ.አ የሆነ ታክሲ በሐምሌ 5 ቀን 1991 ዓ.ም ቤልኤር አካባቢ ገጭቶ ጉዳት ያደረሰብኝ ስለሆነ የጉዳት ካሣ 20,000 (ሀያ ሺ)፣ የሞራል ካሣ 1,000 (አንድ ሺ)፣የተጓደለ ገቢ 123,000 በድምሩ ብር 149,820 (አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃያ ብር ) እንዲከፈለኝ የሚል ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፣በተጠሪ ላይ የደረሰው ቀላል ጭረት ነው፡፡ ጉዳት ደረሰብኝ ለሚለው ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ተጠሪን አደጋው ደረሰ በተባለ ጊዜ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልና የካቲት 12 ወስዶ ያሳከመ መሆኑንና ደህና ነው ተብሎ የተሰናበት መሆኑን ገልጾ የተከራከረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ከዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል ያቀረበው ማስረጃ ጉዳት ማድረሱን ያረጋግጣል በማለት በርትዕ 15,000 (አሥራ አምስት ሺ) የጉዳት ካሳ፣የሞራል ካሣ 1000 ጠቅላላው 16,000 (አሥራ ስድስት ሺ) እንዲከፈል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡



ይህ ችሎት ሰኔ 20 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት ለተጠሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው የተወሰነው ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ቀርቦ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር እንዲሰማ ትዕዛዝ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ተጠሪ የጋዜጣ ጥሪ ተደርጐለት ሊቀርብ ባለመቻሉ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትዕዛዝ ሰጥቶ የቀረበውን የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መርምሯል፡፡

በዚህ ጉዳይ በሥር ፍ/ቤት በከሳሽ በኩል ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጡ የተባሉት ምስክሮች ያረጋገጡት ነገር ሲኖር ተጠሪ በደረሰበት አደጋ የካቲት 12 ሆስፒታል እየተመላለሰ ይታከም የነበረ መሆኑን ነው፡፡ አሁን በመጨረሻ ተጠሪ ለጉዳቱ ማስረጃ አድርጐ ያቀረበው የሕክምና ማስረጃ አደጋው ደረሰ በተባለ ጊዜ ሕክምና ሲከታተልበት ከነበረው ሆስፒታል ሳይሆን ከዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል መሆኑ ታውቋል፡፡ ተጠሪ በእርግጥ ጉዳት ደርሶበት ቢሆን ኖሮ የሕክምና ማስረጃዎቹን አሟልቶ ሊያቀርብ ይገባ የነበረው ሕክምና ከተከታተለበት ሆስፒታል እንጂ ከቆይታ በኋላ ምንም የሕክምና ክትትል ካላደረገበት ሆስፒታል ሊሆን ባልተገባ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ በሥር ፍ/ቤት ውሳኔ መሠረት የሆነው ማስረጃ ተጠሪ ለክሱ መነሻ በሆነው መኪና ሳቢያ ጉዳት የደረሰበት ለመሆኑ የሚያስርዳ አይሆንም፡፡ ምንም እንኳን ይህ ችሎት ተጠሪ በወቅቱ ሕክምናውን ይከታተል ነበር ከተባሉባቸው ሆስፒታሎች የሕክምና ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ ያደረገው ጥረት የተፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ ያልቻለ ቢሆንም ተጠሪ በበኩ ጉዳዩን ተከታትሎ ዳር ለማድረስ ያልፈለገ መሆኑ ሲታይ ለስር ፍ/ቤት ቀርቦ ለጉዳቱ ማረጋገጫ ተደርጐ የተወሰደው የሕክምና ማስረጃ አጠራጣሪ ሊሆን እንደሚችል ይህ ችሎት ተቀብሎታል፡፡

ባጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የሕክምና ማስረጃ ለክሱ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው ስለመሆኑ የተረጋገጠ ነገር ሳይኖር የተደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

የሥር ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው የዳግማዊ ሚኒሊክ ሆስፒታል የሕክምና ሰርተፍኬት ለክሱ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የለውም ብለናል፣

-የፌ/መ/ደ/ፍቤት በመ/ቁ.01187 ጥቅምት 13 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ኀዳር 20 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ.26303 የሰጡዋቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፡፡

-መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰበር መ/ቁ. 23924

የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቢሲንያ ባንክ - እስክንድር ጉይተኦም ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- አበበ ከበደ (አቶ) - ጠበቃ ግርማ ሃይሌ ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በስህተት ወደማይመለከተው የባንክ ሂሣብ የገባውና የተወሰደውን ገንዘብ ይመለስልኝ በማለት አመልካች ባቀረበው ክስ መነሻነት የታየውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ለቀረበበት ክስ የመከላከያ መልስ ከመስጠቱም በተጨማሪ በበኩሉም ከሂሣቡ ያለአግባብ ወጥቶ ተወስዶአል ያለውን ገንዘብ ይከፈለው ዘንድ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቦአል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከመረመረ በኂላ፣ አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጎአል፣ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ግን የተቀበለው ሲሆን፣ በዚህ መሠረትም አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን አጽንቶአል፣ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም አመልካች መጋቢት 11 ቀን 1998 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በተጠሪው የባንክ ሂሣብ ውስጥ በስህተት ገባ የተባለውን ገንዘብ ተጠሪ ሊመልስ አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ

ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተውን መዝገብ (ቁ. 144) አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው አመልካች ካቀረባቸው ማስረጃዎች መሃል ተጠሪ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ሲከፍት የሞላው ቁጥር 003 እንደነበር፣ እና አቶ ዮሐንስ ክፍሌ የተባሉት ደግሞ ልዩ የቁጠባ ሂሣብ ቁጥር 003 መክፈታቸውን፣ አቶ ሚካኤል ስዩም የተባለ ሰው በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ልዩ የቁጠባ ሂሣብ ብር 29,417.00 ያስገባበት የጥሬ ገንዘብ ማስገቢያ ቅጽ እና የባንኩ ገንዘብ ያዥ ገንዘቡን ለመቀበሉ የፈረመበትና ማህተም ያደረገበት ደረሰኝ፣ ከዚህ በኋላ ተጠሪ በተለያዩ ጊዜአት ገንዘብ ወጪ አድርጎ መውሰዱን የሚያሳዩ ቼኮች እና የባንኩ ዋና ተቆጣጣሪ ለባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅና የቦርዱ ሊቀመንበር ያቀረበው ማስታወሻ እንደሚገኙ ከመዝገቡ አረጋግጠናል፡፡ ተጠሪም ባቀረበው መልስ ገንዘቡን ሊመልስ እንደማይገባ በመግለጽ የተከራከረ ቢሆንም፤ በማስረጃ ረገድ ግን የተባለውን ገንዘብ በትክክለኛ መንገድ ወደ እሱ የገባ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ በመከላከያ ማስረጃነት የጠቀሳቸው በባንኩ ተንቀሳቃሽ ሂሣብ መክፈቱን፣ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው የተመዘገበ ነጋዴ መሆኑ እና ባንኩ (አመልካች) በሂሣቡ ውስጥ ብር 32,951.00 እንዳለው አረጋግጦ ጽፎለት የነበረ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ ብር 29,417.00 ባንክ እንዲገባ ያዘዘው አቶ ሚካኤል ስዩም በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ስም በተከፈተው ልዩ የቁጠባ ሂሣብ እንዲገባ እንጂ በተጠሪ ስም በተከፈተው ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ውስጥ እንዲገባ አላዘዘም፡፡ በእርግጥ ይህ ገንዘብ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በእነ አቶ ዮሐንስ ክፍሌ ስም በተከፈተው ልዩ ሂሣብ መግባት ሲገባው የባንኩ ሠራተኛ በፈጸመው ስህተት የተነሣ በተጠሪ ስም በተከፈተው ተንቀሳቃሽ ሂሣብ ውስጥ እንዲገባ ስለመደረጉ አመልካች በክሱ ገልጾአል፡፡ በኋላ በባንኩ ዋና ተቆጣጣሪ በተደረገው ማጣራትም ገንዘቡ በስህተት ወደማይገባው ሂሣብ ቁጥር ገብቶ መገኘቱ ታውቆአል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሊነሳና መልስም ሊያገኝ የሚገባው ዋናው ጥያቄ አመልካች እንደክሱ ለማስረዳት አቅርቦ ካሰማው ማስረጃ ውጪ ምን የተለየ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይጠበቅበት ነበር? የሚለው ነው፡፡ በበኩላችን እንደምናየው አመልካች የጉዳዩን አነሳስና ሂደት በትክክል የሚያሳዩ ማስረጃዎችን አቅርቦአል፡፡ ማስረጃዎቹ ሚዛን ውስጥ ገብተው ቅለታቸውና እና ክብደታቸው ሊታይ ይችል የነበረው ተጠሪ ገንዘቡ ከተባለው ወጪ በሆነ ሁኔታ ማለትም በትክክለኛ መንገድ ወደ ሂሣቡ የገባ መሆኑ የሚያሳዩ ማስረጃ አቅርቦ ቢሆን ነበር፡፡ ከክርክሩ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው እንኳንስ መከላከያ ማስረጃ ሊያቀረብ ቀርቶ ገንዘቡ ወደ ሂሣቡ ከየት በኩል እንደገባለት እንኳን ሊገልጽ አልቻለም፡፡ ይህም ማለት የማስረዳት ሸክሙን ያልተወጣው ወይም መከላከል ያልቻለው ተጠሪ ነው ማለት ነው፡፡ ሁኔታው ይህ በሆነ ጊዜም አመልካች እንደክሱ አላስረዳም ከሚል መደምደሚያ ላይ ለመድረስ የሚያስችል የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 00144 ታሕሣሥ 29 ቀን 1996 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27479 ጥር 10 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ያለአግባብ የወሰደውን ብር 29,417 (ሃያ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ አስራ ሰባት ብር) ክሱ ከቀረበበት ሚያዝያ 30 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ 9% (ዘጠኝ በመቶ) በመጨመር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡

3. አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና 23 በር ችሎት መዝገብ ሲያስከፍት የከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ተጠሪ ይተካለት ብለናል፡፡

4. አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነው ብር 3250(ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) በስህተት ወደተጠሪ ሂሣብ ገብቶአል በተባለው ብር 29,417.00 የሚጠቃለል በመሆኑ አመልካች የሚከፍልበት ምክንያት የለም ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

**ት ዕ ዛ ዝ**

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመጣው ቁጥር 144 የሆነው መዝገብ መደመጣበት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 24818

የካቲት 4 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ይልቃል በእውቀቱ - ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ስዩም አባዲ ወኪሉ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና አደጋ ደረሰ የተባለውን ጉዳት መሠረት በማድረግ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብ/ክ/መ/ በደቡባዊ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረውም የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ የአሁኑ አመልካች ንብረት በሆነው የጭነት መኪና ተሳፍሮ ሲሄድ ሳለ መኪናው በመገልበጡ አደጋው የደረሰበት መሆኑን በመግለጽ ካሣ እንዲከፈለው ክስ መስርቶአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ኃላፊነቱንና የኃላፊነቱን መጠን በማስመልከት ክርክሩን ያሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፣ አመልካች ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ በመሆኑ ብር 55370.00 /ሀምሣ አምስት ሺ ሶስት መቶ ሰባ/ ካሣ ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እና የሰበር ችሎትም ውሣኔው ትክክል ነው ብለውታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 8 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሥር ፍ/ቤቶች አመልካችን ኃላፊ በማድረግ የሰጡት ውሣኔ ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2089 /2/ አንፃር

ሲታይ ያለውን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ ካሣ የጠየቀበት ጉዳት ደረሰብኝ የሚለው በአመልካች መኪና ተሳፋሮ ሲሄድ በነበረበት ጊዜ መኪናው በመገልበጡ ነው፡፡ መኪናው ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የተመደበ ሳይሆን የደረቅ ዕቃ መጫኛ እንደሆነም አላከራከረም፡፡ በእርግጥ አመልካች በአጠቃላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ አይደለሁም በማለት የተከራከረ ሲሆን በተለይ ደግሞ የተጠሪን በመኪናው ላይ መሳፈርም ይክዳል፡፡ ተጠሪም ተሳፍሮ ሲሄድ ጉዳቱ እንደደረሰበት ከመግለጽ አልፎ በምን ሁኔታ መኪናው ላይ ሊሳፈር እንደቻለ ሊያስረዳ አልቻለም፡፡ መኪናውን ያሽከረክር ከነበረው ሹፌር ጋር ያደረገው ውል እንደነበረ በክርክሩ ላይ አላነሳም፡፡ በአጠቃላይ ገንዘብ ከፍዬ ነው የተሳፈርኩት አይልም፡፡ በመሆኑም በእርግጥም በመኪናው ተሳፍሮ ነበር፡፡ እንዲሁም በመኪናው መገልበጥ ምክንያትም ጉዳቱ ደርሶበታል ቢባልስ አመልካች ኃላፊ የሚሆንበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለው ነጥብ መመርምሩ ተገቢ ይሆናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ በአመልካች መኪና ላይ ተሳፍሮ መጓዙ በመኪናው መጠቀሙን ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድም ተጠቃሚ የሆነው ተጠሪው ብቻ ነው፡፡ የመኪናው ባለቤት /አመልካች/ ከተጠሪ ገንዘብ /የትራንስፖርት/ በመቀበል ጥቅም አላገኘም፡፡ ከዚህ የተነሣም ሁኔታው ጥቅም የሌለው ግንኙነት በሚል ከተደነገገው ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2089 አንፃር የሚታይ ይሆናል፡፡ ግንኙነቱ ጥቅም የሌለው በሆነ ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ወገን ከውል ወጪ ኃላፊነት ድንጋጌዎችን ጠቅሶ ለመከራከርና ካሣ ለመጠየቅ እንደማይችል በንዑስ ቁ. /1/ የተመለከተ ሲሆን፣ ባለሀብቱም ሆነ ጠባቂ ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉት ጥፋት ከፈፀሙ ብቻ እንደሆነ በንኡስ ቁ. /2/ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተጎጂው ከውል ውጪ ኃላፊነት ድንጋጌን ጠቅሶ ካሣ መጠየቅ የሚችለው ጉዳቱ የደረሰበት በንብረቱ ባለቤት ወይም በጠባቂው ጥፋት መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የአመልካች ወይም የሹፌሩ



ጥፋት ስለመኖሩ ሊያስረዳ አልቻለም፡፡ ይልቁንም ክሱን በአመልካች ላይ የመሠረተው ባለቤትነቱን መሠረት በማድረግ ብቻ እንደሆነ ነው ከመዝገቡ ማየት የቻልነው፡፡ ስናጠቃልለው ተጠሪ ከአመልካች የጉዳት ካሣ የሚጠይቅበት የሕግ ምክንያት አለ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔም የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት በትግራይ ብ/ክ/መ/ የደቡብ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 448/97 /00458/96/ በታሕሣሥ 6 ቀን 1998 ዓ.ም. የተሰጠው እና በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14674 መጋቢት 4 ቀን 1998 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ አይደለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 27565

ታህሣሥ 01 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ አለማየሁ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ደምሴ ወርቅነህ - ቀረቡ፡፡

2. ጄነሲስ ፊርምስ ኢት/ኃ/የተ/የግ/ማ - አልቀረበም፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የጀመረው በምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪና አቶ ሙሉጌታ ጌታቸው በተባሉት ላይ በመሠረተው ክስ አቶ ሙሉጌታ ጌታቸው የ2ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነችውን መኪና ሲያሽከረክር የ1ኛ ተጠሪ ታክሲን ገጭቶ ጉዳት በማድረሱ እና ታክሲዋ ከጥቅም ውጪ በመሆኗ የታክሲዋን ዋጋ ብር 80,000 (ሰማንያ ሺ) ፣ ታክሲዋ የምታስገባው ገቢ የ211 ቀናት በቀን 100 ብር ታስቦ ብር 21,000 (ሀያ አንድ ሺ) እና መኪናዋን ለማስጎተት የወጣው 200 ብር በድምሩ 101,300 ብር እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ መድን ድርጅት ጣልቃ እንዲገባለት በጠየቀው መሠረት አመልካች ወደ ክርክሩ ጣልቃ ስለገባና ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ታክሲዋ ከጥቅም ውጪ በመሆኗ የመኪናዋን ዋጋ 80,000 ብር የተቋረጠ ገቢ ብር 18,300 እና መኪናዋን ለማስጎተት የወጣውን ብር 200 2ኛ ተጠሪና መድን ድርጅት በመድን ሽፋኑ መሠረት እንዲከፈል ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዟል፡፡



የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ይህ ችሎትም መኪናው ወድሟል ተብሎ የመኪናው ዋጋ ከተከፈለ በኋላ እንደገና የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፤ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የ1ኛ ተጠሪ መኪና ንብረትነቱ የ2ኛ ተጠሪ በሆነ መኪና ተገጭቶ ሙሉ ለሙሉ መውደሙ የሥር ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት 2ኛ ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ተብሏል፡፡ በደረሰው ጉዳትም የ1ኛ ተጠሪ መኪና ሥራ ላይ ተሠማርቶ ሊያስገኝ ይችል የነበረው ገቢ ተቋርጧል፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ በመኪናው ላይ በደረሰው ጉዳት ብቻ ሣይሆን በጉዳቱ ምክንያት ለተጠሪ ገቢ ማጣትም ተጠያቂ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አንዱ ጉዳት ብቻ ተመርጦ እንዲካስ የሚደረግበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ጉዳት ሊካስ የሚገባው ከጉዳቱ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እንደሆነ በፍ/ሕ/ቁ. 2090 የተመለከተ በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ የመኪናውን ዋጋም ሆነ የታጣውን ገቢ እንዲከፍል መወሰኑ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ የሕግ ነጥብ ላይ የሠበር ችሎት በመ/ቁ. 12479 እና 25589 የሰጠውን ትርጉም መመልከት ይቻላል፡፡

የአሁን አመልካች ካሣውን እንዲከፍል የተወሰነው ለ2ኛ ተጠሪ የመድን ሽፋን በመስጠቱ ምክንያት ነው፡፡ አመልካችም መኪናው ወድሟል ተብሎ የመኪናው ዋጋ ከተከፈለ በድጋሚ የታጣ ገቢ እንዲከፈል መወሰኑ ሁለቴ እንዲካስ ማድረግ ነው ከማለት በቀር የታጣ ገቢ ሊከፈል የማይገባበትን ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ሌላ ክርክር አላቀረበም፡፡ በእርግጥ በሠበር ችሎት በሰጡት የመ/መልስ ላይ ለመኪናው ዋጋ በተከፈለው ገንዘብ መኪና ገዝተው በመጠቀም ገቢው እንዳይቋረጥባቸው ማድረግ ሲገባቸው ወይም የተቋረጠ ገቢን የሚተካ የመድን ዋስትና /Consequential loss policy/ በመግዛት ገቢያቸው እንዳይቋረጥባቸው ማድረግ ሲገባቸው ይህንን ሣያደርጉ የመጣባቸውን ጉዳት ሊጠይቁ አይገባም በማለት የተከራከሩ ቢሆንም አመልካች

ለ2ኛ ተጠሪ በሠጠው የመድን ሽፋን ውል የታጣ ገቢ ላለመክፈል የተስማሙ ለመሆኑ ወይም ሌላ ተመሣሣይ ክርክር አላቀረቡም፡፡ ከሥር ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው የመኪናውን ዋጋና የተቋረጠ ገቢ አጣምረን ልንከፍል አይገባም የሚል በመሆኑና ይህ ደግሞ ከፍ ሲል ከተዘረዘረው ምክንያት ተቀባይነት ያለው ክርክር ባለመሆኑ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ማለት አልተቻለም፡፡

**ው ሣ ኔ**

የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04782 በ12/7/98 የሰጠው ውሣኔ እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40263 በ5/3/99 የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 27623

ኀዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ማኀበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ -ነ/ፈጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ውባየሁ አበበ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሲከፍለኝ የነበረውን የጡረታ አበል ሌላ ባል ሳላገባ አግብተሻል በሚል ምክንያት ያቋረጠ ስለሆነ እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች የጡረታ አበል ክፍያውን ያቋረጠው ያለ አግባብ ስለሆነ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ በመስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በድምጽ ብልጫ ይግባኙን በመሰረዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ክስ የቀረበበት ጉዳይ በፍ/ቤት ሊታይ የሚችል ስለመሆኑ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የጡረታ አበል ክፍያን በተመለከተ ይህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 18342 ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የማኀበራዊ ዋስትና ባለሥልጣንን በአዲስ መልክ ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 38/88 አንቀጽ 5፣ 8 እና 11ን በመተርጎም የማኀበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን በሕጉ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የማኀበራዊ ዋስትና መብት ጥቅምን በሚመለከት በሚሰጠው ውሣኔ

ላይ ይግባኝ የሚቀርበው ለማኀበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደሆነ ጉባኤውም የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ መሆኑን በሕግ ተለይተው በአስተዳደራዊ ውሣኔ እንዲቋጩ በተባሉ ጉዳዮች ላይ መደበኛ ፍ/ቤት የመዳኘት የሥረ ነገር ሥልጣን እንደሌለው በመዘርዘር የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ተጠሪ ተቋርጦብኛል የሚሉት የጡረታ አበል ክፍያን በተመለከተ አቤቱታውን ማቅረብ የሚገባቸው ለማኀበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን ወይንም በአሁኑ አጠራር ለማኀበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ መሆን ያለበት ሲሆን ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን ለማኀበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ከሚያቀርብ በስተቀር ከላይ እንደተመለከተው በዚህ ጉዳይ ፍ/ቤቶች የሥረ ነገር ሥልጣን የሌላቸው በመሆኑ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ውሣኔ መስጠቱ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12570 በ22/9/98 የሰጠው ውሣኔና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 09916 በ16/2/99 ዓ.ም. በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ይህን ጉዳይ በተመለከተ መደበኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 28612

የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ጋረደው ቢራቱ ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን - ጥሩወርቅ ኃ/ማርያም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

አከራካሪው ጉዳይ ከውል ውጪ የደረሰን ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የቀረበ የካሣ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተውም ሠራተኞቹ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 12 ቀበሌ 06 ክልል የቁፋሮ ሥራ ሲያካሂዱ 200 ደንበኞችን በያዘ የስልክ ኬብል ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ በደረሰው ጉዳት የተነሳም የብር 5180.62 (አምስት ሺ አንድ መቶ ሰማንያ ብር ከስልሣ ሁለት ሣንቲም) ኪሣራ ደርሶብኛል፡፡ ስለዚህ ተከሣሹ ይህን ገንዘብ ከነወጪው ይክፈለኝ በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ በመቀጠልም ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው በማለት የወሰነ ቢሆንም፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሚከፈል ካሣ የለም በማለት መዝገቡን ዘግቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ በአመልካቹ

የስልክ ኬብል ላይ ጉዳት ማድረሱ ተረጋግጦ ኃላፊ ነው ከተባለ በኋላ ካሣ ግን አይከፍልም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች በኬብሉ መጎዳት ምክንያት የደረሰበትን ኪሣራ አስልቶ ከነምክንያቱ በዝርዝር አቅርቧል፡፡ በኪሣራ የተጠየቀው ገንዘብ ብር 5180.62 /አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ብር ከስድሳ ሁለት ሣንቲም/ ሲሆን ይህም ኬብሉን ለመጠገን ጥቅም ላይ ለዋሉ እቃዎች መግዣ እና ጥገናውን ላካሄዱ ባለሙያዎች ያወጣውን ወጪ የሚያጠቃልል ነው፡፡ ማስረጃዎቹንም አይይዞ አቅርቧል፡፡ ይህም የሚያሳየው አመልካች ካሣ ጠያቂ እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2141 በተደነገገው መሠረት የደረሰበትን ጉዳት ልክ የሚያሳዩ ማስረጃዎች አቅርቦ ማስረዳቱን ነው፡፡ በአንፃሩ ግን ተጠሪ በክሱ የተመለከተውን ኪሣራ አለማድረሱን በማስመልከት ያቀረበው የማስተባበያ ማስረጃ የለም፡፡ በእርግጥም ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ የተባለው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ ኃላፊነትቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን እንዳለበት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2091 ተመልክቶአል፡፡ በዚህ ድንጋጌ አባባል ጉዳቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ከደረሰው ጉዳት ጋራ ማመዛዘን የሚቻልበት አንዱ ዋነኛው መንገድ ማስረጃ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አመልካች የጉዳቱን ልክ የሚያሳይ ማስረጃ አቅርቦአል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው እየተባለ በሌላ በኩል ግን ላደረሰው ጉዳት ካሣ አይከፍልም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00032 ነሐሴ 27 ቀን 95 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26756 ኀዳር 13 ቀን 99 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ ክስ የቀረበበትን ብር 5180.62 /አምስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ብር ከስድሳ ሁለት ሣንቲም/ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲሁም በዚህ ሰበር ችሎት ከተከፈለው ዳኝነት ጋር ይክፈል ብለን ወስነናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 28750

ኀዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ ዝናቡ ታደሰ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ዘውዱ ዓሊ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ በአመልካችና በሥር 1ኛ ተከሣሽ ላይ በክስ የጠየቀውን ገንዘብ ተከሳሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ሊከፍሉ ይገባል በማለት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ በመስጠቱና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ይህንኑ ውሣኔ በማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አነሳስም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካችና በሥር 1ኛ ተከሣሽ ላይ ባቀረበው ክስ 1ኛ ተከሣሽ ከባንክ ጋር ባደረጉት ስምምነት ኤል-ሲ ተከፍቶላቸው ከውጭ ዕቃ እንዲገባላቸው የተደረገ ሲሆን ነገር ግን ባንኩ ሳይጽፍላቸውና ሳይወከሉ በባንኩ ስም ወይም ትዕዛዝ የመጣውን ዕቃ በሕገ ወጥ መንገድ ከጉምሩክ ወስደዋል፡፡ በመሆኑም ክስ ለቀረበበት ገንዘብ ብር 395,738.59 (ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺ ሰባት መቶ ሰላሣ አምስት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ) ተጠያቂ ናቸው፡፡ እንዲሁም ሁለተኛ ተከሣሽ (የጉምሩክ ባለሥልጣን) በባንኩ ባለቤትነት የመጣውን ዕቃ ባለመብት ላልሆነው አንደኛ ተከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 20/1/ እና በጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣውን የዕቃ አወጣጥ ማንዋል በመጣስ በመልቀቁ ኃላፊነት ያለበት ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሾች ደርሶ የየበኩላቸውን የመከላከያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን 2ኛ ተከሣሽ የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 20/1/ የተዘረዘሩትን ዶክመንቶች የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት አስመጪ የተባለው ወገን ነው፡፡ አስመጪው ጉምሩክ እነዚህን ዶክመንቶች ሲጠይቀው የማቅረብ ግዴታ አለበት ማለትም ጉምሩክ እነዚህን ዶክመንቶች የማየት ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ ወይም እነዚህን ዶክመንቶች የሚሰጡት ወገኖች ካልፈቀዱ በስተቀር ባለንብረቶቹ አይስተናገዱም ማለት አይደለም ብሏል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የገባው ዕቃ ባለቤት እኔ ነኝ በማለት የከሰሰ ቢሆንም በቀረቡት ማስረጃዎች ዶክመንቶቹ በሙሉ የሚያስረዱት የዕቃው ባለቤት 1ኛ ተከሣሽ መሆናቸውን ነው፡፡ በመሆኑም አንደኛ ተከሣሽ ዕቃው ወደ ጉምሩክ መጋዘን ሲገባ ባሉት ዶክመንቶች ቀረጥና ታክስ ከፍዬ ልስተናገድ ባሉበት ጊዜ የጉምሩክ ባለሥልጣን ይህንኑ መፍቀዱ ተገቢነት አለው በማለትና ሌሎችንም መከራከሪያዎች በማቅረብ ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ 2ኛ ተከሣሽ /አመልካች/ በ1987 ዓ.ም. በወጣው የጉምሩክ ሥራና የቁጥጥር ማንዋል መመሪያ መሠረት ዕቃዎችን ለማስረከብ የባንክ ፈቃድን የመጠየቅ ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን ይህንኑ ግዴታውን በመጣስ ዕቃውን ለ1ኛ ተከሣሽ ያስረከበ ስለሆነ ብር 242,121.45 /ሁለት መቶ አርባ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ አንድ ከአርባ አምስት/ ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ የሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ለእዳው ከሥር 1ኛ ተከሣሽ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ነው መባሉ ለሰበር ቀርቦ መጣራት የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከሥር 1ኛ ተከሣሽ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለመክፈል ይገደዳል ወይ ? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በባንኩ ባለቤትነት የመጣውን እቃ ባለመብት ላልሆነው አንደኛ ተከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 60/89 አንቀጽ 20(1) እና በጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣውን የዕቃ አወጣጥ ማንዋል በመጣስ ዕቃውን የለቀቀ ስለሆነ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ሊከፍል ይገባል በማለት ነው፡፡ አመልካችም እንዲለቀቁ የተደረጉት ዕቃዎች ባለቤትነታቸው የ1ኛ ተከሣሽ እንጂ የሣሽ አይደለም በማለት ክሱን በመቃወም ተከራክሯል፡፡

ይሁንና አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ከውጭ አገር እንዲገቡ የተደረጉ ዕቃዎችን ለ1ኛ ተከሣሽ ከማስረከቡ በፊት የባንክ ፈቃድን ጨምሮ የተለያዩ ሰነዶች ተሟልተው ሲቀርቡለት ብቻ መሆኑን የአመልካችን መ/ቤት ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/89 እና አመልካች እራሱ ባወጣው የአዋጁ አፈፃፀም መመሪያ ላይ ተመልክቷል፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2035 መሠረት አንድ ሰው ተለይቶ የታወቀና ግልጽ የሆነ የሕግ ድንጋጌ ወይም የአስተዳደር ደንብ ከተላለፈ ጥፋት ፈጽሟል ሊባል እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በሰነድ አማካይነት መያዣ ያደረገውን ንብረት አመልካች በሕግና በመመሪያ የተጣለበትን ግዴታ በመጣስ ለሥር 1ኛ ተከሣሽ በመልቀቁ በተጠቀሰው



የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2035 መሠረት በጥፋት ላይ የተመሠረተ ከውል ውጭ ኀላፊነት እንዳለበት ይህ ሰበር ችሎት ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በሌላ በኩልም አመልካችና የሥር 1ኛ ተከሣሽ ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ለተጠሪ ኃላፊ ሊሆኑ ይችላሉን? የሚለውን ነጥብ ሲታይ የአንድነትና የነጠላ ግዴታ ከውል ወይንም በቀጥታ ከሕግ ሊመነጭ የሚችል ሲሆን ግዴታው ከውልም ሆነ ከሕግ ቢመነጭም ሁልጊዜም ቢሆን እንደ አንድ ግዴታ የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ የዚህ ዓይነት ግዴታ በሚኖርበት ጊዜም ባለገንዘቡ በሁሉም ባለእዳዎች ላይ የሚኖረው መብት ከአንድ የክስ ምክንያት /Cause of action/ እንደመነጨ በማድረግ ሕጉ ግምት የሚወስድ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1896 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ማንኛውም ከሣሽ የሆነ ወገንም ሌላው ወገን አንድ ግዴታ እንዲፈጽምለት ክስ ሲያቀርብ ተከሣሹን የሚጠይቀው በምን ዓይነት ግንኙነት እንደሆነ ለይቶ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በተጠሪና በሥር 1ኛ ተከሣሽ መካከል ሰነድን መያዣ በማድረግ በተሰጠ ብድር በውል ላይ የተመሠረተ ግንኙነት የተፈጠረ ሲሆን ተጠሪም ይህንኑ በክሱ ለይቶ በመጥቀስ በውሉ ላይ ተመሥርቶ ሊከፍለኝ ይገባል የሚለውን ጠይቋል በሌላ በኩልም ተጠሪ ክሱን ሲያቀርብ 2ኛው ተከሣሽ የአሁን አመልካች በሰነድ አማካይነት መያዣ ያደረግሁትን ንብረት በሕግና በመመሪያ የተጣለበትን ግዴታ በመጣስ ለ1ኛ ተከሣሽ ለቋል በማለት ስለሆነ ኃላፊነቱም ከውል ውጭ በጥፋት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን የሚኖርበትም ግዴታ ከውል ውጭ በፈፀመው ጥፋት ምክንያት በተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰ ከሆነ ይህንኑ ጉዳት መካስ ስለሚሆን በዚሁ መሠረት ተጠሪ ከውል ውጭ ደርሶብኛል የሚለው ጉዳት ካለ ይህንኑ አስልቶና ለይቶ በክስ መጠየቅ ሲገባው የሁለቱ ተከሣሾች ኃላፊነት ከውልና ከውል ውጭ ከተለያየ የክስ ምክንያት የመነጨ በሆነበት ሁኔታ ተጠሪ የውል ግንኙነት ካለው ከ1ኛው ተከሣሽ ከውሉ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት በክስ የሚጠይቀውን ገንዘብ ከውል ውጭ ኃላፊነት ያለበት 2ኛውም ተከሣሽ

/አመልካች/ በአንድነትና በነጠላ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት መጠየቁ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ከውል ውጭ በስ ግንኙነት ሆኖ አመልካችም በዚሁ መልሱ ኃላፊ መሆን እንዳለበት የተረጋገጠ ቢሆንም አመልካች በፈጸመው ጥፋት ምክንያት በተጠሪ ላይ ጉዳት ደርሶ ከሆነ ይህንኑ ጉዳት ተጠሪ አስልቶና ለይቶ ካሣ እንዲከፈለው መጠየቅ ሲገባው በዚህ መልኩ ክሱ ባልቀረበበት ሁኔታ ከተለያየ የክስ ምክንያት የመነጨውን የሁለቱን ተከሣሾች ኃላፊነት በመቀላቀል የውል ግዴታ ካለበት ከ1ኛ ተከሣሽ ጋር አመልካች በአንድነትና በነጠላ ካሣ ሊፍለኝ ይገባል በማለት ተጠሪ ያቀረበውን ክስ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተቀብሎ በዚሁ መሠረት መወሰኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ይህንኑ ማጽናቱ የሕግ ስህተት የተፈፀባቸው ሆነው ተገኝተዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 00388 በ2/4/96 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 29113 በ5/4/99 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕግ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፈፀመው ጥፋት ከውል ውጭ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ ቢሆንም በዚህ ምክንያት ተጠሪ ደርሶብኛል የሚለው ጉዳት ተለይቶ በክስ ያልተጠየቀ ስለሆነ ከሥር 1ኛ ተከሣሽ በአንድነትና በነጠላ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 28865

ህዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጐስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- አቶ ካሣ ግዛው

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በተጠሪ በኩል ጥፋት መፈጸሙን አመልካች ያላስረዳ ሰለሆነ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት በበታች ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ አመልካች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ተከሳሽ በድርጅታችን በመካኒክነት ተቀጥሮ በመሥራት ላይ እንዳለ የዋጋ ግምታቸው ብር 1178.05 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ስምንት ብር ከአምስት ሣንቲም) የሆኑ የመኪና መለዋወጫዎችን በመኪና ላይ ለመግጠም ተረክቦ ያልገጠመ ከመሆኑም በላይ ጠፍቶብኛል በማለት ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ሳያደርግ የቀረ ስለሆነ ተከሳሽ እነዚህን የተከረባቸውን መለዋወጫ ዕቃዎች መልሶ እንዲያስረክብ ወይንም የዋጋ ግምታቸውን እንዲከፍል ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎችን መረከቡን ሳይክድ የሥራ መደቡ የተበላሹ የከሳሽ መኪናዎችን መጠገን እንደሆነና ጥገናውም የሚከናወነው በመደበኛ የሥራ

ሰዓት እንደሆነ በሥራ መውጪያ ላይም እንደማንኛውም ሠራተኛ ተፈትሾ እንደሚወጣ ገልፆ ንብረቱ ሊጠፋ የቻለው በጥበቃ ሠራተኞች ቸልተኝነት ስለሆነ ክሱ ከበቂ ኪሳራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃ አኳያ ተመልክቶ ተከሳሽ የተረከባቸውን የመለዋወጫ እቃዎች እስከ መቼ ድረስ ተሽከርካሪዎች ላይ መግጠም እንዳለበት ወይም በምን ያህል ጊዜ ወደ ጥገና ክፍል መመለስ እንዳለበት የተመለከተ ነገር ስለሌለና ተከሳሽም የተረከባቸውን ንብረቶች ከሥራ ሰዓት ውጭ የመጠበቅ ኃላፊነት የሌለበት ከመሆኑም ሌላ ንብረቶቹን እንዲያስረክብም ሆነ የዋጋ ግምታቸውን ለመክፈል አይገደድም በማለት ክሱን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት አቤቱታውን መርመሮ ተጠሪ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎችን መከረቡና በመኪናዎች ላይም አለመገጠሙ ተረጋግጦ እያለ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም ተብሎ መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ መጣራት እንዳለበት በማመኑ ተጠሪን ጠርቷል፡፡

ሆኖም ተጠሪ በጋዜጣ ተጠርቶ ያልቀረበ ስለሆነ በአመልካች ክርክር ላይ በመመሥረት የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ይህም ችሎት የሰበር አቤቱታውን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ ሊፈታ የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪ ከአመልካች የተረከባቸውን የመለዋወጫ ዕቃዎች በዓይነት ለማስረከብ ወይንም የዋጋ ግምታቸውን ለመክፈል ይገደዳል ወይስ አይገደድም የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡



ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን የመለዋወጫ ዕቃዎች ከአመልካች ላይ መረከረቡን ሳይክድ ነገር ግን ሊጠፉ የቻሉት በመ/ቤቱ የጥበቃ ሠራተኞች ጥፋት መሆኑን ገልፆ በኃላፊነት ሊጠየቅ እንደማይችል ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ሊከፍል አይገባም ወደሚል ድምዳሜ ለመድረስ የቻለው የተረከባቸውን የተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃዎች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ተሽከርካሪዎች ላይ መግጠም እንዳለበት ወይም በምን ያህል ጊዜ ወደ ጥገና ክፍል መመለስ እንዳለበት የተመለከተ ነገር ካለመኖሩም በላይ ተጠሪ የተረከባቸውን ንብረቶች ከሥራ ሰዓት ውጭ የመጠበቅ ግዴታ ስለሌለበትና ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት የጠፉ ስለመሆኑም አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2027፣ 2029 እና 2031 መሠረት ተጠሪ ጥፋት የፈጸመ ስለመሆኑ በአመልካች ማስረጃ ስላልተረጋገጠ ኃላፊ አይሆንም በማለት ነው፡፡

ይሁንና ተጠሪ ከአመልካች ጋር በፈጠረው የሥራ ውል መነሻነት ለክሱ መነሻ የሆኑትን የተሽከርካሪ መለዋወጫዎችን ስለመረከቡ በአመልካች ማስረጃ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ በተጠሪም አልተካደም፡፡ ተጠሪ እነዚህን ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን የመኪና መለዋወጫዎች ከአመልካች ከተረከበ በኋላ በመኪና ላይ እስከሚገጥምበት ጊዜ ድረስ በንብረቶቹ ላይ ለሚደርስ ማናቸውም ጉዳት፣ ብልሽት ወይንም መጥፋት በኃላፊነት ተጠያቂ ሊሆን ስለሚችል ይህ ችግር እንዳይከሰት ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚጠበቅበት ይታመናል፡፡ ተጠሪ ይህንን ጥንቃቄ ማድረግ ባያስፈልገው ኖሮ ቀድሞውንም ቢሆን ዕቃዎችን ፈርሞ መረከብ ባላስፈለገው ነበር፡፡

በሌላ በኩልም ተጠሪ ፈርሞ የተከረባቸውን እነዚህን የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች እንዳይጠፉ፣ እንዳይሰረቁም ሆነ ሌላ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ የሚጠበቅበት በሥራ ሰዓት እንጂ ከሥራ ሰዓት ውጭ እንዳልሆነም ይታመናል፡፡

ሆኖም ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት ሳይሆን ከሥራ ሰዓት ውጭ የጠፉ ስለመሆኑ የማስረዳቱ ሸክም የእራሱ የተጠሪ እንጂ የአመልካች ሊሆን የማይችል ሲሆን ተጠሪም በዚህ ረገድ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡

ተጠሪ ይህንን የማስረዳት ሸክሙን ካልተወጣ ንብረቱ በእራሱ ቁጥጥር ሥር እያለ መጥፋቱን የሚያሳይና በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2027 መሠረት ቢያንስ በቸልተኝነት ጥፋት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ ንብረቶቹ ከሥራ ሰዓት ውጭ የጠፉ ስለመሆኑ ባላስረዳበት ሁኔታ የማስረዳት ሸክሙን ወደ አመልካች በማዞር ንብረቶቹ በሥራ ሰዓት የጠፉ መሆኑን በማስረዳት ተጠሪ ጥፋት መፈጸሙን አላረጋገጠም በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ እንደዚሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 39118 ህዳር 1 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 36028 ጥቅምት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ጥፋት መፈጸሙ የተረጋገጠ ስለሆነ በክስ የተጠየቀውን ብር 1178.05 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ስምንት ከዜሮ አምስት ሣንቲም) ክስ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ጋር ለአመልካች እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ግልባጩ ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 30032

ታህሣሥ 1 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ ነ/ፈጅ ሰለሞን በቀለ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ ክስ ባቀረቡበት የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ኃላፊ ነው በማለት ካሣ እንዲከፍል ውሣኔ በመስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ባለቤቴ የነበረው ወ/ር ጌትነት ፈጠነ መስከረም 28 ቀን 1994 ዓ.ም. የተከሣሽ ንብረት በሆነው መኪና ተሳፍሮ ከባህርዳር ወደ ጎንደር በሚጓዝበት ወቅት መንገድ ላይ መኪናው ተገልብጦ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል፡፡ ሟች በሞተበት ጊዜ ዕድሜው 38 ዓመት የነበረ ሲሆን ጡረታ ለመውጣት 17 ዓመት ይቀረው ነበር፡፡ የወር ደመወዙም ብር 460.00 የነበረ ሲሆን ይህ በ17 ሲባዛ ብር 93,840.00 ስለሚሆን የኀሊና ጉዳት ካሣ ብር 1 ሺህ ጨምሮ በድምሩ ብር 94,840.00 ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት በእራሳቸውና በሶስት ልጆች ስም ጠይቀዋል፡፡

ክሱና ማስረጃው ለተከሳሽ ደርሶም በሰጠው መልስ በተከሳሽና በሟች መካከል የነበረው ግንኙት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት በመሆኑ ሟችም የሞተው በሥራ ላይ እያለ ስለሆነ የሟች ተተኪዎች ተጠቃሚ ሊሆኑ

የሚችሉት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2037 እና 2038 መሠረት የጡረታ አበል በመጠየቅ እንጂ ከአሰሪው ካሣ የሚጠይቁበት የሕግ ድጋፍ የለም፡፡ ይህ የሚታለፍ ቢሆን የቀረበው አቤቱታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2095 አኳያ ሲታይ የሟች ሚስትና ልጆች መጠየቅ የሚችሉት ካሣ ቀለብ ብቻ እንደሆነ የተደነገገ ሲሆን በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 12 መሠረትም ከሳሽ ቀለብ ለመጠየቅ የምትችለው ሠርታ ለመብላት አቅም የሌላት ከሆነ ብቻ ነው የሚል ክርክር አቅርቦ ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር የመድን ሽፋን ውል ያለው መሆኑን በመግለጽ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ አመልክቷል፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትም በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እስከ ብር 10 ሺህ የመድን ሽፋን መስጠቱን አምኖ በኃላፊነትና በካሣ መጠኑ ላይ ከተከሣሽ ጋር ተመሣሣይ የሆነ ክርክር አቅርቧል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ በተከሳሽም ሆነ በጣልቃ ገቡ ኃላፊነትን አስመልክቶ የቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጎ ለደረሰው ጉዳት ተከሣሽ ኃላፊ ነው ካለ በኋላ የካሳ መጠኑን አስልቶ ቁሳዊ ጉዳት /Material damage/ ብር 24 ሺህ የሞራል ካሣ /Moral damage/ ብር 1 ሺህ እንደዚሁም ወጭና ኪሣራ ብር 1 ሺህ በድምሩ ብር 26 ሺህ ለከሳሽ ሊከፍል እንደሚገባና ከዚህ ገንዘብ ላይ ጣልቃገብ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሰጠው የመድን ሽፋን መሠረት ብር 10 ሺህ እንዲከፍል ቀሪውን ብር 16 ሺህ ደግሞ ተከሣሽ እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኙን ባለመቀበል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ለሰበር መቅረብ የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡



ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ክስ በቀረበበት ነገር አመልካች ኃላፊነት አለበት? ወይንስ የለበትም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን መርምረናል፡፡

የተጠሪ ባለቤት የነበረው ሟች ሊሞት የቻለው ንብረትነቱ የአመልካች በሆነው መኪና ተሳፍሮ በመጓዝ ላይ እንዳለ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡ የተያዘውን ጭብጥ በተሟላ ሁኔታ ለመፍታት እንዲቻልም ሟች የሞት አደጋ የደረሰበት በተጠሪ መ/ቤት በመሥራት ላይ እንዳለ በደረሰበት ጉዳት ነው ወይስ በሌላ መሥሪያ ቤት በመሥራት ላይ እያለ የሚለው ነጥብ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክርክር ሟች በወቅቱ ሲሰራበት የነበረው የክልሉ ማረሚያ ቤት ከተጠሪ መ/ቤት ጋር የመዋቅር ግንኙነት እንደነበራቸውና በተጠሪ መ/ቤት ሥር እንደበረ ሲገልጽ አመልካች ደግሞ የክልሉ ማረሚያ ቤት እራሱን ችሎ የተቋቋመ ነበር በማለት ተከራክረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ሰበር ችሎት መዝገቡን ሲመረምር ሟች ተቀጥሮ ሲሰራበት የነበረው የክልሉ ማረሚያ ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ፍትሕ ቢሮ ማለትም ለአሁን አመልካች እንደነበረ ለመገንዘብ ችሏል፡፡ ሁለቱ መ/ቤቶች በአንድ መዋቅር ስር የተደራጁ ነበሩ ከተባለ ደግሞ ሟች በተጠሪ መኪና ሲጓዝ በመኪናው መገልበጥ ምክንያት ከሞተ በሥራ ላይ እንዳለ መሞቱን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የሞት አደጋ ቢደርስበት በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት ካሳ እንዴት ሊከፈል እንደሚችል መረዳት እንዲቻል የአማራ ክልልን የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 74/1994ን ይህ ሰበር ችሎት አስቀርቦ የተመለከተው ሲሆን ቋሚ የሆነ የመንግሥት ሠራተኛ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል እንደሚከፈል በአንቀጽ 46/5/ሀ/ ላይ መደንገጉን ተገንዝቧል፡፡

ስለሆነም የተጠሪ ባለቤት በሞት የተለየው በሥራ ላይ እያለ ባጋጠመው አደጋ ምክንያት ስለሆነና በሥራ ላይ እያለ በአደጋ ምክንያት የሞት ጉዳት የደረሰበት ሰው በክልሉ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት

ለተተኪዎች የጡረታ አበል ከሚከፈል በስተቀር ከዚህ አልፎ ሌላ ተጨማሪ ካሣ ሊከፈል እንደሚችል በተጠቀሰው ሕግ ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች በተረጋገጠው ፍሬ ነገር ላይ ተመሥርተው ክርክሩን ከክልሉ የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ አኳያ ተመልክተው ውሣኔ መስጠት ሲገባቸው የግራ ቀኙን ግንኙነት ከሚገዛው የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ በመውጣት በፍ/ብሔር ሕጉ ከውል ውጭ ባሉ ድንጋጌዎች መሠረት ውሣኔ መስጠታቸው የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ሆነው ተገኝተዋል።

**ው ሣ ኔ**

1. የደቡብ ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4337 ሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10200 መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ሆነው ተገኝተዋል።
2. ክስ በቀረበበት ጉዳይ አመልካች ኃላፊ አይደለም ተብሎ ተወስኗል። ስለሆነም አመልካችም ሆነ የሥር ጣልቃገቡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለተጠሪ ካሣ ሊከፍሉ አይገባም ተብሎ ተወስኗል።
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ።
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 30442

ኅዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
ሐጎስ ወልዱ
ሂሩት መለሰ
ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን - ሕዝቅኤል ዋዲሱ ቀረበ።

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ድንቋ አመኔ አልቀረበችም።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

**ፍ ር ድ**

አከራካሪው ጉዳይ ከውል ውጪ በሆነ ኃላፊነት የተጠየቀን የካሣ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነው። ክርክሩ የተጀመረው በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ በመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ አመልካችን የከሰሰችው ባለቤቴ እና የልጄ አባት የነበረው ሰው በኤሌክትሪክ ሽቦ ተይዞ ሞቶአልና በዚህ ምክንያት በመተዳደሪያ ረገድ የቀረብኝን ገቢ ይተካልኝ በማለት ነው። ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም አመልካችን አስቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተከሣሽ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ነው። በመሆኑም የተቋረጠውን ጥቅም በጠቅላላው ብር 60,800 ለከሣሽ ይክፈል በማለት ወስኖአል። በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ስህተት የለበትም በማለት ይግባኙን ሳይቀበል ቀርቶአል። የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው።

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል። በሰበር ችሎቱ ይመረመራል ተብሎ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ካሣውን መክፈል ያለበት እንዴት ነው የሚለው ነው። በዚህ መሠረትም ይህን

ነጥብ ግራ ቀኝ ወገኖች ካቀረቡት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር በፍሬ ነገር ረገድ ማረጋገጥ እንደቻልነው የተጠሪ ባል የሞተው ንብረትነቱ የአመልካች በሆነ የኤሌክትሪክ ሽቦ በመያዙ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ኃላፊነትን በተመለከተ ያቀረበውን አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ ከኃላፊነት በመቀጠል የተነሳው ክርክር የሃላፊነቱን መጠን የሚመለከት በመሆኑ ይህን ነጥብ በተለይ በማውጣት አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በተጠሪ የክስ ማመልከቻ እንደተገለጸው እና የሥር ፍ/ቤቶችም እንደተገነዘቡት ሟች ሲሞት በ20 ዓመት እድሜ ላይ የነበረ፣ ሥራው ግብርና የሆነ እና የተለያዩ ሰብሎችን በማምረት በዓመት በአማካይ ብር 5000 (አምስት ሺ) ገቢ ያገኝ እንደነበር ነው፡፡ በመተዳደሪያ ረገድ ቀረብኝ ያለችውም ይህን በዓመት ይገኝ ነበር የተባለውን እንዳለ በማስላት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም ርትዕን መሠረት በማድረግ ገቢውን ወደ ብር 3000 ዝቅ በማድረግ እና ሟች ለተጨማሪ 20 ዓመት ሊኖር ይችል ነበር የሚል ግምት በመውሰድ እንደዚሁም ብር 800 የሞራል ካሣ በማከል በድምሩ ብር 60,800 (ስልሳ ሺ ስምንት መቶ) እንዲከፈል ወስነዋል፡፡ አመልካች ይህን ካሣ ከአሠላሉም ሆነ ቀለብን በተመለከተ ከተደነገገው ሕግ አንፃር በማየት አጥብቆ ተቃውሞታል፡፡

የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ አንዳንድ የቅርብ ዘመዶች የሚኖራቸው መብት የሚታየው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2095 ነው፡፡ ተጠሪ ባለቤትዋ በመሞቱ ምክንያት በቀለብ ረገድ ቀረብኝ የምትለውን በገንዘብ ለማስላት በራስዋ እና በሕፃን ልጅዋ ስም ጠይቃለች፡፡ በመሆኑም የጥያቄዋ አግባብነት የሚታየው ከተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2095/1/ አንፃር ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሚከፈለው ካሣ ምግብን /መተዳደሪያን/ በመስጠት እንደሚደረገው ጡረታ መልክና አይነት እንደሚሆን ሕጉ በግልጽ የሚያመለክት በመሆኑ በእርግጥ ተጠሪ ቀለብ ይቆረጥላት ዘንድ አስፈላጊ ሁኔታዎች አሉ ወይ? አመልካች ቀለብ የመስጠት



ግዴታ ያለበት ሆኖ ቢገኝ ኃላፊነቱ ለሕፃንዋ ብቻ ነው ወይንስ ለተጠሪም ጭምር? የሚሉት ነጥቦች በቅድሚያ ሊመረመሩ የሚገባቸው ናቸው፡፡

ቀለብን የመስጠት ግዴታ የሚወሰኑባቸው ሁኔታዎች በዝርዝር ተመልክተው የሚገኙት በፍ/ብ/ሕጉ ከቁጥር 807 ቀጥለው ባሉት ድንጋጌዎች ነው፡፡ ለተያዘው ጉዳይ አወሳሰን ቀጥተኛ ተገቢነት ያለው ድንጋጌ ቁ. 812 ሲሆን፣ ይህም የቀለብ መስጠት ግደታ የሚገባ ሆኖ የሚገኘው ግዴታው እንዲፈጸምለት የሚጠይቀው ሰው ሠርቶ ለመብላት የማይችል እና በችግር ላይ የወደቀ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ ያመላክታል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምንመለከተው አመልካች እንደሚች ባልዋ በወጣትነት ዕድሜ ላይ የምትገኝ ከመሆንዋ በቀር ሠርታ መብላት የማትችል ወይም በቀለብ ማግኘት ረገድ በችግር ላይ እንደምትገኝ አልተገለጸም፡፡ በዚህ ሁኔታም የቀረበ ክርክር የለም፡፡ አመልካች ካሣውን የጠየቀችው ባልዋ በመሞቱ ምክንያት ብቻ በቀጥታ የሚሰጣት እንደሆነ በማመን ነው፡፡ ይህ ግን በሕጉ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ከዚህ የተነሣም በአመልካች በኩል የተጠየቀው የቀለብ ክፍያ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚኖርበት ሠርታ መብላት ለማትችለው የሟች ልጅ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ለአመልካችም ጭምር ቀለብ አስልተው መወሰናቸው ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡ አወሳሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01375 ጥቅምት 15 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51086 ሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡ በዚህም ለአመልካች ይከፈል የተባለው ካሣ አይገባትም በማለት ይህን የውሣኔው ክፍል ሽረናል፡፡

2. አመልካች ከሟች ለተወለደች ሕፃን ትዕግሥት ሰዋገኝ ጥላሁን አካለመጠን እስከደረሰች /አስራ ስምንት ዓመት እስከሞላት/ ድረስ በየወሩ ብር 100 /አንድ መቶ ብር/ በቀለብ መልክ እንዲሰጥ ወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

በዚህ ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለሥር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 31099

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ኒሻን አለማየሁ፡፡ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት የቀረበው አመልካች የአፋር ክልል የዱብቲ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 2057/98 መስከረም 3 ቀን 1999 ዓ.ም እና የአፋር ክልል፣ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0580 ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስላላቸው በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈው የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ ከሕፃንነት ጀምራ አሥራ አራት ዓመት እስኪሆነው ድረስ ያሳደገችውን ሕፃን ወንድማገኝ ይልማ ግቢ ውስጥ ሲጫወት ኤሌክትሪክ ይዞት ስለሞተ፣ ሕፃኑ የእህቴ ልጅ እና ያሣደግሁት የቤተሰቡ አባል በመሆኑ በሕብረት ስምምነቱና በፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ካሣ ይከፈለኝ በማለት በአመልካች ላይ ክስ አቅርባለች፡፡ አመልካች ሕፃኑ ቤተሰብ በሚለው የሕብረት ስምምነት አይሸፈንም፡፡ ስለዚህ ካሣ መክፈል የለብንም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያየው የዱብቲ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ ባቀረበችው ክስ መሠረት ካሣ እንዲከፍል የወሰነ ሲሆን ይህንን ውሣኔ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ከሕብረት ስምምነቱ ድንጋጌና ከፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ውጪ ካሣ እንድከፍል መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሏ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክራለች፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም፡-

1. አመልካች ለተጠሪ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት እንዲከፍል ይገደዳል ወይስ አይገደድም
2. አመልካች ለተጠሪ በፍታብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት የሚከፍለው ካሣ ይኖራል ወይስ አይኖርም የሚሉትን ጭብጦች አይተናል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በድርጅቱ ቤት በሚኖሩ ሠራተኞች ላይ የኤሌክትሪክ አደጋ ቢደርስ ለንብረቱና በሠራተኛው ቤተሰብ ላይ ለሚደርስባቸው ጉዳት እና ሞት ድርጅቱ የካሣ ክፍያ የመክፈልና ሕክምና የማድረግ ግዴታ እንዳለበት የሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 29 ንኡስ አንቀጽ 13 ይደነግጋል፡፡ "ቤተሰብ" በሚለው ውስጥ የሚሸፈኑት በሌላ ሥራ ተሰማርቶ ገቢ የማያገኝ የሠራተኛው ሕጋዊ ሚስት ወይም ባል እንዲሁም እድሜቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆነና በራሳቸው የማይተዳደሩ ልጆችንና የጉዲፈቻ ልጅን ይጨምራል በማለት በሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 7 ተደንግጓል፡፡ ሟች የተጠሪዋ የእህቷ ልጅ እና እሷ ያሣደገችው ቢሆንም በሕግ የተቀመጠውን ሁኔታ አሟልታ በጉድፍቻ ውል መሠረት ያሳደረችው የጉድፈቻ ልጅ አይደለም፡፡ ሟች ተጠሪዋ የወለደችው ልጅ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ባለመሆኑ የሕብረት ስምምነቱ በሰጠው ትርጓሜ የቤተሰቡ አባል ነው ተብሎ የተሸፈነ አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት አመልካች ካሣ ሊከፍለኝ ይገባል በማለት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶችም የሕብረት ስምነቱን ድንጋጌዎች ይዘት በውል



ሣይመረምሩ አመልካች ለተጠሪው በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ካሣ ይክፈላት በማለት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ ስህተት አለበት፡፡

ሁለትኛውን ጭብጥ በተመለከተ ሕፃኑን ለሞት የዳረገውን ኤሌክትሪክ መስመር በአመልካች ኃላፊነት ሥር ያለ የአመልካች ንብረት ነው፡፡ ስለሆነም ለደረሰው ጉዳት አመልካች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2069 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም በሞት ምክንያት የሚከፈል የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ ሊሰጥ የሚችል ዳረጐት እንደሆነ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2095 ስለሚደነግግና ተጠሪ ከሟች ቀለብ ይሰፈርላት የነበረች ስላልሆነች አሁን ባለው የሕግ ማዕቀፍ ሟች በመሞቱ ምክንያት ለደረሰባት ጉዳት ካሣ የመጠየቅ መብት የፍታብሔር ህግ ቁጥር 2095 አይሰጣትም፡፡ ሆኖም ይህ ማለት ሟች በመሞቱ ተጠሪ የሕሊና ጉዳት አልደረሰባትም ማለት አይደለም፡፡ ተጠሪዋ ተንከባክባ ያሣደገችው ልጅ በአደጋው ምክንያት በመሞቱ የሕሊና ጉዳት ደርሶባታል፡፡ ለዚህ ለደረሰባት የሕሊና ጉዳት አመልካች ኃላፊ በመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2116 ድንጋጌዎች መሠረት አመልካች ለተጠሪ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ የሞራል ካሣ ሊፍል ይገባዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአፋር ክልል የዱብቲ ወረዳና የዞን አንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጧቸው ውሣኔዎች ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ብር 1000 /አንድ ሺ ብር/ የሞራል ካሣ ሊከፍላት ይገባል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ እና ኪሣራ ራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 32144

መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

አመልካች፡- ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አልሻ ሲራጅ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጉዳት ካሣ ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው ተጠሪ ስትሆን አመልካችን የከሰሰችው ንብረቱ የሆነ መኪና ባለቤትዋን ገጭቶ በመግደሉ ለእስዋ እና ለሁለት ልጆችዋ የጉዳት ካሣ እንዲከፍላት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለብኝም በማለት እና የሚከፍል ከሆነም በመጠኑ ረገድ ሊታዩ የሚገባቸው ነጥቦች እንዳሉ በመግለጽ ተከራክሮአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ክርክሩን ከመረመረ በኂላ፣ በሟች መሞት ምክንያት ተጠሪ እና ልጆቹ አጡት ያለውን ገቢ በማስላት በጠቅላላው ብር 61,275.90 ለቀብር ሥነ ሥርዓት ማስፈጸሚያ እና ለሃውልት ማሠሪያ ብር 2000 እንዲሁም የሞራል ካሣ ለእያንዳንዳቸው ብር 1000 አመልካች እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ሳይቀበለው ቀርቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተቋረጠ የተባለው ጥቅም የተሰላበትን መንገድ እና የሞራል ካሣውን አወሳሰን በተመለከተ የቀረበው አቤቱታ መመርመር ያለባት ሆኖ በመገኘታቸው ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ነጥቦች ከሥር ጀምሮ ከቀረበው ክርክር የስር ፍ/ቤቶች ከሰጡት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ ክሱን የመሠረተችው በባለቤትዋ መሞት የተነሣ ቀረብኝ ያለችውን ጥቅም በዝርዝር በማስላት ነው፡፡ የስሌቱ መነሻ የሟች ደመወዝ እንደሆነም ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም እንደዚሁ ተጠሪ በክስዋ ላይ የጠቀሰችውን የሟች ደመወዝ /ብር 895/ እንዳለ በመውሰድ ነው ስሌቱን የሠራው፡፡ በሰበር ችሎቱ ሊመረመር የሚገባ ሆኖ የተገኘው ይኸው ነው፡፡ የሟች ደመወዝ ብር 895 አይደለም የሚል ክርክር በአመልካች አልቀረበም፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረበው ክርክር ከጠቅላላ /gross/ ደመወዝ ላይ የሚቀናነሱ ሕግ የሚያውቃቸው ተቀናሾች ሳይቀነሱ የጉዳት ካሣው መሰላቱ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡ በበኩላችንም እንደምንገነዘበው ብር 895 /ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ብር/ የሟች ጠቅላላ /gross/ ደመወዝ እንጂ የተጣራ የወር ገቢው አይደለም፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው ከሠራተኛ ደመወዝ ላይ የሚቀናነሱ በሕግ የታወቁ ተቀናሾች አሉ፡፡ በመሆኑም ሠራተኛው በየወሩ የሚያገኘው ማለትም በእጁ የሚደርሰው ገቢው ከጠቅላላ ደመወዙ ያነሰ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ቀረ የተባለውን ጥቅም ያሰሉት ይህን ነገር ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ነው፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ ስህተት ተፈጽሞአል ለማለት ችለናል፡፡

ቀጥለን የተመለከትነው የሕሊና ጉዳት ካሣን በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ለተጠሪና ሞግዚት ለሆነችላቸው ልጆች በህሊና ጉዳት ካሣ ስም እንዲከፈል የተወሰነው ብር 3000 ነው፡፡ ይህ ሊሆን የቻለውም በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2116 የተመለከተው ብር 1000 በአመልካች እና ሞግዚት በሆነችላቸው ሁለት ልጆች በየስማቸው ተይዞ እንደሚከፈል ተደርጎ ግንዛቤ በመወሰዱ ነው፡፡ በእርግጥ በሕጉ በግልጽ ከተመለከተ የህሊና ጉዳት ካሣ እንደሚከፈል በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2105 ከተቀመጠው ድንጋጌ መገንዘብ

ይቻላል፡፡ መጠኑን በሚመለከትም በማናቸውም ምክንያት ከአንድ ሺህ ብር ሊበልጥ እንደማይችል በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2116 በግልጽ ተደንግጎአል፡፡ ሕጉ የጉዳት ካሣውን በዚህ ሁኔታ ከገደበው ደግሞ ከዚህ በተቃራኒ መወሰን የሚቻል አይሆንም፡፡ በመሆኑም ይህን በተመለከተ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ሲጠቃለል የጉዳት ካሣ አሰላልን እና የህሊና ጉዳት ካሣ አወሳሰንን በሚመለከት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05585 ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 5689 ሐምሌ 9 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. በሟች ሞት ምክንያት ቀረ የተባለው ጥቅም ከጠቅላላው የሟች ደመወዝ ላይ የሚቀነሱት በሕግ የታወቁት ተቀናሾች ተቀንሰው በሚገኘው የተጣራው ገቢ መሠረት ይሰላ በማለት ወስነናል፡፡
3. የሕሊና ጉዳት ካሣው ብር 1000 /አንድ ሺህ ብር/ ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መዝገብ ቁጥር 32250

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ሒሩት መለሠ
መድህን ኪሮስ
ፀጋዬ አስማማው

አመልካች፡- ወ/ሮ አስናቀች ወ/ማርያም ጠበቃው ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- 1. አቶ ከተማ ተሠማ
2. አቶ ሸዋንግዛው ከተማ } ጠበቃቸው ቀርቧል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በተጎጂው ላይ በደረሰ የሞት አደጋ ምክንያት የሚከፈልን የካሣ አከፋፈል ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች የአሁኑን ተጠሪዎች ጨምሮ 3 ተከሣሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ልጃቸው ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ኃለፊዎች ስለሆኑ ካሣ ብር 90,600 (ዘጠና ሺህ ስድስት መቶ) እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሾቹም በኃላፊነቱም ሆነ በካሣው መጠን ላይ ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በአመልካች ልጅ ላይ ለደረሰው የሞት አደጋ 1ኛ ተጠሪ የመኪናው ባለቤት በመሆናቸው፣ 2ኛ ተጠሪ መኪናውን በማሽከርከር አደጋውን ያደረሡ በመሆኑ ኃላፊዎች ናቸው ካለ በኂላ የካሣውን መጠን በተመለከተ ሟች ለአመልካች በየወሩ ብር 300.00 (ሦስት መቶ) ይሰጥ ስለነበር አመልካች 85 ዓመት እስኪሞላቸው ላለው 18 ዓመት ታስቦ እንዲሁም ለቀብር ማስፈፀሚያና ለተለያዩ ወጪዎች ብር 7,077.50 (ሠባት ሺህ ሠባ ሰባት ብር ከሃምሣ ሣንቲም) በድምሩ ብር 71,877 (ሠባ አንድ ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሰባት ብር) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በውሣኔው ቅር በመሠኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በኃላፊነቱ እና በካሣው መጠን ላይ የተሰጠውን

ውሣኔ ያፀና ሲሆን የአከፋፈሉን ሥርዓት በተመለከተ ግን በመተዳደሪያ ረገድ የተቋረጠ ጥቅም መከፈል ያለበት በአንድ ጊዜ ሣይሆን እንደነገሩ ሁኔታ በየጊዜው በመሆኑ ለቀብር የወጣውን ወጭ ብር 2000 እና ውሣኔ እስኪሰጥ ያለው ውዝፍ ቀለብ ብር 4,090 ተጠሪዎች በአንድነት እንዲከፍሉና ቀሪውን የጉዳት ካሣ የየዓመቱን መ/ሰጪ በሚኖሩበት አካባቢ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም ውስጥ እንዲያስቀምጡና መልስ ሰጪ በየወሩ ብር 300 (ሦስት መቶ) በሕይወት እስካሉና 85 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ እንዲቀበሉ ሟች 85 ዓመት ሣይሞላቸው ከሞቱ ባንክ የተቀመጠው ገንዘብ ለይግባኝ ባዮች እንዲመለስ በማለት አሻሽሎ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሠኝተው ይግባኙን ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ይግባኙን በመሠረዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪዎች የየአመቱን በባንክ ወይም በሌላ ገንዘብ ተቋም እንዲቀመጥ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማለቱ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፤ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ለአመልካች ልጅ መሞት ተጠሪዎች ኃላፊ መሆናቸውና የመ/ደረጃ ፍ/ቤት የወሰነው የካሣ መጠን በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የፀና በመሆኑ በዚህ መዝገብ የሚታየው የካሣው አከፋፈል ሥርዓት ብቻ ይሆናል፡፡

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ህ/ቁ. 2095/2/ መሠረት በመተዳደሪያ ረገድ የተቋረጠ ጥቅም መከፈል ያለበት አንድ ጊዜ ሣይሆን እንደነገሩ ሁኔታ በየጊዜው መሆን እንዳለበት እና አመልካች በህይወት እስካሉና 85 እስኪሞላቸው ገንዘቡ በባንክ ወይም በሌላ ገንዘብ ተቋም ተቀምጦ አመልካች በየወሩ ብር 300 እያወጡ እንዲወስዱ የሰጠው ውሣኔ ይህ ችሎትም የሚስማማበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች በባንክ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም ማስቀመጥ ያለባቸው የየአመቱን የካሣ ክፍያ ብቻ እንዲሆን መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አመልካች በሕይወት እስካሉ እና 85 ዓመት እስኪሞላቸው ካሣው በየወሩ ሊከፈላቸው እንደሚገባ ተወስኗል፡፡ በመሆኑም 85 ዓመት እስኪሞላቸውና በሕይወት እስካሉ ካሣውን በየወሩ ሊያገኙ የሚችሉበት የአከፋፈል ሥርዓት አብሮ ሊወሰን ይገባል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዳለው ተጠሪዎች የየአመቱን ካሣ ብቻ እንዲያስቀምጡ የተሰጠው ውሣኔ ግን ምናልባት ተጠሪዎች ከአመልካችዋ በፊት ቢሞቱ አመልካች ካሣውን የሚያገኙበት ሁኔታ ሊቋረጥ የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩን ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካችዋ በሕይወት እስካሉና 85 ዓመት እስኪሞላቸው በየወሩ ካሣውን ማግኘታቸው አስተማማኝ የሚሆነው ተጠሪዎች የተወሰነውን ካሣ አጠቃለው በባንክ ወይም በሌላ ገንዘብ ተቋም ሲያስቀምጡ ነው፡፡ ምናልባት አመልካችዋ ቀድመው ቢሞቱ ተጠሪዎች ገንዘቡን መልሰው መውሰድ የሚችሉበት ሁኔታ የተጠበቀ ሲሆን ተጠሪዎችም ከአመልካችዋ በፊት ቢሞቱ አመልካች ካሣው ሣይቋረጥባቸው ማግኘት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የየዓመቱን የካሣ መጠን ብቻ እንዲያስቀምጡ መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39178 በሰኔ 14 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪዎች የተወሰነባቸውን ካሣ በሙሉ አመልካች በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኝ ባንክ ወይም ገንዘብ ተቋም ያስቀምጡ፡፡ አመልካች በህይወት እስካሉና 85 ዓመት እስኪሞላቸው በየወሩ 300 (ሦስት መቶ) ብር በየወሩ እያወጡ ይውሰዱ፡፡ አመልካች ከ85 ዓመታቸው በፊት ከሞቱ ተጠሪዎች ገንዘቡን ከባንክ አውጥተው ይውሰዱ፡፡ ገንዘቡ የሚቀመጥበት ባንክ በዚህ ውሣኔ መሠረት ማስፈፀም እንዲችል የውሣኔው ግልባጭ ይተላለፍለት፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ገራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 33975

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን - አልቀረቡም፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** ወ/ሮ አበበች ስዩም - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የንብረት ጉዳት ካሣን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን መ/ሰጭ በባሌ ከተማ የሚገኘው ቤቴ ከሮቤ ወደ ሴሩ የሚሠራው መንገድ ስለወጣበት እንዲፈርስና ግምቱ ብር 17,912 /አስራ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ብር/ እንዲከፈለኝ ከተወሰነ በኂላ የአሁን አመልካች ነገ ዛሬ እያለ ስላልከፈለ የቤቱ ግምትና የጠበቃ አበል ከነወጪና ኪሣራው ይክፈለኝ በማለት በአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች በሰጠው መልስ በመንገዱ ግንባታ ምክንያት መ/ሰጭ ቦታውን እንዲለቁ ግምት የተሠራላቸው ቢሆንም ባለንብረቷ በወቅቱ ከኢት/ንግድ ባንክ ጋራ ክርክር ስለነበራቸው ቤቱን ማንሳት ያልተቻለ ሲሆን ሌላ አማራጭ በመጠቀም ቤቱ ሳይነካ መንገዱ ተሰርቶ ተጠናቆ ርክክብ ተደርጓል፣ ስለሆነም ቤቱ በመንገድ ግንባታ ምክንያት ሳይነሳ አንድ ጊዜ ግምቱ ስለተሠራ ብቻ ይከፈለኝ በማለት መልስ ሰጪ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኂላ የባሌ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 01 ጽ/ቤት የክርክሩ መንስኤ የሆነው ቤት በመንገዱ ግንባታ ምክንያት መነሳት አለመነሳቱን ለፍ/ቤቱ እንዲገልጽ ያዘዘ ሲሆን የቀበሌው ጽ/ቤት አከራካሪው ቤት በመንገድ ስፋት ምክንያት የተነካ ስለሆነ በወቅቱ ግምት የተሠራለት ቢሆንም እስካሁን ድረስ አልተነሳም፣ ነገር ግን ቤቱ በፍሳሽ ቦይ ውስጥ የሚውል ስለሆነ መፍረሱ አይቀርም የሚል ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ፍ/ቤቱ በመቀጠል አመልካች ባለንብረቷ የተበደሩትን ገንዘብ ከፍለው ያጠናቀቁና ባንኩ የሚፈልግባቸው ዕዳ የሌለ መሆኑን ባንኩ ለባሌ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ መ/ሰጭ በወቅቱ ከዕዳ ነፃ መሆናቸውና ከባንክ ጋር ክርክር ያልነበራቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቤቱ እስካሁን ያልፈረሰ ቢሆንም ወደፊት መፍረሱ እንደማይቀር ስለተረጋገጠ ቤቱ አልተነካም የሚለው የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም፤ ስለዚህ አመልካች የንብረቱን ግምት፣ የጠበቃ አበል እንዲሁም ወጪና ኪሣራ ለመ/ሰጪ ይክፈል ሲል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ አቤቱታው በአጭሩ መ/ሰጭ ቤቱ ለወደፊት በጎርፍ ይጎዳል የሚል ክርክር ባላቀረቡበትና ጉዳቱ የቤቱን መነሳት የሚያስከትል መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ እንዲሁም በመንገድ ዳር የማያልፍ ውሃ /ጎርፍ/ ንብረት ሳይነካ በቅያሱ ሊስተናገድ እንደሚችል ግምት ሳይወሰድ ላልተነሳና እንዲነሳ ላልተፈለገ ቤት ግምት ይከፈል ተብሎ በሥር ፍ/ቤት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የመ/ሰጭ ቤት አልፈረሰም እየተባለ አመልካች የንብረት ካሣ ይክፈል ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑ ተጣርቶ መወሰን ያለበት ነጥብ ሆኖ ስላገኘው ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው መ/ሰጭ የቤቴ ግምት ተከፍሎኝ ቤቱ እንዲነሳ ከተወሰነ በኂላ አመልካች ግምቱን አልከፈለኝም የሚል ክስ በሥር አቅርበው አመልካች ደግሞ የመ/ሰጭ ቤት ሳይነካ መንገዱ ተሠርቷል፤ ርክክቡም ተደርጓል የሚል መልስ ሰጥቶ፣ ፍ/ቤቱ የቤቱን መነሳትና አለመነሳት ሲያጣራ ቤቱ አለመነሳቱን ወደፊት ግን በቦይ ምክንያት መነሳቱ እንደማይቀር

ከከተማው አስተዳደር በተገለፀለት መሠረት ቤቱ አልተነካም የሚለውን የአመልካችን መከራከሪያ ውድቅ በማድረግ ግምቱ እንዲከፈል መወሰኑንና ይኸው ውሣኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መጽናቱን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ ጉዳይ መ/ሰጭ ካሣ እንዲከፈላቸውና ቤቱ እንዲነሳ ተወስኖ እንደነበር ከመግለጽ በስተቀር በመንገዱ ግንባታ ምክንያት ቤታቸው የተነሳ /የፈረሰ/ መሆኑን አላስረዱም፡፡ ከዚህም በላይ የከተማው አስተዳደር ቀበሌ 01 ጽ/ቤት ቤቱ ያልፈረሰ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ቤቱ እንዲነሳ ተወስኖ በነበረው መሠረት መነሳቱ ካልተረጋገጠ ደግሞ በመንገድ ግንባታ ምክንያት በመ/ሰጭ ላይ ጉዳት ደርሷል ማለት አይቻልም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2091 የጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሰው የሚከፍለው ካሣ መጠን ኃላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ካደረሰው ጉዳት ጋር እኩልና ተመዛዛኝ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሠረት በሕጉ ከተደነገገው የጉዳትና የካሣ ተመዛዛኝነት አንፃር በመ/ሰጭ ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩ ስላልተረጋገጠ ለመ/ሰጭ ሊከፈል የሚገባ ካሣ አይኖርም፡፡

ከዚህም ባሻገር የመሬት ይዞታ ለሕዝብ ጥቅም የሚለቀቅበትንና ለንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁ. 455/97 አንቀጽ 7/1/ መሠረት ካሣ የሚከፈለው የመሬት ይዞታውን እንዲለቅ ለተደረገ ባለይዞታ ነው፡፡ መ/ሰጭ ግን ይዞታቸውን እንዲለቁ ታስቦ ካሣ ሊከፈላቸው የቤቱ ግምት እንደተሠራ ከመግለጽ በስተቀር ይዞታቸውን መልቀቃቸውን በማስመልከት አልተከራከሩም፡፡ ማስረጃም አላቀረቡም፡፡ ስለሆነም መ/ሰጭ ይዞታቸውን እንዲለቁ ሳይደረጉ ይዞታውን እንዲለቅ ለተደረገ ባለይዞታ ሊከፈል የሚገባው ካሣ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም የደረሰ ጉዳት መኖሩ ሳይረጋገጥ አመልካች ለመ/ሰጭ ግምት ይክፈል ተብሎ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 08763 የካቲት 8 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 51879 ጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. መ/ሰጭ ላይ የደረሰባቸው ጉዳት ስለሌለ በስር ፍ/ቤት አመልካች ለመ/ሰጭ ይክፈል ተብሎ የተወሰነው የቤቱ ግምት ለመ/ሰጭ ሊከፈል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 34138

ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

አመልካቾች፡- 1. ሲስተር ገነት ጌታቸው ወኪል ጌታቸው ይማም ቀረበ

2. ሕፃን ናሆም አበበ

ተጠሪ፡- ወንድወሰን ኃይሉ ወልደማርያም - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በመኪና አደጋ ምክንያት የደረሰን የአካል ጉዳት መሠረት በማድረግ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር አመልካቾች ከሣሾች የነበሩ ሲሆን፣ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረቱት ንብረቱ በሆነው መኪና በደረሰባቸው ጉዳት መጠን ኪሣራ እንዲከፍላቸው ነው፡፡ ከመዝገቡ ማየት እንደቻልነው አመልካቾች የተጠሪ ንብረት በሆነው መኪና ስለመጎዳታቸው አላከራከረም፡፡ ክሱን ያስተናገደው በአፋር ብ/ክ/መ/ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ለደረሰው ጉዳት ተጠሪ ኃላፊ ነው በማለት ለ1ኛ አመልካች ብር 20,000 እንዲከፈላት ሲወስን፤ የሁለተኛ አመልካች የጉዳት መጠን ግን ገና አልታወቀም የሚል ምክንያት በመስጠት የጉዳት ኪሣራ እንዲከፈል አልወሰነም፡፡ ሕፃኑ (2ኛ አመልካች) ሕክምና ላይ ነው ያለው በማለት ተጠሪ ኃላፊነት ወስዶ ለሕክምናና ለተለያዩ ወጪዎች ይክፈል የሚል ተጨማሪ ውሣኔ መስጠቱንም ተመልክተናል፡፡ በዚህ መልክ የተሰጠው ውሣኔ በክልሉ ጠ/ፍ/ቤም ጉድለት የለበትም ስለተባለ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡



ይህ የሰበር ችሎትም አመልካቾች ህዳር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተደረገው 1ኛ አመልካች በጉዳቱ ምክንያት ሣይከፈላት የቀረውን ደመወዝ በሚመለከት በዝምታ የመታለፉን እና ለ2ኛ አመልካች የጉዳት ካሣ ያለመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም እነዚህን ነጥቦች ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ተጠሪ በሁለቱም አመልካቾች ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ስለመሆኑ እስካላከራከረ ድረስ አግባብ ያለው የጉዳት ካሣ እንዲከፈል መወሰኑ የግድ ነው፡፡ በዚህ መዝገብ የተነሣው የካሣ ጥያቄ መሠረት ያደረገው ከውል ውጪ የደረሰን ኃላፊነት በመሆኑ መታየት ያለበት በፍትሐብሔር ሕጉ በአንቀጽ 13፤ በተለይም በዚሁ አንቀጽ በምዕራፍ 1 በክፍል 3 ስር ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2090(1) እና 2091 እንደተመለከተው በጉዳቱ ምክንያት ተበዳዩ የሚካሰው ለጉዳቱ ተመዛዛኝ በሆነው መጠን ነው፡፡ የጉዳት ካሣው ሲወሰን ደርሶ የተገኘውን (የታየውን) ኪሣራ በማየት ብቻ ሣይሆን፣ ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተውንም እግንዛቤ ውስጥ በማግባት ጭምር ሊሆን እንደሚገባ ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2092 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የብዙ አገራት ከውል ውጭ የሚደርስ ኃላፊነት ሕጎች ሁለት ግቦችን ማለትም ጉዳቱን የመካስ (insurance goal) እና የጥፋት ባህሪን የመግራት (deterrence goal) ተብለው የሚታወቁትን መሠረት በማድረግ የተቀረፁ ሲሆን፣ የአገራችን ሕግም እንደዚሁ ተመሣሣይ ዓላማ አካቶ እንደተቀረፀ በሕጉ ላይ ማብራሪያ የፃፉት ፕሮፌሰር ጆርጅ ቺቺ ኖቪች /The Ethiopian law of Compensation for Damage/ በሚለው የማብራሪያ መጽሐፋቸው ገልፀውታል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2091 እና 2092 በተቀመጡት መርሆዎች መሠረት ካሣና ጉዳት እኩል መሆን እንዳለበት ይህም በመርህ ደረጃ ተጎጂው ከጉዳቱ አትራፊ መሆን እንደማይገባውና ከደረሰበት ጉዳት

በታች መካስ እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተግባርና በተጨባጭ ሲታይ የጉዳት መጠኑ በፍ/ቤት የሚወሰን ቢሆንም፤ ጉዳዩ የሕግ ጥያቄ ብቻ ባለመሆኑ ወስብስብነት ያለው ከመሆኑም በላይ ሕጉ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት ብቻ ሣይሆን ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳትም የተረጋገጠ ሲሆን እንዲካስ ስለሚፈቅድ ወደፊት ስለሚሆን ነገር እርግጠኛ መሆን ስለማይቻል በካሣ አወሳሰን ረገድ ስሌትን የማዛነፍ ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በካሣ አወሳሰን ረገድ ከንብረት ጉዳት ይልቅ አተማመኑ የበለጠ ውስብስብ  የሚሆነው ጉዳቱ በሰው አካል ላይ የደረሰ ሲሆን ነው፡፡ በእርግጥ በጉዳቱ ምክንያት የተከፈለ ወጪ፣ ወይም በግልጽ የሚታይ የቀረ ጥቅም ወይም ገቢ ለመድኃኒት መግዣ፣ እንደዚሁም ለሰው ሠራሽ የአካል ምትክና ተጎጂው ወደ ሆስፒታል የተመላለሰበት ወጪ የጉዳት ካሣው አካል ስለሆነና በቀላሉም በማስረጃ የሚረጋገጥ በመሆኑ በአወሳሰን ረገድ አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ጉዳቱ የዘላቂነት ባህርይ ሲኖረውና የተጎጂው የመሥራት አቅም በሙሉ ወይም በከፊል ሲጓደል በጉዳት ካሣው አተማመን ረገድ አስቸጋሪ ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም፡፡ ስለዚህም ካሣው ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዘን አለበት ሲባል መታየት የሚገባው በአጠቃላይ በተጎጂው ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት እንደሰው በአጠቃላይ የመሥራት ኃይል ቅነሣ (General utility) አንፃር እንጂ ከጉዳቱ በፊት ሲሠራው የነበረውን ሥራ ላለመሥራት ጉዳቱ ያስከተለው ልዩ ጫናና የቅነሣ መጠን /special utility/  ግምት ውስጥ በማስገባት አይሆንም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በተጨባጩ ዓለም ሲታይ እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ሥራ ለመሥራት ብቻ ሣይሆን፣ በአጠቃላይ እንደሰው ለመኖር የተለያየ ፋይዳና ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ በሁለቱም አመልካቾች ላይ ዘላቂ የሆነ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ በ1ኛ አመልካች ላይ የደረሰው በቀኝ እግርዋ ላይ ከባድ የስብራት ጉዳት ሲሆን፣ ይህም 18% (አሥራ ስምንት በመቶ) እንደሆነ በሐኪሞች ተረጋግጦአል፡፡ 2ኛ አመልካችም የደረሰበት ጉዳት በመቶኛ ተሰልቶ



ያልቀረበ (ገና በሕክምና ላይ በመሆኑ) ቢሆንም፤ ጉዳቱ በግልጽ የሚታይ እና ከፍተኛ እንደሆነ ሐኪሞች በሰጡት ማረጋገጫ ላይ ተመልክቶአል፡፡

ይኸውም በግራ ሰውነቱ የተወሰነው፣ በቀኝ የራስ ቅሉ የስብራት እና ጭንቅላቱ ውስጥ የመድማት ጉዳት እንደደረሰበት ከዚህ የተነሣም ለረዥም ጊዜ ራሱን ስቶ እንደቆየና አሁንም በሕክምና ላይ እንደሆነ ተገልጾአል፡፡ በመሆኑም በሁለቱም አመልካቾች ላይ ዘላቂ የሆነ ከፊል ስንኩልነት /permanent partial disablement/ ተብሎ ሊመደብ የሚችል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት 1ኛ አመልካች በርትዕ ብር 20,000 እንድትካስ የወሰኑ ቢሆንም፤ ለ2ኛ አመልካች ግን በተመሣሣይ ሁኔታ ካሣ አልወሰኑም፡፡ በበኩላችን እንደምንገነዘበው 2ኛ አመልካችም የአካል ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ርትዕን መሠረት በማድረግ ካሣ ሊከፈለው ይገባል፡፡ ሌላም መወሰን ሲገባው በዝምታ የታለፈው 1ኛ አመልካች በጉዳቱ ምክንያት በደመወዝ ረገድ ቀረብኝ ያለችው ገቢ ሲሆን፣ ይህም ጉዳቱ በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል በመሆኑ ውሣኔ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህም ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥናቸውን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በአፋር ብ/ክ/መ/የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 0574 ሐምሌ 4 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 992 ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. 1ኛ አመልካች በጉዳቱ ምክንያት በደመወዝ ረገድ ቀረብኝ የምትለው ገቢ ግራ ቀኝ ወገኖች ከሚያቀርቡት ማስረጃ አንፃር ታይቶ ይወሰን ብለናል፡፡
3. 2ኛ አመልካችም እንደ1ኛ አመልካች ዘላቂነት ያለው የአካል ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ዞኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ግምት ውስጥ

በማግባት እና ርትዕን መሠረት በማድረግ ተገቢ ነው የሚለውን የጉዳት ካሣ ይወስንለት ብለን ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

4. ተጠሪ ኃላፊነቱን ወስዶ ለ2ኛ አመልካች ሕክምና ተያያዥ ወጪ ይክፈል በሚል በከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በበኩላችንም ተቀብለነዋል፡፡ አልተነካም፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የደረሰውን ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰበር መ/ቁ. 34906

ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

መድኅን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት

ቤተልሄም ሲሣይ ቀረበች

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቂ ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሐሰት ውንጀላዎችን የያዘ ደብዳቤ በመፃፉ ስሜ ጠፍቶአልና የሕሊና (የሞራል) ጉዳት ካሣ ይከፈለኝ በማለት ተጠሪ በመሠረተችው ክሥ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ክስ የመሠረተችው ታዬ ለማ በተባለ የድሬዳዋ ሪጂን ቴሌኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ ላይ ሲሆን፣ ይህ ሰው ለክሱ በሰጠው መልስ ደብዳቤውን የፃፈው ከተጠሪ ጋር ባለው የግል ግንኙነት ሣይሆን፣ ከኮርፖሬሽኑ ሥራ ጋር በተያያዘ ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ አመልካች በክርክሩ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባለት ጠይቋል፡፡ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነው በዚህ መሠረት ሲሆን አመልካች ለቀረበው ክስ የበኩሉን የመከላከያ ክርክር አቅርቧል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤት የሁሉንም ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኃላ፣ ተከሣሹን ከክሱ በማውጣት አመልካችን ኃላፊ አድርጎአል፡፡ በመቀጠልም አመልካች ብር 3000 ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን ያጸና ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 2 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪን በሚመለከት ለኮርፖሬሽኑ በአንድ የሥራ ኃላፊ በቀጥታ የተፃፈው ሪፖርት የስም ማጥፋት ነው በሚል አመልካች ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ስሜን የሚያጠፋ ውንጀላ አለበት የምትለውን ደብዳቤ የፃፈው ሰው የሷ የበላይ ዐለቃ ወይም ኃላፊ ነው፡፡ ደብዳቤው የተፃፈው ደግሞ ለቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ዋና መሥሪያ ቤት ነው፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ የምናየው በቴሌኮሙኒክሽን ኮርፖሬሽን አደረጃጀት መሠረት የሪጂን ሥራ አሥኪያጅ በስሩ ሆና የምትሠራን ሠራተኛ (ተጠሪን) በሚመለከት የበላዩ ለሆነው ለዋናው መሥሪያ ቤት ደብዳቤ በቀጥታ መፃፉን ነው፡፡ አመልካች እና ደብዳቤውን የፃፈው ሰው በፍሬ ነገር ረገድ ያቀረቡት ክርክርም እንደተመለከትነው የበታች የሥራ ኃላፊ በሥሩ የሚያስተዳድራቸውን ሠራተኞች በሚመለከት ሪፖርት በዝርዝር በማቅረቡ የሠራተኞቹን ስም አጥፍቶአል ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ በደብዳቤዎቹ ላይ የሐሰት ውንጀላዎችን የሚያመለክቱ አገላለጾች አሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ የኔን ስም ለማጥፋት ተብሎ የገቡ ናቸው በማለት ተከራክራለች፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ደብዳቤው የተጠሪን ስም የሚያጠፋ በእውነት ላይ ያልተመሠረተ አገላለጽን የያዘ ነው በማለት ነው አመልካች ካሣ እንዲከፍል የወሰኑት፡፡ ከላይ እንተደገለፀው ለደብዳቤው መፃፍ ዋና ምክንያት ሆኖ የሚታየው የሪጂኑ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ በሥራዋ የምታሣየውን ትክክል ያልሆነ ጠባይ እና ተገቢ አይደሉም የተባሉትን ድርጊቶችዋን በሚመለከት ለበላይ ኃላፊ ለማሣወቅ (ሪፖርት ለማድረግ) በመፈለጉ ነው፡፡ በእርግጥ በደብዳቤው ውስጥ ከተጠሪ



እይታ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት የለውም ሊባል የሚችል አገላለጽ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ አይነቱ አፃፃፍ ተጠሪን ቅር የሚያሰኝ ቢሆን ደግሞ በዚያው በኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ታይቶ እልባት የሚሰጠው ነው የሚሆነው ፡፡ የሪጅኑ ሥራ አስኪያጅ ደብዳቤውን በቀጥታ የፃፈው ለበላይ መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች እንጂ ከዚህ ውጪ ላሉት ማለትም ጉዳዩ ለማይመለከታቸው ወገኖች አይደለም፡፡ ይህ በራሱ የሚያሣየው ደግሞ የደብዳቤው ዓላማ ሪፖርት ከማቅረብ ውጪ መታየት የማይችል እንደሆነ ነው፡፡ በሪፖርቱ የተገለፀው ነገር እውነት ነው አይደለም የሚለው ደግሞ የሚወስነው ሪፖርቱ በቀረበለት የበላይ ኃላፊ ነው በመሆኑም በሥራ አስኪያጁ በተፃፈው ደብዳቤ ኃላፊነትን የሚያስከትል (የፍትሐብሔር) የስም ማጥፋት ድርጊት ተፈጽሞአል የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 8329 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 03295 ኅዳር 23 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ካሣ የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

# የቤተሰብ ህግ



የሰ/መ/ቁ. 21740

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ተገኔ ጌታነህ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አስረስ መስፍን ቀረቡ፡፡

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ ቀረቡ፡፡

መዝቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በአማ/ብሔ/ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 04313 መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ የአሁን አመልካች ቅር በመሰኘታቸው ነው፡፡

የአሁን አመልካች ክርክሩ በተነሣበት የወረዳ ፍ/ቤት ከሳሽ ሲሆኑ ያቀረቡት አቤቱታም ባለቤቴ መ/አለቃ መኮንን ለማ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ስለሆነ ሚስትነቴ እና የልጆቼ ወራሽነት ይረጋገጥልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም በዚሁ የወረዳ ፍ/ቤት በተቃዋሚነት ቀርባ ተከራክራለች፡፡ ያነሳችውም የመከራከሪያ ነጥብ አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን ሚስት አይደለችም፡፡ ሚስት እኔ ነኝ የሚለው ነው፡፡

የወረዳው ፍ/ቤትም የአመልካችን አቤቱታ ካቀረበችው የሰው ማስረጃ፣ የፅድር ሰነድ እና የማኀበራዊ ፍ/ቤት ውሣኔ ጋር እገናዝቦ ከመረመረ በኋላ የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሟች ሚስት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል የአሁን መልስ ሰጭ የሟች ሚስት መሆናቸውን በሥ/ፋ/መ/ቁ. 155/95 ያስወሰኑ ቢሆንም በፍ/መ/ቁ. 148/86 ባደረጉት ክርክር ጋብቻው የፈረስ መሆኑን ስለሚረጋገጥ የካቲት 01 ቀን 1993 ዓ.ም. ስለሚስትነት ማስረጃው

የሚገልፀው ውሣኔ በፍ/መ/ቁ 148/86 የካቲት 05 ቀን 1993 ዓ.ም. ጋብቻው ፈርሷል በሚል የተሰጠው ውሣኔ ይሽረዋል፡፡ ስለሆነም የአመልካችን ሚስትነት ተቀብዬ አጽድቄያለሁ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን መልስ ሰጭ የይግባኝ አቤቱታ ለከፍተኛው ፍ/ቤት በማቅረቧ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይግባኝ ባይ (የአሁን መልስ ሰጭ) የምትከራከረው የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን ሚስት አይደለችም በሚል በመሆኑና የእርሷንም ሚስትነት አስቀድማ ያረጋገጠች በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ መካከል አከራካሪ ነጥብ ሆኖ መወሰድ ያለበት የአሁን አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሟች ሚስት ናት ወይስ አይደለችም የሚለው ነው፡፡ ይህንንም በሚመለከት ሚስትነትን በሁኔታ ስለማረጋገጥ የሚደነግገው ሕግ በሚጠየቀው አኳኋን አላስረዳችም፡፡ ስለሆነም መልስ ሰጭ ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሟች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት አይደለችም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታ መነሻ ግራ ቀኙ በክልል ጠ/ፍ/ቤት ተከራክረዋል፡፡ ይህ ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ መስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በተመሳሳይ መንገድ የይግባኝ ባይን (የአሁን አመልካችን) ሚስትነት ውድቅ ካደረገ በኋላ የወ/ሮ ውብነሽ ታከለን ሚስትነት ጉዳይ በሚመለከት ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ ከሟች መ/አለቃ መኮንን ለማ ጋር ባደረጉት ክርክር የጋብቻውን መፍረስ እና አለመፍረስ አስመልክቶ እንደገና በጉባኤ ታይቶ እንዲወሰን ተመርቶ እያለ በመካከል ሟች መ/አለቃ መኮንን ለማ ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ሟች በሞቱበት ጊዜ ወ/ሮ ውብነሽ ሚስት አልነበሩም ማለት አያስችልም፡፡ ስለሆነም የሟች ሚስት ናቸው የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር በይዘቱ



ከወረዳ ፍ/ቤት ጀምሮ ካደረጉት ክርክር የተለየ ባለመሆኑ በድጋሚ ማስፈሩ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን መልስ ሰጭ በተቃዋሚነት በጉዳዩ ቀርባ የተከራከረችው የአሁን አመልካች የሟች ሚስት አይደሉም የሚሉበትን ክርክር በማቅረብ ነው፡፡ መልስ ሰጭ ይህንኑ ክርክር ለማቅረብ የሚያስችላቸውን የእራሳቸው የሚስትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም በዚህ በግራ ቀኙ መካከል በተነሳው ክርክር ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ነጥብ የአሁን አመልካች የሟች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ሊሆኑ የማይችልበትን የፍሬ ነገር እና የሕግ ክርክር በአሁን መልስ ሰጭ በኩል ቀርቧል ወይስ አልቀረበም? በተቃዋሚ በኩል ይህን መሰል ክርክር ካልቀረበስ የአሁን አመልካች የሟች ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበዋል ወይስ አላቀረቡም? የሚለው ነው፡፡ ከዚህ ነጥብ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከት መልስ ሰጭ ሚስት እኔ ነኝ በሚለው ላይ አትኩረው የተከራከሩ ከመሆኑ በቀር የአሁን አመልካች ሚስት ሊሆኑ ያልቻሉበትን ክርክርና ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ምንም እንኳ የእርሷ ሚስትነት ከክርክሩ አካሄድ አኳያ ጥያቄ ውስጥ የገባ ባይሆንም የአሁን አመልካች የሟች የመ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት መሆኔ ተረጋግጦ ማስረጃ ይሰጠኝ የሚለውን አቤቱታ በዚያው ደረጃ ሊያቋርጥ የሚችል ክርክርና ማስረጃ ግን አላቀረበችም፡፡ ሰለሆነም የአሁን አመልካች የሟች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ለመሆኗ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርባለች? በሚለው ነጥብ ላይ ጉዳዩ የተወሰነ ነው፡፡ ይህንንም በሚመለከት በከፍተኛው ፍ/ቤት የቀረቡት ምስክሮች ምንም እንኳ አመልካችና ሟች ባልና ሚስት ሆነው አብረው ሲኖሩ እናውቃለን በማለት ያረጋገጡ ቢሆንም ሲጋቡና የጋብቻው ሥርዓት ሲፈፀም ነበርን፤ እናውቃለን በማለት ያላስረዱ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ እንደሚደነግገው ሚስትነትን በጋብቻ ሁኔታ አስረድተዋል ማለት አይቻልም በማለት የሰጠው ድምዳሜ ይህንን ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በመተርጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 699/1/ የጋብቻ ጽሑፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ነው ሲል ከደነገገ በኋላ ሁለት ሰዎች የባልና ሚስትነት ሁኔታ አላቸው የሚባለው ባልና ሚስት ነን እየተባባሉ አብረው የሚኖሩ እንደሆነና ቤተዘመዶቻቸውና ሌሎችም ሰዎች በዚሁ ሁኔታ መኖራቸውን ሲያረጋግጡላቸው ነው በማለት ለይቶ አስቀምጧል፡፡ በመሠረቱ ይኸው ድንጋጌ ግልጽ ነው፡፡ ሕግ ግልጽ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ደግሞ የሕግ ትርጉም ሥራ እንደማያስፈልግ የሕግ አተረጓጎም ዘዴ ያስገነዝባል፡፡ በግልጽ በሕግ በተመለከተው አኳኋን አመልካች በማስረጃ ያረጋገጠች ለመሆኑ እራሱ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ትርጉም ሥራ እንዲገባ ምክንያት የሆነው በዚህ ድንጋጌ ቁጥር 699/2/ የተመለከተው በተለያዩ ሁኔታ ካልታየ በቀር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 708 ከተመለከተው ከጋብቻ ውጭ በግብረ ሥጋ ግንኙነት መኖር ከሚለው በምን ሊለይ ይችላል የሚለውን በመያዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ አለ የተባለው ግንኙነት የሚመለከት ሁኔታ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 708 የተጠቀሰውን የሚመለከት ነው የሚባል ከሆነ ይህንን የማሳየት እና የመከላከል ተግባር የሚለየው በተከራካሪ ወገን ተግባርና ግዴታ ነው፡፡ ለዚህም ነው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 700/2/ የባልና ሚስትነት ሁኔታ አለመኖሩንን ለመከራከር የሚቻለው የተከራካሪዎች ዘመዶች የሆኑ ወይም ያልሆኑ አራት የመከላከያ ምስክሮችን በማስመስከር ነው የሚለውን መደንገግ ያስፈለገው፡፡

ስለሆነም አመልካች /የአሁን/ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 699/2/ ለሚደነግገው ሁኔታ የሟች የመ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ለመሆኗ በበቂ ሁኔታ ማረጋገጧ እየታወቀ ከላይ እንደተገለፀው አግባብነት ያለውን ድንጋጌ በትክክል ካለመረዳት የተነሣ የሟች ሚስት መሆኗን አላረጋገጠችም በማለት ማስረጃው አግባብነት እንደሌለው ተደርጎ ሚስት አይደለችም ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡



<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አመልካች ወ/ሮ አስረስ መስፍን የሟች መ/አለቃ መኮንን ለማ ሚስት ናቸው፡፡ እንዲሁም ይኸው ፍርድ በውጤት ደረጃ መልስ ሰጭም የሟች ሚስት መሆናቸውን አረጋጋጭ ነው ብለናል፡፡
2. የአማ/ብ/ሕ/ክል መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 04313 በመስከረም 30 ቀን 1998 ዓ.ም እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት በቁጥር 01052 በሰኔ 30 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፤ ይፃፍ፤ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 23021

ሐምሌ 12 ቀን 1999

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብድራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህ - ጠበቃ አቻምየለህ ተፈሪ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የሟች አቶ አማረ ይልማ ሚስት ናቸው ተብሎ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ተሽሮ ሚስት አይደሉም ተብሎ በመወሰኑ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሆኑት ባቀረቡት አቤቱታ የሟች አቶ አማረ ይልማ ሚስትነቴ ይረጋገጥልኝ በማለት አመልክተው ፍ/ቤቱም የአመልካችን ምስክሮች ሰምቶ በሰኔ 24 ቀን 1995 ዓ.ም. በዋለው ችሎት አመልካች የሟች አቶ አማረ ይልማ ሚስት ናቸው በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን ከዚህ በኋላም የአሁን ተጠሪ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም በሞግዚት አድራጊያቸው በወጣት ወንድወሰን አማረ ስም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአቤቱታውም ይዘት በአመልካች ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህና በሟች አቶ አማረ ይልማ የነበረው ጋብቻ የቤተዘመድ ጉባኤ በሰጠው ውሣኔ እና ፍ/ቤቱም በሐምሌ 23 ቀን 1976 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መፍረሱ የተረጋገጠ ስለሆነና አመልካቿም ከዚህ ጊዜ በኋላ ከሟች ጋር በትዳር ያልኖሩ መሆናቸው ሟች ነዋሪ ከሆኑበት ቀበሌ ለባንክ በተፃፈ ደብዳቤ የተገለጸ በመሆኑ አመልካች ሚስት ሳይሆኑ ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ሞግዚት የሆንኩለትን የወጣት ወንድወሰን አማረን መብት የሚነካ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሣኔ ይሰረዝልኝ የሚል ነው፡፡

የተጠሪ መቃወሚያም ለአመልካች ደርሶ በሰጡት መልስ ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ፈርሶ እንደነበር ሳይክዱ ከፍቺው በኋላ ንብረት ሳይከፋፈሉ ትዳራቸውን ቀጥለው እንደነበር ከፍቺው በኋላ በደንቡ መሠረት ጋብቻ አልተፈጸመም ቢባል እንኳ ጋብቻ መኖሩን በሁኔታ ማስረዳት እንደሚቻል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የሚፈቅድ በመሆኑ ከፍቺ በኋላም እንደ ባልና ሚስት መኖራቸውን በምስክሮች ማስረዳት ስለሚቻል ከፍቺ በኋላ ጋብቻ አልተፈጸመም በማለት በተቃዋሚ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን እንዲያፀናው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በግራ ቀኙ በኩል የተቆጠሩትን ምስክሮችን ከሰማ በኋላ በአመልካችና በሟች መካከል የትዳር ሁኔታ ስለመኖሩ በአመልካች ምስክሮች እንዳልተረጋገጠ በውሣኔው ላይ አስፍሮ ይልቁንም በአመልካች ልጅ በአቶ ዮናስ አማረ ጥያቄ አመልካችና ሟች አቶ አማረ ይልማ በነዋሪነት ከተመዘገቡበት ቀበሌ በሶስት ምስክሮች ተረጋግጦ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተፃፈው ደብዳቤ ሟች ከአመልካች ጋር የነበራቸው ትዳር በፍቺ ከፈረሰ በኋላ እስከ እለተሞታቸው ትዳር እንዳልነበራቸው የሚያስገነዝብ ስለሆነ ጋብቻ ስለመፈጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖርን በማስረዳት ፍ/ቤቱ የሕግ ግምት ሊወስድ እንደሚችል በቤተሰብ ሕግ ቁጥር 97/1/ ላይ የተደነገገ ሲሆን ይህ ግምት በበቂ ማስረጃ ሊፈርስ እንደሚችል በዚሁ አንቀጽ 97/2/ ላይ ስለተመለከተና በአመልካችና በሟች መካከል የትዳር ሁኔታ ስለመኖሩ አስቀድሞ የተሰጠው ውሣኔ በበቂ ማስረጃ የተስተባበለ ስለሆነ ቀደም ሲል አመልካች የሟች ሚስት ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተሰርዟል በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይና /አመልካች/ ሟች አማረ ይልማ በ1966 ዓ.ም. ተጋብተው በ1976 ዓ.ም. ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ለአራት ወራት ተለያይተው ኖረው መልስ ሰጪ ታርቀው እንደነበርና ጋብቻው ፈርሶ ከነበረ በኋላም

የንብረት ክፍፍል ተደርጎ እንዳልነበረ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል
በማለት በውሣኔው ላይ አስፍሮ አመልካችና ሟች መታረቃቸው ከተረጋገጠ
የሚኖረውን ውጤት በተመለከተ የተፋቱ ባልና ሚስት ግንኙነታቸውን ለማደስ
ቢፈልጉ እንደገና መጋባት አለባቸው ወይንስ በእርቅ ስምምነት ወደነበሩበት
ይመለሳሉ የሚለውን የቤተሰብ ሕጉ ምላሽ እንደማይሰጥና ነገር ግን በሃገራችን
ባሕል መሠረት የተፋቱ ባልና ሚስት ከፍቺ በኋላ ሲታረቁ ድጋሚ ጋብቻ
ሲፈጽሙ እንደማይስተዋሉና የእርቅ ስምምነቱ በእራሱ እንደ ባልና ሚስት
ለመኖር ሃሣብ ያላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ሲሆን በተመሳሳይም
አመልካችና ሟች በፍቺ ከተለያዩ በኋላ መታረቃቸውን እንደ ባልና ሚስት
ሆነው በጋብቻ የመኖር ውጤት ያለው መሆኑን የሚያስገነዝብ ከመሆኑም
በላይ ከፍቺውም በኋላ ንብረት ያልተከፋፈሉ ስለሆነና የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጋብቻ
የለም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት ሽሯል፡፡

በዚሁ ውሣኔ ቅር የተሰኙትም የአሁን ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታቸውን
ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ
አመልካች ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የሟች ሚስት
ነበርኩ የሚሉት አዲስ ጋብቻ ከሟች ጋር ፈጽመው ወይንም ጋብቻው
ስለመፈጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖሩን አስረዳለሁ በማለት ሳይሆን ጋብቻው
ከፈረሰ በኋላ ታርቀን አብረን ኖረናል በማለት ስለሆነ መታረቅም ሆነ አብሮ
መኖር ጋብቻን እንደመፈጸም አያስቆጥርም የሚል ትችት አስፍሮ የፌዴራል
ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻር አመልካች የሟች ሚስት አይደሉም በማለት
ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም ለዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው ይህንኑ ውሣኔ
በመቃወም ሲሆን ችሎቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ጋብቻው የፈረሰው
በፍቺ ወይንስ በሞት የሚለው ነጥብ ለሰበር ችሎት ቀርቦ መጣራት
እንደሚገባው በማጤኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ተጠሪም
በበኩላቸው የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍ አለመሆኑን በመዘርዘር
አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡



በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት
የሚገባው የሕግ ነጥብ በአመልካችና በሟች አቶ አማረ ይልማ መካከል
የነበረው ጋብቻ በ1976 ዓ.ም. በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ሟች እስከሞቱበት 1995
ዓ.ም. ድረስ በመካከላቸው በድጋሚ ጋብቻ ተፈጥሯል ወይንስ አልተፈጠረም
የሚለው በመሆኑ ይህንኑ የሕግ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው እንደሚከተለው
ተመርምሯል፡፡

አመልካችና ሟች አቶ አማረ ይልማ በ1966 ዓ.ም. ተጋብተው በ1976
ዓ.ም. ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ በመካከላቸው
የነበረው ጋብቻ በ1976 ዓ.ም. በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ ከአራት
ወራት በኋላ ተመልሰው ታርቀው አብረው መኖር እንደጀመሩ በፌዴራል
መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ በአመልካች ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 94 መሠረት ጋብቻ መኖሩን
ማስረዳት የሚቻለው በጋብቻ የምስክር ወረቀት መሆኑ የተመለከተ ሲሆን
የምስክር ወረቀቱ በሌለ ጊዜ የትዳር ሁኔታ መኖርን በማስረዳት ጋብቻ እንዳለ
ማረጋገጥ እንደሚቻል በዚሁ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 96 እና 97 ላይ
ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩልም የተፋቱ ባልና ሚስት በሚታረቁበት ጊዜ በድጋሚ
ጋብቻ መፈጸም የሚገባቸው ስለመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡
በእርግጥ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በድጋሚ መጋባት አዲስ ጋብቻ
ከመመሥረት የተለየ ስለማይሆን ድጋሚ ጋብቻ መመሥረትን በተመለከተ
በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ሊሆን አይችልም የሚል ክርክር ሊያስነሳ እንደሚችል
ቢታመንም በተያዘው ጉዳይ አመልካችና ሟች ከ10 ዓመት የጋብቻ ጊዜ በኋላ
በ1976 ዓ.ም. ተፋተው ብዙም ሳይቆዩ ከአራት ወራት በኋላ ሟች
እስከሞቱበት 1995 ዓ.ም. ድረስ አብረው እንደኖሩ በአመልካች ምስክሮች
የተነገረው ሲታይ እራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት እንደሚቆጥሩና ኀብረተሰቡም
ባልና ሚስት ናቸው በማለት የተቀበላቸው መሆኑን የሚያሳይና ይህም

በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 96 መሠረት በመካከላቸው የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመካከላቸው የትዳር ሁኔታ መኖሩ ከተረጋገጠ ደግሞ ጋብቻ መፈጸሙን በአንቀጽ 97/1/ መሠረት የሕግ ግምት /Legal presumption/ መውሰድ የሚቻል ሲሆን ይህንን የሕግ ግምት ማፍረስ የሚቻለው በአንቀጽ 97/2/ መሠረት ይህንን በሚክደው ወገን አስተማማኝ ማስረጃ በሚቀርብ ጊዜ ነው፡፡

በዚህ ረገድ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካችና ሟች አቶ አማረ ይልማ ሲኖሩበት ከነበረው የቀበሌ አስተዳደር ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተፃፈ ደብዳቤ ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ በኋላ ሟች ትዳር ያልነበራቸው መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም ይህ ማስረጃ ሕጉ እንደሚጠይቀው የሕግ ግምቱን ለማፍረስ አስተማማኝ ማስረጃ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 21648 በታህሳስ 25 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32637 በሐምሌ 28 ቀን 1997 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡
2. በአመልካች ወ/ሮ አበባወርቅ ጌታነህና በሟች አቶ አማረ ይልማ መካከል የትዳር ሁኔታ መኖሩ ስለተረጋገጠ አመልካች የሟች ሚስት ናቸው ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 23493

ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ
ዓብዱልቃድር መሐመድ
አሰግድ ጋሻው
ሒሩት መለሠ
ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አንማው ዘገየ

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ወርቁ መኰንን

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ከሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ሚስት ማን ነች? የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡

ክስ የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤት በዚህ ነጥብ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቶ የአሁን መልስ ሰጭ ከሟች ጋር በ1983 ዓ.ም ጋብቻ የፈፀመች ቢሆንም በኑሮ አለመግባባት በእርሷ ክስ አቅራቢነት በወረዳው ፍ/ቤት በ1992 ዓ.ም ጋብቻው እንዲፈርስ ተደርጓል፡፡ ይህንንም እርሷ አልካደችውም፡፡ በእርሷ በኩል የቀረበው ክርክር እንደገና በመስከረም 08 ቀን 1995 ዓ.ም ታርቄያለሁ የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለማህበራዊ ዋስትና መ/ቤት የቀረበውን ማስረጃ እንደተመለከትነው በወረዳው ፍ/ቤት በተሰጠው የፍቺ ውሣኔ መሠረት ሟች ከአሁን መልስ ሰጭ ለተወለዱት ልጆች እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ የልጅ ቀለብ በወር 50.00 ሲከፍል የቆየ መሆኑን ነው፡፡ መልስ ሰጭ እንደምትለው በ1995 ዓ.ም ታርቃ ቢሆን ኖሮ ሟች ለልጆች ቀለብ ባልከፈለ ነበረ፡፡ ይህም የሚያመለክተው መስከረም 08 ቀን 1995 ዓ.ም ታርቄያለሁ ስትል ያቀረበችው ማስረጃ እምነት የሚጣልበት አለመሆኑን ነው በማለት መልስ ሰጭ የሟች ሚስት አይደለችም፤ በተቃራኒው

የአሁን አመልካች የሟች ሚስት መሆኗን በበቂ ማስረጃ አስደግፋ ያስረዳች ስለሆነ ሚስት ናት በማለት ወስኗል፡፡

የይግባኝ አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤትም የይግባኝ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የአሁን አመልካች በደምበጫ ወረዳ ፍ/ቤት መልስ ሰጭ ደግሞ በደ/ማርቆስ ወረዳ ፍ/ቤት ሚስትነታቸውን አረጋግጠው አስወስነዋል፡፡ ሚስትነት ተረጋግጦ የተሰጠውን ውሣኔ አንዳቸው የአንዳቸውን አላሻሩትም፤ ውሣኔው ሕጋዊ ውጤት ያለው ነው፡፡ ስለሆነም ሁለቱም ሚስቶች ናቸው በማለት ከመብት በኋላ የጡረታ አበሉ ለማን ይገባል የሚለውን በሚመለከት አበል በየጊዜው ለመክፈል ከደመወዝ ተቀናሽ እየሆነ ከተጠራቀመው የሚከፈል እስከሆነ ድረስ ከሟች ጋር ረዘም ላለ ጊዜ አብራ ለቆየችው መሆን ይገበዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ መልስ ሰጭ ለ1983 ዓ.ም ጀምሮ ከሟች ጋር በትዳር የቆየች በመሆኑ የጡረታ አበሉ ለመልስ ሰጭ ይክፈል ከሚለው መደምደሚያ ደርሷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥ/ፍ/ቤት የጡረታ አበሉ ለመልስ ሰጭ ሊከፈል ይገባል ለሚለው ውሣኔው መሠረት ያደረገው ምክንያት ሕጋዊ መሠረት የለውም፤ እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኞችን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የአመልካችን ሚስትነት ለይቶ በአግባቡ ወስኖ እያለ የጠ/ፍ/ቤት ሁለታችንንም ሚስቶች ናቸው በማለት መወሰኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭም ውሣኔው ሊፀና ይገባል የምትልበትን ምክንያት በመግለጽ ተከራክራለች፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል እንደተመለከትነውም ሁለቱም ወገኖች በየፊናቸው የሟች ሚስት እና የልጆቻቸው ሞግዚት መሆናቸውን በተለያዩ ፍ/ቤት አረጋግጠው አስወስነዋል፡፡ ይህ ውሣኔ በይግባኝ አማካኝነት የተሻረ ለመሆኑ በግራ ቀኙ በኩል የቀረበ መከራከሪያ የለም፡፡ ይህም ሲሆን ሚስትነትን በማረጋገጥ የተሰጠው ውሣኔ ሕልውና ያለው እና ሕጋዊ ውጤትን የሚያስከትል ነው፡፡ የጠ/ፍ/ቤቱ ይህንኑ መሠረት አድርጎ ሁለቱም ወገኖች አመልካችና መልስ ሰጭ የሟች ሕጋዊ ሚስቶች ናቸው ሲል የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ይሁን እንጂ የጠቅላይ ፍ/ቤት በዚህ ውሣኔ መገደብ ሲገባው ከዚህ አልፎ የጡረታ አበሉ ለየትኛዋ ሚስት ይገባል የሚለውን ጭብጥ ይዞ እና ይህንንም ለመለየት ከሟች ጋር ለረዥም ጊዜ በትዳር የኖረችው የትኛዋ ናት የሚለውን መሠረት አድርጎ የጡረታ አበሉ ለአሁን መልስ ሰጭ ሊከፈል ይገባል ሲል መወሰኑ በዚያው ጉዳይ ሁለቱም የሟች ሚስቶች ናቸው በሚል ከሰጠው ውሣኔ ጋር የሚጣርስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንደቀረበለት ጥያቄ ሚስትነት በማረጋገጥ ረገድ ዳኝነት መስጠት ሲገባው ከተጠየቀው ዳኝነት ውጭ በመሄድና የሚስትነትን ውሣኔ ውጤት በሚያስቀር አኳኋን መወሰኑ ሥነ ሥርዓታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. ወ/ሮ አንማው ዘገዬ እና ወ/ር ወርቂ መኰንን ሁለቱም የሟች ሚስቶች ናቸው፤ የጡረታ አበሉም ለሁለቱም ሊከፈል ይገባል ብለናል፡፡
2. የአ/ብ/አ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 07542 በየካቲት 16 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
3. የምሥ/ጎጃ/መስ/ዞን ከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1039 በመስከረም 20 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ/ 23632

ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** ወ/ት ፀዳለ ደምሴ - ቀረበች

**ተጠሪ፡-** አቶ ክፍሌ ደምሴ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው የአሁኗ አመልካች የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ባቀረበችው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በቦንጋ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት የሕፃን ቢንያም ክፍሌ ወላጅ አባት ስለሆንኩ ፍ/ቤቱ ለሕፃኑ ሞግዚትና አስተዳዳሪ አድርጎ ይሾመኝ በማለት የቀረበውን አቤቱታ ፍ/ቤቱ መርምሮ የሕፃኑን ሞግዚትና አስተዳዳሪ አድርጎ ሾሞታል፡፡ የአሁኗ አመልካች በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት የአሁኑ ተጠሪ ሕፃኑን ከመውለዱ በስተቀር ምንም ዓይነት እርዳታ አላደረገም፤ ተንከባክቦም አላሳደገም በማለት የተቃውሞ አቤቱታ ያቀረበች ሲሆን ተጠሪ ሕፃኑ ከእናቱ የሚወርሰውን ሀብትና ንብረት ፍለጋ እንጂ ለሕፃኑ ጥቅም ብሎ ስላልሆነ ተጠሪ ሞግዚት እንዲሆን የተላለፈው ውሣኔ ተሽሮ በምትኩ እኔ አክስቱ ላለፉት 12 ዓመታት ተንከባክቤ ያሣደኩት ሞግዚት ሆኜ እንድሾም ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችውን መቃወሚያ የወረዳው ፍ/ቤት መርምሮ አባት ላለው ልጅ አመልካች የሞግዚትነት ጥያቄ ማቅረብ አትችልም በማለት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጎ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ ሕፃኑን እስከዛሬ ድረስ ሣያሣድግ አሁን እናቱ ስትሞት ላሣድግ ማለቱ ሀብትና ንብረት ፍለጋ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት የሚያዳግት ቢሆንም የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/96 አንቀጽ 235/1 ከወላጆቹ አንዱ በሞት የተለየው ሕፃን በሕይወት ያለው ወላጅ ሞግዚትና አስተዳዳሪ እንደሚሆንለት ስለሚደነግግ የወረዳው ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ተገቢ ነው በማለት መልስ ሰጭን አስቀረቦ ሣያከራክር በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የለም በማለት የአሁኗን አመልካች አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የሰበር ቅሬታ ማመልከቻው የቀረበው ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት መጋቢት 6 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት በዚህ ጉዳይ የሕፃን ቢንያም ክፍሌ አክስት የሆነችው የአሁኗ አመልካች ሞግዚት ለመሆን ያቀረበችውን ጥያቄ የሥር ፍ/ቤቱ ውድቅ ያደረገበትን የሕግ አግባብ ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ መልስ ሰጭም መጥሪያ ደርሶት መልሱን ባለማቅረቡ የጽሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር ቅሬታ ማመልከቻውን ከሥር ፍ/ቤት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 36 ስለ ሕፃናት መብት ደንግጓል፡፡ በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ሁሉ የመንግሥታዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተቋማት እንዲሁም ፍርድ ቤቶችና የአስተዳደር ባለሥልጣናት ወይም የሕግ አውጭው አካላት የሕፃናትን ደህንነት በቀደምትነት እንዲያስቡ በአስገዳጅነት ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው የአለም አቀፍ ስምምነቶች መካከል የሕፃናትን መብት በሚመለከት 1984 ዓ.ም የፀደቀውና በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 9(4) መሠረት የሀገሪቱ የሕግ አካል የሆነው የሕፃናት መብት ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(1) መሠረት ፍርድ ቤቶችም ሆኑ ሌሎች አካላት ሕፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ውሣኔ ሲሰጡ የሕፃናቱን ጥቅምና ደህንነት በዋነኛነት መመልከት እንደሚገባቸው

ተመልክቷል። እንደሚታወቀው የልጆቻቸው መብትና ደህንነት በማስጠበቅ ረገድ ከወላጆቻቸው የበለጠ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ሰው ሊኖር ስለማይችል ሕግ አውጭው በመርህ ደረጃ የተቀበለው በመሆኑ በሕይወት ያለው አባት ወይም እናት የሕፃን ልጁ ሞግዚት እና አስተዳዳሪ አድርጎ የመሾሙ አሠራር አገራችንን ጨምሮ የበርካታ አገራት ተሞክሮ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ መሠረት በፌዴራልም ሆነ በክልል የቤተሰብ ሕጎች ውስጥ ወላጆች ለሕፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ ስለመሆናቸው በግልጽ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ያሉ ቢሆንም እነዚህ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ሞግዚት ወይም አስተዳዳሪ የተባለው ወላጅ በሕገ መንግሥቱ እንደተመለከተው ለሕፃኑ ጥቅምና ደህንነት እስከሠሩ ጊዜ ድረስ ብቻ እንደሆነ ሊስተዋል የሚገባ ጉዳይ ነው። በሌላ አነጋገር በአባት ወይም በእናት የሞግዚትነት ሽፋን የሕፃናትን መብትና ደህንነት የሚጎዱ ወይም ሊጎዱ የሚችሉ ሥራዎች ሁሉ በዳኞች ቀሪ እና ፈራሽ ሊሆኑ የሚችሉበት አግባብ በሕጉ የተለያዩ ክፍሎች መገኘቱ ይህንኑ የሕፃኑን መብትና ጥቅም በዋነኛነት ለማስከበር የተደነገገ ነው። በዚህ ረገድ በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች ሕፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሲመረምሩ ከዝርዝር ሕጎቹ በተጨማሪ በሕገመንግሥት አንቀጽ 36(2) በአስገዳጅነት የተቀመጠውን የሕፃናትን ደህንነት ከግምት ውስጥ ያስገባ ውሣኔ ላይ እንዲደርሱ የግድ ይላል። ይህን በመተላለፍ የሚሰጡ ማናቸውም ውሣኔዎችና ልማዳዊ አሠራሮች የሕገ መንግሥቱን ኃይለቃል የሚቃረኑ ስለሚሆኑ ፈራሽነታቸው የማያጠራጥር ነው።

ወደያዝነው ጉዳይ ስናመራ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሕፃን ቢንያም ክፍሌን ሞግዚትነት አስመልክቶ የቀረበላቸውን ጉዳይ ሲመረምሩ ከሕጎቹ ግልጽ ድንጋጌዎች ባሻገር ሕገመንግሥቱ ያስቀመጠውን የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም የማስከበር መርህ ተግባራዊ ማድረግ ሲገባቸው በተለይ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ደረጃ የሞግዚትነት ጥያቄ ያነሣው ሕፃኑ ልጅ « ከእናቱ በውርስ ከሚያገኘው ንብረትና ሀብት ላይ ተካፋይ ለመሆን አስቦ ስለመሆኑ» የከፍተኛው ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ ገልጾ ሕፃኑን ከመውለድ ውጭ ከአስር ዓመታት በላይ ዞር



ብሎ ያላየውን፣ ያልተንከባከበውን፣ ያላሣደገውን እንዲሁም ፍላጎቱን እንኳን ያልጠየቀትን ሕፃን በሰላምና በእንክብካቤ ካደገበት ቤት አስወጥቶ በአሁኑ ተጠሪ ሞግዚትነት ሥር ይተዳደር ተብሎ የተደረሰበት መደምደሚያ የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም ያላገናዘበ ነው። የሥር ፍ/ቤቶች ከሕጎቹ ግልጽ ቃላት ባሻገር የሕጎቹን አላማና መንፈስ በቅጡ ሣያጤኑ የአንቀጾቹን ግርድፍ ቃላት ብቻ በመውሰድ ሕገመንግሥቱን በሚጋፋና የሕፃኑን መብትና ደህንነት በሚጎዳ አኳኋን የሰጡት የሞግዚትነት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል።

## ው ሣ ኔ

- የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ ከፋ ዞን የቦንጋ ዙሪያ ወረዳ ፍ/ቤት ታህሣሥ 17 ቀን 1998 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 29/98 እንዲሁም የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በየካቲት 21 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ. 01001 በተጨማሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መጋቢት 1 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ.14275 የሰጡዋቸው ውሣኔዎችና ትእዛዞች ተሽረዋል፣
- የአሁኗ አመልካች ወ/ሪት ፀዳለ ደምሴ የሕፃን ቢንያም ክፍሌ ሞግዚትና አስተዳዳሪ ሆና ሕፃኑ ከሟች ወላጅ እናቱ ከወ/ሮ ፋንታዬ ኃ/ሚካኤል የሚያገኘውን ማናቸውም የውርስ ሀብት ተረክባ ሕፃኑን በመልካም አስተዳደግና ደህንነት ተንከባክባ እንድታሣድገው ተሹማለች።
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 24295

መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ደስታ ገብሩ

ሒሩት መለሠ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች ፡-** ወ/ሮ ጽጌ ድረሴ

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ መሰለች ረዳ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የንብረት ይገባኛል ጥያቄን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ስትሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው ከሟች ባለቤትዋ ጋር አፈራሁት ያለችውን ንብረት እንድታስረክባት ነው፡፡ አመልካችም ለቀረበባት ክስ መልስ ሰጥታለች፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ ክስ የቀረበባቸውን ንብረቶች /መኖሪያ ቤት እና ልዩ ልዩ የቤት ቁሳቁሶች/ ለከሳሽ ታስረክብ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሳሳይ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ሚያዝያ 9 ቀን 1998 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ከሟች ባለቤትዋ ጋር አፈራሁት የምትለውን ንብረት በሙሉ መጠየቅ ስለመቻል አለመቻልዋ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡



በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ የንብረት ይገባኛል ጥያቄ ያነሳችው የሟች ሚስት መሆንዋንና በዚህ መሠረትም ንብረቱ በጋራ ያፈራችው እንደሆነ በመግለጽ ነው፡፡ አመልካችም ተጠሪ የሟች ሚስት አይደለችም ወይም በተባለው ንብረት ላይ የጋራ መብት የላትም የሚል ክርክር አላነሳችም፡፡ አመልካች ያነሳችው አንድ መቃወሚያ ሲሆን፣ ይህም የቤቱ ግምት ተጋኖአል የሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃወሚያውን በመቀበል ቤቱን በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል እንዲገመት አድርጐአል፡፡ በዚህ መሠረትም ቤቱና በዝርዝር የተገለጹት የቤት ዕቃዎች እንዳሉ ለተጠሪ እንዲሰጡ ወስኗል፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ቤት እና የቤት ዕቃዎች የባልና ሚስት የጋራ ሃብቶች ናቸው፡፡ በንብረቶቹ ላይ ባልና ሚስቱ ያላቸው መብት እኩል አይደለም የሚል ክርክር አልተነሳም፡፡ በባልና ሚስቱ መካከል የነበረው ጋብቻ በባልየው ሞት ምክንያት ፈርሶአል፡፡ ጋብቻ ሲፈርስ በንብረት ክፍፍል ላይ የራሱ የሆነ ውጤት እንደሚኖረው በቤተሰብ ሕጉ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በግልጽ ተለይተው የታወቁ ናቸው፡፡ አንደኛው ተጋቢ ከሌላኛው ተጋቢ ወገን የበለጠ ወይም ያነሰ መብት አለው የሚል ክርክርም አልተነሳም፡፡ ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ እኩል የሆነ /የጋራ/ መብት እንዳላት ከመግለጽ አልፋ ከድርሻዋ በላይ የምትወስድበት ምክንያት እንዳላት አላስረዳችም፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 90 እንደተደነገገው የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተጠሪ መጠየቅ ያለባት ወይም ልታገኝ የሚገባት የንብረቶቹን ግማሽ ብቻ ነው፡፡ ግማሹ የሟች ባለቤትዋ ድርሻ በመሆኑ ይህንኑም ጠቅልላ የምትወስድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

የስር ፍ/ቤቶችም ይህን በሕግ የተመለከተውን የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ሥርዓት ባለመከተል ውሣኔ መስጠታቸው ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00676 መጋቢት 30 ቀን 1997 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38807 መጋቢት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪ መውሰድ ያለባት ድርሻዋ ማለትም የቤቱ እና የቤት እቃዎቹ ግማሽ ነው ብለናል፡፡ በዚህ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈፀም ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



የሰ/መ/ቁ. 24625

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ተገኔ ጌታነህ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ራሕማ ዓሊ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

አቤቱታው የንብረት ይገባኛል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተችው ተከሣሽ የሟች ባለቤቱ ማሩ ሱሌይማን ንብረት የሆነ ቤት ይዛ ስለምትገኝ የእኔንና ከሟች የወለድኩትን ልጄን ድርሻ ታካፍለን በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሣሽና ተከሣሽ የሟች ሚስቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቤቱን ግማሽ ሁለቱ ይካፈሉ፡፡ ግማሹን ደግሞ ለልጁ ይሁን በማለት ሲወስን፣ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ቤቱ የተገዛው ሟች እና ተጠሪ ባፈሩት ገንዘብ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት አመልካች ከቤቱ ልትካፈል አይገባም ሲል ወስኖአል፡፡ የመጨረሻውን ይግባኝ የሰማው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አከራካሪው ቤት አመልካችና ማሩ ሱሌይማን በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ የተገዛ ሆኖ ሳለ፣ አመልካችና

ማሩ ሱሌይማን አብረው አልኖሩም፣ ቤቱ የተገዛበት ገንዘብም ማሩ ሱሌይማን ከተጠሪ ጋር በነበረበት ጊዜ የተገኘ ነው በሚል ምክንያት አመልካች ከቤቱ ድርሻ የላትም የመባሉን አግባብነት መርምሮ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ነጥብ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አከራካሪው ቤት የተሠራው በአመልካች እና በሟች ማሩ ሱሌይማን መካከል ተመሥርቶ የነበረው ጋብቻ ፀንቶ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ በተጋቢዎቹ መካከል የተመሠረተው ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ወቅት የተገኘ ንብረት የተጋቢዎች የጋራ ሃብት ነው ተብሎ የሕግ ግምት እንደሚወሰድበት በሕግ ተደንግጓል፡፡ ይህ የሕግ ግምት ቀሪ ማድረግ የሚቻለው አንደኛው ተጋቢ ንብረቱ የግል ሃብቱ እንደሆነ ካስረዳ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው አከራካሪው ቤት የሟች የግል ንብረት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ቤቱ የሟች የግል ንብረት መሆኑ በሕግ አግባብ ካልተረጋገጠ እና ከፍ ሲል የተጠሰቀውን የሕግ ግምት ቀሪ የሚያደርግ የተለየ ሁኔታ እስከሌለ ድረስ አመልካች በቤቱ ላይ መብት የላትም ለማለት የሚቻልበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር አመልካችን ከንብረቱ አንዳትካፈል ማድረግ ደግሞ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአማራ ብ/ክ/መ/የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07983 ታሕሣሥ 22 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 05615 መጋቢት 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡



2. በአማራ ብ/ክ/መ/ የደባርቅ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡ በመሆኑም የንብረቱ ክፍፍል በዚሁ ወረዳ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ብለናል፡፡

ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25005

ኀዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** መኮንን በላቸው ቀርበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አለሚቱ አደም ቀረበች፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሳውን የንብረት ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገኖች በየበኩላቸው ያቀረቡት የንብረት ጥያቄ እና በዚህ ረገድ ያነሱት የመከራከሪያ ነጥብ በዝርዝር ታይተዋል፡፡ ክርክር ከተደረገባቸው ንብረቶች መካከል ዋነኛው በወረዳ 19 ቀበሌ 55 ክልል ውስጥ ይገኛል የተባለው በቁጥር 318 የሚታወቀው መኖሪያ ቤት ነው፡፡ በተደረገው ክርክር ተጠሪ የዚህን ቤት ብቸኛ ባለቤት እንደሆነች የገለጸች ስትሆን፣ አመልካች ደግሞ ቤቱ ጋብቻው ጸንቶ በነበረበት ጊዜ የተሠራ /የተፈራ/ የጋራ ንብረት ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ የዚህን ፍ/ቤት ውሣኔ በይግባኝ የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ ቤቱ ከጋብቻው በፊት ተጀምሮ የነበረ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት የተጠሪ የግል ሃብት መሆን አለበት፡፡ አመልካች ለቤቱ ያወጣው ገንዘብ ታስቦ ይመለስለት በማለት ወስነዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 21 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን ቅሬታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡



አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ለቤቱ ስራ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉ በዝርዝር ተገልጾ ሳለ የጋራ ባለሃብት ሊሆን አይችልም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

መዝገቡን በአጠቃላይ መርምረን እንደተገነዘብነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ያረፈበት መሬት ጋብቻው ከመፈጸሙ በፊት ተጠሪ በማኀበር ከተመራች በኋላ የቤት ስራው መስከረም 29 ቀን 1979 ዓ.ም. መጀመሩን፣ ጋብቻው ታሕሣሥ 26 ቀን 79 ዓ.ም. በመፈጸሙን፣ ቤቱ ሥራው አልቆ ለማኀበሩ አባላት የተከፋፈለው በጥቅምት ወር 1980 ዓ.ም. መሆኑን፣ ቤቱ ተስፋፍቶ የተሠራውና ቤትም የሆነው ጋብቻው ከተፈፀመ በኋላ እንደሆነ፣ ለቤቱ ማሠሪያ ከባንክ በብድር ገንዘብ የወሰደችው ተጠሪ ብትሆንም፣ ከ1981 ዓ.ም. ጀምሮ ጋብቻው በፍቺ እስከፈረሰበት 93 ዓ.ም. ድረስ በአመልካች በኩል ሲከፈል መቆየቱን የስር ፍ/ቤቶች በማስረጃ አረጋግጠዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ፍ/ቤቶቹ በፍሬ ነገር ረገድ ይህን ቢያረጋግጡም የቤቱ ስራ የተጀመረው ከጋብቻው በፊት ማለትም መስከረም 29 ቀን 1979 ዓ.ም. /ሦስት ወር የማይመዝን ጊዜ/ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ የተጠሪ የግል ሃብት ነው የሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው አከራካሪው ቤት በእርግጥም ቤት የሆነው አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻቸውን ከፈጸሙ በኋላ እንደሆነ የሥር ፍ/ቤቶች በቀረበላቸው ማስረጃ በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ለቤቱ መሥሪያ በሚል ከባንክ በብድር የተወሰደውን ገንዘብ ሲከፈል የቆየው በአመልካች በኩል እንደሆነ እና ይህም የሆነው ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት የሚባለው ባልና ሚስቱ ከግል ንብረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኙትን ገቢዎች ሁሉ እንደሚያጠቃልል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕ/አዋጅ ቁ. 213/92/ አንቀጽ 62/1/ ተመልክቶአል፡፡ አንደኛው ተጋቢ ሃብቱ የግሉ ስለመሆኑ ካላስረዳም ንብረቱ በአንደኛው ተጋቢ

ስም ብቻ የተመዘገበም ቢሆን የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው ተብሎ በሕግ እንደሚገመት በዚሁ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 63/1/ ተደንግጎአል፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ አከራካሪው ቤት ያረፈበት ቦታ /መሬት/ ከጋብቻው በፊት ተጠሪ በማኀበር የተመራችው ከመሆኑ እና ጋብቻው ሊፈጸም ጥቂት ጊዜ ሲቀረው ሥራው ከመጀመሩ በስተቀር በተጠሪ የግል ጥረት እና ሃብት ብቻ የተገነባ ነው የሚባል አይደለም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ጋብቻው በተፈጸመበት ጊዜ ወይም ከዚያ በፊት ቤቱ የተጠሪ የግል ሃብት ነው ተብሎ በጋብቻ ውል ተለይቶ አልተመለከተም፡፡ እንደምንመለከተው እንግዲህ ቤቱ በማንኛውም መለኪያ የተጠሪ የግል ሃብት ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በዚህ ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 2141 ታሕሣሥ 7 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 36010 ሚያዝያ 18 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ ተሻሽለዋል፡፡
2. አከራካሪው ቤት የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ሃብት ነው፡፡ ሁለቱም እኩል የመካፈል መብት አላቸው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 25281

ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ተገኔ ጌታነህ
መስፍን ዕቁበዮናስ
አብዱራሂም አህመድ
ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ ቀርባለች፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ቀልቤሣ አበው ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 6 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩ የስር አመጣጥ አመልካች የስር ከሣሽ በመሆን በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ ጋብቻ መሥርተው ሲኖሩ ከየካቲት 1 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱንና የጋራ ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ባመለከቱት መሠረት የንብረት ዝርዝር አቅርበው ከዚህ ዝርዝር ውስጥ በጋራ የሠሩትን ቤት እንዲካፈሉና ተጠሪ ቤቱን አከራይተው ስለሚጠቀሙና ኪራዩም በወር ብር 350 (ሦስት መቶ ሃምሳ) ስለሆነ የ10 ዓመት ኪራይ ብር 36000 (ሰላሳ ስድስት ሺ) አመልካች ስላገኙ ቤቱ ተገምቶ የግምቱን ግማሽ በመክፈል ልጆቼን እንዳሳድግበት በማለት ጠይቀዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ተጠሪ ቤቱ የተሠራበትን ቦታ ከአመልካች ጋር በጋብቻ ከመተሣሰራቸው በፊት ያገኙት ስለሆነ አመልካች የቦታው ይዞታ ተካፋይ የሚሆኑበት ምክንያት የለም፡፡ ሆኖም ቤቱ የተሰራው ግራ ቀኙ ጋብቻ ከመሠረቱ በኋላ ስለሆነ በባለሙያ ተገምቶ የቤቱን ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ፡፡ የኪራይ ገቢን በተመለከተ አመልካች በማስረጃ

አስደግፈው ባለማቅረባቸው ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ፀንቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መነሻነት ሲሆን ይህ ፍርድ ቤት አቤቱታውን መርምሮ መልስ ሰጪን ካስቀረበ በኋላ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክሩንም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ በዚህም መሠረት የስር ፍርድ ቤት ያለአመልካች ስምምነት የቤቱን ግምት አጋማሽ ከተጠሪ ይቀበሉ በማለት መወሰኑ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ይህ ፍርድ ቤት እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች የቤቱን ግምት ግማሽ ተቀብለው እንዲወጡ የተወሰነውን በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተጠሪ የቦታውን ይዞታ ያገኙት ከአመልካች ጋር በጋብቻ ከመተሳሰራቸው በፊት በመሆኑ በዚህ ይዞታ ላይ አመልካች ተካፋይ የሚሆኑበት ምንም ምክንያት የለም የሚል መሆኑን ተረድተናል፡፡ ከፍርድ ቤቱ ውሣኔ ለመረዳት የተቻለው ቤትና ቦታውን ነጣጥሎ ማየቱን ሲሆን ፍርድ ቤቱ ይህን ለማድረግ ያስቻለውን ድንጋጌ አልጠቀሰም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1131 ላይ እንደተመለከተው በአመልካችና በተጠሪ መካከል ቤቱን በተመለከተ የጋራ ባለሀብትነት መብት በፍርድ ቤቱ ውሣኔ የተመሠረተ ከመሆኑ አኳያ አመልካች በቤቱ ላይ ያገኙት የጋራ ባለሀብትነት መብት የመሬቱ ይዞታንም ስለሚያጠቃልል መብታቸው በይዞታውም ላይ የተዘረጋ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ድንጋጌ መሠረት በቤት ላይ የተገኙ መብቶች እንደ አንድ ሙሉ ክፍል መሬቱንም እንደሚያጠቃልሉና በተከታዩ አንቀጽ 1132 ላይ እንደተመለከተው ቤቱም የመሬቱ አንድ አቋም ሆኖ የሚቆጠር በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1131 መሠረት የቤቱ የጋራ ባለሀብትነትና ቤቱ የቆመበት መሬት የተጠሪ የግል ባለይዞታነት በተመለከተ ግራ ቀኙ አስቀድሞ ያደረጉት ውል ባለመኖሩ ይህ በሌለበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ከጋብቻው በፊት የመሬቱ ባለይዞታ ነበር በማለት መወሰናቸው አግባብ ካለመሆኑም በላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተትም ነው፡፡



በሌላም በኩል የጋራ ሀብትን ለማከፋፈል አመቺ በማይሆንበት ጊዜ ግራ ቀኙ ንብረቱን አንዳቸው እንዲያስቀሩ መስማማት እንደሚቻል፣ ለመስማማት ያልተቻለ ቢሆን ግን ንብረቱ ተሸጦ ገንዘቡን እንደሚከፋፈሉ፣ በንብረቱ አሻሻጥ ካልተስማሙ ደግሞ ንብረቱ በአንደኛው ጠያቂነት በጨረታ እንደሚሸጥ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 92 በግልጽ ደንግጓል፡፡ ከዚህ ውጪ ተከራካሪ ወገኖች በንብረቱ አከፋፈል ካልተስማሙ በስተቀር ፍርድ ቤቶች በራሳቸው ተነሣሽነት ንብረቱን ለአንደኛው ተከራካሪ ወገን እንዲሰጥ የማድረግ ሥልጣን እንደሌላቸው ከድንጋጌው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ የሥር ፍርድ ቤቶች ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ቤቱ ለአንዳችን ብቻ ይገባል በማለት እየተከራከሩ ባሉበት ሁኔታ ተጠሪ ቤቱን እንዲያስቀር በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 33271 የካቲት 10 ቀን 1997 ዓ.ም. እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 38782 መጋቢት 27 ቀን 1998 ዓ.ም. ቤቱ ለተጠሪ ይገባል በማለት የሰጧቸው ውሳኔዎች ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ቤቱን በዓይነት መካፈል የሚችሉ ከሆነ እንዲካፈሉ፣ መካፈል የማይችሉ ከሆነ አንዱ ለሌላው ግምቱን ሰጥቶ ቤቱን እንዲያስቀር፣ በዚህ ካልተስማሙ ቤቱ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እንዲካፈሉ ያደርግ ዘንድ ታዟል፤ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25588

የካቲት 6 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- መርየን ሃሰን ዑመር - ቀረበች

ተጠሪ፡- መውሊድ ተኸል እስማን - አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የባልና ሚስት የግልና የጋራ ሀብትን የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች ተጠሪው የወሰደብኝን የግሌ የሆነውን አንድ ክፍል ቤት፣ ቀደም ሲል የሰጠሁትን 96 ፍየሎች እና በመካከላችን አለመግባባት ከመፈጠሩ በፊት ከቤቴ ውስጥ አስቀምጬው የወሰደብኝን ብር 5900 ይመልስልኝ በማለት በሶማሌ ክልል ደገሐቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካችና ተጠሪ በትዳር ተሳስረን የቆየን ቢሆንም የየግላችን የሆነ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት የለንም፣ ስለተባሉት ፍየሎችና ስለገንዘቡ አንድም የማውቀው ነገር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ሕጋዊ የትዳር ትስስር እንዳላቸው ገልፆ በክሱ ላይ የተጠቀሰው አንድ ክፍል ቤት የአሁን አመልካች የግል ንብረት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፣ 96ቱን ፍየሎች አመልካች ለተጠሪ የሰጧቸው መሆኑን በምስክሮች አስረድተዋል፣ ብር 5900 ተጠሪ ከአመልካች መውሰዳቸው ግን አልተረጋገጠም በማለት ወስኗል፡፡



የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ክሱ ሊቀርብ የሚገባው ለሸሪአ ፍ/ቤት ነው፣ ቤቱን የሠራሁት እኔ መሆኔን በምስክሮች አረጋጫለሁ፣ ካርታውንም በአመልካች ስም እንዲመዘገብ ያደረግኩት በቅን ልቦና መሆኑን እያረጋገጥኩ ፍ/ቤቱ አይገባህም ሲል የወሰነብኝ ያለአግባብ ነው በማለት ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን የአሁን አመልካችም ከተጠሪ ጋር በትዳር ተሳስረን ስንኖር በጋራ ያፈራነው አንድም ንብረት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ እንዲፀና እና ይግባኙ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ቤቱ የተሠራው አመልካችና ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ እያሉ መሆኑ በምስክሮች ስለተረጋገጠ ካርታው በአመልካች ስም መመዝገቡ ብቻ ቤቱ የአመልካች የግል ንብረት መሆኑን እያረጋግጥም ስለዚህ ቤቱ የሁለቱ የጋራ ሀብት ነው፣ ፍየሎቹን አመልካች ለተጠሪ ሠርቶ እንዲጠቀም ብለው የሰጧቸው መሆኑ ስለተረጋገጠና አመልካችም ክዶ ስላልተከራከረ እንዳመነ ተቆጥሮ የፍየሎቹን ዋጋ ብር 14400 /አሥራ አራት ሺህ አራት መቶ ብር/ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈል በማለት ወሰነ፡፡

የአሁን ተጠሪ በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ አመልካችና ተጠሪ ንብረቶቹን ያፈራነው በጋራ ስለሆነ የስር ፍ/ቤት የፍየሎቹን ዋጋ ተጠሪ ይክፈል በማለት የወሰነው ያለአግባብ ነው በማለት ቅሬታቸውን የገለፁ ሲሆን አመልካችም የስር ክርክራቸውን በመድገም መልስ ሰጥተዋል፡፡ ችሎቱ በመ/ቁ. M/G/14/98 በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በስር ፍ/ቤት የተፈፀመ የሕግ ስህተት ስለሌለ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ፀንቷል በማለት ወሰነ፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ የአሁን ተጠሪ ለሰበር ችሎቱ በድጋሚ አቤቱታ በማቅረባቸው ችሎቱ ጉዳዩን በሌላ ጊዜ በድጋሚ በማየት በዚያው መዝገብ በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ሌላ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ችሎቱ በሁለተኛው ውሣኔ የስር ፍ/ቤቶች የቀረበላቸው ጉዳይ የቤተሰብ ጉዳይ መሆኑን ሲገነዘቡ ጉዳዩ በሸሪአ ፍ/ቤት እልባት እንዲያገኝ ማድረግ ሲገባቸው ይህንን አላደረጉም፣ የሰበር ችሎቱም በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመውን ይህንን ስህተት

ባለማጤን በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፣ ስለዚህ ጉዳዩ ወደ ደገሐቡር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ይህንን ውሣኔ በመቃወም የአሁን አመልካች በሰኔ 20 ቀን 1998 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ለዚህ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ የክልሉ ሰበር ችሎት ለሁለተኛ ጊዜ በሰጠው ውሣኔ በፍርድ ሊወሰን የሚችልን ማንኛውምንም ጉዳይ ለፍ/ቤት የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት ሕገ መንግሥታዊ መብቴን በሚጥስ መልኩ ጉዳዩ በሸሪአ ፍ/ቤት ሊታይ ይገባል በማለት የወሰነ ስለሆነ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡ ችሎቱም የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ በመመርመር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አጽድቄዋለሁ ያለውን ውሣኔ በሌላ ቀን ችሎት ሽሬዋለሁና ክርክሩ በሸሪአ ፍ/ቤት ይታይ ብሎ የወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነው የክልሉ ሰበር ችሎት በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ ራሱ ደግሞ በማየት በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ሌላ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በመሠረቱ አንድ ፍ/ቤት አንድ ጊዜ አይቶ ውሣኔ ያሳረፈበትን ጉዳይ በድጋሚ ሊያይም ሆነ ሊወስን በመርሕ ደረጃ የማይችል ሲሆን ነገር ግን በሕግ ላይ በተቀመጡ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ በድጋሚ ጉዳዩን ሊመለከተው ይችላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን የስር ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ጉዳዩ በድጋሚ ይታይልኝ ብለው ስላመለከቱ ብቻ ጉዳዩን እንደገና አይቶ ሁለተኛ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አንድ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆንና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከላይ በተገለጹት ምክንያቶች የስር ፍ/ቤት ሁለተኛ ውሣኔ መስጠቱ ስህተት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ



1. የሶማሌ ብ/ክ/መ/ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ M/G/14/98 በግንቦት 24 ቀን 1998 ዓ.ም. ለሁለተኛ ጊዜ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የሶማሌ ብ/ክ/መ/ ሰበር ሰሚ ችሎ 206 ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 05/1/210/97 ዓ.ም. በኀዳር 17 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት በመ/ቁ. M/G/14/98 በመጋቢት 16 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 26839

ኅዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አስካለ ለማ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ሣህለ ሚካኤል በዛብህ - ቀረቡ፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በንብረት ክፍፍል ላይ ያደረጉት ክርክር ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ላይ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ተጠሪ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በ82 ካ.ሜ. ላይ የተሠራ ቪላ ቤት ከጋብቻ በፊት የተሰራ የግላቸው መሆኑንና ሌሎችን ንብረቶች ዘርዝረው በማቅረብ ለመካፈል ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ደግሞ የግል ቤቴን ሽጬ ባገኘሁት ገንዘብ ቤቱን ከማኅበሩ ተረክበን አፍርሰን አሁን ያለውን ይዞት እንዲኖረው አድርገን ስለሰራነው የግሉ አይደለም፤ እዳው ከጋብቻ በኋላ ነው የተከፈለው እንዲሁም ከሌሎቹ ንብረቶቹ ውስጥ በውርስ ያገኘኋቸው የግል ንብረቶቼ ይገኙበታል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ከጋብቻ በኋላ ተሰሩ የተባሉት ስራዎች ተገምተው ብር 82,293 (ሰማኒያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት) ስለሆኑ የዚህን ዋጋ ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች ከፍለው ቤቱን ያስቀሩ በማለትና በሌሎቹም ንብረቶች የክፍፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ውሣኔን አጽንቶታል፡፡



የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ ግምት ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ሂደት እንደተረዳነው ተጠሪ ግምት ከፍለው ቤቱን እንዲያስቀሩ የተወሰነው ቤቱ ከጋብቻ በፊት የተገኘ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት ነው፡፡ በመሆኑም ክርክር የተነሳበት ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት ነው ወይስ የተጠሪ የግል ሃብት የሚለው ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ባልና ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኟቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀሩ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 57 ያመለክታል፡፡ አንድ ንብረት ከግል  እና ከጋራ ሃብት ተቀላቅሎ የተገኘ ከሆነ ግን ንብረቱ የጋራ ወይም የግል ተብሎ እንደሚቆጠር የሕጉ ድንጋጌ በግልጽ አያመለክትም፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ድንጋጌውን ከአላማው አኳያ መተርጎም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከጋብቻ በፊት የነበረ ንብረት የጋራ እንዳይሆን የተፈለገበት ምክንያት ጋብቻ ንብረት ለማግኘት በሚል ሃሣብ ብቻ እንዳይቋቋምና እንዳይፈርስ ለመከላከል ሲባል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ምንም ንብረት ያልነበረው ሰው ንብረት ያለውን ሰው በማግባት ጋብቻ ሲፈርስ ያላፈራውን ንብረት የሚካፈልበት ሁኔታ ማመቻቸት ለፍትሕ እና ለሕሊና ተቃራኒ ነው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ነገር ግን ለአንድ ንብረት መገኘት ተጋቢዎቹ ያደረጉት አስተዋጽኦ ተመርምሮ እንደነገሩ ሁኔታ የግል ወይም የጋራ ሊባል ይገባል፡፡ ይህንንም ለመወሰን በንጽጽር ሲታይ አብዛኛው መዋጮ የተደረገው ከግል ነው ወይስ ከጋራ የሚለውን ከግምት ማስገባቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ ንብረቱ በአብዛኛው ከጋራ ሃብት መዋጮ የተገኘ ከሆነና የግል ንብረቱ ትንሽ ከሆነ ንብረቱ የጋራ ሆኖ መቆጠሩ ፍትሐዊ ይሆናል፡፡ የንብረቱ የተወሰነ ክፍል ከጋብቻ በፊት ተገኝቶ እንኳን ቢሆን አነስተኛ የሆነው ድርሻ

ከግል ሃብት ከንብረቱ ላይ በመቀላቀሉ ብቻ ንብረቱ የግል እንዲሆን ማድረጉ ፍትሐዊ አይሆንም፡፡

ከዚህ ተነስተን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ በእርግጥ ቤቱ የተጀመረው ከጋብቻ በፊት ቢሆንም ቤቱ ተሠርቶ የተጠናቀቀው ከጋብቻ በኂላ እና ለቤቱ መስሪያ የተወሰደው ብድርም ከጋብቻ በኂላ መከፈሉን መዝገቡ ያስረዳል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህን ካረጋገጠ በኂላ ከጋብቻ በፊት የተሠራው ሥራ ምን ያሕል እንደሆነ ሳያጣራ እንዲሁም ከጋብቻ በኂላ የተሰራውንም ቢሆንም በገበያ ዋጋ ሳይሆን የመሃንዲስ ግምት ብቻ በማስቀረብ የዚህን ግምት ግማሽ ብቻ አመልካች ለተጠሪ ከፍለው እንዲያስቀሩ መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቤቱ ተጀምሮ ከማለቁ በፊት ጋብቻው እንደተፈፀመና የተጠናቀቀውም ከጋብቻ በኂላ መሆኑን፣ ለቤቱ መስሪያ የተወሰደው ብድርም ቢሆን ከጋብቻ በኂላ መከፈሉ አብዛኛው ወጪ ከጋራ ሃብት የወጣ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በእርግጥ በንብረቱ ላይ የተቀላቀለውን የግል ሃብት በተቀላቀለው መጠን የግሉ የሆነው ተጋቢ ሊወስድ ይገባል፡፡ ይህም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁጥር 86/1/ ስር ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር የሚስማማ ነው፡፡ በመሆኑም ቤቱ የተጀመረው ከጋብቻ በፊት በመሆኑ ብቻ ቤቱ የተጠሪ የግል ሃብት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሰበት መደምደሚያ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 913 በግንቦት 29 ቀን 1996 ዓ.ም ክርክር የተነሳበትን ቤት በተመለከተ የሰጠው የውሣኔ ክፍል ብቻ ተሽሯል፡፡
2. የክርክር ምክንያት የሆነው ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሃብት ነው፡፡
3. ከጋብቻ በፊት የተሠራው ሥራ ተገምቶ ግምቱ ለተጠሪ ይከፈል፡፡ ቤቱን ከተቻለ ግራ ቀኙ በዓይነት ይካፈሉ፣ ካልተቻለ አንዱ ለአንዱ የቤቱን የገበያ ዋጋ ግምት ከፍሎ ያስቀር፣ በዚህ የማይስማሙ ከሆነ ቤቱ ተገምቶ በሃራጅ ተሸጦ የሽያጩን ገንዘብ እኩል ይካፈሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 26953

ኀዳር 13 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አብዱራሂም አህመድ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ - ቀረቡ፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ በሰጠው ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በአመልካች ጠያቂነት የቀረበ የሰበር ጉዳይ ነው፡፡

በወረዳው ፍ/ቤት የአሁን መልስ ሰጭ ከሣሽ ነበሩ፡፡ ያቀረቡትም አቤቱታ ከመልስ ሰጪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ የፈረሰ መሆኑን መነሻ በማድረግ የንብረት ክፍፍል ይደረግልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካችም በተከሳሽነት ቀርቦ ያካፍለኝ ስትል ከጠየቀችው ንብረት መካከል በእጁ የሚገኘው ቤት በወንድሜ ገንዘብ የተገዛ በመሆኑ የእኔና የእርሷም አይደለም፡፡ እንዲያውም በእርሷ እጅ የጋራ ንብረት የሆነ ቤት የሚገኝ ስለሆነ ልታካፍለኝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም ይህ በእኔ እጅ ይገኛል በተባለው ቤት ላይ የአሁን አመልካች እንዳችም መብት የለውም፡፡ በግል ልጄ የደም ዋጋ የተሠራ ነው የሚል ክርክር አቅርባለች፡፡

የወረዳው ፍ/ቤትም ይህንኑ የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ ሁለት ቤት በሁለቱም እጅ እንደሚገኝ እና አንደኛው ቤት በዋጋ ከሌላው ቤት

የማይበልጥ ስለመሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ በእጃቸው ያለው ቤት ድርሻቸው ሊሆን ይገባል ሲል ወስኗል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም በይግባኝ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ይህንኑ ውሣኔ በማጽናት አሰናብቷቸዋል፡፡ ለዚህ ውሣኔ የአሁን መልስ ሰጭ ቅር ተሰኝታ የይግባኝ አቤታዋን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርባላች፡፡

ጉዳዩን በሁለተኛ ደረጃ ይግባኝ የሰማው ይኸው ጠቅላይ ፍ/ቤት ሁለቱንም ወገኖች ካከራከረ በኋላ ምንም እንኳ የአሁን አመልካች በእኔ እጅ የሚገኘው ቤት በወንድሜ ገንዘብ የተሰራ እንጂ የጋራ ሀብት አይደለም በማለት የተከራከረ ቢሆንም፣ ይህ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ስለሆነም የቤቱን ግምት ድርሻውን ብር 1000.00 እንዲከፍላት፤ በአሁን መልስ ሰጭ ልጅ ሞት ምክንያት በተገኘ የደም ዋጋ ገንዘብ የተሠራ ነው የተባለው ቤት የጋራ ሀብት ነው የሚል ከሆነ ዳኝነት ሲጠይቅ የሚታይ እንጂ ለማካካሻ ምክንያት ሊሆን አይችልም በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክርም በይዘቱ በሥር ፍ/ቤት ከቀረበው የተለየ አይደለም፡፡ እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በአመልካች እጅ ያለው ቤት በትዳር እያሉ የተሠራ ስለመሆኑ ክርክር ያስነሳ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች በመከራከሪያ ነጥብነት ያቀረበው በእጁ ያለው ቤት በወንድሙ ገንዘብ የተገዛ ስለሆነ የእኔም የእርሷም አይደለም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ንብረቱ በእጁ የሚገኝና የሚገለገሉበት መሆኑ ክርክር አላስነሳም፡፡ ይህም ከሆነ በትዳር እያሉ የተገኘ ማናቸውም ሀብት የጋራ እንደሚሆን ሕጉ ግምት ወስዷል፡፡ ይህንን ግምት የማፍረስ ግዴታ የተከራካሪው ወገን ነው፡፡ ተከሪ ... ሬም የአሁን አመልካች በወንድሜ ገንዘብ የተገዛ ነው ሲል በአባ( ... ያቀረበው ክርክር እንጂ በማስረጃ አስደግፎ አላስረዳም፡፡ ማስረጃ አለው አንኳ ቢባል ይኸው ንብረት ከወንድሙ በስጦታ ለግሉ ተብሎ የተሰጠ መሆኑን ሊያመለክት ይገባል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዳኝነት በአግባቡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡



አለ የተባለውን ቤት በሚመለከት መልስ ሰጭ በግል ልጁ ሞት ምክንያት በተሰጠ የደም ካሣ ዋጋ የተሰራ ስለሆነ የግል ሀብቴ ሆኖ ይቀጥላል አለች እንጂ አባባሉን የሚደግፍ የሕግ ክርክር አላቀረበችም፡፡ ይልቁንም የካሣ ክፍያው ምክንያት ምንም ይሁን ምን የካሣ ክፍያ አግኝታለች፡፡ በዚህም የካሣ ክፍያ ቤቱ የተሰራ ለመሆኑ አልካደችም፡፡ የካሣ ክፍያ ደግሞ ገቢ ነው፡፡ በትዳር እያሉ የተገኘ ገቢ እስከሆነ ድረስ ከላይ በተሰጠው የሕግ ምክንያት የጋራ ነው፡፡ የግሏ ለመሆኑ በተለየም መንገድ ቢሆንም የማያስረዳ የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አላቀረበችም፡፡ ስለሆነም ይህም በመልስ ሰጭ እጅ የሚገኘው ቤት የጋራ ሀብት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ንብረቱ የጋራ ነው የሚል ክርክር አመልካች ክስ አቅርቦ እራሱን በቻለ አኳኋን ዳኝነት ከመጠየቅ በቀር በማካካሻነት ሊከራከርበት አይችልም በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ቢሆን ይህ ቤት የመልስ ሰጭ የግል ሀብቷ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ አልደረሰም፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ የፍቺ ተከታይ የሆነ የንብረት ክፍፍል ነው፡፡ ምንም እንኳ መነሻ የሆነውን የንብረት ጥያቄ የአሁን አመልካች ታቅርብ እንጂ አመልካችም በእርሱ በኩል የሚቀርብ የንብረት ክፍያ ጥያቄ ካለ በመልስ ሰጭ እጅ የሚገኘውን ንብረት በመዘርዘር ድርሻ ክፍያውን ለመጠየቅ የሚከለክለው የክርክር አቀራረብ ሥርዓት የለም፡፡ የንብረት ማጣራት እና የንብረት ክፍፍል ጥያቄው የፍቺ ውሣኔን ተከትሎ የሚመጣ እንደመሆኑ ሌላኛው ወገን በተከሣሽ ከሳሽነት ተሰይሞ ተገቢውን ዳኝነት ክፍሎ ሊጠይቅ ይገባዋል የሚያሰኝም አይደለም፡፡ ስለሆነም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ የአመልካችን ክርክር አስመልክቶ ዳኝነት ሲጠየቅ የሚታይ እንጂ በቀረበው ጉዳይ የሚስተናገድ አይደለም ሲል በክርክሩ ዳኝነት ሳይሰጥበት ማለፉ በክርክር አቀራረብ ሥርዓት ረገድ መሠረታ( ... ህተት መፈፀሙን አረጋግጠናል፡፡ ይኸው ነጥብም ቢሆን በግራ ቀኙ ... ተገቢው ክርክር የተደረገበት እና ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በመልስ ሰጭ እጅ የሚገኘው ንብረት በሕጉ ግምት የጋራ በመሆኑ እና የሁለቱንም ቤቶች ዋጋ በንጽጽር ተመልክቶ በየእጃቸው

ያለው ቤት ድርሻቸው መሆኑን በመግለጽ የወረዳው ፍ/ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ በአግባብ ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 01/98 በሰኔ 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ የተሻረ ሲሆን የወረዳው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01837 ሰኔ 01 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቤት 7978 በሐምሌ 19 ቀን 1997 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካች እና በመልስ ሰጭ እጅ የሚገኙት ቤቶች ሁለቱም የጋራቸው ስለሆነ በየእጃቸው ያለው ድርሻቸው ነው፤ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 27697

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** አቶ ርዕሶም ገ/መድኀን - ጠበቃ አበበ ኃይሌ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አልማዝ ጊላሚካኤል - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸው ጸንቶ ባለበት ጊዜ ተሸጧል የተባለን መኪና ዋጋው ለትዳር ጥቅም ስለመዋሉ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የሽያጩን ገንዘብ ግማሹን አመልካች ለተጠሪ ይክፈሉ በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት ሲሉ ተጠሪ ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኂላ ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ባቀረቡት የንብረት ዝርዝር ከቤት በወጣሁ ጊዜ የግል አልባሳቶቼን ይዤ ስላልወጣሁ አመልካች እነዚህን አልባሳቶቼን እንዲሰጠኝ፣ የሠ/ቁ 3-38794 የሆነው መኪና ከጋብቻ በኃላ የተገዛና የጋራ ንብረት ስለሆነ የመኪናውን ዋጋ ግማሽ ድርሻዬን እንዲሰጠኝ እንደዚሁም በጋብቻ ወቅት ያፈራናቸው የቤት ዕቃዎች ተቆጥረው የሚገኙ ስለሆነ ግማሽ ድርሻዬን እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ የነበሩት የአሁን አመልካች በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውን የፈጸሙት ግንቦት 27 ቀን 1987 ዓ.ም. እንደነበረና ጋብቻቸውን በፈጸሙ ጊዜም ተጠሪ ከጋብቻ በፊት የነበራቸው አንድ መኪና እና አንድ ቤት በጋብቻ ውሉ የግላቸው ሆኖ

እንደተመዘገበና የቀድሞው መኪና ተሸጦም አቤቱታ የቀረበበትን የሠ/ቁ 3-38794 መኪና ተጠሪ እንደገዙና ይህም መኪና በመካከላቸው ክርክር ከመጀመሩ በፊት በመስከረም 8 ቀን 1991 ዓ.ም በተፃፈ ውል እንደተሸጠና ገንዘቡም ለምን ጥቅም እንደዋለ በመዘርዘር በአጠቃላይም ተጠሪ ለአመልካች የሚያካፍሉት ምንም ንብረት እንደሌለ በመጥቀስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የንብረት ክርክሩ በዚሁ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ አመልካች የጠየቋቸው የግል አልባሳትና የቤት ቁሳቁሶችን በተመለከተ ተጠሪ ክደው ያልተከራከሩ ስለሆነ የግል አልባሳቶቻቸውን እንዲያስረክቧቸው የቤቱ ቁሳቁሶቹንም ከተቻለ በዓይነት እንዲከፋፈሉ ካልተቻለም ተገምተው በግምቱ መሠረት እንዲከፋፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

መኪናውን በተመለከተ ከጋብቻ በፊት ተጠሪ የነበራቸው መኪና በጋብቻ ውሉ የግል ተደርጎ የነበረ ቢሆንም ይህንኑ መኪና በጋብቻ ጊዜ ሸጠው ሌላ መኪና ሲገዙ ይሄው መኪና የግል ሀብታቸው እንዲሆን በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 58/2/ መሠረት ተጠሪ በፍ/ቤት ያላስመዘገቡ ስለሆነ በአንቀጽ 62/2/ መሠረትም የጋራ ሀብት ስለሚሆን መኪናው ተሸጧል የተባለበትን ብር 240 ሺ.ህ ግማሹን ብር 120 ሺ.ህ ከነወለዱ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

የሥር ተጠሪ የአሁን አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤትም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ መ/ሰጭ ከቤት በወጣሁ ጊዜ የግል አልባሳቶቹን ይዤ ስላልወጣሁ ይግባኝ ባይ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በይ/ባይ በግልጽ ያልተካደ ስለሆነ የግል አልባሳቶቻውን ሊያስረክብ ይገባል ... ሊወሰንም ይ/ባይ ለመልስ ሰጪ ሊያስረክቡት የሚገባ ምንም ንብ... ...ለ በግልጽ ከመካዳቸውም በላይ በዚህ ረገድ መ/ሰጭ የቆጠሩት ማስረጃ ይ/ባይ የመሃላ ቃላቸውን እንዲያወርዱ በመጠየቅ ሲሆን በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ይ/ባይ የመሐላ ቃላቸውን እንዲያወርዱ ባለመደረጉ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መሐላ እንዲያወርዱ ተደርጎ መ/ሰጭ የግል አልባሳታቸውን ጥለው እንዳልሄዱ ያረጋገጡ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ይ/ባይ የመ/ሰጭን የግል አልባሳቶችን ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ አይደለም በማለት ሽሯል፡፡

የሠ/ቁ. 3-38794 የሆነውን መኪና በተመለከተ ይግባኝ ባይ የሚያቀርቡት ክርክር መኪናው የተሸጠው ግራ ቀኙ ከመፋታታቸው ከ11 ወራት በፊት አካባቢ በመሆኑ ከፊሉ ገንዘብ በጋራ ለጋራ ችግራቸው እንዳዋሉትና በቀሪው ገንዘብም ብዛት ያለው ወርቅ ገዝተው በመ/ሰጭ አክስት ቤት ማስቀመጣቸውን ቢሆንም ይህንን ለማስረዳት ያቀረቧቸው ምስክሮች ቀርበው እንደተሰሙት ይግባኝ ባይና መ/ሰጭ ተጣልተው በሽማግሌዎች ፊት እርቅ በፈጸሙበት ጊዜ የተገዛበትን ዋጋና ግራሙን የማያውቁት ወርቅ በመ/ሰጭ አክስት ቤት ሲያስቀምጡ ማየታቸውን እንጂ ለመ/ሰጭ አክስት በአደራ ተሰጥቷል የተባለው ወርቅ በመኪናው ሽያጭ ገቢ የተገዛ ስለመሆኑ ካለመሆኑም በላይ ወርቁ የመ/ሰጭ አክስት ቤት ስለመቀመጡም ቢሆን በምስክርነት ማቅረብ ይገባቸው የነበረው የመ/ሰጭ አክስትን ነበር የሚል ትችት በውሣኔው ላይ አስፍሮ የመኪናው ሽያጭ ገንዘብ ለግራ ቀኙ ጥቅም መዋሉን ይግባኝ ባይ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ይግባኙን ባለመቀበል የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካችና ተጠሪ በፍቺ ከመለያየታቸው በፊት በአንድነት እየኖሩ ተሸጠ የተባለው መኪና የሽያጭ ገንዘብ ለግራ ቀኙ መጠቀሚያ ስለመዋሉ በማስረጃ አልተረጋገጠም ተብሎ የሽያጩን ገንዘብ ግማሹን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተጠሪ ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙ ... ...ሯል፡፡ የሰበር አቤቱታውም ከሕጉ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካችና ተጠሪ ጋብቻቸውን የፈጸሙት ግንቦት 27 ቀን 1987 ዓ.ም. እንደሆነ ይሄው ጋብቻቸው በፍቺ የፈረሰው ደግሞ ኅዳር 7 ቀን 1992 ዓ.ም. እንደሆነና እንደዚሁም ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነው የሠ/ቁ. 3-38794 የሆነው መኪና የተሸጠው መስከረም 1 ቀን 1991 ዓ.ም. መሆኑ እነዚህ ፍሬነገሮች ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የተጠቀሰው መኪና ጋብቻው በፍቺ ከመፍረሱ 1 ዓመት በፊት ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ መሸጡና ጋብቻው በፍቺ በፈረሰ ጊዜ የመኪናው ሽያጭ ገንዘብ በሙሉ ወይንም በከፊል አመልካች እጅ እንደሚገኝ በማስረጃ ካልተረጋገጠ ጠቅላላ የመኪና ሽያጭ ገንዘቡ በጋብቻ ጊዜ ለጋራ የትዳር ጥቅም እንደዋለ የባልና ሚስትን ሃብት ስለማጣራት በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ከተደነገገው ከቁጥር 85-93 ካሉት ድንጋጌዎች አንጻር የሕግ ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡

የዚህ የሕግ ግምት ተጠቃሚ የሆነ ወገንም ንብረቱ በጋብቻ ጊዜ የተሸጠ መሆኑን ካስረዳ በቂ ሲሆን ሌላው ወገን ደግሞ ጋብቻው በፍቺ በፈረሰ ጊዜ ከንብረቱ የሽያጭ ገንዘብ በሙሉ ወይንም በከፊል የሚገኝ መሆኑን ካስረዳ የሽያጩ ገንዘብ በጋብቻ ጊዜ ለጋራ ጥቅም ውሏል የሚለውን የሕግ ግምት እንዳፈረሰ ይቆጠራል፡፡

አመልካች ለክርክሩ መነሻ ምክንያት የሆነው መኪና በጋብቻ ጊዜ የተሸጠ መሆኑን በማስረዳት የሽያጩ ገንዘብ ለጋራ የትዳር ጥቅም እንደዋለ ሕጉ በወሰደው ግምት ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ በሌላ በኩልም ተጠሪ ጋብቻው በፈረሰ ጊዜ የመኪናው ሽያጭ ገንዘብ በሙሉ ወይንም በከፊል በአመልካች እጅ እንደሚገኝ ያላስረዱ በመሆኑ የሕግ ግምቱን ማፍረስ አልቻሉም፡፡

በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ይ/ባይ ከመኪናው ሽያጭ ገንዘብ ላይ ብር 115,000 /አንድ መቶ አሥራ አምስት ሺህ/ የሚያወጣ ወርቅ ለመ/ሰጭ ገዝቼ ወርቁም መ/ሰ[illegible] 218 ቤት እንዲቀመጥ የተደረገ ስለመሆኑ የሚያውቁልኝ ምስክሮች እን... ....ሼ እነዚህ ምስክሮች በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሊሰማልኝ ሲገባ አልተሰሙልኝም የሚል ክርክር በማቅረባቸው



ፍ/ቤቱ እነዚህን ምስክሮች አስቀርቦ ቢሰማም ወርቅ ተገዝቷል የሚለው የይግባኝ ባይ ክርክር ለትዳር ጥቅም ውሏል በሚለው የሕግ ግምት ውስጥ የሚጠቃለል ሆኖ ሳለ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልገው በሕግ ግምቱ ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ሲገባው የይግባኝ ባይን የተሳሳተ የክርክር መስመር ተከትሎ ማስረጃ በመስማት ከመኪናው የሽያጭ ገንዘብ ላይ ይ/ባይ ለመ/ሰጭ ወርቅ ስለመግዛታቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የመኪናውን ሽያጭ ገንዘብ ግማሹን ይግባኝ ባይ ለመ/ሰጭ እንዲከፍሉ ውሣኔ መስጠቱ እንደዚሁም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ይህንኑ የሕግ ግምት ሳያገናዝብ ውሣኔ መስጠቱ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06189 በሚያዝያ 28 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20828 በጥቅምት 30 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የሠ/ቁ. 3-38794 የሆነው መኪና አመልካች የሸጡት በግራ ቀኙ መካከል የነበረው ጋብቻ ጸንቶ ባለበት ጊዜ ስለሆነና ገንዘቡም ለጋራ የትዳር ጥቅም እንደዋለ ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አኳያ የሕግ ግምት ስለሚወሰድና ተጠሪም ይህንኑ የሕግ ግምት ያላፈረሱ ስለሆነ የሽያጩን ግማሽ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ 27869

ኀዳር 10 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጐስ ወልዱ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

አመልካች ፡- ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠ/ተፈራ ሙሉጌታ ቀረበ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ ቀረቡ

2. አቶ ትሁት ማሞ ጠ/ደረጀ ወርቁ ቀረበ፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡

በተጠሪዎች መሐከል የነበረው ጋብቻ በ10/03/95 ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍል ክርክሩ ቀጥሎ ባለበት ሁኔታ የአሁኑ አመልካች የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ናቸው የተባሉት የአ/አበባና በደ/ዘይት ከተማ የሚገኙት ቤቶች 2ኛ ተጠሪ ለማህበሩ በአይነት መዋጮ የሰጡት በመሆኑ ቤቶቹ የማህበሮቹ ናቸው በማለት ተቃውሞ አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ 2ኛ ተጠሪ የትኛውን ቤት ለማሕበሩ እንዳዋጡ የሚያሳይ የቤት6 አድራሻና ቁጥር በግልጽ በመመሥረቻ ፅሁፉ ላይ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም በሕጉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ማስተላለፍን የተመለከተው የመመዝገብ ተግባር አልተፈፀመም፤ የቤቱን የባለቤትነት ምስክር ወረቀት አቅርቦ ቤቱ የኩባንያው መሆኑን አላስረዳም በማለት ተቃውሞውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም ቤቱ ለኩባንያው በመዋጮ ተሰጥቷል ወይ የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ሲል መልስ ሰጪ እንዲቀርቡ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፁሑፍ እና በቃል አሰምተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን መርምሯል፡፡

አመልካች ክርክር የተነሳበት ቤት ለማህበሩ በመዋጮ ተሰጥቷል የሚለው 2ኛ ተጠሪ ቤቱን ለማህበር መስጠታቸው በማሕበሩ መመሥረቻ ጽሁፍ ላይ ተመልክቷል፡፡ የማሕበሩ መመሥረቻ ጽሁፍም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ተመዝግቧል በማለት አመልካች ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የተከራከረው በመመስረቻ ጽሁፍ ላይ በመዋጮ ተሰጠ የተባለው ቤት አድራሻውን ቁጥሩ በግልጽ ያልተጠቀሰና የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለሌላ 3ኛ ወገን ለማስተላለፍ በህጉ የተመለከተው የምዝገባ ስርዐት ያልተሟላ ነው በማለት ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ በማህበሩ ተዋጣ ሲባል እኔ አልተስማማሁም በማለት ነው፡፡

በአንድ የንግድ ማህበር ውስጥ የአክስዮን ባለድርሻ ለመሆን አባላቱ ድርሻቸውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት ሊያዋጡ ይገባል፡፡ ኃ/ የተወሰነ የግል ማህበር ሲቋቋም በሚዘጋጀው የመመስረቻ ጽሑፍም እያንዳንዱ ማህበርተኛ ያስገባው የመዋጮ የገንዘብ ልክና በዓይነት ያገባው የመዋጮ ግምት ሊገለጽ እንደሚገባ በንግድ ህጉ ቁጥር 517/ሡ/እና/ረ/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ በንግድ ህጉ ላይ በዓይነት የተዋጣው ንብረት በምን አይነት ዝርዝር ሁኔታ መመስረቻ ጽሁፉ ላይ ሊገለጽ እንደሚገባ በግልጽ የተመለከተ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የተዋጣው የንብረት አይነት በማያሻማ ሁኔታ ለመለየት በሚያስችል መልኩ ሊገለጽ ይገባል፡፡ ንብረቱን በትክክል ለመለየት ወይም ለማወቅ የሚያስችል ሁኔታ ካለ ግን የተለያዩ ዝርዝር ነገሮች አልተገለፀም በሚል ብቻ መዋጮ አልተደረገም ማለት ተገቢ አይሆንም፡፡

በተያዘው ጉዳይ 2ኛ ተጠሪ የኩባንያው 27% አክስዮን ባለድርሻ የሆኑት በዓይነት ባዋጡት መዋጮ መሠረት ነው፡፡ ከዚህም መዋጮ አንዱ በአ/አበባ የሚገኘውና ክርክር የተነሳበት ቤት መሆኑን አመልካች ይገልፃል፡፡ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የቤቱ አድራሻና ቁጥር ተለይቶ ያልተጠቀሰ

በመሆኑ በመዋጮ የተሰጠው ክርክር የተነሳበት ቤት ነው ሊባይ አይችልም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ እኛም እንዳየነው በመመስረቻ ጽሁፍ ላይ አ/አበባ የሚገኘው ቤት በወዋጮ የተሰጠ መሆኑ ከመገለፁ በቀር የቤቱ አድራሻና ቁጥር ተለይቶ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ ያዋጡት የቱን ቤት ነው የሚለው ሊመለስ ይገባል 2ኛ ተጠሪ በመዋጮ የተሰጠው አ/አበባ የሚገኘው ቤት ክርክር የተደረገበት ሳይሆን ሌላ ቤት ነው፣ በአ/አበባ ውስጥ ከአንድ ቤት በላይ አለኝ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የለም፡፡ አንድ ውል ግልጽ ባልሆነ ጊዜ ደግሞ ሊተረጐም የሚገባው የተዋዋዮቹ ሐሳብ ምን እንደነበረ በመፈለግ ጭምር እንደሆነ የፍ/ህ/ቁ. 1733 ያመለክታል፡፡ 2ኛ ተጠሪም በአ/አበባ ያላቸው አንድ ቤት ብቻ ከሆነ ለኩባንያው በዓይነት ለማዋጣት ያሰቡት ይህንኑ ቤት ነው ተብሎ ነው ሊተገኰም የሚገባው 2ኛ ተጠሪ ያዋጡት ሌላ ቤት እንደሆነ ክርክር ሳያቀርቡ የቤቱ አድራሻና ቁጥር ተለይቶ ባለመገለፁ ብቻ በግልጽ የተሰጠ መዋጮ የለም በማለት የቀረበው ክርክር የህግ መሠረት የለውም፡፡

ከዚህ ሌላ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ያለን መብት ለማስተላለፍ የባለቤትነት ስም የማዛወር ሥርዓት አልተፈፀመም የሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ የመመስረቻ ጽሑፍ በውልና ማስረጃ መዝገባ ጽ/ቤት የተመዘገበ እና በሚመለከተው የኢንቬስትመንት ባለሥልጣን ዘንድ ቀርቦ እንደተመዘገበ ተረድተናል፡፡ የቤቱ ሥም በኩባንያው ተዛውሮ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ውስጥ አለመመዝገቡ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ እንዳይሆን ከሚከለክላቸው በቀር ንብረቱ በዓይነት በመዋጮ መሠጠቱን ውጤት አያሳጣውም፡፡ ይህንንም ከፍ/ሕ/ቁ. 2878 መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል 2ኛ ተጠሪ ንብረቱ የጋራ ሃብት በመሆኑ ያለእሳቸው ፈቃድ ለ3ኛ ወገን ሊተላለፍ እንደማይችል ተከራክረዋል፡፡ በእርግጥ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሆነ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሀብትነትን ወይም ሌላ መብት ለ3ኛ ሰው ለማስተላለፍ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት



ማስፈለጉ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 68/1/ ሥር የተመለከተ ሲሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢም ውሉ እንዲፈርስ ለፍ/ቤት ጥያቄ በማቅረብ ውሉ እንዲፈርስ ማድረግ ይችላል፡፡ (የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 69/1/) ውሉ የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሳይኖር በመደረጉ ብቻ ከጅምሩ ውጤት አልባ ሳይሆን ይልቁንም ውጤት እንዳይኖረው አንደኛው ተጋቢ ለፍ/ቤት ጥያቄ በማቅረብ ማስፈረስ ያስፈልገዋል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ይኸው 2ኛ ተጠሪ ከማህበሩ ሌላዋ የአክስዮን ባለድርሻ ጋር ያደረጉት ስምምነት እንዲያፈርስላቸው ለፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው አላስፈረሱም፡፡ በመሆኑም ውሉን ሲዋዋሉ ስለማላውቅ ቤቱ ለማህበሩ በመዋጮ ሊሰጥ የማይገባው የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በአጠቃላይ ክርክር የተነሳበትን ቤት 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ማህበር በአይነት ያዋጡት በመሆኑ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በሚል የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለው ነው፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 9392 በ10/01/1998 በወረዳ 17 ቀበሌ 21 ቁጥር 432 የሆነው ቤት 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች ማህበር በአይነት ያዋጡት የማህበሩ ቤት አይደለም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ከፍ ሲል ቁጥሩና አድራሻው የተጠቀሰው ቤት ለአመልካች በዓይነት የተዋጣ ንብረት ነው፡፡
3. ቤቱን በተመለከተ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔን በማጽናት በመ/ቁ. 42402 ህዳር 21/1999 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ነ/ዓ

የፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 29343

ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

መድህን ኪሮስ

አመልካች፡- 1. ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ
2. ወ/ት ሌንሳ ኢላላ } ጠበቃ ተስፋዬ ዘውዴ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ት አበባ አድማሱ ጠበቃ ጥጋቡ ጌጤ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች በተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክስ 1ኛ ከሳሽና ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ በጋብቻ ሥርዓት ግዴታ ውስጥ እያሉ 2ኛዋን ከሳሽ ወልደዋል፡፡ ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ የካቲት 29 ቀን 1995 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን ተከሳሽ የሟች ልጅ ናቸው፡፡ ሟች እና 1ኛ ከሳሽ ታህሣሥ 18 ቀን 1962 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተጋብተው በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ቁጥር 836 በሆነ መኖሪያ ቤት እየኖሩ በካርታ ቁጥር 31619 አቶ አክሊሉ አጥላባቸው ከተባሉ ግለሰብ የገዙትን መኖሪያ ቤት እያከራዩ ለትዳር ጥቅም አውለዋል፡፡ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ለመንግስት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ ባልና ሚስቱ ተነጋግረው ለዚህ ክስ ምክንያት የሆነውን በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ቁጥር 836 የሆነውን ቤት በጋራ ሀብትነት መርጠው የኪራይ ገቢ ይሰበስቡበት የነበረውን ከላይ የተገለፀውን መኖሪያ ቤት በትርፍነት ለመንግሥት አስረክበዋል፡፡

የ1ኛዋ ከሳሽ እና የሟች የጋራ ሀብት የሆነውን እንዲሁም የ2ኛዋ ከሳሽ የውርስ ድርሻ የተቋቋመበትን መኖሪያ ቤት ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ በሞት ከተለዩበት ከየካቲት 29 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ተከሳሽዋ በይዞታቸው ሥር አድርገው በወከሏቸው ግለሰቦች አማካይነት እያከራዩ በኪራዩ ገቢ እስካሁን በብቸኝነት ይጠቀሙበታል፡፡ ይሄው ቤት በአነስተኛው በወር ብር 3.500 ሊከራይ የሚችል ሲሆን ሟች ሕይወታቸው ካለፈበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ በብቸኝነት በመሰብሰብ ያለአግባብ የበለፀጉ ስለሆነ የ2 ዓመት ከ5 ወር ገቢው ብር 101.500 /አንድ መቶ አንድ ሺህ አምስት መቶ/ ስለሚሆን የ1ኛ ከሳሽ ድርሻ ብር 50.750 የ2ኛ ከሳሽ ብር 25.375 ተከሳሽ እንዲከፍሉና ቤቱም በሐራጅ ተሸጦ እንድንከፋፈል ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሾች ክስና ማስረጃ ለተከሳሽ ደርሶ በሰጡት መልስ 1ኛ ከሳሽ ከሟች ጋር በጋብቻ ተቆራኝተው በነበረ ጊዜ በካርታ ቁጥር 31619 የተመዘገበውን ቤት ከአቶ አክሊሉ አጥላባቸው ገዝተው ለጋብቻ ጥቅም ሲያውሉት እንደነበር ያቀረቡት ከሀቅ ያፈነገጠ ነው፡፡ የተጠቀሰው ቦታና ቤት አቶ ኢላላ ኢብሳና አቶ ለማ ኢብሳ በጋር ገዝተውት የነበረ ሲሆን አቶ ኢላላ ኢብሳ በመሬቱና በቤቱ ላይ በግላቸው ሙሉ መብት አልነበራቸውም፡፡ ቤቱ በጋራ ሐብትነት ተመርጦ ነው በማለት ከሳሾች በክሳቸው የጠቀሱትም ሐሰት ነው፡፡ ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ለመንግስት ያስረከቡትን ቤት ከአቶ ለማ ኢብሳ ጋር የጋራ ስለነበር የግሌ ነው ብሎ ለመምረጥ የሚያስችል መብት ስላልነበራቸው ቤትና መሬቱን ከማስረከብ በስተቀር ምንም ማድረግ የማይችሉ ስለነበርና ቤቱም ተከፍሎ ባላለቀ የባንክ ብድር ዕዳ ተይዞ የነበረ በመሆኑ በእነዚህ ምክንያቶች ቤትና ቦታውን መንግሥት በትርፍነት ወረሰው እንጂ ባልና ሚስቱ መክረው አላስረከቡትም፡፡

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 09 የሚገኘውና መለያ ቁጥሩ 836 የሆነው መኖሪያ ቤት ሟች እና 1ኛ ከሳሽ ጋብቻ ከፈፀሙበት ታህሣሥ 18 ቀን 1962 ዓ.ም በፊት በ1957 ዓ.ም የተሠራና በጋብቻ ወቅትም የጋራ እንዲሆን የፈቀዱበት ውል የሌለ ስለሆነ የሟች የአቶ ኢላላ ኢብሳ የግል ንብረት ነው፡፡

አቶ ለማ ኢብሳ ለረጅም ዘመን የሟች ወኪል በመሆን ንብረታቸውን ያስተዳድርላቸው የነበረ ሲሆን ሟች ሲሞቱ ተከሳሽ አሜሪካን አገር እኖር ስለነበር የሟችን ቤት እኔ አልተረከብኩም፤ አላከራየሁም፡፡ አቶ ለማ ኢብሳን የወከልኩት ለወደፊቱ በውርስም ሆነ በሌላ ምክንያት ለማገኘው ንብረት ወኪል እንዲሆነኝ እንጂ የሟችን ቤት እንዲያስተዳድርልኝ አልወከልኩም በማለት ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱን ከሰማ በኋላ የክርክሩ መሠረት የሆነው ቤት የሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና የ1ኛ ከሳሽ የጋራ ሐብት ነው ወይንስ አይደለም?

ተከሳሽ ይህንኑ ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት በወኪላቸው አማካይነት ይዘውታል ወይ? ቤቱን በተመለከተ የተጠየቀውን ገንዘብ ተከሳሽ ለመክፈል ይገደዳሉን? የሚሉትን ጭብጦች መሥርቶ ጉዳዩን መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ክልል የሚገኘው የመ/ቁጥር 836 የሆነው ቤት ሟችና 1ኛ ከሳሽ ከመጋባታቸው በፊት በ1957 ዓ.ም የተሠራና በሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ስም የተመዘገበ ስለመሆኑ በተከሳሽ በኩል ማስረጃ የቀረበ ከመሆኑም በላይ ከሳሾችም በክርክር ወቅት ይህንን ያላስተባበሉ ሲሆን ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ ከሳሽ ይህን ከጋብቻ በፊት የተሠራውን ቤት የጋራ የጋብቻ ንብረት ያደረጉበት የጋብቻ የውል ሰነድ የለም፡፡

1ኛ ከሳሽ ክስ የቀረበበት ቤት የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ሌላ የመከላከያ ነጥብ ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ ከሳሽ በጋብቻቸው ወቅት ያፈሩትን በካርታ ቁጥር 31619 የሚታወቀው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 11/1/ መሠረት ለመንግስት አስወርሰው /አስረክበው/ ለአሁኑ ክርክር መሠረት የሆነውን ቤት በስምምነት መርጠው ያስቀሩት ቤቱ በአዋጁ መሠረት የጋራ ንብረት ሆኗል የሚል ነው፡፡ ነገር ግን የአዋጁ ድንጋጌ ሲታይ ቤተሰብ ወይንም ግለሰብ አንድ ቤት እንደሚፈቀድለት እንጂ ይህ አንድ ቤት ከንብረት ሕግ አንፃር የማን



ንብረት ነው የሚለውን አይመልስም፡፡ በአጠቃላይ ከሳሽ ቤቱን በስምምነት መርጠን ይበሉ እንጂ የግል ንብረት የሆነውን የጋራ ንብረት ለማድረግ በሕግ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ በማቅረብ ያላስረዱ ስለሆነ 1ኛ ከሳሽ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

የኪራይ ክፍያን አስመልክቶ በክስ የተጠየቀውን በተመለከተም ተከሳሽ አከራይተው ሲጠቀሙ የነበረ ስለመሆኑ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ጥያቄው በአግባቡ አልቀረበም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

በመጨረሻም 2ኛ ከሳሽ በቤቱ ላይ የውርስ ድርሻ ያላቸው መሆኑ ስለተረጋገጠ 2ኛ ከሳሽና ተከሳሽ የሚስማሙ ከሆነ ቤቱ ተገምቶ አንዱ ለሌላው የግምቱን ግማሽ በመክፈል ቤቱን እንዲያስቀረው በዚህ መልኩ ስምምነት ካልተገኘ ቤቱ ተገምቶ በሐራጅ ተሸጦ የሽያጩን ውጤት ገንዘብ እኩል እኩል እንዲካፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሳሾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታው ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 08 ክልል የሚገኘውና ቁጥር 836 የሆነው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ የጋራ ሀብት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ አመልካች የተጋቡት ታህሳስ 18 ቀን 1962 ዓ.ም ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ደግሞ ሁለቱ ከመጋባታቸው በፊት በ1957 ዓ.ም በሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ የተሠራ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ አመልካች በጋብቻ ተሳስረው እያሉ በካርታ ቁጥር 31619 በአቶ አክሊሉ አጥላባቸው ስም የተመዘገበውን ቤት ገዝተው አከራይተው ሲጠቀሙ ቆይተው የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ሀብት የሚያደርገው አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ ይህንኑ በጋብቻ ጊዜ የገዙትን ቤት በትርፍነት ለመንግስት አስረክበዋል፡፡ በሌላ በኩልም ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በባንክ ብድር ተሠርቶ የነበረ ስለሆነ ብድሩ በጋብቻ ጊዜ ተከፍሎ የተጠናቀቀ ከመሆኑም በላይ ባልና ሚስቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 11/1/ መሠረት እንደ አንድ ቤተሰብ መቆጠር እንዳለባቸው ሕጉ ስለሚያስገድድ ምርጫቸው መሆኑን አሳውቀው መንግስት በትርፍነት እንዳይወርሰው በማድረግ የጋራ ሀብት አድርገውታል በማለት ነው፡፡

ተጠሪም በበኩላቸው በካርታ ቁጥር 31619 የተመዘገበውን ቤት 1ኛ አመልካችና ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ስለመግዛታቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካለማቅረባቸውም በላይ ቤቱን ከአቶ አክሊሉ አጥላባቸው ላይ ታህሳስ 16 ቀን 1965 ዓ.ም በተደረገ ውል የገዙት ሟች አቶ ኢላላ ኢበሳና አቶ ለማ ኢብሳ ናቸው፡፡ ከአቶ አክሊሉ አጥላባቸው ላይ የተገዛው ቤት በአንድ በኩል የ1ኛ አመልካችና የአቶ ኢላላ ኢብሳ በሌላ በኩል የአቶ ለማ ኢብሳ ንብረት የነበረ ሲሆን ይህን ቤት በትርፍነት ለመንግስት አስረክበዋል ቢባል እንኳ በሟች አቶ ኢላላ ኢብሳ ስም የተመዘገበውንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ግን የጋራ ንብረት ስለመደረጉ በአመልካቾች ማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በካርታ ቁጥር 31619 የተመዘገበው ቤት ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና 1ኛ አመልካች በጋብቻ ተሳስረው በነበረ ጊዜ የተገዛ ስለመሆኑ ተጠሪ አምነው ነገር ግን የተገዛው 1ኛ አመልካች ከሟች ባለቤታቸው ጋር በመሆን ሳይሆን ሟች አቶ ኢላላ ኢብሳና አቶ ለማ ኢብሳ የገዙት ነው በማለት ክርክር ቢያቀርቡም የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ሀብት



ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ይህንኑ ቤት ለመንግስት በትርፍነት ያስረከቡት 1ኛ አመልካችና ሟች ባለቤታቸው እንደነበሩ በአስረጂነት የቀረበው የመረካከቢያ ቅጽ የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በላይ ቤቱን በትርፍነት ያስረከቡት ሟች ብቻ ናቸው ቢባል እንኳን ይህ ሁኔታ የአቶ ለማ ኢብሳን የጋራ ባለሀብትነት ሊያረጋግጥ የማይችል በመሆኑ ይህ ችሎት በካርታ ቁጥር 31619 የተመዘገበው የ1ኛ አመልካችና የሟች ባለቤታቸው የነበረ መሆኑን ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በሌላ በኩልም አንድ ሰው ወይንም አንድ ቤተሰብ ከአንድ መኖሪያ ቤት በላይ በባለቤትነት መያዝ እንደማይችል በተጠቀሰው አዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 11/1/ ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ አዋጅ በወጣበት ጊዜ 1ኛ አመልካችና ሟች ባለቤታቸው አቶ ኢላላ ኢብሳ በጋብቻ ተሳስረው ይኖሩ የነበረ እንደመሆኑ መጠን ከአዋጁ አኳያ እንደ አንድ ቤተሰብ መቆጠራቸው ስለማይቀር በጋብቻ ጊዜ ካፈሩት ቤትና ከጋብቻ በፊት ከተሠራውና የሟች የግል ንብረት ከነበረው ቤት መካከል አንዱን መርጠው በትርፍነት ለመንግሥት ማስረከብ ግድ ስለሚሆን በዚሁ መሠረት በጋብቻ ጊዜ ያፈሩትን ቤት መርጠው ማስረከባቸው ሌላውን በሟች ስም ተመዝግቦ የሚገኘውንና ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት የጋራ ማድረጋቸውን እንደሚያስገነዝብ መረዳት አያዳግትም፡፡

በእርግጥ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍርዱ ላይ እንዳሰፈረው ከተጋቢዎች መሀል አንዱ የግሉ የሆነውን ቤት የጋብቻው የጋራ ንብረት ማድረግ ቢፈልግ በቀድሞውም ሆነ በአዲሱ የቤተሰብ ሕግ መሠረት የዚህ ዓይነት ስምምነት ወይንም የጋብቻ ውል ሊኖር እንደሚገባ መደንገጉን መገንዘብ ቢቻልም 1ኛ አመልካችም ሟች ባለቤታቸው በጋብቻ ጊዜ ያፈሩትን ቤት በትርፍነት ለመንግሥት ‘ 229 ኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የሟች የግል ንብረት የነበረውንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ከአዋጁ መንፈስ አኳያ ያለምንም ሌላ ተጨማሪ ስምምነት ይህ ሁኔታ በእራሱ ቤቱን የጋራ ማድረጋቸውን ስለሚያስገነዝብ የሥር ፍ/ቤቶች ለክሱ

ምክንያት የሆነው ይሄው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሟች ባለቤታቸው አይደለም በማለት የሰጡት ውሣኔ ከአዋጁ ጋር ያልተጣጣመና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41151 በታህሳስ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ክልል ቁጥር 836 የሆነው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሟች ባለቤታቸው አቶ ኢሳላ ኢብሳ የጋራ ንብረት አይደለም ማለቱ እደዚሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23027 በየካቲት 9 ቀን 1999 ዓ.ም የከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በቂርቆስ ክ/ከተማ ቀበሌ 09 ክልል የሚገኘው የቤት ቁጥር 836 የሆነው ቤት የ1ኛ አመልካችና የሟች ባለቤታቸው አቶ ኢሳላ ኢብሳ የጋራ ንብረት ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ከላይ የተጠቀሰውና የ1ኛ አመልካችና የሟች አቶ ኢሳላ ኢብሳ ቤት ተገምቶ በ1ኛ አመልካችና የሟች ወራሾች በሆኑት 2ኛ አመልካችና በተጠሪ መካከል ስምምነት ከተገኘ አንዱ ለሌላው የግምቱን ግማሽ በመክፈል ቤቱን እንዲያስቀረው ተወስኗል፡፡ በዚህ መልኩ መስማማት ካልቻሉ ቤቱ ተገምቶ በሐራጅ እንዲሸጥና የሽያጩን ገንዘብ ግማሹን 1ኛ አመልካች እንዲወስዱ ግማሹን ደግሞ 2ኛ አመልካችና ተጠሪ እኩል እንዲካፈሉ ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



የሰበር መ.ቁ. 29402

ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ ቀረበች

ተጠሪ፡- የ፤አለቃ አስመላሽ ኃይለሥላሴ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሣውን የንብረት ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በማህበራዊ ፍ/ቤት ሲሆን በዚህ ወቅት በተደረገው ክርክር ባልና ሚስቱ በጋራ ያፈሩት ቤት እንዳለ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ቤቱ የአመልካች እና የተጠሪ የጋራ ንብረት ነው በማለት ፍ/ቤቱ በአንድ በኩል የወሰነ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቤቱ የተሠራበት ቦታ የተጠሪ የግል ሀብቱ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ቦታው ለክፍፍል አይቀርብም፤ የተጠሪ የግሉ ሆኖ ይኑር በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበላቸው የበላይ ፍ/ቤቶችም ውሣኔው ስህተት የለበትም ብለዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች መጋቢት 7 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ቤቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ከተባ/ 231 ነታው ግን የተጠሪ የግል ንብረት ይሁን ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከቀረበው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ንብረት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ.47/67 ከታወጀመበት ጊዜ ጀምሮ እና በአሁኑም ጊዜ የከተማ ቦታ በግለሰቦች በርስትነት የሚያዝ አይደለም፡፡ የቦታው (መሬቱ) ባለቤት መንግሥት በመሆኑ ግለሰቦች በቦታው ላይ የመጠቀም መብት ነው የሚኖራቸው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ይህን ቦታ ወይም መሬት የእዚህኛው ወይም የዚያኛው የግል ንብረት ነው ብሎ መወሰን የማይቻል እንደሆነ ነው፡፡ በእርግጥ በቦታው ላይ የተሠራው ቤት የአንዱ ወይም የሌላው የግል ንብረት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ቤት የሚሠራው በመሬት ላይ እንደመሆኑ ቤትን ካረፈበት መሬት (ቦታ) ለይቶ (ነጥሎ) ማየት አይቻልም፡፡ በአንድ በተወሰነው መሬት (ቦታ) ላይ ቤት የሠሩ ሰዎችም በቦታው ላይ የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል ወይም እንዳላቸው ይገመታል፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምንመለከተው አመልካች እና ተጠሪ ንብረትነቱ የመንግሥት በሆነው ቦታ (መሬት) ላይ የጋራ ቤት ሠርተው ሲኖሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህ መሠረትም ቤቱ እኩል የጋራቸው ነው እስከተባለ ድረስ በቦታው (ቤቱ ባረፈበት መሬት) ላይ ባላቸው የመጠቀም መብት ልዩነት መፍጠር አይቻልም፡፡ ከፍ ሲል እንዳመለከትነውም ቤቱ ካረፈበት መሬት (ቦታ) ተነጥሎ የሚታይ ባለመሆኑ ወይም ከመሬቱ ውጪ ሊታይ ስለማይችል አመልካች ቤቱ ካረፈበት መሬት በመለስ ባለው ብቻ ነው የጋራ ባለሃብት የምትሆነው ብሎ መደምደም ትክክል አይደለም፤ ትርጉምም አየኖረውም፡፡ በሌላ አነጋገር በዚህ ድምዳሜ መሠረት አመልካች በቤቱ ላይ የእኩል መብት አላት ተብሎ ተወስኖአል ለማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ የተነሣም አመልካች የጋራ መብት ያላት በቦታው (በመሬቱ) ላይ ባረፈው ሕንፃ (ቤት) ላይ ብቻ ነው በሚል በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1. በማህበራዊ ፍ/ቤት፣በመቀጠልም በወረዳ ፍ/ቤት እና በመጨረሻም በትግራይ ብ/ክ/መ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 18601 የካቲት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች ያለምንም ልዩነት ማለትም ቤቱ ባረፈበት መሬት ላይ ያለውን የመጠቀም መብት ጨምሮ የቤቱ እኩል ባለሀብት ናት ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀም ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 30959

ታህሣሥ 01 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካቾች፡-** 1. ወሮ ተወዳጅ ገ/ሥላሴ - ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ሙሉ ገ/ሥላሴ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ዘለቀ ዘውዴ

2. አቶ አንዳላፍር ዘውዴ ጠ/ወንድወሠን ተ/ማርያም ቀረበ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች የሟች ሌ/ኮ ገ/ስላሴ በሻህ ልጆች ለመሆናቸው እንዲረጋገጥላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ ፍ/ቤቱ ተመልክቶ ልጅነታቸውን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በኋላ አመልካቾች የሟች ልጆች አለመሆናቸውን ተጠሪዎች ተቃውመው ወደ ክርክሩ ገብተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ አይቶ በአመልካቾች እና በሟች መካከል የልጅነት ሁኔታ መኖሩ ተረጋግጧል በማለት ቀድሞ የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ ተጠሪዎች ይህንን ውሣኔ በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን አከራክሮ በአመልካቾችና በሟች መካከል የልጅነት ሁኔታ የለም ሲል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡ በዚሁ ውሣኔ ላይ አመልካቾች ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኛቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም አመልካቾች የሟች ልጆች አይደሉም መባሉ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች አኳያ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ ላይ አመልካቾች የሟች ሌ/ኮ ገ/ስላሴ በሻህ ልጆች ለመሆናቸው የልጅነት ሁኔታ መኖሩ ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሠጣቸው ጥያቄ ማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ አመልካቾች የሟች ልጆች አለመሆናቸውን ተቃውመው ተከራክረዋል፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154 እና ተከታዮቹ ሥር ልጅነት የሚረጋገጥባቸው መንገዶች ተዘርዝረዋል፡፡ ልጅነት የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ፣ የልደት ምስክር ወረቀት ከሌለ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ የልጅነት ሁኔታ ከሌለ ደግሞ ተወላጅነትን በማስረዳት ማረጋገጥ እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡ ከነዚህ ሁኔታዎች ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ልጅነት የሚታወቅበት ሁኔታ ነው፡፡ በቤተሰብ ሕጉ ቁጥር 156 አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህ ሁኔታ መኖሩን ማስረዳት ከተቻለ ፍ/ቤቱ ልጁ ነው ሲል የሕግ ግምት እንደሚወስድና ይህንን ግምት ግን ልጅ ነው የተባለው ሰው ሊሆን እንደማይችል በማስረዳት ማፍረስ እንደሚችል የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 157 ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ስንመለከት ሟች አመልካቾችን እንደ ልጆቻቸው ያሳድጓቸው እንደነበር ትምህርት ቤትም አባት በመሆን እንዳስመዘገቧቸው፣ በመረዳጃ እድር ቅጽ ውስጥ ልጆች ብለው እንዳስመዘገቧቸው፣ በሠፈርም በት/ቤትም የሟች ልጆች ሆነው እንደሚታወቁ ተገንዝበናል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የልጅነት ሁኔታ የለም ያለው አመልካቾች

በጋብቻ ውስጥ ወይም ከጋብቻ ውጪ መወለዳቸው አልተገለፀም፣ ሟች አመልካቾች የሟች ልጆች እንዳልሆኑ ገልፀው የተውት ኑዛዜ አመልካቾች እንዲፀድቅ መጠየቃቸው ልጆች አለመሆናቸውን ያመኑ መሆኑን ያሣያል በማለት ነው፡፡ ነገር ግን የልጅነት ሁኔታን ለማረጋገጥ ልጁ በማኅበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት መሆኑን ከማረጋገጥ ባለፈ ልጁ በጋብቻ ውስጥ ወይም ከጋብቻ ውጪ የተወለደ ለመሆኑ ማስረዳት አስፈላጊ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሕጉ የማይጠይቀውን ተጨማሪ ሁኔታ አመልካቾች አላስረዱም በሚል የተሠጠው ውሣኔ አግባብነት የለውም፡፡

ሌላው ሟች በተውት ኑዛዜ ላይ አመልካቾች ልጆች አለመሆናቸውን መግለፃቸው በራሱ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ አይደለም፡፡ የልጅነት ሁኔታ አለመኖሩን ለማስረዳት በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 157/2/ መሠረት ልጅ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ኑዛዜውን አመልካቾቹ እንዲፀድቅ መጠየቃቸው አመልካቾች የሟች ልጆች አይደሉም ወደሚለው መደምደሚያ አያደርስም፡፡

በአጠቃላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው ፍሬ ነገር አመልካቾች የልጅነት ሁኔታ ያላቸው መሆኑን እያሳየ ሕጉ የማይጠይቀውን ተጨማሪ ሁኔታ አመልካቾች አላስረዱም በማለት የልጅነት ሁኔታ የለም በሚል የተሠጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4487 በሐምሌ 21 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 26992 በሚያዝያ 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20534 በጥር 22 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 31430



ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
ሐጐስ ወልዱ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ
ሡልጣን አባተማም

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ አዲስ አለም አከለ ቀርባለች፡፡

**ተጠሪ** ፡- የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ ተወካይ ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የጋብቻን በፍቺ መፍረስ ተከትሎ የተነሳውን የንብረት /ገንዘብ/ ክፍፍል ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው አመልካች እና ተጠሪ የንብረት ክፍፍል ያደረጉ ሲሆን፣ ከዚህ ክፍፍል በኋላ ሊስማሙ ያልቻሉት ተጠሪ በብሩንዲ በሰላም ማስከበር ተግባር ላይ ተሰማርቶ ለነበረበት ጊዜ በድጐማ መልክ ተከፍሎታል በተባለው ገንዘብ ክፍፍል ላይ ነው፡፡ አመልካች ይህ ገንዘብ የተገኘው ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት /ፀንቶ በነበረበት ጊዜ/ እስከሆነ ድረስ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ነው በማለት ስትከራከር፤ ተጠሪ ደግሞ ገንዘቡ ከደመወዝ የተለየና በድጐማ መልክ የተሰጠኝ በመሆኑ የግሌ ነው፡፡ ከባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሚደመር አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የሰማው የወረዳ ፍ/ቤት እና ይግባኙን የሰማው የከፍተኛ ፍ/ቤት ገንዘቡ የባልና ሚስቱ የጋራ ሃብት ነው በማለት የወሰኑ ሲሆን፣ ለመጨረሻ ጊዜ ይግባኙን የሰማው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ግን የተጠሪን ክርክር በመቀጠል ገንዘቡ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት የሚባል አይደለም፡፡ ለክፍፍል አይቀርብም በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 21 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን

ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በድጐማ መልክ ተገኝ የተባለው ገንዘብ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የማይሆንበት የሕግ ምክንያት አለ ወይ? የሚለውን ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካራው ገንዘብ በድጐማ መልክ ለተጠሪ የተከፈለው ጋብቻው ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ነው፡፡ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ነጥብም ከዚህ ፍሬ ነገር የሚነሳ ሆኖ መወሰን ያለበት ደግሞ አግባብ ባለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት ነው፡፡ በዚህ ረገድ አግባብ ያለው የቤተሰብ ሕግ የአማራ ብ/ክ/መ/የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀጽ 73 እንደሆነ በስር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተመልክቶአል፡፡ ባልና ሚስት ተጋብተው አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ሠርተው፣ ጥረው፣ ግረው የሚያገኙዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብቶቻቸው እንደሆኑ በተጠቀሰው አንቀጽ 73/1/ እና /2/ በግልጽ ስለመመልከቱም በፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ተገልጾአል፡፡ የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ሕጉ እንዲህ አይልም የሚል ምክንያት አልሰጠም፡፡ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው ነጥብ ገንዘቡ ባልና ሚስቱ በመረዳዳትና በመተጋገዝ በጋራ ያፈሩት ነው ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡

በበኩላችን እንደምናየው ሕጉ ግልጽ ነው፡፡ ሕጉ ለጋራ ንብረት መሠረት ይሆን ዘንድ በዋነኛነት ያስቀመጠው በጋብቻው ጊዜ /ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ/ መገኘቱን ነው፡፡ ባልና ሚስቱ በጋብቻ ተሳስረው ባሉበት ጊዜ የሚገኘው ንብረት በሁለቱም የጋራ መተጋገዝ እንደተገኘ መቆጠር እንዳለበት ሕጉ ወስኗል፡፡ ባልና ሚስቱ በተለያየ ቦታ የመገኘታቸው ጉዳይ እግምት ውስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ ባል በአንድ ቦታ፤ ሚስት ደግሞ በሌላ ቦታ ለተወሰነ ጊዜ ቢኖሩ እንኳ ሕጉ የሚገምተው ሁለቱም ለትዳራቸው እኩል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብሎ ነው፡፡ በመሆኑም ንብረቱ በሕጉ ተቀባይነት ባለው አግባብ የአንዱ ተጋቢ ወገን የግል ሃብት መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ በጋብቻው ወቅት የተገኘው ንብረት ሁሉ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው የሚሆነው፡፡



በያዝነው ጉዳይ እንደምናየውም ተጠሪ በድጐማ ተሰጠኝ የሚለው ገንዘብ የጋራ ሀብት የማይሆንበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሳም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 1046/98 ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ለተጠሪ በድጐማ መልክ ተከፈለ የተባለው ገንዘብ በባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሚካተት በመሆኑ አመልካች እና ተጠሪ እኩል ይካፈሉት ብለን ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይበለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ

የሰ/መ/ቁ. 31891

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካቾች፡-** እነ አቶ አንለይ እንየው (7 ሰዎች) ጠበቃ ፍቅሩ ታደሰ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መሬም ጡሃ ጠበቃ ውቤ ጓዴ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ የሟች አቶ ይሃ ይብሬ ሚስትና አካለመጠን ያላደረሱ ሁለት ልጆች ሞግዚትና አስተዳዳሪ ናቸው በማለት ፍ/ቤቱ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ የአሁን አመልካቾች እህት የነበሩት ወ/ሮ ጥሩዬ እንየው የተባሉት ቀርበው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት ባቀረቡት መቃወሚያ በሟች አቶ ይሃ ይብሬና በተጠሪ መካከል የነበረው ጋብቻ በእስልምና ኃይማኖት ሥርዓት መሠረት ፈርሷል፡፡ ተጠሪ ከሟች የወለዷቸውን ሁለት ልጆች ጥለው ወደ ውጭ አገር ከሄዱ ጊዜ ጀምሮ ልጆቹን በእናትነት አሳድገውም ሆነ ተንከባክበው አያውቁም፤ ልጆቹን ያሳደግኩት አመልካች ነኝ፡፡ ተጠሪ የሟች ሚስት ሳይሆኑ በሐሰተኛ ምስክር አማካይነት የተሰጣቸው የሚስትነት ማስረጃና በሚያሳድጓቸው ልጆች ስም የተሰጣቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ማስረጃ ያለአግባብ ስለሆነ እንዲመልሱ ይወሰንልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ለተጠሪ ደርሶ በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካች በተጠሪና በሟች አቶ ይሃ ይብሬ መካከል ጋብቻ መኖሩን ሳይክዱ በመቃወሚያነት ያቀረቡት ምክንያት ተጠሪ ከኢትዮጵያ ውጭ ለ12 ዓመት ያህል ከኖሩ በኋላ አሁን የተመለሱት አቶ ይሃ ይብሬ ከሞቱ በኋላ ነው ከሚል



በስተቀር ከሟች ጋር የነበራቸው ጋብቻ በሕግ አግባብ የፈረሰ ስለመሆኑ ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ በሌላ በኩል ሟችና ተጠሪ በባልና ሚስትነት አብረው እየኖሩ 2 ልጆችን ወልደዋል፡፡ ተጠሪ ለወለዷቸው ልጆች ሞግዚት ልሁን ብለው መጠየቃቸውና ሞግዚትነታቸው በፍ/ቤት ማሳወጃቸው ጥፋተኛ አያደርጋቸውም፡፡ ስለዚህ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በተጠሪና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ ከ12 ዓመት በፊት ፈርሷል ቢሉም በፍ/ቤት ውሳኔ ስለመፍረሱ ያቀረቡት ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ለ12 ዓመት ተለያይተው መኖራቸው ብቻ በራሱ ጋብቻውን ሊያፈርሰው የማይችል በመሆኑ አቤቱታው በአግባቡ ያልቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠው ውሳኔ ሊሰረዝ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች ወራሾች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሮ መወሰን ተገቢ መሆኑን በማመኑ በዚሁ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በተጠሪና በሟች አቶ ይሃ ይብሬ መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ አልፈረሰም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነት አለውን? የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረውም በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች በተጠሪና በሟች አቶ ይሃ ይብሬ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል በማለት ያቀረቡትን ክርክር ፍ/ቤቱ ሳይቀበለው የቀረው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን

ማስረዳት የሚቻለው በፍ/ቤት የተሰጠን ውሳኔ በማቅረብ እንጂ በምስክር ፍቺን ማስረዳት ስለማይቻል አመልካች ፍቺውን በምስክር ላስረዳ ያሉት በአግባቡ ባለመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

ሆኖም ግን ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14290 በሰጠው ውሳኔ በባልና ሚስት መካከል ያለ ጋብቻ በፍ/ቤት በተሰጠ የፍቺ ውሳኔ ፈርሷል ባይባልም የተጋቢዎች ተለያይቶ ለረጅም ጊዜ መኖር በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መሥርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ ተቋርጧል ሊባል ይችላል በማለት የሕግ ትርጉም የሰጠበት ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች የጋብቻ መፍረስ ከፍርድ ውሳኔ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሊረጋገጥ አይችልም በማለት የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከዚሁ አኳያም በዚህ ጉዳይ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ተጠሪና ሟች አቶ ይሃ ይብሬ ለ12 ዓመታት ተለያይተው እንደኖሩ በዚህ ጊዜም ተጠሪ በውጭ አገር በመኖር ላይ እንዳሉ ሌላ ባል አግብተው እንደነበር አመልካች ተከራክረው ይህንኑ ክርክራቸውን በምስክር ለማስረዳት መጠየቃቸውን ይህ ችሎት ከመገንዘቡም በላይ ተጠሪ በውጭ አገር በነበሩ ጊዜም ሟች አቶ ይሃ ይብሬና አመልካች ጋብቻ የፈጸሙ ስለመሆናቸውም ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በተጠሪና በሟች መካከል የነበረው ጋብቻ ይህ ሰበር ችሎት አስቀድሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ተቋርጧል ወይንስ አልተቋረጠም የሚለውን ለመወሰን ከፍ ብሎ በአመልካች የተጠቀሰው ፍሬ ነገር ማለትም ተጠሪና ሟች አቶ ይሃ ይብሬ ለ12 ዓመታት ተለያይተው ስለመኖራቸው በዚህም ጊዜ ውስጥ የባልና የሚስት ዓይነት ግንኙነት ያልነበራቸው ስለመሆኑና ተጠሪም በውጭ አገር በነበሩ ጊዜ ሌላ ባል ስለማግባታቸው በአጠቃላይ በዚህ ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት የባልና ሚስት ግንኙነት ያልነበራቸው ስለመሆኑ ሊያስረዱ የሚችሉት አመልካች የቆጠሯቸው ምስክሮች ተሰምተው ለጉዳዩ እልባት ሊሰጠው ይገባ እንደነበር ይህ ችሎት ለመረዳት ችሏል፡፡



ስለሆነም አመልካች በዚህ ረገድ የቆጠሯቸው ምስክሮች ሳይሰሙ ጋብቻው በፍርድ ውሳኔ ስላልፈረሰ የጸና ነው በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08924 መጋቢት 8 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38179 ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከላይ በፍርዱ ላይ በተመለከተው መሰረት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ. 31946

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው ቀርባለች

**ተጠሪ፡-** ተመስገን ደሣለኝ ቀርቧል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጋብቻ ውልን የሚመለከት ነው፡፡

የግራ ቀኙ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኂላ የቀጠለውን የንብረት ክፍፍል በተመለከተ አመልካች ጥያቄያቸውን ለጃቢ ጠህናን ወረዳ ፍ/ቤት አቅርበዋል ተጠሪም በመሃከላችን የጋብቻ ውል አለ በዚህም መሠረት አመልካችን ያገባኂት በአመት 120.00 /መቶ ሃያ/ ብር ልከፍላት ልብስ ከዛው ከደሞዟ ሊታሰብ የሕክምና ወጪ ልሸፍን እንጂ በእኩል ባለመብት እንድትሆን አልተስማማሁም በማለት አመልካች ንብረት ለመካፈል ያቀረቡትን ጥያቄ ተቃውመዋል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ወረዳ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቶ የጋብቻ ውሉ ሕጋዊ አይደለም በማለት አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ተቀብሎ ንብረቶቹን የግራ ቀኙን የጋራ ስለሆኑ እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ የወረዳ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ስህተት የለውም በማለት የይግባኝ ቅሬታውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ በመቀጠል ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሁለተኛ ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ግራ ቀኙ የንብረት ግንኙነታቸውን በተመለከተ ተጠሪ ለአመልካች በወር ከሚያገኘው ገቢ ውስጥ ለዓመት ብር 120.00 (መቶ ሃያ) ሊከፍላት ከዚህ ውጪ ሌላ ንብረት ግንኙነት እንደማይኖር መስማማታቸው ሕጉን አይቃረንም በማለት ተጠሪ አመልካች ሳትገባ የሠራውን ሆነ ከገባች ወዲህ ታድሷል የተባለውን ቤት እንድትካፈል መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ አመልካች ቤቱን ልትካፈል አይገባም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል ላይ ተጠሪ ለአመልካች በዓመት ብር 120.00 (መቶ ሃያ) ሊከፍላትና ከዚህ ውጪ ሌላ የንብረት ግንኙነት እንደማይኖር መስማማታቸው ሕግን አይቃረንም መባሉን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በማድረጉ ተጠሪ ቀርበው መልሣቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ እንደተረዳነው ግራ ቀኙ ባልና ሚስት መሆናቸው ያልተካደ ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪው ነጥብ የንብረት ክፍፍል ነው፡፡ አመልካች በጋብቻ ጊዜ የተገኘ ንብረት የግል እስካልተባለ የጋራ ነው ሲሉ የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተጋቢዎቹ የንብረት ግንኙነታቸውን በተመለከተ ሊስማሙ ስለሚችሉ በዚሁ መሠረት የተስማሙና የጋብቻ ውሉም ሕግን የሚቃረን ባለመሆኑ የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ስህተት የለውም ብለዋል፡፡

የአ/ብ/ክ/መ የቤተሰብ ሕግ ልክ እንደ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ተጋቢዎቹ የንብረት ግንኙነታቸውን አስመልክቶ ሊስማሙ እንደሚችሉ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የንብረት ግንኑነታቸውን በመሰላቸው መንገድ ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ስምምነቱን በሚወስኑበት ጊዜ መሠረታዊ የእኩልነት መብትን በሚጥስ መልክ ሊፈፀም አይገባውም፡፡ በሕገ- መንግሥቱ አንቀፅ 34(1) ሴቶች በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ግዜ እኩል መብት እንዳላቸው ያመለከተ ሲሆን አንቀጽ 35/2/ም ቢሆን ሴቶች በጋብቻ ከወንዶች ጋራ እኩል መብት እንዳላቸው ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም በጋብቻ ዘመን በተፈራ ንብረት ላይ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እኩል መብት እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ ባደረጉት የጋብቻ ውል ተጠሪ ለአመልካች በዓመት ብር 120.00

እንደሚከፍላትና ከዚህ ውጭ አመልካች በጋራ ንብረታቸው ላይ ምንም ዓይነት መብት እንዳይኖራት ያደረጉት ስምምነት ከላይ የተጠቀሰውን የሕገመንግሥቱን የእኩልነት መብት ድንጋጌን የሚፃረር ነው፡፡ማንኛውም ሕግ ወይንም ልማዳዊ አሠራር ከሕገመንግሥቱ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት እንደሌለው በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ላይ ተመልክቷል፡፡

ከዚህም ሌላ አንድ የውል ግዴታ በሕግ አግባብነት ባልተቋቋመ ጊዜ በዚህ ውል መሠረት እንዲፈጽም ጥያቄ የቀረበለት ወገን ውሉ የማይረጋ ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ይህንን ውል አልፈጽምም ማለት እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1809 የተመለከተ ሲሆን አመልካችም ከተጠሪ ጋር የተደረገው ውል ሕግን የሚፃረር ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የተከራከሩ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ስምምነት መሠረት ሊገደዱ የማይገባ ሆኖ ሣለ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመሻር የአመልካችን የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11110 ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ከላይ እንደተጠቀሰው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ ንብረት ሊካፈሉ ይገባል ተብሎ በጃቢ ጣህናን ወረዳ ፍ/ቤት በ14.4.99 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የምዕራብ ጎጃም ዞን ከ/ፍ/ቤት ይግባኙ አያስቀርብም በማለት በጥር 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 32130

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ሒሩት መለሠ
መድኀን ኪሮስ
አሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** እነ እማዋይሽ ካሣ /6 ሰዎች/ ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አስቴር አህመድ - ጠበቃው ቀርቧል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ አባትነት እንዲታወቅ የቀረበን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ እናታቸው በአመልካቾች ቤት በሠራተኛነት ተቀጥረው ሲሠሩ ከሟች አህመድ ይማም ጋር ከጋብቻ ውጪ በነበራቸው ግንኙነት የተወለዱ መሆኑና ሟችም ልጅነታቸውን ተቀብለው ሲረዱዋቸውና ሲንከባከቧቸው የነበረ በመሆኑ አባትነታቸው እንዲታወቅላቸው አመልክተዋል፡፡ አመልካቾችም ሟች ከእነርሱ በቀር ሌላ ልጅ የሌላቸው መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ ልጅነታቸውን ለማወቅ የሚበቃ አይደለም በማለት ጥያቄያቸውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኙን ያየው ፍ/ቤት የቀረበው ማስረጃ ሟች ተጠሪን በመንከባከብና በማስተማሩ ወይም በማሣደጉ ላይ እንደ አባት የተሣተፈ ለመሆኑ የሚያረጋግጥና ተጠሪ በሟች ስም ተመዝግበው በስሙ ትጠራ እንደነበር ተረጋግጧል በማለት ተጠሪ ከሟች አህመድ ይማም የተወለደች ልጅ ናት በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካቾች ቅሬታ በአጭሩ በአ/ብ/ክመ/ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154/ሠ/

መሠረት አንድን ሰው አባት ብሎ ለመወሰን ልጁን ለማስተማርና ለማሣደግ የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ማድረጉና ይህ እንክብካቤ እና እርዳታ የተደረገው ተንከባካቢው ከወላጅነት ስሜት በመነጫ አኳኋን አባት ነኝ ከሚል እምነት የተነሣ መሆኑ መረጋገጥ ያስፈልገዋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሟች በርህራሄ እና ከሃይማኖታዊ ሥርዓት አፈፃፀም የተነሳ ተጠሪን ከመርዳት ውጪ ልጄ ናት ብሎ የረዳበት ጊዜ እንደሌለ ተረጋግጦ እያለ አባት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ትርጉም ተጠሪ የሟች አህመድ ይማም ልጅ መሆኗ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መረጋግጡን ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል በማለቱ ተጠሪ ቀርበው መልስ ሠጥተዋል፡፡ በመልሳቸውም ሟች ተጠሪን እየተንከባከቡ ያሣደጉት በበጎ አድራጎት መንፈስ ሳይሆን የወለዷት ልጅ መሆንዋን በመግለጽ እንደሆነና ገንዘብ ይልኩላት የነበረውም በአባትነት መንፈስ መሆኑ ስለተረጋገጠ ውሣኔው ስህተት የለውም ብለዋል፡፡

ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተጠሪ ጥያቄ ሟች አቶ አህመድ ይማም አባታቸው መሆናቸው እንዲረጋገጥ የቀረበ ነው፡፡ የአ/ብ/ክ/መ/ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሟች የተጠሪ አባት ናቸው የሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 154/ሐ/ እና 154/ሠ/ መሠረት ሟች ተጠሪን በማሣደግ እንደአባት ተሣትፈዋል በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ለውሣኔው መሠረት ያደረገው አንቀጽ 154/ሠ/ አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ በማስተማር ወይም በማሣደጉ ላይ እንደ አባት በመሆን የተሣተፈ እንደሆነ አባት ተብሎ በፍርድ ሊወሰን ይችላል፡፡ ይህ የክልሉ ድንጋጌ ከፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ምንም ልዩነት የሌለው መሆኑንም ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ አባት ነው ለመባል ሊረጋገጥ የሚገባው ፍሬ ነገር ምንድነው የሚለውን ማየቱ ጠቃሚ ነው? ድንጌጋው በግልጽ እንደሚያመለክተው አንድን ሰው አባት ነው ለማሠኘት ይኸው ሰው ልጁን ሲንከባከብ ሲያስተምር ወይም በማሣደጉ ሂደት ሲሣተፍ የነበረ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ነገር ግን እንክብካቤውንና እርዳታውን ማድረጉ በራሱ ሰውየውን አባት አያሠኘውም፡፡ ምክንያቱም ይህ እንክብካቤና እርዳታ ከርህራሔ እና ከሰብአዊነት ስሜት በመነጨም ሊደረግ የሚችል በመሆኑ ነው፡፡ ግለሰቡ አባት ነው ወደሚለው መደምደሚያ ለመድረስ ይህ እንክብካቤና እርዳታ አባት ነኝ ከሚል እምነትና ስሜት የመነጨና እንደ አባት በመሆን የተደረገ መሆኑም ጭምር ሊረጋገጥ ይገባዋል፡፡ ከዚህም በላይ እንክብካቤውን ሲያደረግ የነበረው ሰው ከእናትየው ጋር ልጅ ለመውለድ የሚያስችል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑም ሊረጋገጥ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም ከቀረበው ማስረጃ በእናትየውና አባት ነህ በሚባለው ሰው መሃከል ልጁን ለመካድ የሚያስችል ግንኙነት ሊኖር ይችላል የሚል እምነት የሚያሳድር ቅርበት መኖሩ እንዲሁም አባት ነህ የተባለው ሰው እርዳታውንና እንክብካቤውን ያደረገው እንደ አባት በመሆን መሆኑ ካልተረጋገጠ እርዳታ በማድረጉ ብቻ አባት ነው ወደሚለው መደምደሚያ መሄዱ የሕጉን አላማ የተከተለ አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ስንመለከት የተጠሪ እናት ከሟች እናትና አባት ቤት ተቀጥራ ስትሠራ ከሟች መውለዷን ሟች የነገራቸው መሆኑንና ሟች አንዳንዴ ገንዘብና ልብስ ይረዳት የነበረ መሆኑን በሚኒስትሪና በማትሪክ ካርዶች በሟች ስም ትጠራ የነበረ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህም ፍሬ ነገር ሟች ተጠሪ ልጄ ናት ብሎ ነግሮናል እንዲሁም አንዳንዴ ገንዘብ ይሰጣት ነበር ልብስም ያሠፋላት ነበር ከማለት ውጪ ይህንኑ እርዳታ አባት ነኝ በሚል እምነትና ስሜት ይፈጽሙ እንደነበር በሟችና በተጠሪ እናት መሀከል ተጠሪ ልትወለድ የሚያስችል ቅርበት የነበረው ግንኙነት መኖሩን አያረጋግጥም፡፡ በመሆኑም ሟች ተጠሪን አንዳንዴ መርዳታቸው ብቻ አባት ናቸው፡፡ ወደሚለው መደምደሚያ አያደርስም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በትምህርት ቤት በሟች ስም መጠራታቸው ወይም መመዝገባቸው ብቻ ሟች የተጠሪ አባት ናቸው አያሰኝም፡፡

በአጠቃላይ የአ/ብ/ክ/መ/ ሚች አህመድ ይማም የተጠሪ አባት ናቸው በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የአ/ብ/ክ/መ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 1050/98 ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07151 በሐምሌ 26 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 33126

ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ የዝና ተስፋሁን ቀረበች

ተጠሪ፡- መምህር ጥሩአየሁ እውነቱ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ጋብቻ አለ ወይስ የለም በሚል ጭብጥ ላይ ተመሥርቶ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች ስትሆን በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተችው ከ1972 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሳስረን ለ25 ዓመት ኖረናል፣ በዚህ ጊዜም አምስት ልጆች ወልደናል፣ ተከሣሽ ግን በመካከላችን የተመሠረተውን የጋብቻ ግንኙነት እንደሌለ በመቁጠር ግዴታውን ሊወጣ ስላልቻል ፍ/ቤቱ ተከሣሽን አስቀርቦ በመጠየቅ ተገቢው ውሣኔ ይሰጠኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በአንድ በኩል ከአመልካች ጋር በአንድ ቤት ለ25 ዓመት ያክል አብረው መኖራቸው እና በዚህ ጊዜ ውስጥ አምስት ልጆች መውለዳቸውን ሲያምን፤ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በሠራተኛነት የቀጠራት እንጂ ሚስቱ እንዳልሆነች፣ በመሃከላቸው የተመሠረተ ጋብቻም እንደሌለ በመግለጽ ክዶ ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በኋላም ፍ/ቤቱ በሁለቱም በኩል የቀረበውን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተመሠረተ ጋብቻ የለም፡፡ ባልና ሚስት አይደሉም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ

የቀረበላቸው የበላይ ፍ/ቤቶችም ውሣኔውን አጽንተዋል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መስከረም 12 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራት ግንኙነት የባልና ሚስት ሁኔታን አያሣይም የመባሉንና አመልካች በ2ኛ ደረጃ ያነሣችው ከጋበቻ ውጪ አብሮ የመኖርን መነሻ ያደረገ ክርክርም እንደዚሁ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም እነዚህን ነጥቦች ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጡትን ውሣኔዎች በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ አመልካች በወረዳ ፍ/ቤት ክስ የመሠረተችው የተጠሪ ሚስት ነኝ፤ በመሃከላችን የጋብቻ ግንኙነት አለ በማለት ቢሆንም፤ ሚስት አይደለሽም በማለት ፍ/ቤቱ ከወሰነ በኂላ ከጋብቻ ውጪ አብሮ መኖርን መሠረት ያደረገ የንብረት ክፍፍል  ውሣኔ እንዲሰጥላት ጭምር በመከራከር ዋነኛ ጉዳዩን በይግባኝ የሰሙት ፍ/ቤቶችም በዚህ ነጥብ ጭምር ውሣኔ መስጠታቸውን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ሌላው ከተሰጡት ውሣኔዎች መገንዘብ የቻልነው ፍ/ቤቶቹ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የጋብቻ ግንኙነት የለም ለማለት የቻሉት ክርክሩን ከቀረቡላቸው ማስረጃዎች ጋር አገናዝበው ከመረመሩና ካመዛዘኑ በኂላ እንደሆነ ነው፡፡

በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ በማስረጃ አመዛዘን ረገድ ስህተት ፈጽመዋል ለማለት የምንችልበት ምክንያት ስለሌለ ጋብቻን በሚመለከት አመልካች ያቀረበችውን አቤቱታ አልተቀበልንም፡፡

ጋብቻ አለ ወይስ የለም የሚለውን ነጥብ በተመለከተ የቀረበውን ክርክር በዚህ ሁኔታ ካለፍን ቀጥለን የምንመለከተው ጋብቻ ሳይፈፀም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች እና ተጠሪ በአንድ ቤት ለ25 (ሃያ አምስት)



ዓመት ያክል አብረው ከመኖራቸውም በላይ፤ በዚህ ጊዜም አምስት ልጆችን ወልደዋል፡፡ ተጠሪም ይህን በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠውን ሃቅ የሚቀበል ቢሆንም፤ በሌላ በኩል ግን ከአሠሪና ሠራተኛ ያለፈ ግንኙነት የለንም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ይህም ሆኖ ግን እሱ እንደሚለው በሠራተኛነትም ደመወዝ እየከፈላት ስለመቆየቱ አላስረዳም፤ በዚህ መልክም አልተከራከረም፡፡ ክርክሩን በይግባኝ ሰምቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤትም ሲሆን፣ አመልካች የተጠሪ የቤት ሠራተኛ ናት ብሎ አልደመደመም፡፡ ውሣኔውን የሰጠው የአመልካች ምስክሮች ጋብቻ ስለመፈፀሙ አላስረዱም፤ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት ሆነው አብረው ስለመኖራቸውም በማስረጃ አልተረጋገጠም ማለት እንደሆነ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ በሰማው በደብረማርቆስ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በአመልካች ተቆጥረው ከተሰሙት ምስክሮች አንዱ የአመልካች እና የተጠሪ ትልቁ ልጅ እንደሆነና እሱም በሰጠው ምስክርነት አባትና እናቱ ባልና ሚስት ናቸው ብሎ እንደሚያምን ማስረዳቱን ከወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ ተመልክተናል፡፡ እንደምንመለከተው ተጠሪ አመልካችን ከሃያ አምስት ዓመት በፊት በቤት ሠራተኛነት ቀጥሬያታለሁ ቢልም፤ ለሃያ አምስት ዓመት ያክል አብረው የኖሩት ግን እሱ ከሚለው በእጅጉ በተለየ ሁኔታ ነው፡፡ አብረው ለብዙ ዓመታት መኖራቸው ብቻ ሣይሆን አምስት ልጆች ወልደው በጋራ ሲያሣድጉም የመቆየታቸው ሁኔታ ሲታይ በጋብቻ ተሣስረው ከሚኖሩት ወንድና ሴት ተለይተው የሚታዩ አይመስሉም፡፡ ትልቁ ልጃቸው እንደባልና ሚስት አድርጎ የሚያያቸው መሆኑን ለፍ/ቤቱ ያስረዳውም ከዚህ በመነሣት እንደሆነ መገመቱ የሚያስቸግር አይደለም፡፡ በበኩላችን እንደምናየው የአመልካች እና የተጠሪ አብሮ የመኖር ሁኔታ በፌዴራሉ መንግሥት የቤተሰብ ሕግም ሆነ በአማራ ብ/ክ/መ/ የቤተሰብ ሕግ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብኖ መኖርን በተመለከተ የተቀመጡትን መስፈርቶች በሚገባ የሚያሟላ ነው፡፡ ሲጠቃለል በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የጋብቻ ግንኙነት አለ ለማለት ባይቻለም፤ ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት በመሆን አብረው መኖራቸው ግን

የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ በመሆኑም ከጋብቻ ውጪ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የሚያሣይ ሁኔታ በሚል በስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ትክክል አይደለም፡፡ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 09277 ሐምሌ 9 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች እና ተጠሪ ጋብቻ ሣይፈጽሙ እንደባልና ሚስት ሆነው አብረው ኖረዋል ብለን ወስነናል፡፡ ይህ በንብረት ግንኙነታቸው በኩል የሚኖረው ውጤት በክልሉ ሕግ ጉዳዩ በተጀመረበት ወረዳ ፍ/ቤት ቀጥሎ ይታይ ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 33411

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አለቃ ኪሮስ ገብሩ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የአፈፃፃም ክርክር ሲሆን፣ በዋናው ጉዳይ ግራ ቀኙ ጋብቻቸውን በስምምነት ለማፍረስ ተዋውለው ስምምነታቸውን በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. በት/ብ/ክ/መ/ ሕንጣሎ ዋጅራት ወረዳ ጣቢያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት በውሣኔ እንዲያፀድቀው አድርገዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች ተጠሪው በስምምነቱ መሠረት የጋራ ንብረት ክፍፍሉን ሊፈጽሙ ፈቃደኛ አልሆኑም በሚል በሚያዝያ 2 ቀን 1999 ዓ.ም. በት/ብ/ክ/መ/ ኢንጣሎ ወረዳ ጣቢያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት የጋራ ያሏቸውን ንብረቶች በመዘርዘር ያካፍሉኝ ሲሉ በተጠሪው ላይ የአፈፃፀም ክስ መሥርተዋል፡፡

የአሁን ተጠሪ /የሥር የአፈፃፀም ተከሣሽ/ በሚያዝያ 13 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ የአሁን አመልካች በክሣቸው የዘረዘሯቸውን የጋራ ንብረቶች ለማካፈል ፈቃደኛ መሆናቸውን ገልፀው በክሱ ከተዘረዘሩት ንብረቶች መካከል የወፍጮ ድርጅት ያካፍለኝ ለተባለው ፀጋዬ ገብሩ ከተባሉት ግለሰብ በ10,000 ብር የገዛነው ቢሆንም ስመ ንብረቱ ያልተዛወረ የግዢ ውሉም ያልፀድቀ በመሆኑ ላካፍላት አልችልም ስለዚህ ወይ ባለቤትነት ስም እስኪዛወር ትጠብቅ ወይ የግዢ ገንዘቡን ግማሽ ብር 5000 (አምስት ሺ.ህ) ትውሰድ ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የአፈፃፀም ክርክሩ የቀረበለት የጣብያ ደጀን ማ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ጉዳት መርምሮ በግንቦት 11 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ፣ ቀደም ሲል ቀርቦ በፀደቀው የፍቺ ስምምነት መሠረት በጣብያ ደጀን ዓዲኾሎ የሚገኘው የወፍጮ ድርጅት የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት መሆኑ መግልጽ የሠፈረ እና ይህንኑ ድርጅት እኩል ለመካፈል የተስማሙ በመሆኑ ግራ ቀኙ የወፍጮ ድርጅቱን ከነ ሙሉ መሣሪያዎቹ እኩል ይካፈሉ ሲል ወስኗል።

የጣብያ ደጀን ማ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኙት የአሁን ተጠሪ ቅሬታቸውን ለህንጣሎ ወረዳ ፍ/ቤት በይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤት ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል። በመቀጠል ተጠሪ ቅሬታቸውን ለት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቅርበዋል።

የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የተጠሪን አቤቱታ ተቀብሎ አመልካችን በማስቀረብ ግራ ቀኙን ያከራከረ ሲሆን በነሐሴ 4 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የክርክሩ መነሻ የሆነው መፍጮ በአሁን ተጠሪ ወንድም በአቶ ፀጋዬ ገብሩ ስም እንደሚታወቅ የአሁን አመልካች አልካዱም። ንብረትነቱ በአሁን ተጠሪ ስም እንደተላለፈም የቀረበ ማስረጃ የለም፣ በመሆኑም ለዚህ ወፍጮ ግዢ ገንዘብ እንደተከፈለ እንጂ ውል ተፈጽሞ ወደ ስማቸው እንደተላለፈ እስካልተደረጋገጠ የጋራ ተብሎ ወደ ተከራካሪዎቹ የትዳር ንብረት ክፍፍል ሊገባ አይችልም በሚል ግራ ቀኙ ለወፍጮ ግዢ የተከፈለውን ብር 10,000 የጋራ በመሆኑ ገንዘቡን እኩል ይካፈሉት ሲል የስር ፍ/ቤችን ውሣኔ ሽሯል።

ይህ መዝገብ ለዚህ ችሎት የቀረበውም የት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪው ለአመልካች ወፍጮ የተገዛበትን ዋጋ ብር 10,000 ያካፈሏቸው ሲል የሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች በጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ መሠረት ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘት ሲጠቃለል በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. ባደረግነውና በፍ/ቤት በፀደቀው የፍቺ ስምምነት የወፍጮ ድርጅቱን እኩል ለመካፈል በግልጽ ተስማምተን፣ የስሙ



አለመዛወር የንብረት ክፍፍሉን ተግባራዊነት የሚያግድ ሆኖ ሣለ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ከተከራካሪዎች ባልቀረቡለት ጥያቄ የግዢ ውሉ እንደሚፈርስ አድርጎ ለግዢ የተከፈለውን ገንዘብ እንድንካፈል መወሰኑ አላግባብ በመሆኑ ይሻር የሚል ነው።

ይህም ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ የክርክሩ ምክንያት የሆነው ወፍጮ ድርጅት ባልና ሚስቱ /አመልካችና ተጠሪ/ ቢገዙትም በስማቸው አልዞረም በሚል የጋራ ሀብት አይደለም ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ጭብጥ በመያዝ ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን በጽሑፍ አከራክሯል። እኛም የግራ ቀኙን ክርክርና የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔዎች መርምረናል። እንደመረመርነውም ተጋቢዎቹ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን የወፍጮ ድርጅት በተመለከተ በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም. ተደርጎ በፍ/ቤት በፀደቀው የፍቺ ስምምነታቸው ላይ ክፍፍሉን አስመልክቶ በግልጽ ፈቃዳቸውን ሰጥተው ተስማምተዋል። ይህን ስምምነት ግራ ቀኙ ያልካዱት በሌላ ስምምነት ያልቀየሩት ወይም ያላሻሻሉት እና በፍ/ቤትም የፀደቀ ከመሆኑ አንፃር ይህ ስምምነት በግራ ቀኙ መልካም ፈቃድ እስካልተሻረ ድረስ ተጋቢዎቹ በስምምነቱ ቃል የማይገደዱበት ምክንያት አይኖርም። በሌላ በኩል በማንኛውም የክርክር ደረጃ ቀርቦ በአከራካሪው ንብረት ላይ መብት አለኝ፤ የጋራ ሀብት ተብሎ ለግራ ቀኙ ሊካፈል አይገባም በሚል በ3ኛ ወገን የቀረበ ክርክር የለም። ተጠሪው አከራካሪ የሆነው ንብረት በ3ኛ ወገን ስም የሚገኝ ነው ይበሉ እንጂ የተጠቀሰውን 3ኛ ወገን ወክለው ስለ ንብረቱ ለመከራከር መብት ያላቸው መሆኑን አላመለከቱም፣ እንዲሁም ንብረቱ በእጁ አይገኝም በሚል ክደው ያቀረቡት መከራከሪያ የለም። የወፍጮ ድርጅቱ ክፍፍል ላይ ያጋጠመ እክል ለመኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በፍቺ ስምምነቱ መሠረት አይፈፀምም መባሉ ተገቢ አይደለም። በአጠቃላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 373/2/ የአፈፃፀም ፍ/ቤት በዋናው ፍርድ የታዘዘውን ከመፈፀም ውጪ ባለቀው ጉዳይ እንደ አዲስ ማከራከር እንደማይኖርበት በግልጽ ተደንግጎ እያለ የት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ከፍቺ ስምመነቱ ቃልና ስምምነቱን ካፀደቀው ውሣኔ ይዘት ውጭ

የወፍጮ ድርጅቱ የግራ ቀኙ የጋራ ሃብት አይደለም፤ ለግዢው ለ3ኛ ወገን የተከፈለውን ብር 10,000 ተጠሪው ለአመልካች እኩሌታውን ይክፈሏቸው ሲል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1/ የክርክሩ ምክንያት የሆነው በት/ብ/ክ/መ/ በጣቢያ ደጀን ኦዲኾሎ የሚገኘው የወፍጮ ድርጅት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት በመሆኑ በሕዳር 15 ቀን 1999 ዓ.ም ባደረጉት ስምምነት መሠረት ክፍፍሉ ይፈፀም፡፡

2/ የወፍጮ ድርጅቱን በስምምነት ማካፈል ካልተቻለ የወፍጮ ድርጅቱ ተገምቶ አንደኛው ወገን የግምቱን ግማሽ ገንዘብ ከፍሎ ድርጅቱን ለራሱ ያስቀር፡፡

3/ አንደኛው ወገን የግምቱን ግማሽ ለሌላኛው ከፍሎ ድርጅቱን ማስቀረት ካልቻለ የወፍጮ ድርጅቱ በሐራጅ ተሸጦ ግራ ቀኙ የሽያጩን ገንዘብ እኩል ይካፈሉ፡፡

4/ የት/ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20701 በነሐሴ 4 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

5/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 33440

ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም - ጠበቃ ሰለሞን ገ/ሚካኤል

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ ገብረስላሴ - ጠበቃ አያሌው ካሕሳይን

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በቅድሚያ የአሁን ተጠሪ የሚች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ ነኝ በማለት የወራሽነት ማስረጃ ካገኙ በኋላ የአሁን አመልካች እዚሁ ፍ/ቤት ቀርበው ሚች እህቴ ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ ሳትወልድ የሞተችና ከተጠሪውም ጋር ምንም ዓይነት ዝምድና የሌላቸው ስለሆነ ተጠሪ የሚች ወራሽ ነው ተብሎ በዚህ መዝገብ የተሰጠው ማስረጃ ሊሰረዝ ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ልጅነትን በተመለከተ የከተማ ነክ ፍ/ቤት ለመወሰን በሕግ ሥልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ ተጠሪ የሚች የወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅነትን በተመለከተ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ውሣኔ በተገኘ ጊዜ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ልጅነት የልደት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ማስረዳት እንደሚቻል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 154 ላይ የተመለከተ ሲሆን ከዚህ ድንጋጌ ማንኛውም ፍ/ቤት የሕግ ግምት በመውሰድ ልጅነትን ማረጋገጥ የሚችል በመሆኑ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት አቤቱታው ይቅረብ ሊባል

የሚችለውም የልደት የምስክር ወረቀት ሳይቀርብ አመልካች ልጅ መሆኑን በሁኔታና በሰው ምስክር ለማስረዳት በጠየቀ ጊዜ ነው ካለ በኋላ ይግባኝ ባይ የአሁን ተጠሪ የሟች የወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ ስለመሆኑ በልደት የምስክር ወረቀት የተረጋገጠ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት የይግባኝ ባይ ልጅነት በቅድሚያ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ሊረጋገጥ ይገባል በማለት አቤቱታውን ሳይቀረበል መቅረቱ በአግባቡ ስላልሆነ ይግባኝ ባይ የሟች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ ከሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ ስለሚሆን መ/ሰጭ ሊወርሱ ስለማይችሉ በመ/ቁ. 5205/98 ኅዳር 1 ቀን 1998 ዓ.ም. ወራሽ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ ተሠርዟል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን አመልካች በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው ለከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ ቢያቀርቡም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት የሕግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በተጠሪ ልጅነት ላይ ተመስርቶ የቀረበውን ክርክር የከተማ ነክ ይ/ሰሚ ፍ/ቤት ተመልክቶ ውሣኔ መስጠቱ በሕግ በተሰጠው ሥልጣን ሥር የሚሸፈን ስለመሆኑ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የሰበር አቤቱታውም ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው ልጅነት የሚረጋገጥበት ዋናው ማስረጃ የልደት ምስክር ወረቀት እንደሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 154 ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህ ማለት ግን የልደት ምስክር ወረቀት ክርክር ሊነሳበት የማይችል ሙሉ እምነት ሊጣልበት የሚችል /Conclusive/ ማስረጃ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡ አመልካችም ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ልጅ መሆኔን ያረጋግጥልኛል በማለት ያቀረቡት የልደት ምስክር ወረቀት በተጭበረበረ መንገድ የተገኘ



ከመሆኑም በላይ ሟች በሕይወት ዘመናቸው ልጅ አልወለዱም በማለት ተከራክረዋል፡፡ በተጠሪ ልጅነት ላይ በዚህ መልኩ ክርክር የተነሳበት ከሆነም የተጠሪ ልጅነት ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ክርክር ተደርጎበት ውሣኔ የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡

በዚሁ መሠረትም የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር የተነሳበት የተጠሪ ልጅነት ጉዳይ በቅድሚያ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት ዕልባት ሊሰጠው ይገባል ማለቱ አግባብነት ያለው ሆኖ ሳለ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግን የልደት ምስክር ወረቀቱ በማስረጃ ሊስተባበል እንደማይችል በመቁጠር የተጠሪ ልጅነት ጉዳይ ከዚህ በኋላ ክርክር ሊደረግበት አይችልም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ መሻሩ እንደዚሁም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ይህንን ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03902 በሰኔ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 04714 በሐምሌ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 4979/97 በታህሳስ 4 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ብይን ጸንቷል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 33875

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

መድኀን ኪሮስ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ የሻረግ አባትኩን ቀረቡ።

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ መሠረት አድማሱ ቀረቡ።

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

**ፍ ር ድ**

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁንዋ ተጠሪ የአቶ ኪዳነወርቅ ብርቁ ሚስት ስለመሆናቸው መጋቢት 16 ቀን 1996 ዓ.ም. በመ/ቁ. 12185 በዚሁ ፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቁራ ምድብ 1ኛ ፍትሐብሔር ችሎት የተወሰነላቸው ሲሆን የአሁንዋ አመልካች የሟች አቶ ኪዳነወርቅ ብርቁ ሚስት እኔ ነኝ፤ ወ/ሮ መሠረት አድማሱ የሟች ሠራተኛ እንጂ ሚስት አልነበሩም በማለት ተቃውመዋል።

ተቃውሞው የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ወ/ሮ መሠረት አድማሱ አቅርበው ያሰሙዋቸው ምስክሮች አቶ ኪዳነወርቅ ብርቁ ድግስ ደግሰው ለተጠሪው ሕዝብ ወ/ሮ መሠረት አድማሱ ሚስቴ ናት፤ ከእንግዲህ ባልና ሚስት ነን ብለው መናገራቸውንና ከዚያም በኋላ አብረው በመኖር ልጆች መውለዳቸውን ያስረዱ በመሆኑና ተቃዋሚዋ ያሰሙዋቸው ምስክሮች ደግሞ የሰጡት ምስክርነት ይህን የሚያፈርስ ባለመሆኑ ተቃውሞው ተቀባይነት የለውም በማለት ቀደም ብሎ የተሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 360/2/ መሠረት አጽንቷል።



የአሁንዋ አመልካች ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል። የፌ/ከ/ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የወ/ሮ መሠረት አድማሱ ምስክሮች ሟች ድግስ ደግሰው ባልና ሚስት ነን ብለው ተናግረዋል ብለው ቢያስረዱም ይህ አባባል በጽሁፍ በሽማግሌዎች ፊት እስካልተደረገ ጊዜ ድረስ ተደረገ የተባለው ጋብቻ በባሕላዊ ጋብቻ ሥር አይወድቅም። የሥር ፍ/ቤት የወ/ሮ መሠረት አድማሱን ሚስትነት የወሰነው ጋብቻው በሰርተፍኬት ወይም በትዳር ሁኔታ ሳይረጋገጥ ነው በማለት ውሳኔውን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል።

የአሁንዋ ተጠሪ ደግሞ በፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ካዳመጠ በኋላ ይግባኝ ባይዋ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያሰሙዋቸው ምስክሮች ሟች ድግስ ደግሰው ሰው ጠርተው በሕዝብ ፊት ከእንግዲህ ከወ/ሮ መሠረት አድማሱ ጋር ባልና ሚስት ነን በማለት በመናገር የጋብቻውን መመሥረት ያበሰሩና አብረው በመኖርም ልጆች መውለዳቸውን ያስረዱ በመሆኑ የጋብቻው መኖር በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 97/1/ መሠረት በሁኔታ ተረጋግጧል። ይህ ሁኔታ ደግሞ በመልስ ሰጭ ማስረጃ በአንቀጽ 97/2/ መሠረት አልተስተባበለም። የሥር ፍ/ቤት ለባሕላዊ ጋብቻ የሰጠው ትርጉምም የተሳሳተ ነው በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመሻር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል።

የአሁንዋ አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠውን ፍርድ በመቃወም ነው። አመልካች በአቤቱታቸው ያካተቱት ቅሬታም ተጠሪ የሟች ሠራተኛ እንጂ ሚስት አይደሉም። ሕጋዊ ሚስት እኔው ነኝ። የተሰሙት የተጠሪ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት በሟችና በተጠሪ መካከል ባሕላዊ ጋብቻ ስለመመስረቱ አያስረዳም። ወቅቱ በ1976 ዓ.ም. ቦታውም አዲስ አበባ በመሆኑ በዚህ ጊዜ የሚፈፀም ባሕላዊ ጋብቻ በሽማግሌዎች ፊትና በጽሁፍ ሰፍሮ የግራ ቀኙንና የሽማግሌዎችን ፊርማ ባረፈበት ሁኔታ መሆን

ነበረበት፡፡ በሚችና በተጠሪዋ መካከል ተደረገ የተባለው ጋብቻ ይህን የሚያሟላ አይደለም፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የመልስ ሰጭ ምስክሮች በድግስ ወቅት ሚች ሚስቴ ናት ሲሉ ሰምተናል በማለት የሰጡትን ምስክርነት ብቻ መነሻ በማድረግ የእኔ ምስክሮች ተጠሪዋ ሚስት ሳይሆኑ የሚች ሠራተኛ ናቸው ደመወዝም ይቀበሉ ነበር በማለት ያስረዱትን ባለመቀበል ተጠሪዋ የሚች ሚስት ስለመሆናቸው በሁኔታ ተረጋግጧል በማለት የሰጡት ውሣኔ በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 4 እና 97/2/ የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪዋ ባሰሙዋቸው ምስክሮች ከሚች ጋር በባሕላዊ ሥነ ሥርዓት ጋብቻ የፈፀሙ ስለመሆኑ አላስረዱም እንጂ ፍ/ቤቱ አስረድተዋል እንኳን ቢል ተጠሪዋ ከ1977 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. ድረስ የሚች ኪዳነወርቅ ብርቄ የጽዳት ሠራተኛ እንደነበሩ የሚያሳይ ማስረጃ መቅረቡ እንዲሁም ሚች ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ጥር ወር 1994 ዓ.ም. ሲሆን ተጠሪዋ ከ1980 ዓ.ም. ጀምሮ ከሚች በመለየት አቶ ሽፈራው መንክር የተባሉትን ሰው አግብተው ሁለት ልጆች ወልደዋል፡፡ ከዚህ ሁኔታም ተጠሪዋ ከሚች ተለያይተው ሚች ከዚህ ዓለም እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ የየራሳቸውን ኑሮ ይኖሩ የነበረ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ባለበት ተጠሪዋ የሚች ሚስት ናቸው መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት እና ፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሮ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እንዲፀና እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ ደግሞ በሰጡት መልስ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሚስትነቴን ያረጋገጠልኝ ጥቅምት 15 ቀን 1976 ዓ.ም. ዘመድ ጠርተን ድግስ ደግሰንና ጋብዘን ከዚህ በኋላ ባልና ሚስት ነን ተጋብተናል በማለት መጋባታችንን በማሳወቅ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት መፈፀማችንን ከዚህ በኋላም ባልና ሚስት ሆነን ልጅ መውለዳችንን በማስረጃ በመረጋገጡ ነው፡፡ አመልካች በወቅቱ ተጠሪ የሚች ባለቤት አይደለችም ሠራተኛው ናት ከማለት በስተቀር በማስረጃ ያረጋገጥኩትን የጋብቻ ሁኔታ ስላለመኖሩ አላስረዱም፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት



የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሣኔ የሻረው ባሕላዊ ጋብቻን በሽማግሌና በፊርማ ሥነ ሥርዓት መከናወን አለበት የሚል በጣም ጠባብ ትርጉም በመስጠት ነው፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ትርጉም ሲሽር ሕጉ በአማራጭ ያስቀመጣቸውን ሁኔታዎች ከግምት ያስገባ አይደለም፡፡ ከዚህም አልፎ በጽሑፍና በውል አባት ሽማግሌ ፊት መደረግ አለበት የሚለው ድምዳሜ የአ/አበባ ከተማ ማኅበረሰብ ሊወክል የሚችል ባሕላዊ አመራር ነው ብሎ ለመደምደም በቂ መነሻ አይሆንም በማለት ያስቀመጠው ትንታኔ የሕጉን መንፈስ በትክክል የሚገልጽ በመሆኑ ውሣኔው አንዳችም የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተጠሪ መልስ ሰጥተዋል፡፡

በተጨማሪ ተጠሪ ከሚች ጋር የተዋወቅነውና የትዳር ጥያቄም ቀርቦልኝ የተጋባነው ሚች በሚያንቀሳቅሱት የባሕል ሕክምና ድርጅት ውስጥ በረዳት ሐኪምነት ተቀጥሬ በነበረበት ወቅት ስለመሆኑ አልክድም ብለዋል፡፡ ሆኖም ከሚች ጋር ከተጋባን በኋላ ተለያይተን ኖረን አናውቅም፡፡ ሚች ከመሞታቸው በፊት ተለያይተው ተጠሪዋ ሌላ ባል አግብታ ነበር የተባለው በስር ፍ/ቤት ያልቀረበና በማስረጃም ያልተረጋገጠ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከሚች ባለቤቴ የወለድኩትን ልጅ ያሳደግነውና በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 19 ቀበሌ 49 ክልል የቤት ቁጥር 008 እና 009 የሆነውን ድርጅትና የመኖሪያ ቤት ያፈራነው በጋራ ነው፡፡ በሰበር መ/ቁ. 20938 የተሰጠው ውሣኔም አሁን ከቀረበው ክርክር ጋር ተዛማጅነትና ተመሣሣይነት የለውም፡፡

በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ምንም የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ውሣኔው እንዲጸናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ከመዝገቡ ጋር አያይዘዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ ተጠሪዋ የጋብቻ ሁኔታን አረጋግጠዋል ወይስ አላረጋገጡም? አመልካችስ የጋብቻ ሁኔታውን አስተባብለዋል ወይስ አላስተባበሉም? የሚሉት ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ግራ ቀኙ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባካሄዱት ክርክር የተጠሪ ምስክሮች ያስረዱት ሚችና ተጠሪዋ ድግስ ደግሰው ሰው

ጠርተው ሟች ከዛሬ ጀምሮ ከተጠሪዋ ጋር ባልና ሚስት ሆነዋል ብለው ማሳወቃቸውን ከዚያም በኋላ ልጅ ወልደው አብረው የኖሩ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ማስረጃ ደግሞ ጋብቻው በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 4 መሠረት በባሕላዊ ሁኔታ የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በአንፃሩ የአሁንዋ አመልካች ያሰሙዋቸው ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት ተጠሪዋ የሟች ሠራተኛ መሆናቸውንና ከሟች ጋር ስለመጋባታቸው ግን የሚያውቁ መሆናቸውን ነው ያስረዱት፡፡ መጀመሪያ ተጋብተው ግን ደግሞ ሟች ከመሞታቸው በፊት የተፋቱ ስለመሆኑም እንዲመሰክሩ አልተጠየቁም፡፡ እነሱም ይህን አስመልክተው ያሉት ነገር የለም፡፡ ይህ የአመልካች ምስክሮች ምስክርነት ደግሞ ተጠሪዋ ከሟች ጋር የትዳር ጋብቻ ያላቸው መሆኑን በቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 97/1/ ያስረዱትን የሚያስተባብል አይደለም፡፡ ይህን መሠረት በማድረግ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በተጠሪዋና በሟች መካከል ጋብቻ ነበር በማለት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት አልነበረም፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም በሰጠው ውሣኔ በአሁንዋ ተጠሪና በሟች መካከል ባሕላዊ ጋብቻ ስለመመስረቱ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚፈፀም ባሕላዊ ጋብቻ በሽማግሌ ፊት በጽሑፍና በፊርማ ነው የሚከናወነው በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መንደርደሪያ የሆነውን የሕግ ትርጉምም ተቀባይነት የለውም ሲል በውሣኔው ላይ ያሰፈረውን ትንታኔ ስንመለከትም ውሣኔውና ለውሣኔው መሠረት ተደርጎ የተወሰደው ትንታኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪዋ ከሟች ጋር ፈፀምኩት የሚሉትን ባሕላዊ ጋብቻ ስለመመሥረቱ ለማስረዳት የሚጠበቅባቸው የአመሠራረቱን ሁኔታ ማስረዳት ነው፡፡ በምስክሮቻቸው ያስረዱትም ጋብቻውን ለሌሎች ለማሳወቅ ታስቦ ድግስ መዘጋጀቱንና ሰዎች መጠራታቸውን የተጠሩት ሰዎች ከተገኙ በኋላ ሟች ከእንዲህ ከወ/ሮ መሠረት አድማሱ ጋር ባልና ሚስት ሆነናል ዕወቁልን በማለት የተናገሩ መሆናቸውን ከዚያም በመቀጠል ባልና ሚስት ሆነው አብረው መኖራቸውንና ልጅም መውለዳቸውን ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ጋብቻ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥም የሚፈፀም ነው፡፡ በዚህ



ሁኔታ ባሕላዊ ጋብቻ እንዳይፈፀምም የሚከለክል ምክንያት የለም፡፡ ተጋቢዎች ከፈለጉ ጋብቻውን በጽሑፍ በመፈራረም ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡ ከፈለጉ ደግሞ በቃል ለማኅበረሰቡ እወቁልን ብለው በመናገር ሊመሰርቱት ይችላሉ፡፡

በመሆኑም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ምንም ዓይነት የሕግ ስህተት ያለበት ባለመሆኑ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26737 ጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አበለት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 34149

መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ ወርቁ መንገሻ ጠበቃ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አለሙ በቀለ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 5947 ኅዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ሊታረም ይገባዋል በማለት አመልካች ኅዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪው ጠጅነሽ በቀለ ጋር ጥቅምት 1 ቀን 1994 ዓ.ም በሕጋዊ ጋብቻ ተጋብተን ስንኖር ዋጋዬ አለሙ የተባለች ልጅ ወልደናል፡፡ አሁን ልጅቱን እንዳሣድግ ብጠይቃቸው ተከሳሾች እንቢ ስላሉኝ ልጄን ተረክቤ እንዳሣድግ ይደረግልኝ በማለት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበ ሲሆን አመልካቾች በተከሳሽነት ቀርበው የሕጻኗ ስም አዳነች በቀለ እንደሆነና እናቷ በሞት ስትለይ ግልጽ ኑዛዜ የተወች በመሆኑ ሕፃኗም የከሳሽ ልጅ ስላልሆነች ክሱ እንዲሰረዝ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካቾች የሟች ወ/ሮ ጠጅነሽ በቀለ እህቶች መሆናቸውን በመግለጽ እናንተ የከሳሽን አባትነት ለመቃወም መብት የላችሁም በማለት ሕፃኗን ለተጠሪው እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሃብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ዘግቶታል፡፡ አመልካቾች ከሟች ጋር በሕጋዊ ጋብቻ ለመኖሩና ልጅቷም በጋብቻው ወቅት ወይም ጋብቻ ከፈረሰ ከሶስት መቶ ቀን በፊት የተወለደች መሆኑን የሚያስረዳ እንዲሁም ፣ ሕፃኗ የበቀለ አበበ ልጅ ለመሆኗ እኛ ማስረጃ አቅርበን እያለ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 147 በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ይታረምልኝ በማለት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪው መጥሪያው ደርሶት ያልቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ብይን ተሰጥቷል፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ጉዳይ አባትነትን በመካድ የቀረበ ክስ ባለመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የጠቀሳቸው የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ ድንጋጌዎች አግባብነት የላቸውም፡፡ ተጠሪው ልጄ ናት የሚላት ዋጋዬ ዓለሙ ሟች ጠጅነሽ በቀለ ጋር በጋብቻ በነበሩበት ወቅት የተወለደች መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪው ልጄን ያስረክበኝ ብሎ ለመጠየቅ በመጀመሪያ ከልጅቱ እናት ወ/ሮ ጠጅነሽ በቀለ ጋር በጋብቻ ተጣምረው ይኖሩ እንደነበር፣ በጋብቻ እየኖሩ እያለ ልጅቱ የተወለደተች መሆኑን በማስረጃ የማስረዳትና የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው እነዚህን ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ያስረዱልኛል ብሎ የቆጠራቸውን ምስክሮች አልሰማም፡፡ ተጠሪው የልጅቱ አባት መሆኑን በማስረጃ ካላስረዳ የልጅቱ አክስት የሆኑ ተጠሪዎች ማንም አባት ነኝ ብሎ ለመጣ ሰው ልጅቱን አሳልፈው እንዲሰጡ የሚያስገድዳቸው የሕግ ድንግጌ የለም፡፡ የልጅቱ አባት ያልሆነ ሰው አባቷ ነኝ ብሎ ሲቀርብም የልጅቱ አባት አይደለም፣ ስለዚህ በአግባቡ አያሳድጋትም የሚለውን ምክንያት አንስተው እንዳይከራከሩ የአማራ ክልል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 147 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 አይገድባቸውም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ሣይሰማ ተጠሪው የሕፃኗ አባት ስለሆነ አስረክቡ በማለት

የሰጠው ውሣኔና የጠቅላይ ፍርድ ቤቱም ውሣኔው የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 5947 ህዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ውሣኔዎች ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ በመስማት የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ አመልካች ለራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 34387

ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- አቶ ከበደ ሙሔ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 51375 ግንቦት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 32029 ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ በሕጋዊ ጋብቻ ተሣሥረው ለበርካታ ዓመታት በባልና ሚስትነት የኖሩ ሲሆን፣ ጋብቻቸውን በፍች አፍርሰዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የጋራ ንብረታቸውን ለመካፈል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የጋራ ንብረት ዝርዝር አቅርበው ትዕዛዝ ተሰጥቶበታል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ተጠሪ እስከ ጥር 29 ቀን 1998 ዓ.ም. አመልካች የተቀበሉት የጡረታ አበል ታስቦ እንዲከፈለኝ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ጥያቄ ማቅረባቸው ነው፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የጡረታ አበል ይሰጠኝ ጥያቄ የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት በከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው፣ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች የሚያገኙት የጡረታ አበል የጋራ ንብረት ነው

በማለት የጡረታና ማኅበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ከግንቦት ወር 1999 ጀምሮ ግማሽ የጡረታ አበል ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኙን የሰማው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለም በማለት ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ አመልካች አሁን የማገኘው አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ብር የጡረታ ገንዘብ ወታደር ቤት እያለሁ በአይኔ ላይ ጉዳት ደርሶብኝ በቦርድ በመውጣቴ የማገኘው ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት የባልና የሚስት የጋራ ሀብት ነው በማለት ተጠሪዋ ግማሹን እንድትወስድ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት ያመለከተ ሲሆን ተጠሪዋ በበኩሏ የጡረታ አበሉ በትዳራችን ጊዜ የተጠራቀመ በመሆኑ ግማሹን እንድወስድ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለች ተከራክራለች፡፡

በሥር የቀረበው ክርክርና በሰበር ግራ ቀኙ የሚያነሱት የመከራከሪያ ነጥብ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪዋ ከግንቦት 1999 ጀምሮ ግማሽ የጡረታ አበል ልታገኝ ይገባታል በማለት የሰጠው ውሣኔ ሕግን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ነጥብ አይተናል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔውን በሚሰጥበት ወቅት የተከተለውን ሥርዓት ስንመረምረው፣ ተጠሪ የጡረታ አበል፣ ታስቦ ሊሰጠኝ ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት እስከ ጥር 29 ቀን 1998 ዓ.ም. አመልካች የወሰዱትን የጡረታ አበል መሆኑን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በውሣነው በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ የጠየቁትን ጋብቻቸው ከመፍረሱ በፊት ተለያይተው እያለ አመልካች ተቀብለው የተጠቀሙበት የጡረታ አበል ታስቦ እንዲሰጣቸው እንጂ ጋብቻው ከፈረሰ በኂላ አመልካች ከሚያገኙት የጡረታ አበል ግማሹን እንዲወስንላቸው በሥር ፍርድ ቤት አልጠየቁም፡፡ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያላቀረቡትንና በሥር ያልተከራከሩበትን አዲስ ነገር በይግባኝ ደረጃ ለማንሣትና ለመጠየቅ



እንደማይችሉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 328 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በሥር ያልጠየቁትና ያልተከራከሩትን ጉዳይ በማንሣት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ ከግንቦት ወር 1999 ዓ.ም. ጀምሮ አመልካች ከሚያገኙት ጡረታ ግማሹን ሊከፍላት ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ግድፈት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የሚያገኙት የጡረታ አበል፣ የመንግሥት ሠራተኛ በነበሩበት ሠዓት ከደመወዛቸው ተቆርጦ የተጠራቀመ ነው የሚለው አባባል መሠረታዊ ስህተት ያለበትና የጡረታ አበሉ መንግሥት በኩል ተቀማጭ የሚሆን ገንዘብ ያለ በመሆኑ ለአንድ ሠራተኛም የጡረታ አበል የሚከፈለው እድሜው በገፋበትና ጉልበቱ በደከመበት ጊዜ መጦሪያ የሚሆነውና ለመኖር የሚያስፈልገውን ወጭ በከፊልም ቢሆን በመሸፈንና ለማኅበራዊ ደህንነቱ ዋስትና ለመስጠት መንግሥት ካለው የማኅበራዊ ደህንነትና ዋስትና ፖሊሲ የመነጨ በመሆኑ እንደማንኛውም ገቢ የጋራ ንብረት ነው የሚባል አይደለም፡፡ የአንድ ሰው የጡረታ አበል በማናቸውም መልኩ በዕዳ ሊያዝ ወይም ሊታገድና ሊቀነስ እንደማይችል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 404/ሠ/ በግልጽ የሚደነግግ ሲሆን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን በመተላለፍ አመልካች የሚከፈለው የጡረታ አበል ግማሹ እየተቆረጠ ለተጠሪ እንዲከፈል የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 32029 ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 51375 ግንቦት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማሻሻል የወሰናቸው ሌሎች ጉዳዮች የፀኑ ሲሆን የጡረታ አበልን አስመልክቶ የሰጠው ውሣኔ ብቻ ተሽሯል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራን በተመለከተ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4. አመልካች ከሚያገኘው የጡረታ አበል ተጠሪ ግማሹ ይሰጠኝ ካለ የመጠየቅና የመካፈል መብት የላትም በማለት ወስነናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 35376

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ዳንኤል አሰፋ ቀርቧል፡፡

2. ሕፃን አልአዛር አሰፋ ወኪል ቀርቧል

**ተጠሪ፡-** ወ/ሪት ሔለን ውበቱ ቀርባለች

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሣሽ በመሆን፣ አውራሽ እናቴ ወ/ሮ ስንቄ አስፋው ከአቶ አሠፋ መለሰ ጋር ተጋብተው ሲኖሩ በጋራ ያፈሩት በወ/19 ቀ/55 የሚገኝ ቁጥሩ 223 ቤት እና በውስጡ የሚገኙ የአውራሼ የግልና የጋራ ንብረቶችን የአሁኑ 1ኛ አመልካች አላግባብ ለብቻው ይዞ እየተጠቀመ በመሆኑ የድርሻዬን ያካፍለኝ ቤቱንም በማከራየት ያገኘውን ጥቅም ያካፍለኝ ስትል ታህሣሥ 21 ቀን 1995 ዓ.ም ጽፋ ባቀረበችው ክስ መነሻነት ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፈቀደለት መሠረት ወደ ክርክሩ የገባው 2ኛ አመልካች ከ1ኛው አመልካች ጋር በተመሣሣይ መከራከሪያዎች ለክሱ መልስ የሰጡ ሲሆን የመልሣቸውም ይዘት የተጠቀሰውን ቤት አቶ አሠፋ መለሰ ሥራው ተጠናቅቆ የተረከቡት ከተጠሪዋ አውራሽ ጋር ከመጋባታቸው በፊት ጥር 8 ቀን 1981 ዓ.ም ሲሆን ከተጠሪ አውራሽ ጋር ጋብቻ የፈፀሙት ግንቦት 11 ቀን 1983 ዓ.ም በመሆኑ ይህ ቤት የአቶ አሰፋ መለሰ የግል ቤት እንጂ ተጠሪዋን የውርስ ጥያቄ ለማቅረብ መብት የሚሰጥ የጋራ ሀብት አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ ለቀረበው መልስ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የመልስ መልሱም ይዘት ይህ ቤት የተሠራው በባንክ ብድር በመሆኑ ብድሩ በትዳር ወቅት ከአቶ አሠፋ መለሰ ደሞዝ ለባንክ ሲከፈል ቆይቶ እዳው ተከፍሎ ሣይጠናቀቅ አቶ አሠፋ መለሰ በመሞታቸው መ/ቤታቸው በገባላቸው የሕይወት ኢንሹራንስ መሠረት ተከፋዩ ገንዘብ ለእዳው መክፈያ ውሎ እዳው ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ ተጠናቋል፡፡ ስለዚህ ቤቱ የጋራ ንብረት ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ፣ ከጋብቻ በፊት /ከግንቦት 11/1983 ዓ.ም/ ለቤቱ መሥሪያ የከፈሉት የአቶ አሠፋ መለሰ የግል ንብረታቸው ሲሆን ከዚህ ቀን በኋላ ላለው በተከፈለው መጠን ግን ቤቱ የሁለቱም የሟቾች የጋራ ሀብት በመሆኑ ሁለቱ በግልና በጋራ በከፈሉት ገንዘብ ስሌት መሠረት ቤቱ የግልና የጋራ ሐብታቸው ነው፣ ስለዚህ ቤቱን በዚህ የድርሻ ስሌት መሠረት ግራ ቀኙ ይከፋፈሉት በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኙት የአሁን አመልካቾች ቅሬታቸውን በይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ጥቅምት 17 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ደሞዝ የባልና ሚስት የጋራ ሐብት ከመሆኑ አንፃር ሟች አቶ አሠፋ መለሰ የሚያገኙትን ደሞዝ ለቤት ውስጥ ፍጆታ ማዋል ሲገባቸው ይህንን ሣያደርጉ ከጋብቻ በፊት አስቀድሞ በይዞታቸው ውስጥ ያደረጉትንና የግል ንብረታቸው ለሆነው ቤታቸው እዳ መክፈያ ደሞዛቸውን በማዋላቸው ምክንያት በከፈሉት ልክ ግማሹ ተሠልቶ የጋራ ሐብት ተካፋይ ለሆኑት ወ/ሮ ስንቂ አስፋው ወራሽ /የአሁን ተጠሪ/ እንዲከፈል በማለት ወስኗል፡፡

ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት በማቅረባቸው የፌ/ጠ/ፍ/ቤት አመልካቾቹን አስጠርቶ ግራ ቀኙን አከራክሮ ካበቃ በኋላ ኅዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ደግሞ፣



የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 63 የግል ነው ተብሎ ያልተለየ ንብረት እንኳን የጋራ እንደሆነ እንደሚገመት እየደነገገ በዚህ ጉዳይ ግን የቤቱ እዳ በአብዛኛው ባልና ሚስቱ በጋብቻው ወቅት የጋራቸው በሆነው ደሞዝ መከፈሉ እየተረጋገጠ ብድሩ ከጋብቻ በፊት በመገኘቱ ብቻና ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የመ/ሰጭ /የአሁን አመልካቾች/ አባት ከደሞዛቸው ስለከፈሉ ቤቱ የግላቸው ነው መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

የዚህ መዝገብ መከፈት ምክንያት የሆነው የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም አመልካቾች ጽፈው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ መሠረት ነው፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የአመልካቾችን አቤተታ ተመልክቶ፣ በዚህ ጉዳይ የአመልካቾቹ አባት የሠሩት ቤት እዳው ተከፍሎ ያለቀው ከተጠሪዋ እናት ጋር በጋብቻ ላይ እያሉ ነው በሚል ተጠሪ የእናቷን ድርሻ የቤቱን ግማሽ ልታገኝ ይገባል ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አካሂደዋል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ቤቱ የጋራ ነው ሲል ለመወሰን የቻለው ቤቱ የተሠራው ከባንክ በተገኘ ብድር በመሆኑ እዳው ሲከፈል የነበረው ከአመልካች አባት ደሞዝ በመሆኑ እና ይህ ደሞዝ የጋራ ገንዘብ በመሆኑ ቤቱ የተሠራው የጋራቸው በሆነው ደሞዝ ነው በሚል መንደርደሪያ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ በመሠረቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 57 ባል ወይም ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ወቅት በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የግል ሆነው ይቀራሉ ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ጉዳይ የተጠሪ አውራሽ እናት እና የአመልካች አባት ጋብቻቸውን የፈፀሙት ግንቦት 11 ቀን 1983 ዓ.ም ሲሆን የአመልካቾች አባት የቤቱ ግንባታ ተጠናቆ የተረከቡት ጥር 8 ቀን 1981 ዓ.ም ለመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ አቶ አሰፋ መለሰ ከጋብቻው አስቀድሞ የቤቱ ባለሀብት የሆኑ ሲሆን በወቅቱ ቤቱ የተሠራበት የባንክ እዳ መኖሩ

ባለሐብትነታቸውን አያስቀረውም፡፡ በሌላ አነጋገር አቶ አሠፋ መለሰ ባለዕዳነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቤቱ ባለሐብት ሆነዋል ማለት ነው፡፡ በአንፃሩ ደግሞ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62/1 ባልና ሚስቱ በጋብቻ ወቅት ከግል ጥረታቸው የሚያገኟቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሐብት እንደሚሆኑ ያመለክታል፡፡ ከዚህ አኳያ ከጋብቻ በኋላ ለባንክ እዳ መክፈያ ሲውል የቆየው የአቶ አሠፋ መለሰ ደመወዝ የባልና ሚስቱ የጋራ ገንዘብ ለመሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 70/1/ መሠረት ደግሞ ከባል ወይም ከሚስት የሚጠየቅ ዕዳ በተቀዳሚነት ከባለእዳው ተጋቢ የግል ሐብት መከፈል እንደሚባው ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ የአመልካቾቹ አባት ለግል ቤታቸው ማሠሪያ ከባንክ የተከፈለ የግል እዳቸውን ለመወጣት የጋራ ገንዘብ ከሆነው ከደሞዛቸው ክፍያ መፈፀማቸውን ተገንዝበናል፡፡ የአመልካቾች አባት ይህንን መፈፀማቸው በተጠሪዋ እናት የጋራ ባለገንዘብነት መብት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጥቅማቸውንም የሚቀንስ ተግባር በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የአመልካቾች አባት የተጠሪዋ እናት ባጡት ጥቅም ልክ ሊክሷቸው ይገባል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የይግባኝ ችሎት ሣያነሣው ያለፈው ግራ ቀኙን ግን ያከራከረ ነጥብ አቶ አሠፋ መለሰ ሲሞቱ መ/ቤታቸው በገባላቸው የሕይወት ኢንሹራንስ መሠረት በኢትዮጵያ መድን ድርጅት ተከፋይ የሆነው ለባንክ እዳ መክፈያ የዋለውን ገንዘብ አስመልክቶ የተነሣው ክርክር ነው፡፡ በመሠረቱ የህይወት ኢንሹራንስ ተጠቃሚን አስመልክቶ በተደነገገው የን/ሕ/ቁ. 701/2/ሀ/ ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም እንኳ የኢንሹራንስ ውሉን የፈረመው ሰው ባል ወይም ሚስት ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚ ተብለው እንደሚቆጠሩ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጉዳይ አቶ አሠፋ መለሰ ሲሞቱ ተከፋይ ከሆነው የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ የተጠሪዋ እናት ግማሽ ተጠቃሚ ለመሆናቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ገንዘብ ደግሞ ለባንክ እዳ ክፍያ የዋለ ስለመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ የኢንሹራንስ ገንዘብም ለአቶ አሠፋ መለሰ የግል እዳ መክፈያ መሆኑ የወ/ሮ



ስንቄ አስፋውን ጥቅም የጎዳ በመሆኑ የዚህ ገንዘብ ግማሽ የወ/ሮ ስንቄ ድርሻ በመሆኑ ሊመለስላቸው ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የግል ዕዳው በጋራ ገንዘቡ መከፈሉ የግል የሆነውን ሐብት የጋራ ንብረት ያደርገዋል የሚል ድንጋጌ ባለመኖሩ ሊተካ የሚገባው የወ/ሮ ስንቄ አስፋው ድርሻ የሆነው በጋብቻ ውስጥ ሣሉ ከአቶ አሰፋ መለሰ ደሞዝ ተከፋይ የሆነው ገንዘብ እና የኢንሹራንስ ገንዘብ ግማሽ ብቻ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የወ/ሮ ስንቄ አስፋው ወራሽ የሆኑት ተጠሪዋ ብቻ ሣይሆኑ በዚህ መዝገብ 2ኛ አመልካች የሆነው ሕፃን አልዓዛር አስፋውም ጭምር በመሆኑ ለወ/ሮ ስንቄ አስፋው ድርሻ ውስጥ ተጠሪዋ ሊያገኙ የሚገባው ግማሹን ብቻ መሆኑ ሊሠመርበት ይገባል፡፡ ይህም ማለት በጋብቻ ወቅት ከአቶ አሰፋ ደሞዝ ለቤቱ እዳ ለባንክ የተከፈለው ገንዘብ እና የመድን ድርጅት ዕዳውን ለመጨረስ የከፈለው የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ተደምሮ የድምሩ አራተኛ እጅ /25%/ ለተጠሪዋ ተከፍሎ አራተኛው እጅ ደግሞ /25%/ ለ2ኛው አመልካች ሊከፈል ይገባል ብለን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 8460 የካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27682 ኀዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው ብለናል፡፡ ስለዚህ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ ተጠሪዋ በጋብቻው ወቅት ከአቶ አሰፋ መለሰ ደሞዝ ለቤቱ ዕዳ ለባንክ የተከፈለው ገንዘብ እና የመድን ድርጅት እዳውን ለመጨረስ የከፈለው የሕይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ተደምሮ የድምሩ አንድ አራተኛ /25%/ ይከፈላቸው፡፡ አከራካሪው በወዳ 19 ቀበሌ 55 የሚገኘው ቁጥሩ 223 የሆነው ቤት ግን የአቶ አሠፋ መለሰ የግል ሐብት ነው ብለን ወስነናል፡፡

3/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29899 ጥቅምት 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

4/ ከዚህ ችሎት ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

5/ ግራ ቀኙ የዚህን ፍ/ቤት ወጪ በየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰበር መ/ቁ. 23389

ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አክ/ማኅበር - ጠበቃ ኃይሉ አስምር ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- እነ ባህሩ አብርሃም /12 ሰዎች/ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመ/ቁ 08449 ላይ በታህሣሥ 27 ቀን 1997 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 37119 ላይ በሕዳር 27 ቀን 1998 ለዋለው ችሎት ብይኑን በማፅናቱ አመልካች የካቲት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ባቀረበው ማመልከቻ በስር ፍ/ቤቶች የተፈፀመው የሕግ ስህተት እንዲታረም በመጠየቁ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ የማኅበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ሊመሰርቱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ ምን እንደሚመስል ለማጣራት ሲል ቅሬታው ለተጠሪዎች ደርሶ ታህሣሥ 19 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ቀርበው በጠበቃቸው አማካይነት የቃል ክርክር አድርጓል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ክስ ሲመሰርቱ ተጠሪዎች የአክስዮን ማኅበር አስተዳዳሪዎች ሆነው ከደንብ ውጪ በአክስዮን ማኅበሩ ከተሰራው ሕንፃ ውስጥ የግንባር ሱቆችን በተደረገው ግልጽ ያልሆነ ስብሰባ ያሳለፉት ውሣኔና የወሰዱት

አስተዳደራዊ ውሣኔ ከደንቡ ውጪ ስለሆነ እንዲታገድና እንዲፈርስ የሚል አቤቱታ አቅርበው ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ተጠሪዎችን እንደማይመለከትና እንደማያስከስሳቸው፣ ያስከስሳቸዋል ቢባልም እንኳ በን/ህ/ቁጥር 365/1/ መሠረት በተጠሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚቻለው ማኅበሩ እንጂ አመልካቾች ሊሆኑ እንደማይችሉ በመቃወማቸው ፍ/ቤቱም ክርክራቸውን በመስማት አመልካቾች በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 ሥር የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ሳያሟሉ በተጠሪዎች ላይ ክስ መመሥረት አይችሉም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

በዚህ ችሎትም የታየው መሠረታዊ ጉዳይ አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ በቀጥታ ክስ መመሥረት ይችላሉ ወይ የሚለው የሕግ ጥያቄ ነው፡፡ በንግድ ሕግ አንቀጽ 364 እስከ 367 በተደነገገው መሠረት የአክስዮን ማኀበር አስተዳዳሪዎች ሀላፊነት ለአክስዮን ማኀበሩ አበዳሪዎች፣ ለአክሲዮን ማኀበሩ ባለድርሻ አባላት ወይም ለሦስተኛ ወገን ሊሆን እንደሚችል ተመልክቷል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ላይ ተጠሪዎች የአመልካቾችን መብት በሚጎዳ መልኩ የሰሩ ስለሆነ ሃላፊነት አለባቸው፣ የሰሩትም ሥራ ሊፈርስ ይገባል የሚል ክስ የቀረበባቸው መሆኑ በሥር ፍ/ቤት መዝገብ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የበታች ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረገው የሕግ አንቀጽ የንግድ ሕጉ ቁጥር 365 ቅድመ ሁኔታዎች አልተሟሉም የሚል ነው፡፡ ሆኖም በዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የተመለከተው ማኅበሩ አስተዳዳሪዎችን ለመክሰስ ሲፈልግ ሊያሟላ የሚገባውን ቅድመ ሁኔታዎች እንጂ የተወሰኑ የአክሲዮን ማኀበሩ ባለድርሻዎች የሚያቀርቡትን ክስ አያጠቃልልም፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው አስተዳዳሪዎች ላይ ክስ ለመመሥረት የሚችሉ ወገኖች ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በንግድ ሕጉ ለየብቻ የተደነገጉ ስለሆነ እነዚህን ለይቶ በአግባቡ ማየት የግድ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት አሁን በተያዘው ጉዳይ ላይ አመልካቾች የሚሉት በተጠሪዎች የተፈፀመው ተግባር መብታቸውን የሚጎዳ በመሆኑ አስተዳደሪዎችን /ተጠሪዎች/ በቀጥታ መክሰስ



የበታች ፍ/ቤት አንቀጽ 365ን መሠረት አድርጎ መከልከሉ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡

እኛም ይህንን ሁኔታ ከላይ እንደተመለከተው የተጠያቂነት መሠረቱ ለየብቻ መታየት እንዳለበት የሕጉን ዓላማና መንፈስ መሠረት አድርገን አጽንተነዋል፡፡ በዚሁ መሠረት አመልካቾች የአክስዮን ባለድርሻ አባላት በመሆናቸው የአባልነት መብታቸውን በሚጎዳ መልኩ አስተዳዳሪዎች /የአሁን ተጠሪዎች/ መሥራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ ቀጥታ መከሰስ እንደሚችሉ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 ይፈቅድላቸዋል፡፡

በመሆኑም አመልካቾች የሚጠበቅባቸው በተጠሪዎች ሥራ አመራርና የውሣኔ እርምጃ ተጎጂ መሆናቸውን በንግድ ሕጉ አንቀጽ 367 መሠረት ማረጋገጥ እንጂ የበታች ፍ/ቤት እንደተመለከተው በንግድ ሕግ አንቀጽ 365 የተመለከተውን ቅድመ ሁኔታ ማሟላት አይጠበቅባቸውም፡፡ የንግድ ሕጉ አንቀጽ 365 የተወሰኑ የአክስዮን ማኅበሩ አባላት በአስተዳዳሪዎች ላይ የሚያቀርቡትን ክስ የሚመለከት ስላልሆነ የሥር ፍ/ቤት ተገቢ ያልሆነውን የሕግ አንቀጽ መሠረት አድርጎ የአመልካቾችን ክስ መዝጋቱ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08449 የሰጠው ብይን እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37119 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 341/1/ መሠረት ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ ተመልሶ የፍሬ ነገር ክርክር ውሣኔ እንዲያገኝ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 25306

ኅዳር 12 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን እቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

**አመልካች፡-** አቶ ተስፋዬ ገለቴ - ጠበቃ በፀሎት መኮንን ቀረበ፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ታሪኳ ሳዕከ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ አመልካች ሐምሌ 4 ቀን 1995 ዓ.ም. በአሁኑ መልስ ሰጭ እና በሥር ጣልቃ ገብ በነበሩት በአቶ ሃይደር ከቢር እና በፊንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ላይ መስርቶት የነበረው ክስ፣ በመልስ ሰጭ ባንክ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ በሂሣብ ቁጥር 1011 ከነበረው የተንቀሳቃሽ ሂሣቤ ውስጥ ሳይፈረድብኝና በአፈፃፀምም ሳልገደድ ባንኩ ከፊንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት ታዝዤ ከፍያለሁ በማለት ብር 135,912.08 /አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ብር ከዜሮ ስምንት ሳንቲም/ ወጭ በማድረግ ከፍሏል፡፡ በመጨረሻም ከፊንታሌ ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠ የክፍያ ትዕዛዝ የሌለ መሆኑና ባንኩ የከፈለው በተጭበረበረ ሰነድ መሆኑን ገልጬ ያለአግባብ የከፈለውን ገንዘብ ወደ ሂሣቤ እንዲያስገባልኝ ብጠይቅ እምቢተኛ በመሆኑ፣ የሥራ ግዴታውን ባለመወጣት የከፈለውን ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ከወለዱና ከወጭና ኪሣራ ጋር እንዲከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጭ በበኩሉ በሰጠው መልስ፣ ክፍያ የፈፀመባቸው ትዕዛዞች የመጡት ከፍርድ ቤት መሆኑንና ማኀተሞቹም ትክክለኛ መሆናቸውን አምኖ የከፈለ መሆኑን ገልፆ ፊርማው የዳኛው ስለመሆኑ የማረጋገጥ ግዴታ የሌለበት መሆን በመግለጽ መልስ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ባንኩ ሐሰተኛ



ነው ተብሎ ሊታወቅ በማይችል የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የከፈለ በመሆኑ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት የለም በማለት በነፃ አሰናብቶታል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

ይህ ችሎት በጥቅምት 30 ቀን 1999 በዋለው ችሎት ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ የግራ ቀኙን መልስ እና የመልስ መልስ እንዲሁም የቃል ክርክሩን አሰምቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ በዋነኛነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባው የሕግ ጥያቄ፣ የአሁኑ መልስ ሰጭ በአደራ ተቀብሎ ያስቀመጠውንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ብር 135,912.08 ለሌላ ግለሰብ ከፍሎ በመገኘቱ ገንዘቡን ለመመለስ በኃላፊነት አይጠየቅም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን መመርመር ይሆናል፡፡

በመሠረቱ በአሁኑ አመልካችና በመልስ ሰጭው መካከል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1779 እና በሚቀጥሉት አንቀጾች እንዲሁም ከተያዘው ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ አግባብነት ባለው በንግዱ ሕግ ቁጥር 896 እስከ 902 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት የአደራ ውል ስምምነት ያለ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ የውል ግንኙነት ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ከሌለ በቀር አደራ ተቀባዩ ባንክ በተጠየቀ ጊዜ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ ያለበት መሆኑ ሳይቀር በአደራ የተቀበለውን ገንዘብ አስፈለጊ ለሆኑ ስራዎቹ እንዲገለገልበት መብት የሚያገኝ መሆኑን የንግድ ሕግ ቁጥር 896 በግልጽ ደንግጓል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ ተቃራኒ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ አደራ አስቀማጩ በአደራ ተቀባዩ ዘንድ ያስቀመጠውን ገንዘብ በማንኛውም ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያዝበት የሚችል መብት ያለው ስለመሆኑም በዚሁ ንግድ ሕግ ቁ. 898/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የአሁኑ መልስ ሰጭ በአደራ የተቀበለውን የአመልካችን ገንዘብ አደራ አስቀማጩ ወይም በሕግ አግባብ ሥልጣን የተሰጠው ክፍል ሳያዝው ገንዘቡን አሳልፎ ለሌላ ከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ለክፍያውም ምክንያቱ የማጭበርበር ተግባር ድርጊት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አቶ ሐይደር ከዲር በተባለ ሰው ተፈፀመ በተባለው የማጭበርበር

ተግባር የተጭበረበረው የአሁኑ መልስ ሰጪ ባንክ እንጂ የአሁኑ አመልካች አይደለም፡፡ የአሁኑ መልስ ሰጭ ተጭበርብሮ ከሆነ ያጭበረበረውን ሰው በሕግ አግባብ ከሶ ከሚጠይቅ በቀር ተቃራኒ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ የተቀበለውን የአደራ ገንዘብ አደራ አስቀማጩ በተጠየቀ ጊዜ የማይመልስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የማጭበርበር ተግባሩ ሕጋዊ ስርዓቱን ባልተከተለ የፍርድ ቤት ማኅተም መሆኑ የአደራ ተቀባዩን ባንክ ኃላፊነትም አይቀንሰውም፡፡ በመጨረሻ በዚህ የማጭበርበር ተግባር ሊጎዳ የሚችል ክፍል ቢኖር በቀጥታ የማጭበርበር ተግባሩ ሰለባ የሆነው መልስ ሰጪ ባንክ እንጂ በምትኩ ያልተጭበረበረው አደራ አስቀማጭ ሊሆን የሚችልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

በአጠቃላይ ተቃራኒ ስምምነት በሌለ ጊዜ የአደራ ገንዘብ እንደተጠየቀ የሚከፈል ገንዘብ ነው፡፡ አደራ ተቀባዩ ተጭበርብሬ ነው በማለት የሚያነሳው መቃወሚያ ገንዘቡ እንዲከፈል በተጠየ ጊዜ ከመክፈል የሚያግደው አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአደራ ተቀባይና በአደራ አስቀማጩ መካከል የተደረገ ተቃራኒ ስምምነት መኖሩን ሳያረጋግጥ "መልስ ሰጪ ሐሰተኛ ነው ተብሎ ሊታወቅ በማይችል የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሠረት የከፈለ በመሆኑ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት የለም" በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሐምሌ 30 ቀን 1996 በመ/ቁ. 29968 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት መጋቢት 25 ቀን 1998 ዓ.ም. በመ/ቁ. 33810 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- መልስ ሰጭ ባንክ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ብር 135,912.08 /አንድ መቶ ሰላሣ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ብር ከዜሮ ስምንት ሣንቲም/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል፤



- አመልካች ለዳኝነት የከፈለውን ገንዘብ መልስ ሰጪ ይተካ፤ የጠበቃ አበል 10% ይክፈል፤ ኪሣራ በቁርጥ ብር 2000 /ሁለት ሺህ/ ለአመልካች ይከፈል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 27161

ኅዳር 12 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን እቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ኤልያስ ከፈለ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- እነ አቶ ከድር አህመድ /4 ሰዎች/ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ጥቅምት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩን የሥር አመጣጥ የአሁን ተጠሪዎች በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ በቂርቆስ ክ/ከተማ የሚገኘውን የንግድ ቤት ለኑሮአቸው መቋቋሚያ ተፈቅዶላቸው መንቀሳቀሻ ገንዘብ በማጣት ላሁኑ አመልካች ቦታውን ለ4 ዓመት ማከራየታቸውን፣ ውሉ ከተደረገ በኋላ ቦታው የተሰጣቸው ለዘለቄታው ሣይሆን ለ3 ዓመት ብቻ መሆኑን መገንዘባቸውንና በቦታው ላይ ከብረታ ብረት ወርክሾፕ በስተቀር ሌላ ሥራ መሥራት እንደማይችሉ፣ ከዚህ ውጭ ሠርተው ከተገኙ የሊዝ ውሉ የሚሠረዝ መሆኑ በአስተዳደር አካል የተነገራቸው መሆኑን፣ አመልካች ግን ከሊዝ ውሉ ውጭ እየሠሩ ስለሚገኙ በውሉ ለመቀጠል አስቸጋሪ ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ ከክ/ከተማው ጋር ባረደረጉትም ውል ለሌላ ሶስተኛ ወገን ቦታውን አሣልፎ መስጠት የተከለከለ በመሆኑ ባጠቃላይ ውሉ የተሣሣተ ውል ነው ተብሎ እንዲሠረዝ የሚል ነው፡፡ አመልካችም መልስ እንዲሰጡ በተታዘዙበት እለት ባለመቅረባቸው በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ ከዚህ በኋላ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር እንዲያቀርቡ ተደርጎ ፍርድ ቤቱ አመልካችና ተጠሪዎች ያደረጉት ውል ከሊዝ ውሉ ጋር የማይጣጣም ነው በማለት ውሉን ሠርዞ ግራ ቀኙ ወደየነበሩበት እንዲመለሱ ሲወስን የከፍተኛው ፍርድ ቤትም በይግባኝ ውሣኔውን አጽንቷል፡፡ አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መነሻነት ሲሆን ፍ/ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ መልስ ሰጪን በማስቀረብ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክራቸውንም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል ከሕዳር 6 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ ለአራት ዓመት ማለትም እስከ ኅዳር 6 ወይም 7 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የሚዘልቅ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተረድቷል፡፡

በሌላም በኩል ተጠሪዎች ከቂርቆስ ክ/ከተማ ጋር ያደረጉት የሊዝ ውል ለሶስት ዓመታት የሚዘልቅ መሆኑን ተጠሪዎች በክሣቸው ላይ ገልፀዋል ተጠሪዎች ካቀረቡት ክስ በመነሣት ፍርድ ቤቱ ለመገንዘብ የቻለው ጉዳይ በክርክር ሒደት ላይ እያለ የሊዝ ውሉ የጊዜ ገደብ ያበቃ መሆኑን ነው፡፡ የሊዙ የጊዜ ገደብ ካለቀ ደግሞ ተጠሪዎች የነበራቸውን የክስ መሠረት ያጡ ለመሆኑ አጠያያቂነት የለውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 ላይ እንደተመለከተው ክሱ በማንኛውም ደረጃ ባለ ጊዜ የክሱ መሠረት ማክተሙን ፍርድ ቤቱ ከተረዳ ክሱን እንደሚሠርዝ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪዎች ለሶስት ዓመት ከክፍለ ከተማው ጋር ያደረጉት ውል ማብቃቱ የተረጋገጠ ስለሆነና በዚህም ሣቢያ በቦታው ላይ ምንም አይነት መብት ስለሌላቸው፣ በሌላም በኩል አመልካችም በውሉ ከተመለከተው የአራት ዓመት ጊዜ በላይ በቦታው የተጠቀመ ስለሆነ ግራ ቀኙን መብት በሌላቸው ጉዳይ እየተከራከሩ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በመገንዘቡ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ማየት ሣያስፈልግ የሰበር አቤቱታውን ሠርዘናል በተመሣሣይ ሁኔታም ተጠሪዎችን ተጠቃሚ ያደረገው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔም ከላይ በተመለከተው ምክንያት ከእንግዲህ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

- የሰበር አቤቱታው ተሰርዟል፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና በዚህ ጉዳይ የተጀመረው የአፈፃፀም መዝገብ እንዲዘጋ ታዟል፡፡
- ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁጥር 28923

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማሕበር አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ/ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር አልቀረቡም

2ኛ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነገረፈጅ አቶ አዳነ መጋቡ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ብሔራዊ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ ፍሬ ጉዳዩም አንደኛ ተጠሪ የአማራ ብሔራዊ ክልል ባወጣው ደንብ መሠረት በ1988 ዓ.ም የቦታ ኪራይ ብር 497,943.54 /አራት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ አርባ ሦስት ብር ከሀምሣ አራት ሣንቲም/ እንዲከፍል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ያልከፈለ በመሆኑ እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት በአመልካች ላይ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካችም ይህ ዕዳ የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደነበርና ወደ ባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማሕበር ከመቀየሩ በፊት የነበረ ስለሆነ፣ ሁለተኛው ባለዕዳ፣ ሦስተኛ ወገን ተከራካሪ፣ /ተከሣሽ/ ሆኖ ጣልቃ እንዲገባ

በጠየቁት መሠረት ፍ/ቤቱ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስና አመልካቹና ሁለተኛው ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ የቦታውን ዋና ግብር 454,511.99 /አራት መቶ ሀምሣ አራት ሺ አምስት መቶ አሥራ አንድ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለተኛ ተጠሪ ብር 56,159.44 /ሀምሣ ስድስት ሺ አንድ መቶ ሀምሣ ዘጠኝ ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ ብቻ እንዲከፍል ቀሪውን ዕዳ አመልካች እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በክሱ ተከሳሽ የሆነው የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማሕበር የተመሰረተው 1992 ዓ.ም ነው፡፡ ስለዚህ ፋብሪካው ወደ አክስዮን ማሕበርነት ከመለወጡ በፊት የነበረው ዕዳ እኛን የሚመለከት ባለመሆኑና ሁለተኛው ተጠሪ ይህንን ዕዳ የመክፈል ግዴታ በአዋጅ ቁጥር 182/1992 የተጣለበት ሆኖ እያለ አክስዮን ማሕበሩ ዕዳውን እንዲከፍል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ያለበትና አክስዮን ማህበሩን ለኪሣራ የሚዳርግ በመሆኑ በሰበር ይታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ ወደ አክስዮን ማሕበሩ የሚተላለፉና የማይተላለፉ ዕዳዎችን የመወሰን ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መክፈል ያለበት ዕዳ ነው በማለት ያሣወቀን 56,159.44 /ሃምሣ ስድስት ሺ አንድ መቶ ሃምሣ ዘጠኝ ብር ከአርባ አራት ሣንቲም/ በመሆኑ ከዚህ ውጭ ያለውን ዕዳ አመልካች መክፈል ይገባዋል የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በበኩሉ ዕዳው መከፈል ያለበት ዕዳ መሆኑን ሁለተኛ ተጠሪና አመልካች እንዳልካዱ ገልፆ በሁለቱ መካከል በሚደረገው ክርክር የከተማው አስተዳደር ማግኘት የሚገባውን ክፍያ ሣያገኝ ጉዳዩ እየተንተተ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ታይቶ ዕዳውን ከነወለዱ እንዲከፍሉ ውሣኔ ይሰጥልን በማለት ተከራክሯል፡፡



ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የአመልካችና ተጠሪዎች በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካች ያለበት ዕዳና አጠቃላይ እሴቱ እና መንቀሳቀሻ ካፒታሉ ተለይቶ የባህርዳር ጨርቃጨቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር ተብሎ በአዲስ መልክ በአክስዮን ማህበርነት ከመደራጀቱ በፊት ለአንደኛ ተጠሪ መክፈል የሚገባውን የቦታ ግብር ዕዳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው መንግሥት አመልካች ድርጅት ወደ አክስዮን ማህበር ከመቀየሩ በፊት የነበሩበትን ዕዳዎች በኃላፊነት የሚረከብ አንድ ተቋም ማቋቋም በማስፈለጉ ምክንያት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለ አደራ ቦርድን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደገና በመወሰን ሕግ ያወጣ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 208/1992 መግቢያ ለመረዳት ይቻላል፡፡ የባለአደራ ቦርዱ መሠረታዊ ዓላማም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወደግል ይዞታ በሚዛወርበት ወይም ወደ አክስዮን ማህበር በሚለወጥበት ወይም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ በሚመለስበት ጊዜ ወደ አዲሱ ባለቤት ወደ አክስዮን ማህበሩ ወይም ወደ ቀድሞ ባለቤቱ የማይተላለፉ ሂሣቦችን መሰብሰብ ዕዳዎችን መረከብና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የፍርድ ቤት ጉዳዮችን መከታተል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የባለአደራ ቦርዱ ወደ አክስዮን ማህበርነት የተቀየሩ ወደ ግል የተዛወሩ ወይም ለቀድሞ ባለቤታቸው የተመለሱ የመንግሥት የልማት ድርጅት ዕዳዎችን ለመንግሥት እያቀረበ እንዲከፈሉ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን አዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መዝገብ የባህርዳር ከተማ አስተዳደር የጠየቀው የመሬት ኪራይ የባህርዳር ጨርቀጨርቅ ፋብሪካ ወደ አክስዮን ማህበርነት ከመቀየሩ ከአራት ዓመት በፊት የነበረና የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ የመንግሥት የልማት ድርጅት በነበረበት 1988 ዓ.ም መክፈል የሚገባው ዕዳ ነው፡፡ አሁን ያለው የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር 1992 ዓ.ም ህጋዊ ሰውነት ያገኘ

ድርጅት በመሆኑ ከጅምሩ በፈረሰውና ወደ አክስዮን ማህበርነት በተቀየረው የባህርዳር ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ስም ያቀረበውን ክስ በኃላፊነት ይዞ መከራከር የሚገባው የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ እንደሆነ ከአዋጅ ቁጥር 208/1992 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪ ዕዳውን ላለመክፈል የሚያቀርበው ምክንያት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ አላሳወቀኝም የሚል ነው፡፡ ሆኖም የመንግሥት የልማት ድርጅቱ ወደ አክስዮን ማህበርነት ሲቀየር በፕራይቬታይዜበሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት ዕዳ ሁሉ ወደ አክስዮን ማህበሩ ይተላለፋል የሚል ግልጽ የህግ ድንጋጌ ካለመኖሩም በላይ የዚህ አይነት የህግ አተረጓጐም አክስዮን ማህበሩን ለከፍተኛ ኪሣራ የሚዳርግና የባለአደራ ቦርዱ የተቋቋመበትን መሠረታዊ ዓላማ ጋር የሚቃረን ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በመሆኑም ዕዳው አክስዮን ማህበሩ ከመቋቋሙ በፊት የነበረ እስከሆነ ድረስ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በወቅቱ ያላወቀውና ውሣኔ ያልሰጠበት ዕዳ በአክስዮን ማህበሩ መከፈል ይገባዋል በማለት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 07500 ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
2. የአማራ ክልል የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03792 ሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ የፍርዱ ግልባጭ ይተላለፍ፡፡
3. ሁለተኛው ተጠሪ ብር 454,511.99 /አራት መቶ ሀምሣ አራት ሺ አምስት መቶ አሥራ አንድ ብር ከዘጠና ዘጠኝ ሣንቲም/ እና የከፍተኛው ፍርደ ቤት ውሣኔ ከሰጠበት ከሐምሌ 27 ቀን 1997 ዓ.ም



ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት /9%/ ህጋዊ ወለድ ለአንደኛው ተጠሪ ይክፈል ብለናል፡፡
4. አመልካችና ተጠሪዎች ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# በአዋጅ የተወረሱ ቤቶች



የሰ/መ/ቁ. 22297

ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- የጅማ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት ተወካይ ቲጃኔ አባቡልጉ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሽዋረገድ አባድር ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በወረዳው ፍ/ቤት ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት በጠየቀው ዳኝነት መነሻ አድርጎ ያቀረበው ምክንያት እናቴ በካርታ ቁጥር 928 1392 ካሬ ሜትር በሆነው ቦታ ላይ የቤት ቁጥር 156 የሆነ ቤት አላቸው የእናቴ ወራሽ መሆኔን አረጋግጫለሁ ሆኖም ተከሣሽ የአሁን አመልካች ለሌላ ግለሰብ ስለሸጠብኝ ሁከት ተፈጥሮብኛል የሚለውን ነው፡፡

አመልካችም ይህ በካርታ ቁጥር 928 የተመዘገበው ካርታ የተሰጠው በ1954 ዓ.ም. ነው፡፡ የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤትን የመንግሥት ባደረገው አዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ይህ ክስ የቀረበበት ንብረት የተወረሰ ነው፤ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር የወረዳ ፍ/ቤትም በውርስ አግኝቼ የእራሴ ሆኗል በማለት ከሳሽ ይከራከር እንጂ ይህ ስለመሆኑ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ንብረቱ በአዋጅ ቁጥር

47/67 የተወረሰ ስለሆነ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህም ውሣኔ በከፍተኛው ፍ/ቤት ፀንቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በይግባኝ ካከራከረ በኋላ የአሁን አመልካች ተወርሷል ይበል እንጂ ስለመወረሱ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ንብረቱ በከሳሽ በአሁን ተጠሪ ስም መሆኑን አልካደም የወራሽነት ማስረጃ ቀርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤት መልስ ሰጭ የባለቤትነት ማስረጃ የለውም ማለቱ ተገቢ አይደለም ስለሆነም ካርታ እና ፕላን ያለውን ንብረት በሊዝ መሸጡ ተገቢ አይደለም በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ ሽሯታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይኸው የጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት አመልካችን አሰናብቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጡት ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል በማለት ነው፡፡

ግራ ቀኙም በዚህ ሰበር ችሎት የቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም ተጠሪ ሁከት ተፈጠረበት በተባለው ንብረት መብት ወይም ጥቅም ያለው መሆኑን ለማሣየት መሠረት ያደረገው ወራሽ ነኝ በማለት ነው፡፡ ንብረቱም የአውራሽ የእናቴ ነው ለማለት ያበቃው በካርታ ቁጥር 928 የተመዘገበውን ካርታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ካርታ በ1954 ዓ.ም. የተሰጠ ነው በማለት አመልካች ላቀረበው ክርክር ማስተባበያ አላቀረበበትም፡፡ ክዶም አልተከራከረም፡፡ አመልካች ይህ የንብረቱ የባለቤትነት ማረጋገጫ የተሰጠው አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሲሆን ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ ግን ተወርሷል በማለት ይህንኑ ሕግ መሠረት አድርጎ ለቀረበው ክርክር ተጠሪ አልተወረሰም በማለት ተከራክሯል:: የቤቱ ካርታ የተሰጠበት ጊዜ እና አዋጁ የወጣበት ጊዜ እንደ መነሻ ፍሬ ነገር በመያዝ ንብረቱ የተወረሰ መሆኑን የግምት መነሻ በመስጠት አመልካች ያስረዳ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ይህ ንብረት ያልተወረሰ መሆኑን በሚያመለክት ሁኔታ ማስረጃ



በማቅረብ አላረጋገጠም:: ይልቁንም በቃል በተደረገው ክርክር አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲወጣ እኔ እስር ቤት ነበርኩኝ፤ የደርግ መንግሥት በአምባገነንነት በቀበሌ አማካኝነት ለሌሎች ሰዎች በኪራይ ተሰጠብኝ የሚለውን መግለጽ ንብረቱ በእርግጥም የተወረሰ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ስለሆነም ንብረቱ ተወርሷል ወይስ አልተወረሰም የሚለውን ነጥብ በሚመለከት ማን ክርክሩን መጀመርና ማስረዳት እንዳለበት የሚያመለክተውን ድንጋጌ ባለመከተል እና ይህም ሥርዓት ቢዛነፍም እንኳ ከግራ ቀኙ ማን የተሻለ ማስረጃ አቅርቧል የሚለውን ነጥብ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. አመልካች ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ የፈፀመው ሁከት የለም ብለናል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22312 በሐምሌ 14 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ. 32640 በህዳር 21 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
3. የወረዳው ፍ/ቤት በ/መ/ቁ 532/96 በጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም. እንዲሁም የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 05349 በታህሣሥ 21 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 23608

ኀዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ

ኤጀንሲ ነ/ፈጁ መስፍን በሻህ

ተጠሪ፡- የአቶ ኑር በዛ ተረጋ ወራሾች

ጠበቃ ስንታየሁ ባህሩ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የአሁን ተጠሪዎች አውራሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መነሻነት ሲሆን የክሱም ይዘት ባጭሩ በወረዳ 18 ቀበሌ 34 ክልል ቁጥራቸው ከ001 -007 የሆኑት ቤቶች ያለአግባብ በመንግሥት የተወሰዱ መሆናቸው ታምኖበት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በኩል እንዲመለስልኝ ተወስኖ በዚሁ ውሣኔ መሠረት ቤቶቹን እንድረከብ ታህሣሥ 3 ቀን 1988 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ለተከሣሽ (ለአሁን አመልካች) አመልክቼ እንዳለሁ በኀዳር ወር 1991 ዓ.ም አካባቢ በቤቶቹ ውስጥ የነበሩት ተከራዮችን ሲለቁ ከሣሽ ቤቶችን የተረከብኩኝ ቢሆንም ያቀረብኩት አቤቱታ አስቀድሞ ቤቶቹ ሊመለሱልኝ እንደሚገባ ታምኖበት በተወሰነልኝ መሠረት እንዲመለሱልኝ የሚል ሆኖ ሳለ አቤቱታዬን በትክክል ባለመረዳት ለቤቶቹ የቤት ባለቤትነት መብት እንዲሰጠኝ እንዳመለከትኩኝ ቆጥሮ የሚመለሱት ቤቶች በሙሉ ሣይሆን በከፊል ብቻ ነው በማለት በመወሰኑ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ይግባኝ ያቀረብኩ ቢሆንም ቦርዱ የኤጀንሲውን ውሣኔ በመሻር መዝገቡን የዘጋ ስለሆነ የኤጀንሲውም ሆነ የቦርዱ ውሣኔ ከሥልጣናቸው ውጭ ስለሆነ በፍርድ ሊሰረዝልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡



የከሣሽ ክስና ማስረጃ ለተከሣሽ (ለአሁን አመልካች) ደርሶ በሰጠው መልስ ከሣሽ በክስ አቤቱታቸው በጠቀሷቸው ቤቶች ትርፍነታቸው ተረጋግጦ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የተወረሱ ንብረቶች ናቸው በመሆኑም በመጀመሪያ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ በመቀጠልም የኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ ይህን ጉዳይ ለማየት ሥልጣን እንደሌለው በመግለጽ የመጨረሻ ውሣኔ በመስጠት መዝገቡ እንዲዘጋ ወስኗል፡፡ በአዋጁ ቁጥር 110/87 መሠረት ተከሣሽ የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በፍ/ቤት እንደገና ሊታዩ /Review/ እንደሚችሉ የተደነገገ ድንጋጌ ስለሌለ ፍ/ቤቱ ይህንን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት ሥልጣን የለወም፡፡ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ በመስጠት ክሱ ከበቂ ኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክሩን መርምሮ በተከሣሽ በኩል የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ ኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት በአንቀጽ 79(1) ላይ የዳኝነት ሥልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ እንደሆነ በአንቀጽ 37(1) ላይ ደግሞ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ (Justieable matter) ለፍ/ቤት የማቅረብና ውሣኔ የማግኘት መብት እንዳለው የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በአስተዳደር አካላት የተሰጡ ውሣኔዎችን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማየት ተፈጥሯዊ /inherent/ የሆነ ሥልጣን ያላቸው ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም ተብሎ በተከሣሽ በኩል የቀረበው መቃወሚያ በአግባቡ የቀረበ አይደለም በማለት ውድቅ አድርጎ በፍሬ ጉዳይ ረገድ ግራ ቀኙ ያደረጉትን ክርክር መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 4(1) እና አንቀጽ 3(2) መሠረትና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 001/88 አንቀጽ 3(1) እና (2) መሠረት ከአዋጁ ቁጥር 47/67 ውጭ የተወሰዱ

ንብረቶች ይመለሱልኝ የሚሉ አቤቱታዎችን እንደዚሁም ከአዋጅ ውጭ በተወረሰ ንብረት ላይ አዋጅ ቁጥር 110/87 ከመጽናቱ በፊት በሌላ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠ ቢሆንም ይህ ውሣኔ እንደገና እንዲመረመር አቤቱታ ሲቀርብ ኤጄንሲው ከዚያም ቦርዱ የማየት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሆኖም በአዋጁና በመመሪያው መሠረት ከእነርሱ በፊት ሌላ የአስተዳደር ባለሥልጣን ከአዋጁ ወጭ የተወረሱ ናቸው የተባሉ ንብረቶች ላይ የሰጠውን የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት የሚችሉት አቤቱታ ሲቀርብላቸው እንጂ በገዛ ፈቃዳቸውና በእራሣቸው ጊዜ አይደለም በማለት በውሣኔው ላይ አስፍሮ፤ በተያዘው ጉዳይ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅና የሥራ አመራር ቦርድ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጁንና የመመሪያውን ድንጋጌዎች ጥሰው ከሥልጣናቸው በማለፍ ከሣሽ ቤቶቹን ለመረከብ በተወሰነልኝ መሠረት ርክክቡ ይፈፀምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ያለአግባብ የተወረሱ ቤቶች ይመለስልኝ በማለት አዲስ አቤቱታ ያቀረቡ በማስመሰል ውሣኔ የሰጡ ስለሆነ የኤጄንሲው ሥ/አስኪያጅም ሆነ ቦርዱ ከሥልጣናቸው ውጭ ውሣኔ ስለሰጡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2121 መሠረት ተሰርዟል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን አስመልክቶ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሣይቀበለው የቀረው በአግባቡ እንደሆነና በዚህ ረገድ የቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው ነው ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም ኤጀንሲውም ሆነ የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሰጡት ውሣኔ ከአዋጁም ሆነ ከመመሪያው አኳያ ሲታይ ከሥልጣናቸው ውጭ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔው ሊሰረዝ እንደሚገባ የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ እንዳልሆነ ነገር ግን የኤጄንሲው ሥራ አስኪያጁ ውሣኔ በቦርዱ ተሽሮ ባለበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ በድጋሚ የኤጀንሲውን ሥራ አስኪያጅ ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ አይደለም በማለት በዚህ መልኩ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የፕራይቬታይዜሽን ኤጄንሲ የሰጠው ውሣኔ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ተፈጥሯዊ /inherent/ ስልጣን አላቸው በማለት ኤጀንሲው የሰጠውን ውሣኔ የሥር ፍ/ቤቶች በድጋሚ አይተው ውሣኔ መስጠታቸው አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊጣራ እንደሚገባ በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የተጠሪዎች አውራሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የጠየቁት ዳኝነት /Relief/ ኤጄንሲውም ሆነ ቦርዱ የቀረበላቸው አቤቱታ ከአዋጁ ውጭ የተወሰደ ቤት እንዲመለስልኝ ይወሰንልኝ የሚል ባልሆነበት ሁኔታ ከተጠየቀው ውጭ ሌላ ጭብጥ በመያዝ ውሣኔ የሰጡ ስለሆነ ይሄው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ነው፡፡

ከአዋጅ ውጭ ስለተወሰዱ ንብረቶች በወጣው አዋጁ ቁጥር 110/87 አንቀጽ 4(1) እና (2) መሠረት ከአዋጅ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶችን የባለቤትነት ሁኔታ የማጣራትና የመወሰን ሥልጣን ለአመልካች የተሰጠ ሲሆን የባለቤትነትን ጥያቄ በሚመለከት ኤጀንሲው በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታውን ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ማቅረብ እንደሚችል በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 5/3/ ላይ ተመልክቷል፡፡

በእርግጥ የተጠሪዎች አውራሽ ታህሣሥ 3 ቀን 1988 ዓ.ም ለአመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች ከአወጁ ውጭ የተወሰዱ ስለሆነ ይመለስልኝ በማለት ሣይሆን የቤቶቹ ባለቤትነቱ በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አማካይነት ተረጋግጦ ተወስኖልኝ ርክክቡ የዘገየ ስለሆነ ቤቶቹን እንድረከብ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

የተጠሪዎች አውራሽ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች እንዲመለሱልኝ በሌላ አካል ተወስኖልኛል የሚሉ ከሆነ ቀድሞውንም ቢሆን ቤቶቹን ለመረከብ አቤቱታ ማቅረብ የነበረባቸው ለፍ/ቤት እንጂ ለኤጀንሲው አልነበረም፡፡

በሌላ በኩልም ለኤጀንሲው የቀረበው አቤቱታ ይዘቱ ምንም እንኳን የቤቶቹን ርክክብ የሚመለከት ቢሆንም ኤጀንሲው የተቋቋመው ከአዋጁ ውጭ የተወሰዱ ንብረቶች የባለቤትነት ሁኔታ አጣርቶ ለመወሰን እስከሆነ ድረስ የእነዚህንም ቤቶች የባለቤትነት ሁኔታ ከአዋጁ አኳያ መርምሮ ውሣኔ ቢሰጥ ከሥልጣኑ ውጭ በማለፍ ውሣኔ ሰጥቷል ወደሚል ድምዳሜ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ይልቁንም ኤጀንሲው የተቋቋመበትን አ/ቁ/110/87 ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ ቁጥር 001/88 መሠረት አዋጅ ቁ. 110/87 ከመውጣት በፊት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 ውጭ በተወሰደ ንብረት ላይ በሌላ አስተዳደራዊ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ ተሰጥቶ ባለበት ሁኔታም የውሣኔው አግባብነት እንዲመረመር አቤቱታ ሲቀርብ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ መርምረው ውሣኔ መስጠት እንደሚችሉ የተመለከተ እንደመሆኑ መጠን የተጠሪዎች አውራሽ በዚህ መልኩ ያቀረቡትን አቤቱታ ኤጀንሲውም ሆነ ቦርዱ መርምረው ውሣኔ መስጠታቸው ከስልጣናቸው ውጭ ነው ሊባል አይችልም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በሕገ መንግሥታችን አንቀጽ 37/1/ ላይ ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተመልክቷል፡፡

ከዚህ የሕገመንግሥቱ ድንጋጌ በግልጽ መገንዘብ የሚቻለው ፍ/ቤቶች አንድን አቤቱታ ተቀብለው ውሣኔ መስጠት የሚችሉት ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ በሕግ ለሌላ አካል ያልተሰጠ ጉደይ በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ ነው፡፡

የተያዘውም ጉዳይ በተጠቀሰው አ/ቁጥር 110/87 መሠረት የዳኝነት ሥልጣኑ በግልጽ ለሌላ አካል ማለትም ለአመልካች የተሰጠ ስለሆነና ኤጀንሲውም በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ቅሬታውን ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ማቅረብ እንደሚችልና የቦርዱም ውሣኔ የመጨረሻና አሳሪ /Final and binding/ እንደሆነ በአዋጁ ላይ ስለተመለከተ አቤቱታው ይህንን ሥርዓት ካለፈ በኋላ በኤጀንሲውም ሆነ በቦርዱ የተሰጠው ውሣኔ ከሥልጣን ውጭ ስለሆነ ውሣኔው ሊሰረዝ ይገባል የሚለው የተጠሪዎች አቤቱታ በአንድ በኩል በዚህ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ቤት በድጋሚ ለማየት የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ /legal frame work/ በሌለበት ሁኔታ ከመሆኑም በላይ በሌላም በኩል የፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን በእኛ አገር ሁኔታ ከሕግ የመነጨ እንጂ ተፈጥሯዊ /inherent/ ባልሆነበት ሁኔታ ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የፍ/ቤቱን ሥልጣን አስመልክቶ በቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተመስርቶ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት መመለስ ሲገባው የፌ/ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሣያርም መቅረቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 48/93 በመጋቢት 16 ቀን 1994 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 13021 በታህሣሥ 5 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/ለ/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት አቤቱታ የፍ/ቤት ሥልጣን አይደለም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 27548

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አሰፋ መኮንን

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ቆጽለ መርሻ
2. ወ/ሮ ፀምረ መርሻ } ሻለቃ ገ/መስቀል እንደሻው

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪዎች ከሣሽ በመሆን በአሁን አመልካችና በስር 2ኛ ተከሣሽ በነበረው በአቶ ከበደ ዋጋሪ ላይ በሐምሌ 12 ቀን 1993 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት ክስ፣ በቀድሞው ወረዳ 15 ቀበሌ 28 የቤ/ቁ 360 የሚገኝ በአውራሻችን ስም ቁጥር 14354 የሆነ ካርታ ያለው እና ቁጥር 15/31948 የሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የተሠጠበትን ቤት የአሁኑ አመልካች ለ2ኛው ተከሣሽ እያከራየ በመጠቀም ላይ በመሆኑ ተከሣሾቹ ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡን እና የአሁን አመልካች ከ2ኛ ተከሣሽ የተቀበለውን ኪራይ የመጠየቅ መብታችን ተጠብቆ ይወሠንልን ሲሉ ፍ/ቤቱን ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች በታህሣሥ 9 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ ለቤቱ ተከራይ /ለስር 2ኛ ተከሣሽ/ ቤቱን እንዲለቅ ደብዳቤ ጽፈን ለማስረከብ በሂደት ላይ ሣለን የወረዳ 15 ቀበሌ 28 መ/ጽ/ቤት በፃፈው ደብዳቤ መሠረት በተደረገው ማጣራት የቤቱ ባለንብረት የነበሩት አቶ መርሻ ሀ/ማርያም በትርፍነት ያስረከቡት በመሆኑ የደብተሩ አግባብነት ተመርምሮ ውጤቱ ካልተገለፀልን በቀር ለማስረከብ አለመቻላችንን ለስራና ከተማ ልማት ቢሮ ጽፈን የደብተሩን መሠረዝ በመጠባበቅ ላይ ነን ስለዚህ ከበቂ ኪሣራ ጋር መዝገቡ ይዘጋልን ሲል ተከራክሯል፡፡ የስር 2ኛ ተከሣሽም የበኩሉን መልስ ሰጥቷል፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም በሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ ተከሣሾች ገና ለገና የደብተሩን ጽኑነት እያጣራን ነው ከማለት ውጭ ደብተሩ ዋጋ የሌለው እንደሆነ ወይም የተሠረዘ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም በሌላ በኩል ከሣሾች በ1986 ዓ.ም. በተሠጣቸው የባለቤትነት ደብተርና በቤቱ ላይ ያላቸውን የባለቤትነት መብት ከተከሣሾች ይልቅ በተሻለ ሁኔታ ያስረዱ ስለሆነ ተከሣሾች ለከሣሾች ቤቱን ሊያስረክቡ ይገባል ብሎ የወሰነ ሲሆን የከሣሾቹን የኪራይ ጥያቄ ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአሁን አመልካች የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04279 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ቅሬታቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች በግንቦት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. አሻሽለው ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ የስር ከሣሾች የአሁን ተጠሪዎች በወራሽነት ይገባናል የሚሉት ቤት በአ/ቁ. 47/67 አንቀጽ 13/1/ እና /2/ መሠረት በትርፍነት በመንግሥት ተወርሶ በአመልካች እስከ አሁን ድረስ የሚተዳደር መሆኑን እና በቁጥር 15/31948 ተመዝግቦ የተሠጠው የቤት ባለቤትነት ደብተር ሕግን የሚቃረን መሆኑን በበቂ ሁኔታ አስረድተን እያለ የስር ፍ/ቤቶች ቤቱን ለተጠሪዎች አስረክቡ ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል ሲሉ አቤት ብለዋል፡፡ ይህም ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ተመልክቶ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ተወርሷል እየተባለ ቤቱን ለተጠሪዎች አስረክብ መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት መዝገቡን ለሠበር ችሎት በማስቀረብ ተጠሪዎቹ የጽሁፍ መልሣቸውን እንዲሠጡ አድርጓል፡፡ አመልካቹም ለተጠሪዎች መልስ የመልስ መልሱን አቅርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ይህም ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሯል፡፡

በመሠረቱ አግባብ ካለው አካል /አስተዳደር ክፍል/ የተጠሰ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ባለደብተሩ የማይንቀሣቀሰው ንብረት ባለሐብት ለመሆኑ የሕሊና ግምት የሚያስወስድ ለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195/1/ ላይ እንደመርህ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ሆኖም ይህ ደብተር የተሰጠው ከደንብ ውጪ በሆነ አሰራር መሆኑን የሚረጋገጥበት ሁኔተ ካለ ይህ የህሊና ግምት ፈራሽ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196/1/ ላይ በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል በተያዘው ጉዳይ ላይም የየካ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የክርክሩ መንስኤ በሆነው ቤት ላይ በሚያዝያ 14 ቀን 1986 ዓ.ም. ለተጠሪዎች የከተማ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር መስጠቱ ታውቋል፡፡ የሆነው ሆኖ ይኸው የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ለተጠሪዎች ሰጥቷቸው የነበረው ቁጥር 15/31948 የሆነው የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር የተሠጠው አለአግባብ እና በአዋጅ በተወረሰ የመንግሥት ቤት ላይ መሆኑን አረጋግጦ በቁጥር የሳ10/30/78841/99 በተፃፈ ደብዳቤ የተጠሪዎቹ የባለቤትነት መብት ከግንቦት 9 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ቀሪ መሆኑን ለተጠሪዎች ጭምር ማሣወቁን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ቤቱን ለማስረከብ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የሚመለከታቸው አካላት ተጠሪዎች የያዙት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አጠራጣሪ በመሆኑ አግባብነቱ በመጣራት ላይ መሆኑ በተገለፀለት መሠረት ቤቱን ለተጠሪዎቹ ለማስረከብ እንደማይችል ገልፆ እየተከራከረ የስር ፍ/ቤቶች በደብተሩ ላይ የተያዘውን የምርመራ ውጤት ሣይጠብቁ ወይም ደግሞ ደብተሩን የሰጠውን አካል ማብራሪያ ሣይጠይቅ በደፈናው ደብተር አልተሠረዘም በሚል ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲመልስ ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የስር ፍ/ቤቶች አጠራጣሪ በሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ላይ ተመርኩዘው አመልካች በወረዳ 15 ቀበሌ 28 የቤት ቁ. 360 የሚገኘው ቤት ለተጠሪዎች ይመለስ ሲሉ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካች ክርክር የተነሣበትን ቤት ለመመለስ አይገደድም ብለናል፡፡



3/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04279 በሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

4/ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 41022 በጥቅምት 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 29822

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን እቁበዮናስ

መድኀን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተደደር ጽ/ቤት ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** እነ ወ/ሮ በቀለች አማረብህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ክርክሩ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሾች ወ/ሮ በቀለች አማረብህ፣ አቶ በላይነህ ወንድ አፍራሽ በራሳቸውና በሞግዚት አድራጊዎቻቸው ስም፣ ተከሣሾች ደግሞ የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ፣ አቶ ገብሬ ኃይሌ እና የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት ናቸው፡፡ የክሱ አመጣጥ በተመለከተም ከሣሾች ሐምሌ 20 ቀን 1993 ዓ.ም. በተፃፈ የክስ ማመልከቻ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 6 ቀበሌ 02 ቁጥር 159-160 የሆነውን የግል መኖሪያ ቤት የአንደኛ ከሣሽ እና የአቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ የግል ቤት ሲሆን ቤቱን አቶ ወንድአፍራሽ በትርፍነት ያላስረከቡት እና በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 11 መሠረት ለአንድ ግለሰብ ወይም ቤተሰብ የተፈቀደ ነው፡፡ ቤቱ እንደተወረሰ በማስመሰል ቁጥር 159 በሚል በቀበሌ ቢመዘገብም በአግባቡ ተጣርቶ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ተሰቶት በእጃችን ይገኛል፡፡ አቶ ወንድአፍራሽ በመሞታቸውም የ1ኛ ከሣሽ ሚስትነት እና የሌሎቹ ከሣሾች ወራሽነት ተረጋግጧል፡፡ በአዋጁ መሠረት የተፈቀደልንን መብት ሶስተኛ ተከሣሽ ሊያስረክበን ሲገባ ለሁለተኛ ተከሣሽ አከራይቶት እየኖሩበት ይገኛሉ፡፡ ሁለተኛ ተከሣሽ ከሣሾችን ለመጉዳት ተነሳስተው ቁጥሩ 159 በሆነው ቤት ላይ የተሰጠው ደብተር እንዲመለስ የሚል ደብዳቤ አጽፈዋል፡፡ አንደኛ ተከሣሽም ይህንን የቀላጤ ደብዳቤ በጥቅምት 23 ቀን 1985 ዓ.ም. ጽፏል፡፡ አንደኛ ተከሣሽ እንደ ይግባኝ ሰሚ ሆኖ የሰጠው ደብተር በቀላጤ መሻር አይችልም፡፡ ትዕዛዙም ደብተሩ መሠረዙን አይገልጽም፡፡ ስለዚህ ትዕዛዙ ሕገወጥ ነው፡፡ በሌላ በኩል በትዕዛዙ ላይ ስማቸው የተገለፀው አቶ ሸዋአለም ሃ/ማርያም የቤት ቁጥር 159 ባለቤት ስላልሆኑ እና ለማስረከብም የተሰጣቸው ውክልና ስለሌለ ትዕዛዙ ሕጋዊነት የለውም፡፡ ስለዚህ ደብተሩ እንዲመለስ በቀላጤ ያለአግባብ የተሰጠው ትዕዛዝ እንዲሰረዝ እና ወጪና ኪሣራ እንዲከፈለን እንዲወስንልን በማለት ክስ መስርተዋል፡፡

አንደኛ ተከሣሽ በታህሣሥ 10 ቀን 1994 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ ከሳሾች ቁጥሩ 159 የሆነው ቤት ባለቤት አልነበሩም፤ አይደሉምም፡፡ ቤቱ የተወረሰው ከአቶ ሸዋዓለም ኃይለማርያም ነው፡፡ ከሣሾች ያስረከቡት እና የተወረሰባቸው ቤት አይደለም፡፡ ደብተር የወሰዱትም ያለአግባብ ነው፡፡ ደብተሩን የወሰዱት ያለአግባብ መሆኑ በተደረሰበት ጊዜም ተመላሽ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ አንደኛ ተከሣሽ በአዋጅ ቁጥር 41/85 አንቀጽ 8፣ በአዋጅ ቁጥር 7/86 አንቀጽ 32/1/ እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት በከተማው ባለቤትነት ሥር የሚገኙ ቤቶችን የመቆጣጠር ሥልጣን አለው፡፡ በዚህ ሥልጣኑ መሠረት የሰጠው ማስረጃ ከደንብ ውጪ ሆኖ ሲገኝ ፈራሽ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196 ላይ ተደንግጓል፡፡ ደብተሩ እንዲመለስ ማስገደድም ይችላል፡፡ ይህንን ማድረጉም ሕጋዊ መሆኑን ከሚያመለክት በስተቀር ክስ እንዲቀርብበት የሚያደርግ አይደለም፡፡ ስለዚህ ጥያቄው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ሁለተኛ ተከሣሽም በታህሣሥ 10 ቀን 1994 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ ከሣሽ ያለአግባብ የቤት ባለቤትነት ደብተር ያወጡ መሆኑን በመረዳት አንደኛ ተከሣሽ ደብተሩ እንዲመለስ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ከሣሾች የራሳቸው ባልሆነ ንብረት አሳስተው የወሰዱት ደብተር ውድቅ እንዲሆን የተወሰነ በመሆኑ የመክሰስ መብት የላቸውም፡፡ ይህ ከታለፈ ደግሞ ተከሣሽ ቤቱን ከአቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም ተከራይቼ ስጠቀም አዋጅ ቁጥር 47/67 ሲታወጅ በአዋጁ መሠረት

የኪራይ ፎርም ሞልቼ ኪራዩን ለመንግሥት እየከፈልኩኝ ሳለ አውራሻችን የሚሉዋቸው አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ በማሳሳት የቤት ባለቤትነት ደብተር ማውጣታቸውን በመስማቴ ባደረግኩት ጥቆማ ቤታቸው አለመሆኑ ተረጋግጦ ደብተሩ ተሰርዟል፡፡ ስለዚህ ክሱ ውድቅ ሊሆን የሚጋባው ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሶስተኛ ተከሣሽ ደግሞ በየካቲት 21 ቀን 1994 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው መልስ በአዋጅ ቁጥር 87/89 መሠረት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ፍ/ቤት ነው፡፡ ቤቱ መንግሥት የያዘው ትርፍ ቤት በመሆኑና የሚያስረክብ ሰውም በመታጣቱ ምክንያት ነው፡፡ ቤቱ ትርፍ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻለውም በጊዜው በምን ሁኔታ ላይ እንደነበረ በመመልከት ነው፡፡ በወቅቱ ቤቱን በሚመለከት የተገኘው ሰነድ ቅጽ 000 ሲሆን የቤቱ ባለቤት ማለት አከራይ የነበሩት አቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ከሣሾች ቁጥሩ 160 የሆነውን ቤት አያያዛቸው አጠያያቂ ሆኖ ሳለ በትርፍነት መንግሥት በወረሰው ቤት ላይ /ቁጥር 159/ የባለቤትነት ደብተር ሲያወጡ ተጣርቶ ደብተሩ እንዲመለስ ተወስኖባቸዋል፡፡ ከሣሾች የእነሱ ባልሆነ ቤት ላይ ደብተር ሊያወጡ እና ባለቤት ነን ሊሉ አይችሉም በማለት ተከራክሯል፡፡

በሌላ በኩል አንደኛ ተከሣሽ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ በተከሣሽ ከሣሽነት ክሱም ቁጥሩ 159 የሆነው ቤት በትርፍነት ተወርሶ አቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም ያስረከቡት መሆኑ ታውቆ የወሰዱትን ደብተር እንዲመልሱ በከሣሾች አውራሽ ላይ የተወሰነ ቢሆንም ስላልመለሱ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩን እንዲመልሱ ይወስንልን በማለት ጠይቋል፡፡

ከሣሾች ደግሞ ለቀረበባቸው የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ በሰጡት መልስ አቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም በወቅቱ የቤቱ ተከራይ እንጂ ባለቤት ስላልሆኑ ቤት ለማስረከብ ወይም ለማስወረስ የሚያስችል መብት የላቸውም፡፡ የተከሣሽ ከሣሽ ደብተሩ እንዲመለስ በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ስለሌለው ጥያቄው ውድቅ ሲሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡



ፍ/ቤቱም ቤቱ በትርፍነት በቅጽ 000 ላይ ከመመዝገቡ በስተቀር የተወረሰ ለመሆኑ የሚያሳይ በቅጽ 003 የተሞላ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ቤቱ ቀደም ብሎ የአቶ ይፍሩ አማረብህ መሆኑንና አቶ ወንዳፍራሽ ገመዳ እንደገዙት አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመዉጣቱ በፊት ቤቱን አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ ያከራዩት እንደነበር ቤቱ በአዋጁ መሠረት ያለወመረሱን አቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም ተከራይ እንጂ የቤቱ ባለቤት ያለመሆናቸውን ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም ቤቱ የተወረሰ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በተከሳሾች ያልቀረበ ስለሆነ ተከሣሾች ቤቱን ለከሣሾች እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የተከሳሽ ከሣሽ ያቀረበውን ክስም ውድቅ አድርጎታል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አመልካች በሆነው የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት የቀረበው አቤቱታም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ቤቱ የተጠሪዎች አይደለም ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው የከተማ ነክ ፍ/ቤት ነው፡፡ ፍ/ቤቶቹ ክሱን ያዩት ሥልጣን ሳይኖራቸው ነው፡፡ በወረዳ 6 ቀበሌ 02 የሚገኘው ቁጥሩ 159 የሆነውን ቤት ያስረከቡት አቶ ሽዋለም ሃ/ማርያም ናቸው፡፡ በዚህ መሠረት ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ተወርሷል፡፡ አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ በቤቱ ላይ የቤት ባለቤትነት ደብተር ያወጡት በሌላቸው መብትና ከደንብ ውጭ ነው፡፡ የባለቤትነት ደብተሩ የተወሰደው ከደንብ ውጪ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1196/1/ መሠረት በአስተዳደራዊ ውሣኔ ተሰርዟል፡፡ የቤት ባለቤትነት ደብተሩ በዚህ ሁኔታ መሠረዙም በአግባቡ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክሱ የቤት ባለቤትነት ደብተሩን እንድንመልስ የተሰጠው ትዕዛዝ ይሻርልኝ የሚል ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቶች ተከሣሾች ቤቱን ለከሣሾች እንዲያስረክቡ በማለት የሰጡት ውሣኔ ክስ ያልቀረበበትን ጭብጥ በመያዝ በመሆኑ ውሣኔው ሥነ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው በመሆኑ ውሣኔው እንዲሻርልኝ ሲል አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች ደግሞ በሰጡት መልስ አመልካች በሥር ፍ/ቤት በማስረጃነት ያቀረበው ሰነድ የቤቶቹ መመዝገቢያ ቅጽ የሆነው ቅጽ 000 እንጂ ቤቱ የተወረሰ ለመሆኑ የሚያሳይ ቅጽ 003 አይደለም፡፡ ቤቱ የግል መሆኑ ታውቆ የቤት ባለቤትነት ደብተር ተሰጥቷል፡፡ ክርክሩ የግል ቤት የተመለከተ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ሥልጣኑ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ ክሱም የቀረበው የቤት ባለቤትነት ደብተሩን እንድንመልስ የተሰጠውን ትዕዛዝ ለማሰረዝና ቤቱን ለማስለቀቅ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሚነቀፍበት አንዳችም የሕግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ውሣኔው ፀንቶ ልንሰናበት ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በበኩላችን ደግሞ የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ በወረዳ 6 ቀበሌ 02 የሚገኘውን ቁጥሩ 159 የሆነውን ቤት በሚመለከት የወሰዱት የቤት ባለቤትነት ደብተር እንዲመልሱ በማለት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ቤት ውሣኔ መሻር የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? ቤቱ ለተጠሪዎች ሊመለስላቸው ይገባል ወይስ አይገባም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

መዝገቡን እንደመረመርነውም ተጠሪዎች ክርክር ያስነሳው ቤት የአውራሻቸው የአቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ መሆኑን ለማስረዳት የሞከሩት በሰው ማስረጃ ሲሆን ያቀረቡዋቸው ምስክሮችም አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ቤቱን ከአቶ ይፍሩ አማረብህ የገዙት መሆኑን ነው የገለጹት፡፡ ሌሎች ሁለት ምስክሮች ደግሞ የገለጹት ቤቱ አቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም በኪራይ ይኖሩበት እንደነበሩ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ተጠሪዎች ቤቱ የአውራሻቸው ስለመሆኑ የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡

አመልካች ደግሞ ቤቱን በትርፍነት ያስመዘገቡትና ለመንግሥት ያስረከቡት አቶ ሸዋአለም ሃ/ማርያም በመሆናቸው ቤቱ የአቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ አይደለም በማለት ይህን እንዲያስረዱለት ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሆነው ቅጽ 000 ቤቱ የአቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም መሆኑን ነው የሚገልፀው፡፡

በሌላ በኩል የተጠሪዎች አውራሽ የሆኑት አቶ ወንድአፍራሽ ገመዳ ሌሎች ቤቶቻቸውን በትርፍነት ሲያስመዘግቡ መርጠው ከውርስ ያስቀሩት ቁጥሩ 160 የሆነውን ቤት ስለመሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በትርፍነት አስመዝግበው ለመንግሥት ያስረከቡዋቸው ቤቶች ቁጥር 149፣ 150፣ 151፣ 161፣ እና 162 ሲሆኑ ቁጥሩ 159 የሆነው ክርክር ያስነሳው ቤት ደግሞ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመውጣቱ በፊት ሌላ ሰው የተከራየው ኪራይ ቀመስ ሆኖ መቆየቱንና አዋጁ ከወጣ በኋላም በኪራይ ቤትነት የቀጠለ ስለመሆኑ ክርክሩ ያስረዳል፡፡ የተጠሪዎች አውራሽ ሌሎቹ ቤቶቻቸውን በትርፍነት ሲያስረክቡ ቁጥሩ 159 የሆኑውን ቤት መርጠው ያስቀሩት ስለመሆኑ ወይም ደግሞ በትርፍነት ለመንግሥት ያስረከቡት መሆኑን የሚልጽ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች ለመገንዘብ የሚቻለውም የተጠሪዎች አውራሽ ቤቱን በምርጫ ያላስቀሩት ወይም ደግሞ በትርፍነት ለመንግሥት ያላስረከብኩት በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት ያልነበራቸው መሆኑን ነው፡፡

በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የከተማ ትርፍ ቤትና ቦታ የመንግሥት በሆነበት ጊዜ የተጠሪዎች አውራሽ ቤቱን በምርጫ ሳያስቀሩት ወይም ደግሞ በትርፍነት ሳያስመዘግቡትና ለመንግሥት ሳያስረክቡት በአቶ ሸዋለም ሃ/ማርያም አማካኝነት በትርፍነት ተመዝግቦ መንግሥት ተረክቦት በባለቤትነት ሲያስተዳድረው ለአመታት ከቆየ በኋላ በምርጫ ካስቀሩት ቁጥሩ 160 ከሆነው ቤት ጋር በማያያዝ የቤት ባለቤትነት ደብተር ያወጡበት የቤት ባለቤትነት መብት ሳይኖራቸው መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ባጋጠመበት ጊዜ የአስተዳደር ክፍሉ ቀደም ሲል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት የሰጠውን የባለቤትነት የምስክር ወረቀት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196/ሀ/ መሠረት ለማስመለስና ለመሰረዝ እንደሚችል በሕግ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ተጠሪዎች የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ

የቤት ባለቤትነት ደብተሩ እንዲመለስ በማለት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ቤት እንዲሻርልን በማለት ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ደብተሩ ለአስተዳደር ክፍሉ መመለስ የለበትም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ የተጠሪዎች አውራሽ ቤቱን በምርጫ ከውርስ ያስቀሩት ወይም ደግሞ በትርፍነት የተመዘገበና መንግሥት የልወረሰው መሆኑን ባላስረዱበት ይልቁንም ቤቱን በትርፍነት ያስመዘገቡትና ለመንግሥት ያስረከቡት አቶ የሸዋአለም ሃ/ማርያም መሆናቸው በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ቤቱ የተጠሪዎች አውራሽ በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች የሚያስረክቡበት ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ ስንመለከትም ተጠሪዎች የአስተዳደር ክፍሉ የቤት ባለቤትነት ደብተሩን እንድንመልስ የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሰረዝልን በማለት ያቀረቡትን ክስ መነሻ በማድረግ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲመልስ በማለት ፍ/ቤቶቹ መወሰናቸው በአግባቡ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ቤቱን የመረከብ ጥያቄ በተጠሪዎች ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ አልቀረበም፡፡ በጭብጥነትም ተይዞ ግራ ቀኙ አልተከራከሩበትም፡፡ ዳኝነት ባልተከፈለበት፣ በክሱ በግልጽ ባልተጠየቀና በጭብጥነት ተይዞም ግራ ቀኙ ባልተከራከሩበት ነጥብ ላይ ውሣኔ መስጠት ስለማይቻልም የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትና ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04258 የካቲት 17 ቀን 1998 ዓ.ም. የፌ/ከ/ፍ/ቤት ደግሞ በመ/ቁ. 46860 የካቲት 21 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ቀደም ብሎ የወጣው የቤት ባለቤትነት ደብተር የተሰጠው ከደንብ ውጪ ሆኖ ካገኘው ደብተሩን የማስመለስና የመሰረዝ ስልጣን ያለው በመሆኑና ተጠሪዎች በዚህ ጉዳይ ቅሬታ ካላቸው ደረጃውን ተከትለው በአስተዳደር ክፍሉ እንዲጣራላቸው ከሚያደርጉ በስተቀር ደብተሩን እንዲመልሱ የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ቤት ውሣኔ የሚሻርበት ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን እንዲችሉ ብለን መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰበር መ/ቁ. 29860

መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

አብዱራሂም አህመድ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ ቀረቡ

2. ወ/ሮ የሺመቤት አየነው ቀረቡ

3. ወ/ሮ ደብረወርቅ አየነው

4. ወ/ሮ ብዙየ አየነው

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 32110 ግንቦት 9 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 22931 ጥር 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ሚያዝያ 1 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በመጠየቃቸው ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይ በዚህ መዝገብ ተጠሪ የሆኑት ሰዎች አንደኛ ተጠሪ የሟች ፊታውራሪ አየነው ገብረመድህን ሚስት ከሁለተኛ እስከ ሶስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች ደግሞ ልጆች መሆናቸውን በመግለጽ ሟች ፊታውራሪ አየነው ገብረመድህን ለወ/ሮ ወለተኪዳን በህይወት እስካሉ ድረስ ብቻ እንዲኖሩበት መስከረም 22 ቀን 1960 ዓ.ም ባደረጉት የስጦታ ውል በወረዳ 11 ቀበሌ 2 የቤት ቁጥር 631 የሆነውን ቤት ሰጥተዋቸው ነበር፡፡ ወ/ሮ ወለተኪዳን በህይወት በመኖራቸው በዚሁ ቤት ውስጥ ሲኖሩ ቆይተው የሞቱ ስለሆነ ቤቱን ያስረክቡን ብለው አመልካችን በመክሰሳቸው ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር የሰማው የሥር ፍርድ ቤት ለተጠሪዎች ቤቱን ማስረከብ አለባችሁ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ይግባኝ ብለው በፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኙ ከተሰማ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል፡፡ ተጠሪዎች ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡ አመልካችና ተጠሪዎች በዚህ ፍርድ ቤት ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ አዋጅ ቁጥር 47/67 እና የፍትሐብሔር ህጉ የንብረት ድንጋጌዎችና እና የይርጋ ድንጋጌዎችን ስላላቸው ተፈፃሚነት የቃልና የጽሑፍ ክርክር አቅርበዋል፡፡

እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ወ/ሮ ወለተኪዳን ቤቱን ከያዙት በኋላ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ንብረት ለማድረግ አዋጅ ቁጥር 47/1967 ታውጇል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2/3/ሀ/ መሠረት ትርፍ ቤት ማለት አንድ ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ለመኖሪያ ከሚያስፈልገው ወይም ከያዘው አንድ መኖሪያ ቤት ውጪ ያለ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሟች ፊታውራሪ አየነው ለወ/ሮ ወለተኪዳን በቤቱ የመጠቀም መብት ብቻ በውል ያስተላለፉ በመሆናቸው አዋጁ ሲታወጅ በወረዳ 11 ቀበሌ 2 የቤት ቁጥር 631 እና በወረዳ 11 ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 634 ባለቤት እንደሆኑ ከህጉ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሟች ፊታውራሪ አየነው የቤት ቁጥር 634 በምርጫ ይዘዋል፡፡ ይህ ከሆነ ወ/ሮ ወለተ ኪዳን ይኖሩበት የነበረው ቁጥሩ 631 የሆነው ቤት በአዋጁ አንቀጽ 2/3/ሀ/ መሠረት ትርፍ ቤት ነበር፡፡ ፊታውራሪ አየነው ይህንን የመጠቀም መብት ለወ/ሮ ወለተኪዳን በውል ያስተላለፉትን ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አዋጁ በታወጀ በሰላሣ ቀን ውስጥ ማስመዝገብና ማሣወቅ ሲገባቸው በዚህ የህግ ድንጋጌ መሠረት ግዴታቸውን አልተወጡም፡፡ ሆኖም ፊታውራሪ አየነው ቤቱን በአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ 2

መሠረት አለማሣወቃቸው የቤቱ ባለቤት ይዘው ለመቆየት የሚያስችላቸው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማዘጋጃ ቤት ወይም በከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ ትርፍ ቤት ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ የመንግስት ንብረት እንደሆነ በግልጽ ስለሚደነግግ ነው፡፡ በመሆኑም የቤት ቁጥር 631 አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ ትርፍ ቤት የነበረ በመሆኑ ከነሐሴ 1 ቀን 1967 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የመንግስት ንብረት ሆኗል፡፡ ስለሆነም ፊታውራሪ አየነው ከነሐሴ 1 ቀን 1967 ዓ.ም ጀምሮ በፊት በነበረው ስያሜ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 11 ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 631 ላይ የነበራቸው የባለቤትነት መብት በህግ ተቋርጧል፡፡ ይህ ከሆነ የተጠሪዎቹ መብት በሚች ፊታውራሪ አየነው መሞት ምክንያት የማይቋረጡ መብትና ግዴታዎች ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ይህም በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሟች ፊታውራሪ አየነው ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ የባለቤትነት መብት የሌላቸውና በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ መንግስት የዞረ ስለሆነ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ ወ/ሮ ወለተኪዳን ከያዙት ከሠላሣ ዓመት በኋላ የይገባኛል ጥያቄ የማቅረብ መብት የላቸውም የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንፃር በመመልከት ተጠሪዎችን በቤቱ ላይ የይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችላችሁ በቂ ምክንያት የለም ብለው ማሰናበት ሲገባቸው ጉዳዩን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1168 አንፃር ብቻ በመመልከት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የቤቱ ባለቤት ሆነዋል ወይስ አልሆኑም የሚለውን ነጥብ የወሰኑት የቤቱ ባለቤት ፊታውራሪ አየነው እንደሆኑ በመቁጠር ነው፡፡ ነገር ግን ከነሐሴ 1 ቀን 1967 ዓ.ም. ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 47/1967 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የባለቤትነት መብታቸው በህግ ለመንግስት የተላለፈ በመሆኑ በፍርሐብሔር ህግ ቁጥር 1168 መሠረት ወ/ሮ ወለተኪዳን የቤቱ ባለቤት



መሆን አይችሉም የሚለውን መከራከሪያ ለማንሳትና አመልካችን ለመሟገት የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት አካል እንጂ ተጠሪዎች አይደሉም፡፡

በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የክርክሩን መሠረታዊ ጭብጥ ወደ ጐን በመተውና የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን ለመንግስት ለማድረግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 47/1967 ድንጋጌዎች ሳያገናዘቡ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 32110 ግንቦት 9 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 22931 ጥር 21 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 32110 ህዳር 1 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 31490

ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ነ/ፈጅ ቀርቧል፡፡

**ተጠሪ፡-** ሴርኮ እስራኤላዊያን - ጠበቃ ቀርበዋል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ ከሣሽ በመሆን በአመልካቹ ላይ ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም ያቀረበው ክስ፣ የአሁን አመልካች ቤቱን ያለሕግ አግባብ ይዞ በመቆየቱ ከመጋቢት 9 ቀን 1971 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 9 ቀን 1994 ዓ.ም ላለው ጊዜ ያጣሁትን ጥቅም እና የደረሰብኝን ጉዳት ብር 363,931/ሦስት መቶ ስልሳ ሦስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሠላሳ አንድ/ ከወጪና ኪሣራ ጋር ይክፈለኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች ቀርቦ በሰጠው መልስ የተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያቀረበ ሲሆን ከመቃወሚያዎቹም አንዱ በአዋጅ ቁ.193/92 አንቀጽ 2/3/ መሰረት ከአዋጅ ውጭ የተወረሱ ቤቶች በመንግስት እጅ በቆዩበት ጊዜ ለታጣ ገቢ ክፍያ መጠየቅ ስለማይቻል ክሱ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የቀረበውን መቃወሚያ ከግንዛቤ በማስገባት በሰጠው ውሣኔ ቤቱ በመንግስት እጅ የቆየው ከአዋጅ ውጭ ተወስዶ በመሆኑ አዋጅ ቁ.193/92 በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል ስለዚህ ወደ ፍሬ ጉዳይ



ክርክሩ መግባት ሣያስፈልግ የተጠሪውን ክስ ውድቅ አድርጌዋለሁ በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

ተጠሪው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አሰምተዋል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤትም አመልካችን አስቀርቦ ግራ ቀኙን በማከራከር መዝገቡን መርምሮ በሰጠው ውሣኔ የክፍያው ጥያቄ ከዋጅ ቁ. 193/92 አኳያ ተቀባይነት የለውም ተብሎ በስር ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ቢቀርብም የዚህ አይነቱ መቃወሚያ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 244 ስር ያልተሸፈነና የፍሬ ጉዳይ ክርክር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ እስከሰጠበት ድረስ በቁጥር 341 መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ወደ ስር ፍ/ቤት የሚመልሰው ሆኖ አልተገኘም፣ በሌላ በኩል አመልካቹ በስር ፍ/ቤት ያቀረባቸው ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ፍ/ቤቱ ብይን ሣይሰጥ በዚሁ ነጥብ ላይ ተመስርቶ በሰጠው ፍርድ አመልካቹን ረቺ ቢያደረግም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ባለመስጠቱ አመልካች መስቀለኛ ይግባኝ ያላቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ሊመለከተው የሚችል ሆኖ አልተገኘም በሚል አመልካቹ አላግባብ ለበለፀገበት ብር 62,970 /ስልሣ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ/ ከተለያዩ ወጪና ኪሣራ ጭምር ለተጠሪው እንዲከፍል ወስኗል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካቹ ይግባኛቸውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፌ/ከ/ፍ/ቤት እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ፈጽመዋል በማለት አመልካቹ ለዚህ ችሎት ሰኔ 22 ቀን 1999 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ይህም ችሎት የአመልካቹን አቤቱታ መሰረት በማድረግ በዚህ ጉዳይ አመልካች ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ካቀረባቸው የመልስ መቃወሚያዎች ውስጥ አንዱ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ ውድቅ ቢደረግለትም መስቀለኛ ይግባኝ ካላቀረበ በስተቀር በቀሪዎቹ ነጥቦች ላይ የቀረበው ክርክር ሊታይለት አይገባም የመባሉን

አግባብነት ለማጣራት ተጠሪን አስቀርቦ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ መዝገቡንም አግባበነት ካላቸው ህጐች አንፃር መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ለቀረበበት ክስ በስር ፍ/ቤት ቀርቦ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ያላቸውን አምስት ነጥቦችን እና መቃወሚያዎቹ ቢታለፉ በሚል ደግሞ ለክሱ ዝርዝር መልሱን አቅርቧል፡፡ የመ/ደ/ፍ/ቤቱም በሰጠው ውሣኔ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከተባሉት ነጥቦች አንዱን መርምሮ፣ ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክር መግባት ሣያስፈልግ ክሱን ውድቅ አድርጌዋልሁ በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ፍ/ቤቱ አመልካቹ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሲል ያቀረበውን ነጥብ እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነቱ ተቀብሎ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አግባብ ቀሪ መቃወሚያዎችንና የፍሬ ጉዳይ ክርክሮችን ሣይመረምር ክሱን ውድቅ ማድረጉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በማንኛውም ቀመር የክሱ ውድቅ መደረግ አመልካችን ተጠቃሚ ወይም ረቺ የሚያደርግ እንደመሆኑ አመልካቹ ቀሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች እና የፍሬ ጉዳይ ክርክሮች ሊመረመሩ ይገባ ነበር ሲል ይግባኝ እንዲል የሚጠበቅበት አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካቹ ይግባኝ ሊጠይቅ ሲችል አልጠየቀም በሚል የአመልካች መቃወሚያ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አይደለም ለዚህ ጉዳይም አግባብነት የለውም በማለት አመልካቹ ሌሎቹን መከራከሪያዎች እንዳመነ ያህል ሌሎቹን መቃወሚያዎችና የፍሬ ነገር ክርክሮች ሣይመረመር ውሣኔ መስጠቱ የአመልካቹን ፍትህ የማግኘት መብት በእጅጉ የሚያጣብብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእርግጥ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የቀረበው መቃወሚያ ከፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ. 244 አንፃር አግባብነት የለውም ማለቱ የሚነቀፍ ባይሆንም፣ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ ለማድረግ የተከተለው አካሄድ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት ሲያገኝ በሚፈፀመው አግባብ ከመሆኑ አንፃር ሌሎች በፍ/ቤቱ ያልተመረመሩ መቃወሚያዎችና መከራከሪያዎች መኖራቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ መቃወሚያው በማንኛውም ምክንያት ውድቅ ሲደረግ እንደሚፈፀመው ሁሉ



በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ቀሪ መቃወሚያዎችንና መከራከሪያዎችን መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ወደ ስር ፍ/ቤት ሊመልሰው ሲገባ አመልካቹ ይግባኝ አልጠየቁምና ቀሪ መከራከራያዎቻቸው አይታዩም ሲል ውሣኔ መስጠቱ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም ሲል ይግባኙን መሰረዙ በተመሣሣይ ሁኔታ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1) የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39329 ሚያዝያ 14 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ብይን ውድቅ መደረጉን ተገንዝቦ የቀሩትን መቃወሚያዎችና መከራከሪያዎች መርምሮ የመሰለውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341 መሰረት ይመለስለት ብለናል፡፡
2) የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 40110 በግንቦት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
3) የፌ/ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27255 መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
4) ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 31682

መጋቢት 12 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሒሩት መለሠ

መድህን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ

ተጠሪዎች፡- 1. ዘላለም ይልማ ባልቻ

2. መሠረት ይልማ ባልቻ

3. አዳሙ ይልማ ባልቻ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የዚህ ክርክር መነሻ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪዎች ከወረዳ 5 ቀበሌ 23 አስተዳደር እና አቶ ፈይሣ ቦንሣ ከተባሉት ግለሰብ ጋር ባደረጉት ክርክር በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ቁጥራቸው 308 እና 309 የሆኑትን ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 መሠረት መወረሣቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ቤቶቹ ለተጠሪዎቹ ይመለሱ ሲል የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ይህ ተከራካሪ ባልሆንኩበት የተሠጠው ውሣኔ እንዲነሣ ሲሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358ን ጠቅሰው በመቃወም ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልክተዋል፡፡ አመልካቹ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በሐምሌ 17 ቀን 1998 ዓ.ም. ጽፈው ያቀረቡት ማመልከቻ ይዘት ሲጠቃለል ቁጥሩ 309 የሆነው ቤት በአ/ቁ. 47/67 መሠረት በትርፍነት የተወረሠ ሲሆን አመልካቹ በአ/ቁ/2/1995 አንቀጽ 46/1/ መሠረት ቤቱን እንዲያስተዳድር ስልጣን ተሠጥቶታል በመሆኑም ተጠሪዎች /የስር ከሣሾች/ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ባላቀረቡበት ሁኔታ ቤቱን እንዲረከቡ የተሰጠው ውሣኔ መብቱን የሚጎዳ በመሆኑ ሊነሣ ይገባዋል የሚል ነው፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የአመልካቹን ተቃውሞ እና የተጠሪዎቹን መልስ መርምሮ



በጥቅምት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ. 21594 በሰጠው ፍርድ በመቃወም አመልካች ቁጥሩ 309 የሆነውን ቤት ለማስተዳደር መብት ያለው መሆኑን ያላስረዳ በመሆኑ ፍ/ቤቱ በጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ሊነሣ የሚገባ ሆኖ አላገኘውም ሲል ተቃውሞውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት አመልካች አቤቱታቸውን በይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካቹም የስር ፍ/ቤቶች ተቃውሞውን ውድቅ ማድረጋቸው አ/ቁ. 47/67ን በሚገባ ያልመረመረና ያላገናዘበ በመሆኑ ቁጥር 309 የሆነው ቤት ለተጠሪዎች እንዲመለስ የተሠጠው ውሣኔ በውሣኔ እንዲሻር ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሐምሌ 2 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡ ይህም ችሎት የአመልካቹን የሠበር አቤቱታ መርምሮ ክርክር የተነሣበት ቤት በአ/ቁ 47/67 መሠረት ለመወረሱ ማስረጃ አልቀረበም በሚል ቤቱ ለተጠሪዎች እንዲመለስ መወሰኑ አግባብ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲል ተጠሪዎችን አስቀርቧል፡፡ የሰበር ተጠሪዎችም ለአመልካች አቤቱታ በሐምሌ 30 ቀን 1993 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካቹም አቤቱታውን በመልስ መልሱ አጠናክሮ ቀርቧል፡፡

ይህም ችሎት የግራ ቀኙን ክርክርና የሥር ፍ/ቤት ውሣኔዎችን በጥሞና መርምሯል፡፡ እንደተመረመረውም ከሁሉ አስቀድሞ ምላሽ የሚሻው ጭብጥ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቀድሞውንስ ቢሆን በዚህ ጉዳይ የቀረበለትን ክስ ተቀብሎ የማከራከር ስልጣን ነበረው ወይ? የሚለውን ነጥብ መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በወረዳ 5 ቀበሌ 23 አስተዳደር ጽ/ቤት እና በአቶ ፈይሣ ቦንሣ ላይ ያቀረቡት ክስ ተከሣሾቹ በአ/ቁ. 47/67 ያልተወሰነበትን ቁጥራቸው 308 እና 309 የሆኑት ቤቶች አላግባብ ስለያዙብን ለቀው እንዲያስረክቡን የሚል ነበር፡፡ የአሁኑ የሰበር አመልካችም ሆነ በስር ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረው የቀድሞው ወረዳ 5 ቀበሌ 23 ጽ/ቤት ለክርክሩ መንስኤ የሆኑት ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 ተወርሰው የሚያስተዳድሯቸው

መሆናቸውን በመግለጽ ተከራክረው የነበረ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ቤቶቹ ስለመወረሣቸው የሚያረጋግጥ ተገቢው ቅጽ አልቀረበም በሚል ቤቶቹ ለአሁን ተጠሪዎች እንዲመለስ በማለት ወስኗል፡፡ በመሠረቱ አዋጅ ቁጥር 47/67ን መነሻ አድርጎ አላግባብ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን አዋጁን ለማስፈጸም ለተቋቋመው የሚኒስቴር መ/ቤት በኩል እየተመረመሩ ተገቢውን ውሣኔ ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ በአዋጁ ተመልክቷል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ የምርጫ ቤቴን በቀላጤ፣ በቃል ትዕዛዝ ወይም በመመሪያ ከሕግ ውጭ ተወሰደብኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሠረት ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን እንደሚገባቸው በሕጉ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ ክፍሎች የሚሰጡ የባለቤትነት ማስረጃዎችን መሠረት አድርገው በሚቀርቡ የባለሃብትነት ጥያቄዎች ላይ ፍ/ቤቶች እንደነገሩ ሁኔታ ስልጣን ከሚኖራቸው በቀር ተወርሰዋል ተብለው በመንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት አድርገው ፍ/ቤቶች የቤቱን መወረስና አለመወረስ ለማረጋገጥ ማስረጃዎች መርምረው የሚደርሱባቸው መደምደሚያዎች ለፍ/ቤቶች በሕግ ያልተሰጣቸው ስልጣን ከመሆኑም ባሻገር የአስፈፃሚ አካላቱን ስልጣንና ተግባር በግልጽ የሚቃረን ነው፡፡ በዚህ በተያዘው ጉዳይ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ክርክር በተነሣባቸው ቤቶች ላይ ከአስፈፃሚ አካላቱ የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ባላቀረቡበት ሁኔታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆኑት ቤቶች በአ/ቁ. 47/67 መሠረት ትርፍ ናቸው ተብለው ለመወረሣቸው መቅረብ ይገባው የነበረው ቅጽ 003 በወረዳ 5 ቀበሌ 23 ጽ/ቤትም ሆነ በአሁኑ አመልካች አልቀረበም በሚል ቤቶቹ አልተወረሱም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡



## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪዎች አግባብ ካላቸው አስፈፃሚ አካላት የባለቤትነት ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ በሕግ ባልተሰጠው ስልጣን ቤቶቹ በአ/ቁ. 47/67 ተወርሠዋል ወይስ አልተወረሱም የሚለውን ነጥብ መርምሮ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው፡፡
2. ይህ ውሣኔ ተጠሪዎች በቤቶቹ ላይ አለን የሚሉትን መብት አግባብ ላለው አካል አቅርበው ከመጠየቅ አያግዳቸውም፡፡
3. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በጥር 15 ቀን 1998 ዓ.ም. በመ/ቁ 21594 የሰጠው ውሣኔ የቤት ቁጥር 309 በተመለከተ ብቻ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጥቅምት 13 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ 21594 ቁጥር 309ን በተመለከተ ብቻ የሰጠው ፍርድ ተሽሯል፡፡
5. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በሚያዝያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ. 50128 ቁጥር 309ን በተመለከተ ብቻ የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32376

ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃደር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድሕን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት አልቀረቡም

**ተጠሪ-** እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች በአመልካችና በሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ላይ ባቀረቡት ክስ ከወላጅ አባታችን በውርስ የተላለፈልንን በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቀበሌ 10 ክልል የሚገኝ ቤታችንን 1ኛ ተከሳሽ ከአዋጅ 47/67 ውጭ ያለአግባብ በመያዝ ለ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በመከራየት ላይ ስለሚገኝ ይህንኑ ያለ አግባብ ይዘው የሚገኙትን ቤታችንን ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ቀርቦ በሰጠው መልስ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች በአዋጅ 47/67 መሰረት የተወረሱ ወይንም ያልተወረሱ ለመሆናቸው የሚጠቁም ማስረጃ በ1983 ዓ.ም በመዘረፉ ምክንያት ማቅረብ አልቻልንም፡፡ በአሁኑ ሰአት ይህ ክስ መመስረቱ አግባብነት የሌውና ተከራዮችን የሚጐዳ ነው፡፡ ጉዳዩም መታየት ያለበት በፍ/ቤት ሳይሆን በየፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በኩል ስለሆነ መዝገቡ ሊዘጋ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾችም በበኩላቸው ባቀረቡት መልስ ከሳሾች ቁጥራቸው 204(1) እና 204/2/ የሆኑት ቤቶች ሊመለሱልን ይገባል በማለት ቀደም ሲል ለወረዳ 27 ፍ/ቤት ክስ አቅረበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለውም በማለት ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ በድጋሚ ለፍ/ቤቱ ክሱ መቅረቡ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 አኳያ ተቀባይነት ስለሌለው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩ አስቀድሞ ውሳኔ ያገኘ ነው ተብሎ የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ የወረዳ 27 ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው ከማለት በስተቀር የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን ተመልክቶ ውሳኔ ያልሰጠ በመሆኑ ክርክሩ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 ሥር ስለማይወድቅ በዚህ ረገድ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አግባብነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ከዚህም ሌላ 1ኛ ተከሳሽ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ሳይሆን የኢትዮጵያ የፕራይቬታይዜሽን ነው በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ አስመልክቶም በአዋጅ 110/87 መሰረት ለኤጀንሲው ሥልጣን የተሰጠው በቃል ትእዛዝ፣ በቀላጤ ወይንም በመመሪያ አንድ ንብረት ተወስዶ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ ስለተመለከተና ከሳሾች በዚህ መንገድ ቤቱ ተወስዶብኛል ያላሉ ስለሆነ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡

ከዚህ በኋላም በፍሬ ጉዳይ ረገድ የተደረገውን ክርክር ከማስረጃው ጋር አገናዝቦ መርምሮ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች የተወረሱ ስለመሆናቸው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ስለሆነ 1ኛ ተከሳሽ ከ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጋር ያደረገውን የኪራይ ውል በማቋረጥ ለከሳሾች ቤቱቹን እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመከተው የከተማ ነክ ይገባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 ሊጠቅስ የሚገባው አንድ የክስ ምክንያት በተከራካሪ ወገኖች ወይም ከእነዚህ ወገኖች ጥቅም የሚያገኙ 3ኛ

ወገኖች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠ በተመሳሳይ የክስ ምክንያት ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ የቀድሞ ወረዳ 27 ፍ/ቤት የቤት ይለቀቅልኝ ክርክሩን ለማየት ሥልጣን ያለው ሌላ አካል ስለሆነ ጉዳዩን አላስተናግድም በማለት በብይን መዝገቡን በመዝጋቱ በቀረበው የክስ ምክንያት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ካለመስጠቱም በላይ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/ረ/ መሰረት የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የከተማው አስተዳደር ከያዛቸው ቤቶች ጋር የሚቀርቡ ክሶችን ለማከራከር የሥረ ነገር ስልጣን ያለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ ባለመቀበል ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የሰበር አቤቱታ ቀርቦለት መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ለዚህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በሥር ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅርቱ ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የሰበር አቤቱታውም ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ነክ መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አመልካች ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበው ከአዋጅ ውጭ የተወሰደን ንብረት ባለቤትነት አጣርቶ ለመመለስ በአዋጅ ቁጥር 110/87 መሰረት ሥልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ሃራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ነው በማለት ሲሆን ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን ሳይቀበለው የቀረው ለኤጀንሲው ሥልጣን የተሰጠው ንብረቱ በቃል ትእዛዝ በመመሪያ ወይንም በቀላጤ ተወስዶ በሚገኝበት ጊዜ እንደሆነ በአዋጁ ላይ ስለተመለከተና ከሳሾች በዚህ መንገድ ክስ የቀረበበት ቤት ተወሰደብን ያላሉ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው በማለት ነው፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን አለው ያለው የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት እንዳለው ክስ የቀረበበት ቤት በቀላጤ፣ በመመሪያ ወይንም በቃል ትእዛዝ ተወስዷል ስላልተባለ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት ሳይሆን የከተማው አስተዳደር ከያዛቸው ቤቶች ጋር የሚቀርቡ ክሶችን ለማከራከር የሥረ ነገር ሥልጣን ያለው የአ/አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41 ላይ የተመለከተ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ሥልጣን አለው በሚል ነው፡፡

ይሁንና ተጠሪዎች ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በቀላጤ፣ በቃል ትእዛዝ ወይንም በመመሪያ ተወስዶብናል ያላሉ በመሆኑ በአ/ቁ. 110/87 መሰረት ጉዳዩ በኢትዮጵያ ሃራይቬታይዜሽን በኩል የሚታይ አይደለም መባሉ ተገቢነት የነበረው ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 41/ረ/ ስር ለከተማ ነክ ፍ/ቤት ሥልጣን የተሰጠው የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ጉዳዮችን በተመለከተ ስለሆነና ይህም ባለቤትነቱ የከተማው አስተዳዳር ስለመሆኑ ክርክር ሳይኖርበት ከባለቤትነት በመለስ የሚነሱ ክርክሮችን በተመለከተ እንደሆነ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በተያው ጉዳይ ተጠሪዎች ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በውርስ የተላለፈልን የግል ቤታችን ነው በማለት ባለቤተነትን የመፋለም ክስ /petitory action/ ያቀረቡ በመሆኑና በቤቱ ባለቤትነት ላይም ክርክር እስከቀረበበት ድረስ ከተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌ አኳያ የከተማ ነክ ፍ/ቤት የሥረ ነገር ሥልጣን ሊኖረው የማይችል በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የከተማ ነክ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት ተመልክተው ውሳኔ መስጠታቸው ለአዋጁ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት እንደሆነ መረዳት የተቻለ ስለሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአ.አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00148 በታህሣሥ 24 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሰኔ የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03006 በጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንደዚሁም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 04058 በግንቦት 8 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአ.አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ ለማየት የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ



የሰ/መ/ቁ. 34249

በሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኅን ኪሮስ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ - ወራሽ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ አለሙ ወንድሙ - ጠበቃ አቢይ ወርቁ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ በወረዳ 7 ቀበሌ 32 ቁጥር 074 የሆነውን ቤት ከአዋጅ 47/67 በፊት የሰራነው ሲሆን በአዋጁም አልተወረሰም፡፡ በዚሁ ቤት በስማችን የንግድ ፈቃድ አውጥተን በኃይለስላሴ ጊዜ ተከሣሾችን በግል ድርጅታችን እንዲሰሩ አስጠግተናቸው ነገር ግን እንዲለቁ ተጠይቀው ፈቃደኛ ስላልሆኑ እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሾችም ቀርበው ክስ የቀረበበት ቤት በአዋጁ ተወርሶ የአከራይ ተከራይ ግንኙነታችን ተቋርጧል፡፡ ኪራይም ለቤቱ ባለቤት ለቀበሌው አስተዳደር እየከፈልን ስለሆነ ከሣሾች ቤቱ ይለቀቅልን በማለት ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትን የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር የቀረበበትን ቤት ማኅደር አስቀርቦ በመመልከት ቤቱ የተወረሰ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ተከሳሾች ይህንኑ ክስ የቀረበበትን ቤት ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም ጉዳዩ በይግባኝና በሰበር ለከተማው ፍ/ቤት ቀርቦ ቤቱ ሊመለስ ይገባል ተብሎ በበታች ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ይህ ችሎት በቅድሚያ የተመለከተው የክርክሩን አመራር በተመለከተ ነው፡፡

የሥር ከሳሾች የአሁን ተጠሪዎች ዳኝነት የጠየቁት የግል የሆነ ቤታችን በሥር ተከሳሾች በአሁን አመልካቾች ያለአግባብ የተያዘብን ስለሆነ እንዲመለስልን ይወሰንልን በማለት ነው፡፡

ተከሳሾችም በበኩላቸው ቤቱ በመንግሥት በመወረሱ ምክንያት ከከሣሾች ጋር የነበራቸው የኪራይ ውል ተቋርጦ ከቤቱ ባለቤት ከቀበሌው አስተዳደር ጋር የኪራይ ውል በመዋዋል ኪራይ እንደሚከፍሉ ገልፀው ክሱ ሊሰረዝ ይገባዋል ብለዋል፡፡

ከሳሾች በአንድ በኩል የቤቱ ባለቤት ነን የሚሉ ከሆነና በሌላ በኩልም ቤቱ በአዋጅ በመንግሥት ተወርሷል ከተባለ ክርክሩ ባለቤትነትን የመፋለም /Petitory action/ ስለሚሆን ቤቱን በውርስ ይዞ በማስተዳደር ላይ ይገኛል የተባለው የቀበሌው አስተዳደር ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ ወገን /Indispensable Party/ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ወገን በሌለበት የሚሰጥ ውሣኔ መብቱን፣ ጥቅሙን ሊነካ እንደሚችል ስለሚታመን ነው፡፡ ይህ ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ወገን በከሳሾች በኩል በተከሳሽነት እንዲጣመር ባይደረግም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 40/2/ ላይ ለፍርድ ቤቱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ማድረግ ነበረበት፡፡

ስለሆነም በየደረጃው ባሉ የከተማ ነክ ፍ/ቤቶች ለጉዳዩ እልባት የተሰጠው ለክርክሩ እጅግ አስፈላጊ የሆነው የቀበሌው አስተዳደር የክርክሩ ተካፋይ ባልሆነበት ሁኔታ ስለሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡



**ው ሣ ኔ**

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትና ሰበር ችሎት በዚህ ጉዳይ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የሚመለከተው የቀበሌ አስተዳደር ለጉዳዩ እጅግ አስፈላጊ ወገን /indispensable party/ ስለሆነ የከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት ይህንኑ ወገን ወደ ክርክሩ በማስገባት አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ክሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# <u>እርቅ ግልግል</u>



የሰ/መ/ቁ. 22857

ታህሣሥ 15 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** እነ አቶ ተክሌ ደግፌ /2 ሰዎች/ የ2ኛ አመልካች ወራሽ ቀረበ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ /2 ሰዎች/ - ጠ/ዳንኤል ቀረበ፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት የፍርድ ባለመብቶች ሲሆኑ 1ኛ አመልካች ደግሞ የፍርድ ባለእዳ ነበሩ፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተያዘው አፈፃፀም የፍርድ ባለዕደ የሆኑት የአሁኑ 1ኛ አመልካች ቤት የፍርድ ባለመብቶቹ እንዲረከቡት የተሰጠውን ትዕዛዝ የአሁኑ 2ኛ አመልካች ተቃውመው ቀርበዋል፡፡ 2ኛ አመልካች ቤቱን ከውሣኔ በኋላ የገዙት መሆኑን ገልፀው አፈፃፀሙ እንዲቋረጥ ጠይቀዋል፡፡ ነገር ግን ፍ/ቤቱ 2ኛ አመልካች ቤቱን የገዙት ከውሣኔ በኋላ ከመሆኑም ሌላ የሽያጩን ውል ያደረጉት ከፍ/ባለዕዳው ጋር እንጂ ከፍርድ ባለመብቶች ጋር ባለመሆኑ ጥያቄያቸው ተቀባይነት የለውም በማለት አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ትዕዛዝ ላይ አመልካቾች ለፌ/ከፍ/ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል ሠርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካቾች በቅሬታቸው ላይ ነሐሴ 13 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ የእርቅ ስምምነት፣ 2ኛ አመልካች በ1ኛ አመልካች ስም ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) ለ1ኛ ተጠሪ በራሣቸውና በ2ኛዋ ተጠሪ ስም ፈርመው ገንዘብ ተቀብለው ታርቀው በዚሁ እርቅ ስምምነት መሠረት አፈፃፀሙ እንዲቋረጥ ለፍ/ቤቱ የቀረበውን

ጥያቄ ፍ/ቤቱ ያለምንም ምክንያት ውድቅ በማድረግ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ማድረጉ ስህተት ነው በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ይህ ችሎትም ጉዳዩ በእርቅ ማለቁ ለፍ/ቤት ቀርቦ እያለ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል መደረጉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ተጠሪዎች ቀርበው መልሣቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ በመልሳቸውም 1ኛ ተጠሪ ስምምነቱን የፈረሙት በሽማግሌዎች ከፍተኛ ተጽኖ እና ጫና እንጂ በነፃ ፈቃዳቸው ካለመሆኑም በላይ ከ2ኛ ተጠሪ የተሰጣቸው ውክልና ሣይኖር በመሆኑ በፍርዱ መሠረት እንዲፈጽሙ መደረጉ ስህተት የለውም ብለዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት በ1ኛ አመልካችና በተጠሪዎች መካከል በነበረው ክርክር ተጠሪዎች የ1ኛ አመልካችን ቤት እንዲረከቡ ተወስኖላቸው እንደነበር፣ ከውሣኔው በኋላ 1ኛ አመልካች ይህንኑ ቤት ለ2ኛ አመልካች መሸጣቸውን፣ ተጠሪዎች ይህንን ቤት ለመረከብ በአፈፃፀም ላይ እያሉ ደግሞ አመልካቾችና ተጠሪዎች ነሐሴ 13 ቀን 1996 በተደረገ የዕርቅ ስምምነት ጉዳያቸውን ለመጨረስ መስማማታቸውን ተረድተናል፡፡

ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት በፍ/ቤት የጀመሩትን ክርክር በፍርድ ሂደት ከመቋጨት ይልቅ በእርቅ ስምምነት ለመጨረስ ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ ክርክሩ በማናቸውም ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም በፍ/ቤት ወይም ከፍ/ቤት ውጪ በዕርቅ ወይም በግልግል ጉዳያቸውን ጨርሠው በፍ/ቤት የጀመሩትን ክርክር ለማቋረጥ እንደሚችሉም ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 274/1/ እና 275/1/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱም ይህን የዕርቅ ስምምነት በጽሁፍ ሲቀርብለት ዕርቁ ለሕግ ወይም ለሞራል የማይቃረን መሆኑን እስካረጋገጠ ድረስ ስምምነቱን ተቀብሎ በፍርድ ቤት የተያዘውን ጉዳይ ማቋረጥ እንደሚገባው ከፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 277/1/ ያመለክታል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ በራሣቸውና በ2ኛ ተጠሪ ባለቤታቸው ስም ሆነው የእርቁን ስምምነት መፈረማቸውን አልካዱም፡፡ የሚያነሱት ክርክር



ስምምነቱን በተጽኖ ነው የፈረምኩት ከ2ኛ ተጠሪም የተሠጠኝ የውክልና ስልጣን አልነበረም የሚል ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ ውሉን ከነፃ ፍላጎታቸው ውጪ በሆነ ሁኔታ እንደፈረሙ ይግለፁ እንጂ በዚህ ሁኔታ ለመፈረማቸው ያስረዱት ነገር ካለመኖሩም ሌላ ውሉ እንዲሠረዝላቸው አላደረጉም፡፡ በመሆኑም በዚህም ምክንያት በስምምነቱ መሠረት ሊፈፀም አይገባም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ከአመልካቾች አቤቱታ 1ኛ አመልካች ከተጠሪዎች በወሰዱት ብድር ምክንያት እዳው ካልተከፈለ ለዕዳው በመያዣ የተያዘው ቤት ተጠሪዎች እንዲረከቡት መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች ቤቱን በመያዣ የያዙበት እዳ ተከፍሏቸው ቤቱን ለመልቀቅ ተስማምተዋል፡፡ ነሐሴ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. ግራ ቀኙ ካደረጉት ስምምነትም ተጠሪዎች ይህ ስምምነት ከመደረጉ በፊት የወሰዱት ገንዘብ ስላነሣቸው ተጨማሪ ገንዘብ እንዲሠጣቸው ያቀረቡትን ጥያቄ አመልካቾች ተስማምተውበት ተጨማሪ ገንዘብ ለተጠሪዎች መክፈሉን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ቤቱን በመያዣ የያዙበት ዕዳ ከተከፈላቸው በኋላ በድጋሚ ቤቱን ለመረከብ አፈፃፀሙ ሊቀጥል ይገባል በማለት የቀረቡት ክርክር ከቅን ልቦና ውጪ ከመሆኑም በላይ ለአንድ ዕዳ ሁለት ጊዜ ክፍያ እንዲፈፀምላቸውና አላግባብ እንዲበለጽጉ የሚያደርግ ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ቢሆን ግራ ቀኙ ያቀረቡት ለእርቅ ስምምነት ለሕግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ መሆን አለመሆኑን መርምሮ ካልሆነ እርቁን በመመዝገብ አፈፃፀሙን ማቋረጥ ሲገባው በውሣኔው መሠረት ቤቱን ተጠራዎች እንዲረከቡ ትዕዛዝ መስጠቱ የእርቅ ስምምነት ጉዳይን ስለመጨረስ የሚደነግጉትን የሥነ ስርዓት ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ በመ/ቁ 05393 ኀዳር 7 ቀን 1998 ዓ.ም. የሠጠው ትዕዛዝ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43087 በታህሳሥ 11 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዞች ተሽረዋል፡፡
2. ግራ ቀኙ ነሐሴ 13 ቀን 1996 ዓ.ም. ያደረጉት ስምምነት ሕግና ሞራልን የማይቃረን በመሆኑ በእርቁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 277 የተመዘገበ በመሆኑ የተጀመረው አፈፃፀም ተቋርጦ በዕርቁ መሠረት እንዲፈጸም ታዟል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 25912

ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

መድኅን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የአቶ ብሩ ቆርቾ ወራሽ ብርቅነሽ ብሩ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ክፍሌ ሐብደታ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00808 ጳጉሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26283 ሰኔ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ይታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪው አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ቁጥሩ 292 የሆነውን ቤት ብር 4500 /አራት ሺ አምስት መቶ ብር/ የሸጡልኝ ስለሆነ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በበኩላቸው ጉዳዩ ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ባደረጉት ዕርቅና ግልግል ያለቀ ስለሆነ ቤቱን ያስረክቡኝ የሚለው ክስ ተገቢነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ አመልካች ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም በተስማሙት መሠረት የተቀበሉትን የቤቱን ዋጋ ብር 760 /ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እና የገደብ መቀጫ ብር 2000 /ሁለት ሺ ብር/ ለተጠሪ አሟልተው ያልከፈሉ ስለሆነ በቤት ሽያጭ ውሉ መሰረት ቤቱን እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤትም በይግባኝ የሚያስቀርብ ነጥብ የለውም በማለት ዘግቶታል፡፡ አመልካች ይኸ ውሣኔ ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረግነውን ስምምነት ወደ ጐን በመተው የተወሰነ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪው በበኩል አመልካቹ በዕርቁ ውል መሰረት ያልፈፀመ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረነዋል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው አመልካችና ተጠሪው ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም የግልግል ውል ያደረጉ መሆኑ አልተካደም፡፡ አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የግልግል ስምምነት አመልካች ከተጠሪው የተቀበለውን ብር 760 /ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እና የቤት ሺያጭ ውሉ በመቅረቱ መቀጫ ብር 2000 /ሁለት ሺ ብር/ ሲከፍል ተጠሪው ደግሞ አመልካች ቤቱን ያስረክበኝ የሚለውን ክስ ለመተው የተስማሙ መሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል፡፡

ይህ በአመልካችና በተጠሪው መካከል የተደረገው የግልግል ስምምነት በመጀመሪያ የተደረገውን የቤት ሽያጭ ውል የማስቀረት ውጤት እንደሚኖረው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3308 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ይህም በመሆኑ ተጠሪው እና አመልካች ግንቦት 27 ቀን 1992 ዓ.ም ያደረጉት የግልግል ስምምነት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 3312 ድንጋጌዎች መሠረት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር በመሆኑ ይኸው በግልግል ውላቸው ላይ የተስማሙበት ጉዳይ ማለትም አመልካች በስምምነታቸው መሠረት ብር 2760 / ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ ብር/ እንዲከፍል ከሚጠይቁ በስተቀር ቤቱን ሸጦልኛልና ያስረክበኝ በማለት በግልግል ውል ቀሪ የሆነውን ጉዳይ የማንቀሣቀስ እና የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ ስለሆነም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በቤት ሽያጭ ውሉ መሰረት ቤቱን ለተጠሪው እንዲያስረክቡ በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገለፁትን የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡



**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00808 ጳግሜ 4 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26283 ሰኔ 10 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 29386

የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ወለላ ተሰማ - ጠበቃ ሽፈራው አመኑ

**ተጠሪ፡-** እማሆይ በላይነሽ መለሠ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት አቤቱታ ሟች ልጄ እመቤት ለገሠ ከሟች አባቷ አቶ ለገሠ ቢነግዴ በውርስ ማግኘት የሚገባትን ንብረት ተጠሪ ይዘው ስለሚገኙ በዓይነት እንዲያካፍሉኝ የማያካፍሉኝ ከሆነም ንብረቶቹ ተሸጠው ድርሻ ገንዘቤን እንዲሰጡኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም የአሁን አመልካች ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱት ክርክርም የሟች እመቤት ለገሠ አውራሽ አቶ ለገሠ ቢነግዴ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ከ27 ዓመት በፊት በመሆኑ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው፡፡ ሟች እመቤት ለገሠ በሕይወት በነበረችበት ጊዜ የሟች አባቷን የአቶ ለገሠ ቢነግዴን የውርስ ንብረት ክፍፍልን በሚመለከት በስምምነት ለመካፈል ባቀረበችው ጥያቄ መሠረት ሽማግሌዎች ንብረት ለይተውና አጣርተው ድርሻዋን ወስዳለች፡፡ በዚህ ዓይነት በግልግል ያለቀ ጉዳይ ይግባኝ ሳይኖረው የመጨረሻ ፍርድ ሆኖ እንደሚቆጠር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3312/1/ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በሟች እመቤት ለገሠና በተከሣሽ መካከል የነበረው የንብረት ክፍፍል በስምምነት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘና ያለቀለት ጉዳይ በመሆኑ የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 244/2/ረ/ መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች የወራሽነት መብታቸውን ያረጋገጡት ሰኔ 22 ቀን 1991 ዓ.ም. ሲሆን ልጃቸው እመቤት ለገሠ የሞተችው ጥር 16 ቀን 1991 ዓ.ም. ነው፡፡ መብት በተረጋገጠበትና ክስ በቀረበበት ጊዜ መካከል 3 ዓመት ያልሞላ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ መሠረት አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በአግባቡ የቀረበ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩ አስቀድሞ በግልግል አልቋል ተብሎ የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተም መስከረም 3 ቀን 1984 ዓ.ም. ከተደረገው የዘመድ ዳኞች ውሣኔ ጋር አቶ ተሾመ ተሰማ የሚች እመቤት ለገሠ ወኪል ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላልተያያዘ ውክልናው በአግባቡ ተሰጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1080/1/ መሠረት ከወራሾች አንዱ ሳይኖር የቀረ ወይም በሚገባ ወኪል ያላዳረገ እንደሆነ የንብረት ክፍፍሉን ዳኞች ካላፀደቁት በቀር ፈራሽ እንደሆነ የተመለከተ ስለሆነ ጉዳዩ አስቀድሞ በግልግል ዕልባት አግኝቷል ተብሎ የቀረበውም መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱ በቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ከሰጠ በኋላ በሟች አቶ ለገሠ ቢነግዴ ወራሽና በባለቤታቸው መካከል ይገኛል የተባለን የጋራ ንብረት ለይተውና አከፋፍለው ውጤቱን በሪፖርት መልክ ለፍ/ቤቱ እንዲገልጹ በማለት ውርስ አጣሪ ሾሞ አጣሪውም የማጣራቱን ሥራ አጠናቀው ሪፖርቱን ለፍ/ቤቱ አቅርበው ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪው ሪፖርት ለሕግም ሆነ ለሞራል ተቃራኒ ያልሆነ ስለሆነ ተቀባይነት አለው በማለት ይህንኑ በመዝገቡ ላይ አስፍሯል፡፡

የሥር ተጠሪ ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይንና ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤትን ትዕዛዝ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመወቃም ሲሆን ይህ የሰበር ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል፤ ጉዳዩም አስቀድሞ በግልግል ዕልባት አግኝቷል በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በበታች ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ወይስ አልሆነም ሲሆን አልሆነም የሚባል ቢሆን ጉዳዩ አስቀድሞ በግልግል ዕልባት አግኝቷል? አላገኘም? የሚለው በመሆኑ በዚህ መሠረት አቤቱታው ከሕጉ ጋር ተገናዝቦ ተመርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ የአሁን አመልካች ክሱ በ3 ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ክርክር ያቀረቡት በፍ/ብሕ/ቁ. 1000/1/ የተመለከተውን በመጥቀስ ነው፡፡

ችሎቱም በቅድሚያ የተመለከተው የፍ/ብሕ/ቁ. 1000/1/ ተፈፃሚነት ከዚህ ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ነው፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000/1/ ላይ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት አንድ ወራሽ የሆነ ሰው የውርስ ሀብትን በያዘ በሌላ ወራሽ ላይ ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ እንደሆነ በመ/ቁጥር 17937 በመጥቀስ ይህ ሰበር ችሎት የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁን አመልካች የሟች እመቤት ለገሠም ሆነ የአቶ ለገሠ ዲነግዴ ወራሽ ባለመሆናቸውና ንብረቱንም የያዙት በወራሽነት ስላልሆነ በተጠቀሰው ሕግ ላይ የተቀመጠው የይርጋ ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት አይኖረውም፡፡

ይህ ድንጋጌ ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በማለት ግን አቤቱታው ጭራሽ የይርጋ ጊዜ የለውም ማለት ስላልሆነ የይርጋ ክርክሩ ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር መታየት የሚገባው ነው፡፡



የሟች እመቤት ለገሠ አባት የነበሩት ሟች ለገሠ ዲነግዴና የአሁን አመልካች ባልና ሚስት እንደነበሩ፣ በመካከላቸው የነበረውም ጋብቻ በአቶ ለገሠ ዲነግዴ ሞት ምክንያት በነሐሴ ወር 1967 ዓ.ም. እንዲፈርስ ሟች እመቤት ለገሠም ግንቦት 25 ቀን 1969 ዓ.ም. የሟች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው ነገር ግን የንብረት ክፍፍል ሳይደረግ በጥር ወር 1991 ዓ.ም. ሟች እመቤት ለገሠ እንደሞቱ ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ከባልና ከሚስት በአንዳቸው ሞት ምክንያት ጋብቻ በሚፈርስበት ጊዜ ከተጋቢዎቹ እያንዳንዱ የግል ሀብቱ መሆኑን አስረድቶ የእራሱን ድርሻ የመውሰድ መብት እንዳለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 684 ላይ ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ ይህ ድንጋጌ ጥያቄው በምን ያህል ጊዜ መቅረብ እንዳለበት ባይደነገግም በጋብቻ ጊዜ የተፈራ የግልም ሆነ የጋራ ንብረት ሳይከፋፈል ለረጅም ጊዜ ቆይቶ ጥያቄውን ከረጅም ጊዜ በኂላ ለማቅረብ የሕጉ ዓላማ ሊሆን አይችልም፡፡ ግንኙነቱን የሚገዛው የቤተሰብ ሕጉ የይርጋ ድንጋጌን በዚህ ረገድ ካላካተተ ወደ ሌሎች ድንጋጌዎች መሄድ ግድ ስለሚል በዚሁ መሠረትም ሲታይ ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆንም የጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ ላይ የተመለከተ ሲሆን የውል ሕግ ደግሞ ዋናው የይርጋ ደንብ በቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ መቃወሚያ ያቀረቡት የሟች እመቤት ለገሠ አባት አቶ ለገሠ ዲነግዴ ከሞቱበት ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ጊዜ በመቁጠር ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪ ክስ ያቀረቡት በአቶ ለገሠ ዲነግዴ እግር ተተክተው ሳይሆን በሟች ልጃቸው በእመቤት ለገሠ እግር በመተካት እንደመሆኑ መጠን ሟች እመቤት ለገሠ ደግሞ የሞቱት ጥር 16 ቀን 1991 ዓ.ም. ሆኖ የልጅ ድርሻ ንብረት ይገባኛል በማለት ክስ ያቀረቡት ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ከማለፉ በፊት በ1994 ዓ.ም. ስለሆነ

ክሱ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ተብሎ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ከውጤት አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ጉዳዩ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ከተባለም ቀጥሎ መታየት የሚገባው ጭብጥ ክርክሩ አስቀድሞ በግልግል ዕልባት አግኝቷል ወይስ አላገኘም የሚለው ጭብጥ ነው፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ሟች እመቤት ለገሠ በሕይወት እያሉ ከአመልካች ጋር በዘመድ ዳኞች አማካይነት መስከረም 3 ቀን 1984 ዓ.ም. የንብረት ክፍፍል አድርገው ድርሻቸውን የወሰዱ ስለሆነ በግልግል ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበው ክስ በአግባቡ አይደለም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 244/2/ረ/ ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት መቃወሚያውን ሳይቀበለው የቀረው በአስረጂነት ከቀረበው የሽምግልና ዳኞች ውሣኔ መገንዘብ የሚቻለው ክፍፍሉ የተደረገው የሟች ወኪል ናቸው በተባሉት በአቶ ተሾመ ተሰማ አማካይነት እንደሆነ ሲሆን ነገር ግን አቶ ተሾመ ተሰማ የሟች ወኪል ናቸው ተብሎ በውሣኔው ላይ ከመጠቀሱ በስተቀር ከውሣኔው ጋር የውክልና ሥልጣኑ አልተያያዘም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1080/1/ መሠረት ከወራሾች አንዱ ሳይኖር የቀረ ወይም በሚገባ ወኪል ያላደረገ እንደሆነ የንብረት ክፍያውን ዳኞች ካላፀደቁት በስተቀር ፈራሽ እንደሆነ የተመለከተ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ የተደረገውም የንብረት ክፍፍል ፍ/ቤት ቀርቦ ያልፀደቀ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡

የውርስ ሀብት ክፍፍልን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1079 እና ተከታዮቹ ላይ የተመለከተው በዚህም ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት እንዳለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 689/2/ የተመለከተ ቢሆንም በቁጥር 1080/1/ ድንጋጌ መሠረት ከወራሾች አንዱ ባልተገኘበት ወይም በሚገባ ባልተወከለበት የተደረገን የንብረት ክፍፍል ዳኞች ካላፀደቁት በስተቀር ፈራሽ ነው ሊባል የሚችለው በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /2/ ሥር እንደተመለከተው በሌለበት ክፍያው የተፈጸመበት



ወራሽ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት እንደሆነ የተመለከተ ከመሆኑም በላይ የዚህ ዓይነቱንም ጥያቄ ወራሹ ማቅረብ የሚችለው የንብረት ክፍፍል በሌለበት መደረጉን ባወቀ በ1 ዓመት ጊዜ ውስጥ እንደሆነና ነገር ግን ሟች ከሞተ 10 ዓመት ያለፈለው ከሆነ በማናቸውም ምክንያት ጥያቄውን ማቅረብ እንደማይቻል በዚሁ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /3/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ አውራሽ መስከረም 3 ቀን ተደርጓል የተባለው የንብረት ክፍፍል በሌለሁበት ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል በማለት ከላይ የተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት አቤቱታ አቅርበው ክፍፍሉ ፈራሽ ነው ተብሎ ያልተወሰነ ከመሆኑም በላይ ተጠሪም ክስ የመሠረቱት ከሟች ልጅ በውርስ የተላለፈልኝ ንብረት ይገባኛል በማለት እንጂ ክፍፍሉ እንዲፈርስ ዳኝነት ያልጠየቁ በመሆኑ በዚህ ሁኔታ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ክፍፍሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ብይን እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይህንኑ ብይን በማጽናት የሰጠው ፍርድ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች በኩል ጉዳዩ አስቀድሞ በግልግል አልቋል ተብሎ የቀረበውን የመጀመያ ደረጃ መቃሚያ በመ/ቁ. 00202 በሚያዝያ 21 ቀን 1995 ዓ.ም ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጠው ብይንና ከዚህም በኋላ በዚሁ መዝገብ ውርስ አጣሪ እንዲቋቋምና የንብረት ክፍፍል እንዲደረግ በግንቦት 14 ቀን 1995 ዓ.ም. እና በሐምሌ 7 ቀን 1996 ዓ.ም. የሰጣቸው ትዕዛዞች እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34902 በጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በተጠሪ አውራሽ መካከል በግልግል ዳኞች አማካይነት መስከረም 3 ቀን 1984 ዓ.ም. የንብረት ክፍፍል መደረጉ የተረጋገጠ ስለሆነ ተጠሪ ድርሻ ንብረቴ ይገባኛል በማለት ያቀረቡት ክስ

ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 244/2/ረ/ መሠረት ተቀባይነት የለውም ተብሎ ተወስኗል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 30536

መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ
ደስታ ገብሩ
ሒሩት መለሠ
ታፈሰ ይርጋ
ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ት ዓለምነሽ ዋቅቶላ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ይልቃል ጌጤ አልቀረቡም፡፡
2. ካጀ ኢ/ል ኃ/የ/የ/ኩባንያ አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የ2ኛ ተጠሪ የሆነውን መኪና 1ኛ ተጠሪ ሲያሽከረክር ጉዳት የደረሰብኝ ስለሆነ ካሣ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃ ለተከሣሾች እንዲደርስና መልስ እንዲሰጡበት ታዞ 2ኛ ተከሣሽ የአሁን 2ኛ ተጠሪ ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከሳሽና 2ኛ ተከሣሽ ባደረጉት ስምምነት ከሳሽ በደረሰባቸው የአካል ጉዳት ብር 30 ሺህ ከአዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ለመቀበል በተስማሙት መሠረት ገንዘቡን ከኩባንያው የተቀበሉ ስለሆነ ክስ ያቀረቡት በዕርቅ ባለቀ ጉዳይ ስለሆነ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ የቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ከሳሽና 2ኛ ተከሣሽ ጉዳዩን በዕርቅ መጨረሳቸውን የቀረበው ማስረጃ ሰለሚያረጋግጥ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት በብይን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ከሣሽ በዚሁ ብይን ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን

ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ በእርቅ ያለቀ ነው ተብሎ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተጠሪዎች ባሉበት ለሰበር ችሎት ቀርቦ መጣራት የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪዎችን ጠርቷል፡፡ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በአድራሻው ባለመገኘቱ በጋዜጣ ተጠርቶ ስላልቀረበ መልስ የመስጠት መብቱ የታለፈ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ግን ቀርቦ የበኩሉን የጽሁፉን የቃል ክርክር አቅርቧል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱ በብይን ተቀባይነት የለውም ወደሚል መደምደሚያ ለመድረስ የቻለው አመልካች የካቲት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት ውል ለደረሰባቸው ቋሚ የአካል ጉዳት ካሳ የሚሆን ብር 30 ሺህ የተቀበሉ ስለሆነና ከዚህ በላይ 2ኛ ተጠሪንም ሆነ መድን ሰጭውን አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያን ላለመጠየቅ ስምምነት ላይ የደረሱ በመሆኑ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ አስቀድሞ በስምምነት ዕልባት አግኝቷል በማለት ነው፡፡

ይሁንና የካቲት 29 ቀን 1997 ዓ.ም. ተደርጓል የተባለው ውል ይዘት ሲታይ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ 2ኛ ተጠሪን በመወከል በካሣ አከፋፈሉ ረገድ ከመልካች ጋር ውሉን እንደተዋዋሉ መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ በስር ፍ/ቤትም ሆነ ለዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ሲከራከሩ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ 2ኛ ተጠሪን በመወከል ይህንኑ ውል ከአመልካች ጋር እንደተዋዋለና በውሉ ላይ የተጠቀሰውንም ብር 30 ሺህ ኢንሹራንስ ኩባንያው ለአመልካች መክፈሉ የተረጋገጠ ስለሆነ ኢንሱራንስ ኩባንያው 2ኛ ተጠሪን በመወከል ከአመልካች ጋር ውሉን መዋዋል የሚችለው ለ2ኛ ተጠሪ በሰጠው የመድን ሽፋን ልክ እንጂ ከዚያ በላይ ሊሆን ስለማይችል የጉዳት አድራሹ መኪና ባለንብረት 2ኛ



ተጠሪ ከብር 30 ሺህ በላይ የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ አስመልክቶ የቀረበበት ክስ በዕርቅ አልቋል ሊባል ስለማይችል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩ በአጠቃላይ በዕርቅ አልቋል በማለት ክሱን ሳይቀበል መቅረቱ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12463 በታህሳስ 12 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ብይን እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 41413 በየካቲት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ መካከል ያለው ክርክር በዕርቅ አልቋል ለማለት ስለማይቻል የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ የበኩሉን ውሣኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 30727

ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

መድኀን ኪሮስ

አልማው ወሌ

አመልካች ፡- የኢትዮጵያ ማዕድን ልማት አ/ማኀበር ነ/ፈጅ ወንድአንተ ነጋሽ

ተጠሪ ፡- ጀቲቲ ትሬዲንግ ሥራ አስኪያጅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ግራ ቀኞችን ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ባደረግነው ውል ከከሳሽ ጋር 10 ኢንች የማይዝግ የብረት ቧንቧ ለማቅረብ ስምምነት የተደረሰ ቢሆንም ተከሳሽ ውሉን በማፍረሱ ያለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት ችግሩን ለመፍታት ከሳሽ የበኩሉን ጥረት ቢያደርግም በተከሳሽ በኩል አዎንታዊ ምላሽ ባለመገኘቱ በውሉ አንቀጽ 10/4/ /2/ መሠረት ጉዳዩን በግልግል ለማየት ተጠሪ የግልግል ዳኛ በ10 ቀን ውስጥ መርጦ እንዲያሳውቀን በጽሁፍ ያሳወቅነው ቢሆንም ፈቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በተከሳሽ ምትክ በሕግና በውላችን መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲመርጥልን በማለት ጠይቋል፡፡

የከሳሽ አቤቱታም ለተከሳሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በሕግም ሆነ በኩባንያው የመመስረቻ ጽሁፍ፤ በመተዳደሪያ ደንቡ እንደዚሁም በሥነ ሥርዓትና በፍ/ብሔር ሕጉ የተቀመጠው የችሎታ መስፈርት ለተጠሪው ወይንም ለእንደራሴው አልተሰጠም ብለዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ተከሳሽ የግልግል ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በእራሳቸው የግል ችሎታ ሳይሆን በሌሎች የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰዎች ስም የሆነ እንደሆነ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ እንዲስማሙ የሚያስችላቸው ልዩ የውክልና ስልት እንዲኖራቸው ይገባል ያሉ ሲሆን አመልካች ወደ ግልግል ዳኝነት እንገባ የሚልበት ጉዳይ በግልግል ስምምነቱ አይሸፈንም እንጂ የሚሸፈን ነው ቢባል እንኳ ወደ ግልግል ዳኝነት ከመግባቱ በፊት በእራሳቸው በተዋዋዮች ድርድር ተጀምሮ በሂደት ላይ ያለው ስምምነት ገና ያልተጠናቀቀ ስለሆነና ይህንንም ለማድረግ ውሉ ስለሚያስገድድ በዚህ ሁኔታ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ተገቢነት ያለውን የክርክሩን ጭብጥ ከያዘ በኋላ ተጠሪ የአክሲዮን ማኀበር ሲሆን ተጠሪና አመልካች ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተዋዋሉት መሠረት ያለመግባባቶችን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት ተደርጐ ካልተቻለ የግልግል ዳኛ በመምረጥ ጉዳዩ እንደሚታይ የተስማሙ ስለሆነ አክሲዮን ማኀበር ያለመግባባቶችን በግልግል ለመፍታት እንደማይችል የሚያመለክት የሕግ ድንጋጌ በሌለበት ሁኔታ ተጠሪ ጉዳዩን በግልግል መጨረስ አልችልም በማለት ያቀረበው ክርክር አግባብነት የሌለው ነው ካለ በኋላ የተፈጠረውን ያለመግባባት በውሉ መሠረት በስምምነት ለመፍታት ከሳሽ /አመልካች/ ተገቢውን ጥረት ስለማድረጉ ካቀረበው ማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ ግራ ቀኙ ያለመግባባታቸውን በስምምነት መጨረስ ስላልቻሉ ጉዳያቸው በግልግል ዳኛ አማካይነት መታየት ስላለበት የየበኩላቸውን የግልግል ዳኛ መርጠው ይቅረቡ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሥር ተከሳሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህ ችሎት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ በግራ ቀኙ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት

በግልግል ዳኛ እንዲታይ በበታች ፍ/ቤቶች መወሰኑ አግባብነቱ ተጠሪ ባለበት ታይቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የዚህን ችሎች ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጥሯል የተባለው አለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ሊታይ ይችላል ወይንስ አይችልም የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን አቤቱታውን መርምረናል፡፡

በቅድሚያም አመልካች ምን ዓይነት የሕግ ሰውነት (legal personality) እንዳለው መመልከት ለጉዳዩ አወሳሰን ጠቃሚ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ሲታይ አመልካች የአክሲዮን ማኅበር እንደሆነ ከክርክሩና ከቀረበው ማስረጃ ለመገንዘብ የተቻለ ሲሆን ይህንንም የሕግ ሰውነት ማግኘት የቻለው አስቀድሞ የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደነበረና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ስለማዛወር በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/91 መሠረት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ለፕራይቬታይዜሽን ዝግጅት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አንድን የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት እንዲለወጥ ማድረግ እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 5/1/ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ መሠረት አመልካች ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተቀየረ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚህ መልኩ የሚቋቋሙና በንግድ ሕጉ መሠረት የሚቋቋሙ የአክስዮን ማኅበራት በአክሲዮን ባለቤትነት በሥልጣንና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ አንድ ዓይነት እንዳልሆኑ ከተጠቀሰው አዋጅ መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ የንግድ ሕግ ቁጥር 307/1/፣ 311፣ 312/1/ለ/፣ 315፣ 347/1/ እና 349 ከመንግሥት የልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማኅበርነት በተለወጡት ላይ ተፈፃሚነት እንደሌላቸው ነገር ግን ሌሎች የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ በአዋጁ ላይ ተመልክቷል፡፡

በዚህም መሠረት የአክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊኖረው እንደሚችል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 348/3/ ላይ የተመለከተ ሲሆን በተያዘውም



ጉዳይ አመልካች አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያለው ስለመሆኑ በአክሲዮን ማኅበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የተመለከተ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በሌላ በኩልም የአመልካች አክሲዮን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12 ሥር የተዘረዘሩ ሲሆን ተጠሪም በዚሁ የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 12/2/ ሥር ዋና ሥራ አስኪያጁ የኩባንያውን የዕለት ተዕለት ሥራ ያከናውናል ተብሎ የተመለከተው ከሌሎች ወገኖች ጋር ውል መዋዋልን በውሉ አፈፃፀም ረገድ ያለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩን በግልግል ለማየት መስማማት እንደሚችልም ስለሚያስገነዝብ በዚሁ መሠረት ውሉ የተፈረመ ስለሆነ ጉዳዩ በግልግል እንዲታይ መወሰኑ አግባብነት አለው በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁንና ዋናው ሥራ አስኪያጅ የኩባንያውን የዕለት ተዕለት ሥራዎች ያከናውናል ተብሎ ሥልጣንና ተግባሩን በሚዘረዝረው የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ ላይ የተጠቀሰ ቢሆንም አክሲዮን ማኅበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ሲታይ ሙሉ በሙሉ በንግድ ሕጉ መሠረት ያልተቋቋመ ስለሆነና ዋናው ሥራ አስኪያጁ ኩባንያውን በመወከል ውል የመዋዋል ሥልጣን እንዳለው መገንዘብ ቢቻልም ከዚህ አልፎ በውሉ አፈፃፀም ረገድ ያለመግባባት ቢከሰት ጉዳዩ በግልግል ዳኛ አማካይነት ዕልባት እንዲያገኝ ለመስማማት እንደሚችል ሥልጣን ያልተሰጠው መሆኑን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ በግልግል ዳኝነት መታየት ይችላል በማለት የሰጡት ውሣኔ ከአዋጅ ቁጥር 146/91 እና ከማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ ጋር ያልተጣጣመ በመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 59068 በየካቲት 17 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 46254 በየካቲት 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ከተቋቋመበት ሕግ አኳያና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ዋናው ሥራ አስኪያጅ በውል አፈፃፀም ረገድ የሚፈጠርን ያለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ዕልባት እንዲያገኝ ለመስማማት ሥልጣን ያልተሰጠው ስለሆነ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጥሯል የተባለው ያለመግባባት በግልግል ዳኛ አማካይነት ሊታይ አይችልም ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 20036

ግንቦት 16 ቀን 1998

ዳኞች:- መንበረፀሐይ ታደሠ
ዓብዱልቃድር መሐመድ
· ምህረቱ
መዐዋ ን እቁበዮናስ
ወ/ት ሒሩት መለሠ

**አመልካች:-** ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ

**ተጠሪ:-** ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ሊከፈል የማይገባው የጡረታ አበል ክፍያን የሚመለከት ነው::

አመልካች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ ተጠሪ የሚች ባለቤታቸውን የወ/ር ተፈራ አድማሱን ጡረታ እየተቀበሉ ሌላ ባል በማግባታቸውና፤ የሚች ባላቸውን ጡረታ አበል እየበሉ ሌላ ባል ያገቡ የጡረታ አበል እንደሚቋረጥባቸው ሕጉ ግልፅ ሆኖ ሣለ፤ ይህንኑ በመቃረን ተጠሪ ሌላ ባል አግብተውም የሚችን ጡረታ ለ 13 አመታት ስለተቀበሉ በድምሩ ብር 7593.75 ይክፈሉ በማለት ጠይቋል::

ተጠሪም ቀርበው ከ13 ዓመት በኋላ የቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ ነው፣ ሌላ ባል አላገባሁም ከጋብቻ ውጪ በነበረን ግንኙነት 2 ልጆች ወልጃለሁ በማለት ተከራክረዋል::

ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም ክስ የቀረበበት የይመለስልኝ ጥያቄ በየጊዜው (በየወሩ) የሚከፈልና ለመጨረሻም ጊዜ ክፍያው የተደረገው በ ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ሲሆን ክስ የተመሠረተው በሰኔ 5 ቀን 1995 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋው ጊዜ አላለፈም፣ ነገር ግን ተጠሪ ሌላ ባል ያገቡ ለመሆናቸው አላስረዳም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል::

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ ውሣኔ ላይ የቀረበለትን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሀ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል::

የአሁኑ አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው:: ይህ ችሎትም በግራ ቀኙ መሃከል ጋብቻ መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ሲል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር አድርጓል:: ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል::

አመልካች ክስ የመሠረተው መክፈል የማይገባኝን የጡረታ አበል የከፈልኩ ስለሆነ ይመለስልኝ በሚል ነው:: ይህ ደግሞ በፍ/ብሔር ሕጉ ያለአግባብ ስለመበልፀግ ከሚናገረው ምዕራፍ ውስጥ የማይገባውን ስለመካፈል በሚለው ክፍል ሥር የሚወድቅ ነው:: አንድ ሠው ሊከፍል የማይገባውን ነገር ከከፈለ እንዲመልስለት የመጠየቅ መብት እንዳለው የፍ/ህ/ቁ 2164 (1) ያመለክታል::

በተያዘው ጉዳይ በጡረታ ሕጉ በባልዋ መሞት ምክንያት ጡረታ የምታገኝ ሴት ሌላ ባል ባገባች ጊዜ የሚች ባሏ ጡረታ አበል መቋረጥ ያለበት ለመሆኑ ተመልክቷል:: የተጠሪ የመጀመሪያ ክርክር ክስ የቀረበበት ጉዳይ 10 አመት ስላለፈው በ10 አመት ይርጋ ይታገዳል የሚል ነው::

የማይገባውን ስለ መክፈል የሚለው ክፍል የሚገኘው ከውል ውጪ ስለሚደርስ ሃላፊነትና ያላግባብ ስለመበልፀግ በሚናገረው አንቀፅ ሥር ነው:: በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በዚሁ አንቀፅ ተካቶ የሚገኘው የይርጋ ጊዜ ይሆናል:: የፍ/ህ/ቁ 2143(1) ተበዳይ ክስ ማቅረብ የሚችለው ጉዳቱ ከደረሠ ጊዜ ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ነው:: አመልካች መክፈል የማይገባውን ነገር መክፈል የጀመረው ከህዳር ከህዳር 1 ቀን 1981 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን ክፍያ ያቋረጠው ግንቦት 30 ቀን 1995 ዓ.ም ነው:: በመሆኑም አመልካች ክስ ከቀረበበት ሰኔ 10 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ ወደኋላ ያለው የሁለት አመት ጊዜ ብቻ በይርጋ ቀሪ የማይሆን ሲሆን ከዚህ ጊዜ በፊት የነበረው የአመልካች ጥያቄ ግን በይርጋ ቀሪ ይሆናል::

ሌላው የተጠሪ ክርክር ከአቶ ገብሩ አሰፋ ጋር ጋብቻ የለንም:: ከጋብቻ ውጪ ባለ ግንኙነት ነው ልጆች የወለድኩት የሚል ነው::

ከፍ/ቤቱ መዝገብ ተጠሪ አቶ ገብሩ አሰፋ ባላቸው መሆናቸውን በቀበሌ ቅፅ ላይ ሞልተው አረጋግጠዋል:: አቶ ገብሩ አሠፋም ቢሆኑ በሚሠሩበት መ/ቤት በሞሉት የሕይወት ታሪክ ቅፅ ላይ ተጠሪ ሚስታቸው መሆናቸውን

አረጋግጠዋል:: ከዚህም በላይ ተጠሪ ከጋብቻ ውጪ ነው ይበሉ እንጂ እንደ ባልና ሚስት በመሆን አንድ ላይ ይኖሩ እንደነበር አልካዱም::

በተሻሻለው የቤተሠብ ሕግ አንቀፅ 95 ላይ ጋብቻ መኖሩን ለማረጋገጥ ሊቀርብ የሚገባው የጋብቻ ምስክር ወረቀት መሆኑን ያመለክታል:: ይህ ማስረጃ በሌላ ጊዜ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 95 እንደተመለከተው የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ጋብቻን ማስረዳት ይቻላል:: የትዳር ሁኔታ አለ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት ራሳቸውን እንደ ባልና ሚስት የሚቆጥሩና የሚኖሩ እንዲሁም ማሕበረሰቡና ቤተዘመዶቻቸው እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው ተብሎ በአንቀጽ 96 ስር ተጠቅሷል ። ይህን ሁኔታ ማስረዳት ከተቻለ ፍ/ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሟል ሲል የሕግ ግምት እንደሚወስድም አንቀጽ 97 ያመለክታል። ሕጉ የጋብቻ ሁኔታ የሚረጋገጥበትን ማስረጃ አይነት ለይቶ ያላመለከተ በመሆኑም ማንኛውም ማስረጃ ሊቀርብ የሚችል መሆኑን መረዳት ይቻላል::

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በተጠሪና በአቶ ገብሩ አሰፋ መሃከል ጋብቻ መኖሩን የጋብቻ (የትዳር) ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት ማስረጃዎቹን አቅርቧል:: ተጠሪ አቶ ገብሩ ባላቸው ለመሆናቸው በቀበሌ ፎርም ላይ ሞልተው ማረጋገጣቸውን እንዲሁም አቶ ገብሩም ቢሆኑ በሚሠሩበት መ/ቤት በሞሉት የሕይወት ታሪክ ቅፅ ተጠሪዋ ሚስታቸው መሆናቸውን አረጋግጠው መሙላታቸውን ከመዝገቡ ተረድተናል:: ይህም ተጠሪና አቶ ገብሩ እራሣቸውን እንደባልና ሚስት እየቆጠሩ የሚኖሩ መሆኑን ማህበረሰቡም በዚሁ መልኩ የተቀበላቸው መሆኑን ያመለክታል:: ነገር ግን የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ የአቶ ገብሩ ሚስት ለመሆናቸው የጋብቻ ሠርትፍኬት አልቀረበም ወይም ሠርተፊኬቱ መጥፋቱ አልተረጋገጠም በማለት በሁለቱ መሃከል ትዳር የለም በማለት የደረሠበት መደምደሚያ ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የቤተሠብ ህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው::



**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. ***ተጠሪ ከሰኔ 10 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ሰኔ 10 ቀን 1995 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የወሰዱትን የሚች ባለቤታቸውን የጡረታ አበል ለአመልካች ይመልሱ::***
2. ***ከሰኔ 10 ቀን 1993 ዓ.ም በፊት አመልካች ለተጠሪ የከፈለው የጡረታ አበል እንዲመለስ ያቀረበው ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኗል::***
3. ***ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ:: መዝገቡ ተዘግቷል:: ለመ/ቤት ይመለስ::***

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

መዝገብ ቁጥር 23334

ሕዳር 24 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሀይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** የአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ፍሬው ማሞ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ደባሣ ገለታ - ቀረቡ

2. አቶ ኤባ ደመራ

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጀመረው በምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ባቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ በሥራ ምክንያት እጁ ገብቶ የነበረውን ስንዴና የስንዴ ዱቄት ለራሱ ጥቅም ስላዋለ ግምቱን 89,750 (ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ) ይክፈል 2ኛ ተጠሪ እስከ ብር 10,000 (አሥር ሺህ ) ለሚደርስ ገንዘብ ዋስ ስለሆኑ ገንዘቡን ይክፈሉ በማለት ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎቹ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት የታየ ሲሆን ፍ/ቤቱ መዝገቡን መርምሮ ተጠሪ 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት ማጉደሉን በፊርማው ስላረጋገጠ ለመተካት ይገደዳል፡፡ 558.5 ኩንታል ስንዴ ለማጉደሉ ግን የፈረመው መተማመኛ ስለሌለ አይጠየቅም በማለት ማጉደሉ የተረጋገጠውን 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት እንዲተካ፣ 2ኛ ተጠሪ ግን ተጠያቂ አይደሉም በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም 1ኛ ተጠሪ ለ558.5 ኩንታል ስንዴ ጉድለት ተጠያቂ አይሆንም የተባለበትን የሕግ አግባብ ለመመርምር አቤቱታው ለሰበር ቀርቦ እንዲታይ



አድርጓል፡፡ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ላይ የምንጠይቀው ዳኝነት የለም በማለቱ ለአቤቱታው መልስ የሰጡት 1ኛ ተጠሪ ብቻ ናቸው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ነሐሴ 10 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈ መልስ 558.5 ኩንታል ስንዴ የጎደለዉ በእርሳቸው ጥፋት ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው ምርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች 1ኛ ተጠሪ 558.5 ኩንታል ስንዴ አጉድለዋል በሚል ክስ ቀርቧል፡፡ ክሱንም ለማስረዳት 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበትን መተማመኛ አቅርቧል፡፡ በዚህ መተማመኛ 1ኛ ተጠሪ ስንዴው በጉድለት መገኘቱን አረጋግጠው ፈርመዋል፡፡ ከዚህም በላይ በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ጉድለት መኖሩን አምነዋል፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ለተገኘው ጉድለት ተጠሪ ኀላፊ አይሆኑም ያሉት በመተማመኛው ላይ ስንዴው የጎደለበት ምክንያቶች የተቀመጡና እነዚህም ጉድለቱ በተጠሪ ጥፋት የተከሰተ መሆኑን አያሳዩም በማለት ነው፡፡

እንግዲህ አመልካች 558.5 ኩንታል ስንዴ አጉድለዋል በማለት ክስ ሲመሰረት ጉድለቱ መኖሩን በቅድሚያ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ በዚህ መሠረት ጉድለቱን የሚያሳይና 1ኛ ተጠሪ የፈረሙበት መተማመኛ አቅርቧል፡፡ ይህ ከሆነ ጉድለቱ በ1ኛ ተጠሪ ጥፋት አለመከሰቱን የማስረዳት ሸክም የማነው የሚለው ጥያቄ ይነሣል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በመተማመኛው ላይ ስንዴው ሊጎድል የቻለበትን ምክንያት 1ኛ ተጠሪ ዘርዝረው አስቀምጠዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ምክንያቶች መዘርዘሩ ብቻ ከተጠያቂነት ሊያድናቸው አይችልም ምንም እንኳን ተጠሪው በስር ፍ/ቤት ያልተከራከሩ ቢሆንም ለሰበር አቤቱታው በሰጡት መልስ ጉድለቱን አምነዋል፡፡ ጉድለቱን አምነው በመተማመኛው ላይ ባመለከቷቸው ምክንያቶች ክሱ አይመለከተኝም የሚሉ ከሆነ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም መወጣት እንዳለባቸው ከፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 258(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ተጠርተው ባለመቅረባቸው ከሀላፊነት ነፃ የሚያደርጋቸውን የፍሬ ነገርና የሕግ ክርክር አቅርበው ክሱን

አልተከላከሉም በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ አዲስ ነገር ደግሞ በሰበር ደረጃ ሊነሣ አይችልም፡፡

በመሆኑም ጉድለቱ መኖሩ ከተረጋገጠና ይህ ጉድለት በተጠሪው ጥፋት ያልተከሠተ መሆኑን ተጠሪው ካላስረዱ ከሀላፊነት ነፃ የሚሆኑበት ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም የጉድለቱ ምክንያቶች በመተማመኛው ላይ ተገልፀዋል በሚል ብቻ ተጠሪ ከተጠያቂነት ነፃ መሆናቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ አጎደሉ ለተባሉት የስንዴ ዱቄትና ስንዴ በክሱ ላይ የተመለከተውን ዋጋ ተቃውመው ያቀረቡት ክርክር ሳይኖር የሥር ፍ/ቤቶች የአንድ ኩንታል የስንዴ ዱቄት ዋጋ አልተገለፀም በሚል 1ኛ ተጠሪ የስንዴ ዱቄቱን በአይነት እንዲመልሱ የሠጡት ውሳኔ አግባብ አይደለም፡፡

## ው ሳ ኔ

1) የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የመ/ቁ00468 በጥር 25 ቀን 1996 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 07116 በታህሳስ 11 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2) 1ኛ ተጠሪ ለጎደለው 16.5 ኩንታል የስንዴ ዱቄት እና 558.5 ኩንታል ስንዴ ተጠያቂ ስለሆኑ ክስ የቀረበበትን 89,750.50 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሣ ብር ከሃምሳ ሣንቲም) ይክፈሉ፡፡ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ሕጋዊ ወለድ ጨምረው ይክፈሉ፡፡
3) ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰ/መ/ቁ. 25899

ግንቦት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ
መስፍን ዕቁበዮናስ
መድኅን ኪሮስ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም

አመልካች፡- የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ምንዳገኝ ቀረቡ።

ተጠሪ፡- ወ/ር ስዩም ካሣ - አልቀረቡም።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የጀመረው በኦ/ብ/ክ/መ/ የአሩሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪው ላይ ሰኔ 11 ቀን 1994 ዓ.ም. ባቀረበው ክስ ሲሆን ይዘቱም ተጠሪው ጡረታ ወጥተው ጡረታ አበል እየተከፈላቸው ከሕግ ውጪ በመንግሥት መ/ቤት /የአሠላ ማዘጋጃ ቤት/ ተቀጥረው ደሞዝም እያገኙ በመሆኑ ከሰኔ 1 ቀን 1987 ዓ.ም. እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1988 ዓ.ም. ድረስ እና ከመስከረም 1 ቀን 1989 ዓ.ም. እስከ ግንቦት 30 ቀን 1993 ዓ.ም. ድረስ የተከፈላቸውን የ72 ወራት የጡረታ አበል ድምር ብር 6604.50 /ስድስት ሺ ስድስት መቶ አራት ብር ከሃምሣ/ ከወለድ ጋራ እንዲመልሱ ይወሰን የሚል ነው።

ተጠሪው በበኩላቸው በሰጡት መልስ እኔ የቀን ሠራተኛ እንጂ ቋሚ ሠራተኛ አይደለሁም፣ ከ1993 ዓ.ም. ወዲህ ግን በደሞዝ ስለተቀጠርኩ ደመወዝን መርጬ የጡረታ አበል ትቻለሁ በማለት ተከራክረዋል።

የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአሰላ ከተማ አስተዳደር የተጠሪን ቅጥር በተመለከተ አስተያየቱን እንዲሰጥ አዞ አስተዳደሩ በፃፈው ደብዳቤ ተጠሪው ከግንቦት 15 ቀን 1987 ዓ.ም. አንስቶ እስከ ጥር 30 ቀን 1995 ዓ.ም. ድረስ የኮንትራት ሠራተኛ መሆኑን ከየካቲት 1 ቀን 1995 ዓ.ም. ጀምሮ

ግን ተጠሪ ቋሚ ደሞዝተኛ መሆኑን በመግለጹ ፍ/ቤቱ ሰኔ 15 ቀን 1997 በሰጠው ውሣኔ በአ/ቁ. 345/95 አንቀጽ 46/1/ እና /2/ መሠረት የጡረታ አበል መውሰድ የማይችለው በቋሚነት የሚሠራ ሠራተኛ ሲሆን ተጠሪው ግን በክሱ በተጠቀሰው ወቅት የኮንትራት ሠራተኛ የነበሩ በመሆኑ ክሱ አግባብነት የለውም ሲል ውድቅ አድርጎታል፡፡

የአርሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘው አመልካች ቅሬታውን በይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ቢያቀርብም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት አቤቱታውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ መዝገብ ለዚህ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለውም አመልካች ሐምሌ 4 ቀን 1998 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው የአ/ቁ. 209/55 እና የአ/ቁ 345/95ን ድንጋጌዎች የሚፃረር በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለታቸው ነው፡፡

እኛም የአመልካችን አቤቱታ ተመልክተን በዚህ ጉዳይ ተጠሪ የጡረታ ተጠቃሚ ሆኖ በመንግሥት ሥራ በኮንትራት የተቀጠረ እንጂ በቋሚነት የተቀጠረ ባለመሆኑ የጡረታ አበልና ደሞዝ አጣምሮ ተቀብሏል በመሆኑም የጡረታ አበሉን ይመልስ በሚል አመልካች ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ የተወሰነው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪን አስቀርበን ግራ ቀኙ የቃል ክርክራቸውን አካሂደዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ የአርሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት የቀረበለትን ክስ ውድቅ ለማድረግ መሠረት ያደረገው የአ/ቁ. 345/95 አንቀጽ 46/1/2/ የጡረታ አበል ሊቀበል የማይችለው በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሠራተኛ እንጂ በኮንትራት ተቀጥሮ የሚያገለግል ሠራተኛን አይመለከትም በሚል ነው፡፡ በመሠረቱ በዚህ ጉዳይ ክስ የተመሠረተው ሰኔ 11 ቀን 1994 ዓ.ም. በመሆኑ አ/ቁ. 345/95 ለጉዳዩ አግባብነት የለውም፡፡ ከዚህ ይልቅ ክስ በተመሠረተበት ወቅት በሥራ ላይ የነበረው እና ለጉዳዩም አግባብነት ያለው አ/ቁ. 209/55 መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የአ/ቁ. 209/55 አንቀጽ 30/2/ ደግሞ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ



ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደመዝ በሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ ከተቀጠረ ከደሞዙ እና ከጡረታ አበሉ አንዱን መምረጥ እንደሚኖርበት በግልጽ ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ድንጋጌ ሥራው ደሞዝ የሚያስገኝ የመንግሥት ሥራ መሆኑን እንጂ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነት ይሁን በቋሚነት የሚል መስፈርት ከግምት ውስጥ አያስገባም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በዚህ ጉዳይ የስር ፍ/ቤት አ/ቁ 345/95ን አጣቅሶ በጊዜያዊና ቋሚ ሠራተኛ መካከል ልዩነትን መፍጠሩ በአ/ቁ. 209/55 ላይ ያልተካተተ ነጥብ ከመሆኑ አንፃር ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ የተቀጠሩት በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት በክሱ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የጡረታ አበል ለመቀበላቸው እስካልተካደ ድረስ ከደሞዛቸው በተጨማሪ የወሰዱትን የጡረታ አበል የማይመልሱበት ምክንያት አይኖርም፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በኦ/ብ/ክ/መ/ የአርሲ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01713 ሰኔ 15 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይህንን ውሣኔ በመ/ቁ. 32888 ሚያዝያ 10 ቀን 1998 ዓ.ም. በማጽናት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ስለዚህ ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በክሱ የተጠቀሰውን አላግባብ የወሰዱትን የ72 ወራት የጡረታ አበል ብር 6604.50 /ስድስት ሺህ ስድስት መቶ አራት ብር ከሃምሣ ሣንቲም/ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ.26480

ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

መስፍን ዕቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሃኑ አመነው

**አመልካች፡-** የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ ቢንያም ዓለማየሁ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ ተጠሪ በጥር 12 ቀን 1995 ዓ.ም በሥር ፍ/ቤት መሥርቶት በነበር ክስ፣ከታህሣሥ 22 ቀን 1984 ዓ.ም ጀምሮ በሌክቸረር 3 ማዕረግ በመነሻ ደሞዝ ብር 850 እተየከፈለው ሲያገለግል መቆየቱን ገልጾ፣በወቅቱ ማግኘት የሚገባውን እድገትና የደሞዝ ጭማሪ እንዳያገኝ በርካታ አስተዳደራዊ በደሎች የደረሱበት መሆኑን፤ ከ1989 ዓ.ም--1991 ዓ.ም አለአግባብ ከሥራ መታገዱን፣ በድጋሚ ከ1992 ዓ.ም እስከ 1994 ዓ.ም ከሥራ መታገዱን በመጨረሻም በቂ ምክንያት ሣይኖር ከሥራ መባረሩን ገልጾ ወደሥራው እንዲመለስ፣ ማግኘት የነበረበት የደረጃ እድገትና የደሞዝ ጭማሪ በአግባቡ ተሰልቶ እንዲከፈለው፤ ከዚሁ ጋር ውዝፍ ደሞዙ ጭምር ብር 157,935 እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በነገረፈጁ አማካኝነት በሰጠው መልስ፣ የአሁኑ ተጠሪ ከሥራ የታገደውም ቀጥሎም የተሰናበተው በዲሲÝሊን ጥፋት መሆኑን፤ ጥፋቱም በኮሌጁ የዲስÝሊን ኮሚቴ እና በማንጅሜንቱ በአግባቡ የተሰጠ ውሣኔ መሆኑን ተረድቶ ቦርዱ ውሣኔውን ያፀደቀ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን የሚመራው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች መልስ ሰጭን ከሥራ ያገደውና ያሰናበተው አለአግባብ ስለሆነ ወደ ሥራው እንዲመለስው፣ በተጨማሪ ከ1988 ዓ.ም



ጀምሮ መልስ ሰጭ ከሥራ እስከተሰናበተ ጊዜ ድረስ ሣይከፈል የቀረውን ደሞዝና የቤት ኪራይ አበል ብር 32,765 /ሰላሣ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ አምስት ብር/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከ/ፍ/ቤትም የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ቅሬታ ላይ ሲሆን የአሁኑ አመልካች ነሐሴ 3 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ የግራ ቀኙ መልስ እና የመ/መልስ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

በዚህ ጉዳይ በሰበር ችሎቱ በጭብጥነት ተይዞ ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ፣ በአመልካችና በመልስ ሰጭው መካከል ተደርጎ ነበር የተባለው የውል ግንኙነት የሚመራው በየትኛው ሕግ ነው? የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን አይተው ለመወሰን ሥልጣን የነበራቸው መሆኑን አለመሆኑን? ነው፡፡ ይህ ችሎት በዚሁ ጉዳይ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን ቅጥር፣ አስተዳደርና የዲሲÝሊን አወሳሰን ማንዋሎችንና የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅን ለማቋቋም የወጣውን ደንብ አግባብ ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

በመሠረቱ የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የተቋቋመው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በደንብ ቁጥር 12/1991 መሠረት ነው፡፡ በዚሁ ደንብ በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው የኮሌጁ አካዳሚክ ሠራተኞች ስለሚቀጠሩበትና ስለሚተዳደሩበት ሁኔታ ተገቢውን ለመወሰን እንዲችል ለኮሌጁ ቦርድ ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከነሐሴ ወር 1993 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የኮሌጁ መተዳደሪያ ዝርዝር ደንብ ወይም «ሌጂስሌሽን» በሥራ ላይ ውሎ ሙሉ ተፈፃሚነት የነበረው ስለመሆኑ ግራ ቀኙ አልተካካዱም በዚህ ደንብ በክፍል አምስት ውስጥ ስለአካዳሚክ ባልደረቦች ምደባና ዕድገት፣ ስለዲሲÝሊን ጥፋቶችን አካሄድና የውሣኔ አሰጣጥ ሥርዓቶች በሰፊው ተደንግጓል፡፡ በዚሁ ክፍል በአንቀጽ 5.4.7 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው በአካዳሚክ ባልደረባ ላይ የሚሰጡ የዲሲÝሊን

ኮሚቴ የመጨረሻ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው በዲኑ ወይም በቦርዱ በሚሰጡ የመጨረሻ ውሣኔዎች መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በያዝነው ጉዳይ በተጠሪ ላይ ተወሰዱ የተባሉት አስተዳደራዊ ውሣኔዎች ከፍ ሲል የተመለከተው የአካሄዱ ሥነ ሥርዓት ተከትለው የተወሰዱ መሆኑ ታውቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አስተዳደራዊ አካሄዳቸውን ተከትለው የተሰጡ የመጨረሻ የዲሲፕሊን ውሣኔዎችን እንደገና መርምሮ ለመወሰን የሚያስችለው የሕግ ሥልጣን ስለመኖሩ በውሣኔው ሣያመለክት የአሁኑ አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያገደውና ያሰናበተው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን? እንዲሁም የአሁኑ ተጠሪ ማግኘት የሚገባውን ደሞዝና የደረጃ እድገት የተነፈገው በተገቢው መንገድ ነው ወይስ አይደለም? የሚልና ሌሎች ጭብጦችን ይዞ የደረሰበት መደምደሚያ ሕግ አውጪው ለትምህርት ተቋማት የሰጠውን ተቋማዊ ነፃነት በጽኑ የሚፃረር ከመሆኑ በተጨማሪ የዳኝነት አካላቱ በሕግ ተለይቶ ባልተሰጣቸው ተግባር ያከናወኑት ተግባር በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ታህሣሥ 27 ቀን 1996 ዓ.ም በመ/ቁጥር 66879 እና የፌ/ከ/ፍ/ቤት ሐምሌ 6 ቀን 1998 ዓ.ም በመ/ቁ. 29061 የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ ያገኘውን ጉዳይ እንደገና አይተው ለመወሰን የሚያስችላቸው ሥልጣን ሣይኖር የሰጡዋቸው ውሣኔዎች ተሽረዋል፣
- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣
- መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰ/መ/ቁ. 28883

ኅዳር 26 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ
ፍስሐ ወርቅነህ
መስፍን ዕቁበዮናስ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማኀበር - ጠበቃ ብስራት ሐመልማል ቀረበ፡፡

ተጠሪ፡- ሚስተር ኒኮላ አስ ፓፓቻት ዚስ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

**ፍ ር ድ፣**

በዚህ ጉዳይ የአሁኑ አመልካች በተጠሪ ላይ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረው ክስ፣ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ሆቴል ለተገለገለበት ክፍያ የሰጣቸው የክፍያ ማዘዣዎች በባንክ ተቀባይነት በማጣታቸው ብር 85,467.24 /ሰማኒያ አምስት ሺ አራት መቶ ስልሣ ሰባት ብር ከሃያ አራት ሳንቲም/ ይክፈል የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በበኩሉ ተከሳሽ የውጭ አገር ዜጋ ስለመሆኑም በ28/5/99 ቃለ መሐላ አቅርቧል፡፡ በዚህ መሠረት የውጭ አገር ዜጋ የክርክሩ ተካፋይ በሚሆንበት ጊዜ ግልጽ ነገር /Foreign Elements/ እንደሚኖር ይታመናል፤ ይህም የግለሰብ ዓለምአቀፍ ሕግን /Private International law/ የሚያስነሳ ይሆናል በአዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 11/2/ሀ/ መሠረት ደግሞ እንዲህ አይነት ጉዳዮችን ለማየት ስልጣኑ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለሆነ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ቀርቦለት የነበረውም የፌ/ከፍ/ቤት ውሣኔውን አጽንቶታል፡፡

የሰበር ቅሬታ ማመልከቻው የቀረበው በዚህ ነጥብ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎት የካቲት 12 ቀን 1999 በሰጠው ትዕዛዝ የውጭ አገር ዜጋ ተከራካሪ

በሆነበት ጉዳይ ላይ የግለሰብ አለምአቀፍ ሕግ ጥያቄ ይነሳል በሚል የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ታዞ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን መልስ እና የመልስ መልስ እንዲሁም ጥቅምት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በችሎት የተደረገው የቃል ክርክር አድምጧል፡፡

በመሠረቱ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11/2/ሀ/ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ /ፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው/ የሚመለከቱ ጉዳዮች በሚኖሩ ጊዜ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ሥልጣን እንደሚኖረው ተመልከቷል፡፡ አዋጁ የፍርድ ቤቱን ስልጣን በዚህ መልክ የደነገገው አንድም፣ ወደፊት በሥራ፣ ላይ የሚውለው የአገሪቱ የግለሰብ አለም አቀፍ ሕግ በሕግ አውጪው አካል ፀድቆ በስራ ላይ ሲውል በዚህ ዙሪያ የሚነሱ የሕግ ክርክሮችን የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን አይቶ እንዲወስን አሊያም አሁን ባለው ሁኔታ ለኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ለዳኝነት በቀረበ አንድ ጉዳይ ላይ ከተከራከሪ ወገኖች አንዱ የኢትዮጵያ ሕግ ከአመልካቹ አገር ሕግ ወይም ከሌላ አገር ሕግ ጋር ይጋጫል ወይም ይቃረናል በማለት በኢትዮጵያ ሕግ እንዳይዳኝ ወይም በራሱ ወይም በሌላ አገር ሕግ ጉዳዩ እንዲታይና እንዲወሰንለት ሲያመለክት ወይም በሌላ አነጋገር ለዳኝነት የቀረበው ጉዳይ በባሕሪው ከአንድ በላይ የሆኑ የሕግ ስርዓቶችን ለጉዳዩ አወሳሰን የሚጋብዝና የየትኛው ሥርዓት ሕግ ተመራጭ ሊሆን ይገባል የሚለው ክርክር ሲነሳ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመጀመሪያ የፍትሐብሔር የዳኝነት ስልጣን አይቶ እንዲወስን ከመደረጉ ውጭ በማናቸውም ሁኔታ ከተከራካሪ ወገኖች አንዱ የውጪ አገር ዜጋ በሆነበት ጊዜ ሁሉ በተከራካሪ ወገን ጥያቄ ባይነሳም ክርክሩ የፕራይቬት ኢንተርናሽናል ሎው ጥያቄ ያስነሳል ብሎ ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡



**ው ሣ ኔ**

- አመልካች በተጠሪ ላይ በር 85,467.24 እንዲከፍለው ያቀረበውን ክስ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የማየት ስልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጥር 30 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ 82621 እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የካቲት 6 ቀን 1999 ዓ.ም. በመ/ቁ. 52718 የሰጡዋቸው ውሣኔዎች ተሽሯል፣
- የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡ በፍ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 343/1/ ተመልሶለታል፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁጥር 29005

ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት

**ተጠሪዎች፡-** 1. ግርማቸው ይላላ ቀረበ፡፡

2. አዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ይሰጠኝ በሚል 1ኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክስ መሠረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪው ክስ የመሠረተው በ2ኛው ተጠሪ ላይ ነበር፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በሁለቱ መካከል የተሰማውን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ 2ኛ ተጠሪ የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ እና ካርታ ለ1ኛ ተጠሪ ይስጥ በማለት ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የአሁኑ አመልካች ክርክሩ የእኔን መብት የሚነካ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 358 መሠረት መቃወሚያ ያቀረበው ከዚህ በኋላ ነው፡፡ ፍ/ቤቱም መቃወሚያውን የተመለከተ ቢሆንም፤ በመጨረሻ ግን ተቃዋሚው /የአሁኑ አመልካች/ ተጠሪነቱ ለ2ኛ ተጠሪ በመሆኑ ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ተካፋይ አልነበረም የሚባል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት መቃወሚያውን ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡



እኛም አመልካች የካቲት 14 ቀን 1999 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ፣ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በአቃቂ ክፍለ ከተማ ስር የተደራጀ አስፈፃሚ አካል ነው፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 10/2/ እንደተመለከተው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያሉት ክፍለ ከተሞች የየራሳቸው ምክር ቤት፣ ዋና አስፈፃሚ እና ቋሚ ኮሚቴ ኖሯቸው የተደራጁ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አካላት ናቸው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 30 እንደተደነገገውም ክፍለ ከተሞች ባልተማከለ የስልጣን ክፍፍል መርህ በተሰጠው የቦታ ክልል ማዘጋጃ ቤት በመሆንና ከከተማው ማዕከል ጋር በመቀናጀት ይሰራሉ፤ በሥራቸው የሚገኙትን ቀበሌዎችም ያስተዳድራሉ፡፡ በአጠቃላይ በአዋጁ አንቀጽ 10 በተመለከተው አይነት የከተማው አስተዳደር የስልጣን አካላት የተደራጁ ሲሆን፣ ከነዚህ አንዱ ክፍለ ከተማ ነው፡፡ ከዚህ እንግዲህ መገንዘብ የሚቻለው እያንዳንዱ ክፍለ ከተማ የራሱ የሕግ ሰውነት ያለው እና በሕግ በተሰጠው የስልጣን ክልል ውስጥ በራሱ ኃላፊነት የሚንቀሳቀስ እንደሆነ ነው፡፡

በዚህ መዝገብ በሁለተኛ ተጠሪነት የተመዘገበው አካል ለሰበር አቤቱታው በሰጠው መልስ ክፍለ ከተሞች ካርታ እና የግንባታ ፈቃድ የመስጠት ስልጣንና ተግባር በቻርተሩ እና ቻርተሩን መሠረት በማድረግ በወጡት የከተማው አስተዳደር አዋጆች እንደተሰጣቸው አረጋግጦአል፡፡ በዚህ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካወጣቸው አዋጆች አንዱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክፍለ ከተማዎችና የቀበሌዎች አስተዳደር ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁ. 1/95ን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁ. 18/97 ሲሆን፣ ይህ

አዋጅ በክፍለ ከተማው ውስጥ ያለውን ቦታ የማስተዳደር ስልጣን የክፍለ ከተማው እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ቦታ ማስተዳደር ደግሞ ለአሁኑ ክርክር መነሻ የሆነውንም እንደሚያጠቃልል በአዋጁ አንቀጽ 2 ተመልክቶአል፡፡ አመልካች በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር መነሻነት ውሣኔ የተሰጠበት ጉዳይ እኔን የሚመለከት ነው በማለት መቃወሚያ ያቀረበውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ነገሩን አጠቃለን ስንመለከተው አመልካች የራሱ የሆነ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይም በሱ የስልጣን ክልል ውስጥ የሚከናወን ነው፡፡ በመሆኑም አያገባህም የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች እነዚህን ሁኔታዎች ባለማገናዘባቸው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 48511 ሚያዝያ 11 ቀን 1998 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47682 ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ጉዳዩ እሱን በቀጥታ የሚመለከት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ያቀረበው መቃወሚያ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተቀብሎ ክርክሩን በመስማት ይወስን ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



የሰበር መ/ቁ. 30298

ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** አቶ የሺወንድም አቡሐይ

**ተጠሪ፡-** አቶ አየነው ማለደ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በተጠሪ ላይ ተሰጥቶ የነበረው የመጥፋት ውሣኔ ሲሰረዝ አመልካች ለ3ኛ ወገን በሽያጭ አስተላልፈውታል የተባለውን ቤት ለተጠሪ ሊመልሱ ይገባል የሚሉት በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞባቸዋል ሲሉ አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ ለሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በአመልካች ጠያቂነት ቀደም ሲል በወረዳ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በተሰጠው የመጥፋት ውሣኔ የተነሣ መሆኑን ገልፀው የግል ንብረቴ የሆነውና የዋጋ ግምቱም ብር 50.000 (ሃምሣ ሺ.ህ) የሆነው ቤት አመልካች ለ3ኛ ወገን በሽያጭ ያስተላለፈው ስለሆነ እንዲመለስ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ቀርበው በሰጡት መልስ ተጠሪ ከእናቴ ጋር ጋብቻ መሥርቶ እያለ እናቴን ጥሎ በመጥፋቱ በሽተኛ ስለነበረች እሷን ለማሣከም ገንዘብ በማስፈለጉ ቤቱ የተሸጠ ሲሆን የሽያጩ ዋጋም በከሣሽ እንደተጠቀሰው ብር 50,000 /ሃምሣ ሺ.ህ/ ሣይሆን ብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺ.ህ/ ነው በማለት ክሱ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን ከቀረበው ማስረጃ አኳያ መርምሮ ተከሣሽ ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት የከሣሽና የእናቴ የጋራ ሀብት ነው የሚል ክርክር ቢያቀርብም ከጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት የቀረበው የሰነድ ማስረጃና እንደዚሁም በከሣሽ በኩል የቀረቡት ምስክሮች በሰጡት ቃል ከሣሽ ከተከሣሽ እናት ጋር ጋብቻ ከመመሥረታቸው በፊት የሠሩት ቤት እንደሆነ ስለሚያረጋግጥ ተከሣሽ ቤቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ ጠፍቷል የተባለ ሰው ከመጣ ጠፍቷል መባሉ ተሠርዞ ወደ ሌላ ሰው ተላለፎ የሚገኝ ንብረትም ሊመለስለት እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171(1) ላይ የተመለከተ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ለከሣሽ ሊመለስ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ተጠሪ ጠፍተዋል በማለት የመጥፋት ውሣኔ ካገኙ በኋላ ወራሽነታቸውን አረጋግጠው የተጠሪን ቤት ለ3ኛ ወገን መሸጣቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ ሲመለሱ ሊመለስላቸው የሚገባው የቤቱ ሽያጭ ዋጋ ወይንስ ቤቱ እራሱ የሚለው ነጥብ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171 አኳያ አቤቱታው ለሰበር ቀረቦ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ በማግኘቱ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ነጥብ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በተጠሪ ላይ የመጥፋት ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሽያጭ ወደ 3ኛ ወገን እንደተላለፈ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የመጥፋት ውሣኔን ውጤት ቀሪ ከሚያደርጉ ምክንያቶች /effects of termination of absence/ ጠፍቷል የተባለው ሰው መመለስ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 171 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም ጠፋ የተባለው ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹን በሚገኙበት አኳኋን መልሶ የመረከብ እንደዚሁም የተሸጡትን ንብረቶች ዋጋ የማግኘት መብት እንዳለው በግልጽ ተመልክቷል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ ንብረትነቱ የተጠሪ የሆነው ቤት መሸጡ ከተረጋገጠ ከላይ ከተጠቀሰው ድንጋጌ አኳያ ተጠሪ ሊረከቡ የሚገባቸው የተሸጠውን ቤት ሣይሆን የሽያጩን ዋጋ ነው ማለት ነው፡፡ የሽያጩን ዋጋ በተመለከተም አመልካች በብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ መሸጡን ሲገልፁ ተጠሪ ዋጋው ብር 50.000 (ሃምሣ ሺህ) እንደሆነ ከመግለጽ በስተቀር በዚህ ዋጋ የተሸጠ መሆኑን ማስረጃ አቅርበው አልተከራከሩም፡፡

ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች በሽያጭ የተላለፈው ቤት ለተጠሪ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 15240 በጥር 28 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ለአመልካች ይገባል ማለቱ እንደዚሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11660 በመጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ይግባኙን ባለመቀበል የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በብር 25.000 (ሃያ አምስት ሺህ) ስለመሸጡ የተረጋገጠ ስለሆነ የህንኑ የሽያጭ ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ